
BAPTIZED
BY BLAZING
FIRE
በሚንበለበለው እሳት
መጠመቅ
2

# እጅግ በትልቁ በኃይል እየበራ በሚንበለበል እሳት መጠመቅ

# #2

## በፓስተር ዮንግ ዱ ኪም

http://www.divinerevelations.info/amharic

**ጌታ** በግልጽ ተናግሯል፡- *“በአሁኑ ጊዜ፣ የአብያተ ክርስቲያናት መንፈሳዊ እንቅስቃሴ እኔ ለእነርሱ ካሰብኩላቸው ጋር በመጋጨት ላይ ይገኛል። ካህናት መንፈሳዊ መሪዎች እና የቤተ ክርስቲያን አባላት እኔን በደንብ (በልምድ) ነው የሚያመልኩኝ እና የሚያውቁኝም በተጻፈ ንድፈ ሀሳብ ብቻ ነው። እጅግ በምቀ ጥልቅ መሻት ኑ እና እኔን ተገናኙኝ።”*

**ጌታችን** በመንፈሳዊ ውጊያዎች ከክፉት መናፍስት ጋር ለመዋጋት መሰማራት ያለውን እውነታ ሊያሳየን እና እኛ በቀጥታ መንግሥተ ሰማይን፣ ሲኦልን፣ መላእክትን እና ሰይጣንን ማየት እንድንችል መንፈሳዊ ዓይኖቻችንን ለመክፈት ይሻል።

ማስታወሻ፡- የመጽሐፉ ርዕስ በእንግሊዝኛው “Baptize by Blazing Fire” የሚል ነው።

## ==== ቀን 16 ====

**ሊ, ዩ-ክዩንግ:** **ክርክሮች (ጭቅጭቆች) በመንግሥተ ሰማይ ያለውን ቤታችሁን እንዲፈርስ (እንዲናድ) ያደርጉታል*

*በመንግሥተ ሰማይ እንዲህ ብዬ ጠየቅሁ፡- “**ኢየሱስ**፣ በመንግሥተ ሰማይ የራሳችን የሆነ ቤት እንዳለን ተነግሮኝ ነበር። የእኔን ቤት ላይ እፈልጋለሁ።”*

እርሱ ወደ ቤቴ መራኝ። ደማቅ የሚያበራ ወርቃማ ቤት ሳይ ለጥቂት ጊዜ ተጓዝን። **ኢየሱስ** አለ፡- *“ይህ የአንቺ ቤት ነው።”* በዛ ቅፅበት፣ በቤቱ ውበት እጅግ ተደነቅሁ። መላእክቱ የእኔን ቤት እየገነቡ እዚህና እዚያ እየሄዱ በሥራ ተወጥረው ነበር።

ቤቴ ምን ያህል ፎቆች እንደሆነ ስጠይቅ፣ አምስተኛው ፎቅ እያለቀ እንደሆነና ከላይ ተጨማሪ ፎቆችን ለመገንባት ተጨማሪ አምዶች እየተሰሩ እንደነበረ ነገረኝ። የወንድም ሀክ-ሱንግን ቤት ደግሞ አየሁ እና የእርሱ ሰባተኛው ፎቅ አልቆ ነበረ።

የዮሴፍን እና የጁ-ኢዩንን ቤቶች ለማየት ስጠይቅ፣ **ኢየሱስ** እንዲህ እያለ የተጨነቀ መሰለ፡- *“ምን ባደርግ ይሻለኛል? ምን ሊደረግ ይችላል?”* ትክክል ያልሆነ ነገር ከነበረ **ኢየሱስ**ን ጠየቅሁት። የሁለቱም ሦስተኛና አራተኛ ፎቆቻቸው ተሠርቶ እያለቀ እንደነበር፣ ነገር ግን ባለፈው እነርሱ ሲጨቃጨቁ ቤቶቻቸው እንደተደረመሱ አብራራልኝ። አንድ ሰው ራስ ወዳድ፣ የሚከራከር (የሚጨቃጨቅ)፣ የሚራገም ከሆነ በሰማይ ያለው ቤታቸው እንደሚፈርስ **ኢየሱስ** አስተማረኝ። ለልጆችና ለጎልማሶች ይህ እውነት ነው። **ኢየሱስ** ለሁለቱም ለዮሴፍና ለጁ-ኢዩን በፍፁም እንዳይጣሉ፣ አለመግባባቶች ሲከሰቱ ለመታረቅ እንዲሞክሩ እንድነግራቸው ነገረኝ።

**ኢየሱስ** የተናደውን ቤት በመመልከት ላይ እያለ በጣም ያዘነ የፊት ገጽታ ነበረው። እርሱ ሀዘኑን ሊሰውር አልቻለም። *“አህ፣ ምን ብናደርግ ይሻላል? ለምንድን ነው ዮሴፍና ጁ-ኢዩን በጣም የሚከራከሩት? ዩ-ክዩንግ፣ ዮሴፍና ጁ-ኢዩን መጣላት እንዲያቆሙ እባክሽን ንገሪያቸው። እነርሱ እርስ በእርሳቸው ላይ ለማሾፍ ይጀምራሉ፣ መጨረሻቸውም በጥል ይሆናል እና ኳስ አንድ ላይ እየተጫወቱ እያለ፣ እየተጨቃጨቁ ይፈጽማሉ። ይህ ቤት በብዙ ችግሮች ነው በእኔ ትእዛዝ በመላእክቶቹ ተገንብቶ የነበረው፤ እንዴት ነው በድጋሚ ወደላይ የምንገነባው?”*

እኔ ከወንድሜ ሀክ-ሱንግ ጋር ብዙ ጊዜ እጣላለሁ እና ስለ ክርክሮቻችን በእውነት ጠንቃቃ መሆን እንዳለብኝ አሁን ተገንዝቤያለሁ።

**ኢየሱስ** እንዲህ እያለ ከንፎች ባሉት ወርቃማ ልብስ አለበሰኝ፦ ***"የእኔ ተወዳጅ ዩ-ክዩንግ፣ አንቺ በጣም ለብዙዎች መስክረሻል እና ስለዛ እኔ በጣም እወድሻለሁ።"*** እኔም ወዲያው መለስሁ፦ *"**ጌታ** ሆይ፣ እኔ ነገም ወጥቼ ለመሰክር ነው።"* **ኢየሱስ**ም መለሰ፦ ***"በእውነት? ቀናዒ ሁኚ እና በዚሁ ቀጥዪ። እኔ ቤትሽን ወደላይ በፍጥነት እገነባለሁ።"***

**ሊ, ሀክ-ሱንግ:** **መንፈሳዊውን ዓለም በጥልቀት በተገናኘን ቁጥር፣ የበለጠ ምስጢራዊ እየሆነ መጣ።*

ወደ ጸሎት ከገባሁ 10 ደቂቃ እየሆነ እያለ፣ ሦስት አጋንንት መጡ። የመጀመሪያው ጭንቅላት የሌለው ወንድ ነበረ። የጠንካራ ንፋስ ድምጽ ያላት፣ ልብስ የለበሰች አንዲት ሴት ጋኔን በሹል ጥፍሮቿ ልትቧጭረኝ ሞከረች። በሁለቱም ጫፎቹ በኩል ጭንቅላት ያለው አንድ በጣም ግዙፍ እባብ፣ ሁለቱም ጭንቅላቶች መጀመሪያ ለመሄድ እየተጣሉ መጣ። እኔ አለቀስሁ፦ *"**ኢየሱስ**፣ አድነኝ። እባክህን እርዳኝ!"* እርሱም በፍጥነት መጣና ሁሉንም አባረራቸው።



በመጸለይ ላይ እያለን **ኢየሱስ** ከበበንና እያንዳንዳችንን አንድ በአንድ ነካን። **ኢየሱስ** የፓስተር ኪምን ራስ እና የታመመ ጀርባውን፣ የዮሴፍን እግር እና የጆኢዩንን ጀርባ ነካ። **ኢየሱስ** አለ፦ ***"ዮሴፍ፣ ከምኞቶችህ አንዱን አካፍለኝ።"*** እርሱም መለሰ፦ *"**ኢየሱስ** ሆይ፣ ወንድም አህ ጆንግ-ሱክ ስራውን እንዲጠብቅና ቤተ ክርስቲያን በትጋት እንዲገኝ እባክህን እርዳው።"* **ኢየሱስ** ተስማማና አመሰገነኝ፦ ***"ሀክ-ሱንግ፣ ዛሬ በጣም ቀዝቃዛ ነው፣ ነገር ግን አንተ ለመመስከርና ወንጌልን ለማካፈል ዛሬ ወጥተህ ነበረ። እጅግ ደስተኛ አድርገኸኛል።"***

**ኢየሱስ** ትቶን ከሄደ በኋላ፣ ልብስ የለበሰች አንዲት ሴት ጋኔን ቀረበችኝ፤ የትምሕርት ቤት ሴት ልጅ ትመስል ነበር። ምንም ትኩረት አልሰጠኋትም ነበር እና በልሳኖች መጸለይ ቀጠልሁ። እየጸለይኩ እያለ፣ ፊቷን በግድ ከፊት ለፊቴ አመጣችውና የአፍንጫዬን ቀዳዳዎች በላባ ኮረኮረች። ትታ እንድትሄድ አዘዝኳት።

ጸሎት በትጋት መጸለይ ከጀመርኩ ጀምሮ እዛ ብዙ የተለያዩ አጋንንት እየመጡና ብዙ ያልተለመዱ ነገሮች እየሆኑ ነበር። በጥልቀት በሄድሁ ቁጥር፣ በምድራዊው ዓለም ውስጥ የማይታዩ ነገሮችን ይበልጥ መገናኘት ጀመርሁ።

**ኪም, ዮንግ-ዱ:** **ምስጢሩን ስላወጣን ቅጣት*

ትናንትና፣ የጎረቤታችን ቤተ ክርስቲያን ፓስተር እና ሚስቱ ሻይ እየጠጣን እንድናወራ መጡ። የጸሎቱን ስብሰባ መቀላቀል ይችሉ እንደሆን ጠየቁ። ግልጽ ሳልሆን ንግግሩን ለማስወገድ ሞከርሁ። ነገር ግን እርሷ በተደጋጋሚ በመጠየቋ ምክንያት እና የማላከብር (ባለጌ) መስሎ መታየት ስላልፈለግሁ፣ በመጨረሻ እጅ ሰጠሁና እሺ አልሁ። እንዲህ ማድረግ እንደሌለብኝ በልቤ ውስጥ አውቄ ነበር። ከባድ ሀዘን ልቤን ሞላው። ምክንያቱም መጽሐፉ ታትሞ እስኪወጣ ድረስ የጸሎታችንን ስብሰባ ከአባላቶቻችን ውጭ ማካፈል እንደሌለብን **ኢየሱስ** እንደነገረን አስታወስሁ። በጸሎታችን አገልግሎት ጊዜና እየጸለይን እያለ ምን እየተካሄደ እንደሆነ እነርሱ ምንም ፍንጭ የላቸውም። እኛ ከርኩስ መናፍስት ጋር በህይወትና ሞት ጦርነቶች ውስጥ ተሰማርተናል።

**ኢየሱስ** ጽኑ እንድሆንና የፓስተሩ ሚስት የጸሎቱን ስብሰባ ለመቀላቀል ያላትን መሻት ሳልቀበል እንድቀር አዘዘኝ። እኔ ወደቅሁ፣ እና በልቦቼ ጥልቅ ልብ ውስጥ፣ ባለመታዘዜ ምክንያት ምን ሊሆን እንደሚችል ፈርቼ ነበር።

የእሁድ ሌሊት ጸሎት አገልግሎት፣ በፓስተሩ ሚስት ያልተፈለገ መገኘት ምክንያት በተለየ ሁኔታ ተጠናቀቀ። በጠዋቱ 2 AM (በኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር ከሌሊቱ 8 ሰዓት) አካባቢ፣ የጸሎቱን ስብሰባ የመጀመሪያ ክፍል ጨረስሁ እና ወደ ቤቷ ልልካት ፈለግሁ፣ እርሷ ግን ልትናገረው ያለ ነገር እንዳለ ሆና ተቀመጠች። ማንም ከጸሎቱ ቡድን ምንም ነገር እንዳይገልጽ ወሰኛለሁ፣ ሚስቴና እኔ ግን ባልታወቀ ሁኔታ የምስጢሩን ዝርዝር በመግለጽ አጠናቀቅን።

እኛ በትእዛዝ መንግሥተ ሰማይን እና ሲኦልን እየጎበኘን እንደሆነና ብዙዎች የመንፈሳዊ እይታ፣ ትንቢት የመናገር፣ ርኩሳን መናፍስትንና ሰማያውያን መናፍስትን የመለየት፣ በልሳኖች መናገር፣ እምነት፣ ጥበብና እውቀት እንደተቀበሉ እኔ ገለጽሁ። እነዚህን ትዕይንቶች ወደፊት የሚታተም መጽሐፍ ውስጥ የመጻፍ ሂደት ላይ እንደነበርሁ ገለጽሁ፣ ስለዚህ እርሷ ተመልሳ ወደራሷ ቤተ ክርስቲያን ሄዳ በትጋት እንድትጸልይ አበረታታኋት።

**እግዚአብሔር** በዚህ እሁድ ምሽት በጸሎቱ ስብሰባ ላይ የእኔን መንፈሳዊ ዓይኖች እይታ ለመክፈት አቅዶ ነበረ እና እርሱ መንፈሳዊ እይታቸው ተከፍቶ በነበረ አባላት ይህን አረጋግጦ ነበር። ነገር ግን **እግዚአብሔር** የእርሱን ምስጢሮች መጠበቅ ባለመቻሌ በጣም ተናዶ ነበር። የእኔ ቀላል አእምሮ አንዳንድ ምስጢሮችን ማውጣት ምንም አይደል ብሎ አስቦ ነበር፣ ነገር ግን በጣም ትልቅ ስህተት ሰርቻለሁ። በዚህም ምክንያት፣ መንፈሳዊ ዓይኖቼን ለመክፈት የነበረው እቅድ ተሰረዘ።

**ኢየሱስ** በሀዘን መጥቶ ነበር። በጸሎት ጊዜ፣ እህት ቤይክ ቦንግ-ንዮ ጭክ ብላ አለቀሰች፡- *"ያልነው ነገር እንዴት ነው እንዲህ ትልቅ ውል የሚሆነው?"* እርሷ በሀዘን ስቅስቅ ብላ አለቀሰች። ምክንያቱም እኔ ምስጢሩን መጠበቅ ስላልቻልሁ፣ እኔ ምስኪን እርጉም የሰው ልጅ ሆንሁ እና ጥፋተኛነቱን ልቋቋመው አልቻልሁም። ሳምሶን እንዴት ነበር የተሰማው? ሳምሶን ናዝራዊ የመሆኑን ምስጢር ሲያወጣ፣ እርሱ ከ**እግዚአብሔር** ጋር የነበረውን ወዳጅነቱን ከድቷል።

**እህት ቤይክ, ቦንግ-ንዮ**: **የጌታ ግላዊ ቁጣ ለፓስተር ኪም*

***"የእኔ ተወዳጅ ቦንግ-ንዮ፣ ለምንድን ነው በጣም ስቅስቅ ብለሽ የምታለቅሽው? የቤተ ክርስቲያንሽ ፓስተር ኪም ዮንግ-ዱ ትልቅ ስህተት ሰርቷል፣ ለምንድን ነው ግን የምታለቅሽው?"*** ኮስተር ባለ ድምፅ ጠየቀ። ***"ፓስተር ኪም ንስሃ መግባት አለበት። በቤተ ክርስቲያንሽ እየሆኑ ያሉ ድርጊቶች በመጽሐፍ መጻፍ እና ለዓለም መገለጽ አለባቸው። እስከዛ ድረስ ምስጢር ሆነ መጠበቅ አለበት። ነገር ግን፣ ለምንድን ነው ምስጢሩን የገለጸውና በእኔ ላይ ኃጢአት የሠራው?"*** **ጌታ** ቅር ተሰኝቶ ነበር።

***"ይህ ምስጢር የዲያብሎስን ትክክለኛ ማንነት ይገልጻል፤ ስለዚህ በመንገዱ ላይ ብዙ ፈተናዎች ይኖራሉ። ለማልቀስ ምንም ምክንያት የለሽም። ምን እንደነገርኩሽ ፓስተር ኪም እንዲያውቅ አድርጊ።"*** የ**ኢየሱስ** አስፈሪ ቁጣ ቀጠለ። ***"ፓስተር ኪም ለጎረቤትየው ፓስተር ሚስት በአደራ የተሰጡ ምስጢሮችን አውጥቷል እና ይህንን ኃጢአተኛ ነገር ለምን እንዳደረገ አላውቅም። የፓስተር ኪም በደል በጣም ትልቅ ነው፣ አንቺ ግን አታልቅሺ።"***

**ኢየሱስ** ማብራሪያ ሰጠ። ***"የቤተ ክርስቲያኑ አባላት በሕብረት የሚጸልዩበት መንገድ እና የተለማመዳቸኋቸው ድርጊቶቹ ሁሉ በዓለም ዙሪያ ትልቅ ድንጋጤ ይልካሉ። ሰይጣን ማንነቱ ለዓለም እንዲገለጽ አይፈልግም እና ማንነቱ ተሰውሮ እንዲጠበቅ በታላቅ ፍላጎት እየሞከረ ነው። እሱንና የእሱን መላእክት የሚገልጡትን የቤተ ክርስቲያኑ አባላት የነበራቸውን እውን ልምምዶች እሱ ይፈራል። መጽሐፉ ከመጨረሱ በፊት ስለነሱ መገኘትና ማንነቶች እነዚህ እውነታዎች ከተገለጡ፣ የሰይጣን ጥቃቶች ይጠነከራሉ እና እናንተ የበለጠ መጠንከር አለባችሁ። በጸሎት ነቅታችሁ የመጠባበቃችሁ ሁሉም ዝርዝሮች ሙሉ በሙሉ ተጽፈው እስኪያልቁ ድረስ፣ ይህ የታተመ ምስጢር ነው። እኔ ለእናንተ ሌላ እድል እሰጣችኋለሁ። ፓስተር ኪም በጸሎትና መጽሐፉን በመጻፍ ላይ ማተኮር አለበት። ደግሞ፣ ትንቢቶች የመናገር ሥጦታ ያላቸው እያንዳንዳቸው ለሌሎች መጸለይን ለሌላ ጊዜ ማስተላለፍ አለባቸው።"***

**ኢየሱስ** ፓስተሮችንና ሚስቶቻቸውን ትኩረት ስለማጣታቸው በጥብቅ ገሠፀ። በስሙ የተገነቡ ሁሉም ቤተ ክርስቲያኖች ችግሮቹ ምንም ያህል ትልቅ ቢሆኑ ለማንኛውም አይነት ችግሮች በራሳቸው ውስጥ መፍትሄ ለመፈለግ መቻል አለባቸው ብሎ **ኢየሱስ** በጥብቅ አለ። *"በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድ ችግር ሲኖር፣ ፓስተሩና ሚስቱ በስምምነት መጸለይ አለባቸው እና ከእግዚአብሔር በእርግጥ መልስ ይኖራል። ከዚህ ወደዚያ እየሄዱ የትንቢት ጸጋ ያላቸውን ሰዎች እንዲጸልዩላቸው በመፈለግ፣ ብዙዎች የመጽናትን ተሰጥዎ አጥተዋል። በጣም ብዙ እንዲህ አይነት ሰዎች አላችሁ እና ይህ እኔን ያሳዝነኛል። በቤተ ክርስቲያናቸው መሠዊያ ላይ ተንበርክከው፣ የፓስተሮች ሚስቶች ከፓስተራቸው ጋር ሲያግዙና ሲጸልዩ፣ እግዚአብሔር ጸሎቶቻቸውን ይመልሳል። ደግሞ፣ ከጸሎታችሁና ጭንቀቶቻችሁን ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ካኖራችሁ፣ ከዛ ጠብቁ፣ ምክንያቱም ያ እውነተኛ እምነት ነው።"*

በከሰዓት በኋላው አገልግሎት ጊዜ፣ ፓስተር ኪም ምንም ያህል ምስጋናውን ቢመራም እና ስብከቱም ምንም ያህል ኃይለኛ የነበረ ቢሆንም፣ **ኢየሱስ** በኃይለኛ ቁጣ አስተያየት ከመስበኪያው ሰገነት ጎን በፀጥታ ቆሞ ነበር። ፓስተር ኪም ቀዝቃዛ ላብ በፊቱ ላይ እየወረደ ስብከቱን አደረሰ፣ ነገር ግን የ**ኢየሱስ** ቁጣ እያነሰ የሚሄድ አይመስልም። ፓስተር የተተወና አሳዛኝ መሰለኝ። እኔም ግልፅና ቅን ጸሎት ወደ **ኢየሱስ** አቀረብሁ። እርሱ ግን በጥብቅ መለሰ:- *"ብቸኛው መንገድ ለፓስተር ኪም በንጹህ ልብ ምህረት መለመን ነው እና ሰማያዊ አባታችን ይመለከትና ይወስናል።"*

**ኢየሱስ** አዘዘ:- *"ከአሁን በኋላ እኚህን ምስጢሮች ወደ ህዝብ ብታወጡ፣ ሁሉም መንፈሳዊ ስጦታዎች ይወሰዳሉ።"* ፓስተር ኪም ራቅ ካሉ ቤተሰቦቹና ቅርብ ጓደኞቹ ጋር ግንኙነት ማስወገድ እና ከውጫዊው ዓለም ራሱን ማግለል ይኖርበታል። ፓስተሩ በጸሎትና **ጌታ** ያሳየውን ሁሉንም ነገር በመጻፍ ላይ ትኩረት እንዲያደርግ **ኢየሱስ** ጠየቀ፣ ስለዚህ እሱ በፍጥነት መጽሐፉን ማሳተም ይችላል።

እኔ ጠየቅሁ:- "*ኢየሱስ ሆይ፣ ከጎረቤት ቤተ ክርስቲያን ወደ ፓስተር ኪም ቤት የመጣችው የፓስተሩ ሚስት በእሁድ ከሰዓት አገልግሎት ላይ ተመልሳ ለማውራትና ለመጸለይ ብትመጣስ? ፓስተራችን ርህሩህ ልብ ያለው ነው እናም አይሆንም ማለት አይችልም።*" **ጌታ**ም በሀይል እንዲህ አለ:- *"እኔ ጠንቋይ ነኝ? ልክ ኮከብ ቆጣሪ እንደሆንኩኝ አርገሽ ለምንድን ነው ሳታቋርጪ የምትጠይቂኝ?"* ለፓስተሮችና ለሚስቶቻቸው፣ እርሱ እንዲህ አለ:- *"ወደ እኔ በመጸለይ፣ እኔን በመፈለግና ወደ እኔ ጮክ ብሎ በማልቀስ ላይ ማተኮር አለባችሁ። ከዛ፣ እኔ እመልስላችኋለሁ። መልሶች ለመፈለግ ከዚህ ወደ እዚያ ለምን እንደምትሄዱ አላውቅም!"* እርሱ ስለዚህ እጅግ ተከፍቶ ነበር።

# ==== ቀን 17 ====

**ዲያቆን ሺን, ሱንግ-ክዩንግ:**

ከእሁድ ጀምሮ፣ ለሦስት ቀናት በልሳኖች እየጸለይሁ ነበር። ሰውነቴ በድንገት በሙቀት እየነደደ ተሰማኝ እና ይበልጡኑ በኃይል በልሳኖች መጸለይ ጀመርኩ። አንድ ብሩህ ደማቅ ብርሃን ወደታች በእኔ ላይ አበራ እና ከንስሐ ጸሎት ጋር ወዲያውኑ አነባሁ። እኔ የፈጸምኳቸው ረጅም የኃጢአቶች ዝርዝር ወደ አዕምሮዬ ሲመጣ እንባዎችና ላብ ፊቴን ሸፈነው።

**እግዚአብሔር**ን ለማምለክ እሁድን ቅዱስ አድርጌ በፍጹም ጠብቄ አላውቅም። ምንም እንኳ በቤተ ክርስቲያኔ ስያሜዬ እንደ ዲያቆኒት ቢሆንም ለፓስተሬ በተደጋጋሚ በጣም መጥፎ ጊዜ ሰጥቼዋለሁ። እርሱ የማይቆጠሩ ማበረታቻዎችን አፈሰሰልኝ፣ እንዲሁም ቁጣን። ነገር ግን እነሱ በአንድ ጆሮዬ ገቡና በሌላኛው ወጡ። ውጫዊ ሁነታዬ አንድ አግባብ ያላት 'ዲያቆኒት' ነበር፣ ነገር ግን ልቤ ከ**እግዚአብሔር** ጋር ምንም አይነት ግንኙነት አልነበረውም። በጸሎቱ ስብስብ ለመገኘት የፈለግሁበት ዋናው ምክንያት ይህ ነበረ እና ለመለወጥ ቆርጬ ነበር።

**ኪም, ዮንግ-ዱ:** **የፓስተር ኪም ንስሐ*

መንፈሳዊ ስጦታዬን ልቀበል የነበረበት ቀን ተራዝሞ ነበረ፣ ምክንያቱም የእርሱን ምስጢር ለመጠበቅ የ**ጌታ**ን ትእዛዝ አልታዘዝሁም ነበር። ይህን ምስጢር ከቅርብ ጓደኛዬ ጋር ተካፈልሁ እና ይህ **ኢየሱስ**ን እጅግ በጣም አናደደው። በሰው ሰውኛው አነጋገር፣ ምንም ማለት አልነበረም (ትልቅ ውል አልነበረም)። ማንም ሊያደርገው የሚችል ስህተት ነው። ነገር ግን የ**እግዚአብሔር** አሳቦች ከእኛ ሀሳቦች ፈፅሞ የተለዩ ናቸው። ወደ መንፈሳዊው ዓለም ውስጥ በጥልቀት እየገባን ስንሄድ፣ ጌታ የበለጠ በመንፈሳዊው ንቁ (አስተዋይ) እየሆንን እንድንመጣ ይፈልጋል። መጽሐፉ እስኪፈፀም ድረስ፣ ራሳችንን ከውጫዊው ዓለም እንድናቆራርጥ (እንድንለይ) እርሱ ፈለገ። ለሦስት ቀናት፣ እኔ ቀንና ሌሊት ንስሐ ገባሁ፣ የ**ጌታ** ቁጣ ግን እያነሰ የሄደ አይነት አልመሰለም። **ኢየሱስ** መጽሐፉን መጻፍ እንዳቆም አዘዘኝ። የሴት ልጄ የጁ-ኢዩን መናፍስትን የመለየት፣ ትንቢት መናገር እና ሁሉም ስድስት መንፈሳዊ ስጦታዎች፣ እንዲሁም የሌሎች አባላት ስጦታዎች መወሰድ መቻላቸው ልቤን በሀዘን ሞላው። ያ እንደ እርግማን ነበር።

ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም ነበር። እንዲህ ብዬ አሰብሁ:- *"እንዴት ነው ይህን ቤተ ክርስቲያን መመገብ የምችለው? እኔ በ**እግዚአብሔር** ተከኛለሁ?"* እኒህ አሳፋሪ ሃሳቦች ልቤን ሞሉት። ግን፣ ወደኋላ መቀመጥና ማቆም አልቻልሁም። ጮክ ብዬ በሀይል ስቅስቅ በዬ ማልቀሴን በመቀጠል አለቀስሁ፣ ተጸጸትሁ ንስሐ ገባሁ፣ ለመንሁ፣ ጮህኩ፣ ላስባቸው በምችለው በሁሉም የተለያዩ የጸሎት ዘዴዎች ጸለይሁ። የምሽቱን ስብከት ሳቀርብ ከፊቴ ያለውን ማየት አልቻልሁም፣ ምክንያቱም ዓይኖቼ በጣም አብጠው ነበር። አብዛኛውን ጊዜ በቀላሉ የማቀርበው ከአራት እስከ አምስት ሰዓት የሚወስደው ስብከት በጣም ከባድ ነበር እና በዛ ምሽት ስብከቴን ማቅረብ አልቻልሁም ነበር። መብራቶቹ ጠፍተው ነበር እና በመዝሙሮች ሁላችንም ስለ ኃጢአታችን ለንስሐ (ለመጸጸት) ጸለይን።

"***ጌታ** ሆይ፣ እባክህን አንድ ተጨማሪ እድል ስጠኝ!"* ጸለይሁ። ጉዳዬን እጅግ በጣም በዝርዝር ለመለመን እኔን የሚመለከቱ እያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ተጠቀምሁ። የጸሎቱ ቡድን እያንዳንዱ አባል አለቀሰ እና በቀናኢነት ከእኔ ጋር ጸለየ። ኦህ፣ በሚያሳዝን ሁኔታ ልቤ ተነክቶ ነበር እና ስለ ቤተ ክርስቲያን አባላቶቼ አመሰግናለሁ! **ጌታ** በእነዚህ ወጣት እና ድሃ የቤተ ክርስቲያን ጉባዔ አባላቶች ላይ ምህረትን አደረገ።

**ጌታ** ልብ የሚነኩ ጸሎቶቻችንን ሲሰማ፣ እርሱ ለእኔ ሌላ እድል ለመስጠት ወሰነ። መጽሐፉ እስኪፈጸም ድረስ፣ ከዚህ ሰዓት ጀምሮ ሁሉም ነገር የግድ ምስጢር ሆኖ መጠበቅ እንዳለበት **ጌታ** በግልጽ ተናገረ። ስለ እነዚህ ነገሮች ከቡድኑ ውጭ ማንም ማወቅ የለበትም። ለቤተ ክርስቲያኑ አባላት እንኳ እያንዳንዱ ነገር እንዲነገር (እንዲታወጅ) **ጌታ** አልፈለገም፣ ነገር ግን የተወሰነ ክፍል ብቻ እንዲካፈል። ርእሱን አስመልክቶ እያንዳንዱ ውይይት (ንግግር) በፓስተሩ መጽደቅና አነስተኛ መረጃ በማካፈል ብቻ መወሰን አለበት።

**የእጆቼ መለወጥ*

እጆቼ ወደላይ ተዘርግተው ለ30 ደቂቃዎች እየጸለይሁ እያለ፣ ሁለቱም ክንዶቼና እጆቼ ለየት ባለ ሁኔታ መንቀሳቀስ ጀመሩ። በመጀመሪያ፣ የቀኝ እጄ መዳፍ ወደ ውጭ ዞረ። በቀጣይነት በልሳኖች ከጸለይሁ በኋላ የግራ መዳፌም እንዲሁ ወደ ውጭ በመዞር ተንቀሳቀሰ።

እንቅስቃሴው በጣም ዝግ ያለ ነበር። ይህ የመንፈሳዊ መነቃቃት እርምጃ ከነበረ ብዬ አሰብሁ። አንድ ሰዓት አልቆየሁም። ለሌሎች አባላት፣ ከጥቂት ጊዜ ጸሎት በኋላ እንኳ **ኢየሱስ** ራሱን ይገልጥላቸው እና ርኩስ መናፍስትን ለማየት ይችሉ ነበር። እኔ ፓስተር (መጋቢ) ነኝ፣ እርሱ ግን ከእኔ ጋር እጅግ በከባዱ ተቋቋመ። የለውጥ አንዳች ምልክት ከማየቴ በፊት በአማካይ ከ20-30 ደቂቃ ይወስዳል እና በዚህ ደረጃ ፈቃዴን ላለማጣት ተሸብሬ ነበር።

ከሁለት እስከ ሦስት ሰዓታት ጸለይሁ፣ እና እንደተለመደው እጆቼ እንቅስቃሴውን ደገሙት፣ በድንገት በራሴ ውስጥ አንድ የኤሌክትሪክ ንዝረት ያለምህረት እያለፈ ሲሄድ ተሰማኝ። *"ይህ ነው፤ ይህ ወደ መንፈሳዊው ዓለም ውስጥ መግቢያዬ ነው?"* ብዬ አሰብሁ እና በጉጉት ተሞላሁ። የኤሌክትሪክ ፍሰቱ በመላው አካሌ ውስጥ በቀጣይነት እያስተጋባ እያለ የበለጠ በኃይል ጸለይሁ።

**የክፉ መናፍስት መንጋ አጠቃ*

እንደተለመደው፣ እጆቼ ወደላይ ተዘርግተው ለአራት ሰዓታት ያህል እየጸለይሁ ነበር። በድንገት ቅርጽ የሌለው አንድ አካል መጣና የእጄን አንጓ ጠመዘዘ። በሾለ መሳሪያ አንገቴን ወጋ እና የጀርባዬ ቀኙ ክፍል በሾለ የተሳለ ቢላ እየተቆራረጠ እንዳለ አይነት ነበር የተሰማኝ። አካሌ ሽባ እየሆነ ሲመጣ በታላቅ ሥቃይ አለቀስሁና ወደፊት ወደቅሁ። እኔ ታገልሁ፣ ነገር ግን መንም ጥቅም አልነበረውም።

አጋንንቱ እንዲህ እያሉ አፌዙብኝ፡- *"መንፈሳዊ ዕይታህ ተነቃቅቶ ለማግኘት ደፈርክ? ይሄንን መነቃቃት ከተቀበልክ፣ እኛ እንዴት አርገን እንደምንተርፍ ታስባለህ? አሁንም እንኳ፣ ሁላችሁም በጣም ስለምትጸልዩ በሀይለኛው ተቀጥተናል! ያለማቋረጥ ማመስገን፣ ስብከቶችህን ማቅረብና መጸለይ ከጀመራችሁ ጀምሮ አንድም እድል የለንም፣ ነገር ግን ዛሬ ቀኑ ላንተ የመጣ ይመስላል። ፈፅሞ ፍንጭ የሌላቸውን ሞኞችን ወሰድክና መንፈሳዊ ስጦታዎችን እንዲቀበሉ ረዳሃቸው። አንተ ለሰራኸው ነገር ትከፍላለክ!"* ከዛ የብዙ ርኩስ መናፍስቱ ስብስብ ሰውነቴ ውስጥ ገቡ።

ትንፋሽ ለማግኘት አቃተትሁ። አጋንንቶቹ በሰውነቴ ውስጥ በመዛመት ተጓዙና የተባባሰ ሥቃይ አስከተሉ። ሁሉንም እንቅስቃሴዎች ለማስቆም ሞከርሁ፣ ነገር ግን ሥቃዩ ቀጠለ። መላው ሰውነቴ ደነዘዘ። እያንዳንዱ ጡንቻ፣ ጅማት፣ መገጣጠሚያና አጥንት በጭንቅ ተሠቃይተው ነበር። በጣም በብዙ ሥቃይ ውስጥ ብሆንም እንኳ ማልቀስ እንኳን አልቻልሁም። በጣም በጮህኩ ቁጥር፣ ቁስሎቹ የበለጠ በሥቃይ ትር ትር ይሉ ነበር።

*"**ጌታ** ሆይ! በጣም ይቅርታ። ኢድነኝ። እባክህን ኢድነኝ! ይህንን ሥቃይ ልሸከም አልቻልሁም?"* አለቀስሁ። የጸሎቱ አባላት ደንግጠው ነበር እና ወዲያውኑ ወደ መሠዊያው ሮጡ። ሁሉም እጅግ ፈርተው ነበር። ምን ማድረግ እንዳለባቸው አያውቁም ነበር፣ ስለዚህ እነርሱ ያለ እርዳታ ምልክት እስኪያገኙ ወደ እኔ ተመለከቱ። *"እናንተ ቆሻሻ ኢጋንንት፣ **በናዝሬቱ ኢየሱስ ስም** ከእኔ ሽሹ!"* ብዬ ጮህኩኝ፤ አጋንንቶቹ አልሄዱም። በብዙ ሌሎች ጊዜያት የ**ኢየሱስ**ን ስም ሳሰማ አጋንንቶቹ ወዲያውኑ ይሸሹ፣ በዚህ ጊዜ ግን ምንም ያህል በሀይል ብጮህ እነሱ አልተንቀሳቀሱም።

እነሱ ወደታች ወደ አንገቴ እየተንቀሳቀሱና ወደኋላ እየተመለሱ ያንቁኝ ጀመር። ሁለቱንም ክንዶቼን በሀይል እየጎዱ እያለ ያለማቋረጥ በመተረቢያ ተረከኩኝ። በመጨረሻም፣ ለመናገር የማይቻል አደረጉት። መተንፈስ ብቻ እችላለሁ እና ያም እንኳ በመላው ሰውነቴ ሁሉ ታላቅ ጭንቀትና ሥቃይ አስከተለ። ሁሉንም ጥንካሬዬን አሰባሰብሁና ሁሉንም የቤተ ክርስቲያኑን አባላት እንዲከቡኝና ህይወታቸው በእሱ ላይ እንደ ተወሰነ ቢሆን አድርገው እንዲጸልዩ አጥብቄ አስገነዘብሁ። *"**ጌታ** ሆይ! **ጌታ** ሆይ! ኢድነኝ!"* እነዚህ ቃላት ከእኔ ውስጥ ያለ ንቃተ ህሊናዬ ወጡ።

**የቤተ ክርስቲያኑ አባላት ኃይለኛ ጸሎት*

አባላቱ ጮክ ብለው አለቀሱ። ምን አይነት ኢጋንንት እኔ ውስጥ እንዳነበሩ በፍጥነት እንዲለዩ የመንፈሳዊ ዕይታ ሥጦታ ያላቸውን አባላትን ጠየቅሁ። ነገር ግን ሁሉም በአንድ ድምጽ በጭራሽ አንዳች ነገር ማየት እንደማይችሉ ተናገሩ። በዚህ ጊዜ ሁሉ፣ የቀኝ እጄ አንጓ ተጠማዞና ሽባ ነበር።

አጋንንቶቹን ለመለየት ይረዳን ዘንድ ወደ **ኢየሱስ** እንዲጣሩ የቤተ ክርስቲያኑን አባላት አጥብቄ አስገነዘብሁ። ረዘም ላለ ጊዜ ጸለይን እና የመንፈሳዊ ዕይታ ስጦታ ያላቸው ምን እንዳዩ ማከፈል ጀመሩ። (ወደ ኤፌሶን ሰዎች 1:18-19) ውስጤ ያለው የአጋንንት መንጋ ከሲኦሉ መሪ ጋኔን ልዩ ትእዛዝ ተቀብለው ነው ወደ **ጌታ** ቤተ ክርስቲያን የመጡት። ያለመታየታቸውና ራሳቸውን ወደ ተለያዩ አይነት የመለወጣቸው ብቃት ሀይለኛ ጸሎት ካልተደረገ በቀር እነሱን ለማየት አስቸጋሪ አድርጎታል። **ኢየሱስ** አለ፦ ***"የእኔ ክቡር በጎች ሆይ፣ ለፓስተራችሁ ባደረጋችሁት ቅን ጸሎቶቻችሁና ለቅሶዎቻችሁ ምክንያት አጋንንቱን እንድታዩ እፈቅድላችኋለሁ።"***

30 የሚጠጉ አጋንንት ነበሩ እና ለማጥቃት ለረጅም ጊዜ አጋጣሚ እየጠበቁ ነበር። የጎረቤት ፓስተሩ እና ሚስቱ ሲጎበኙ፣ አጋንንቱ አጋጣሚ አዩና በጀርባቸው ሹልክ ብለው ገቡ። የሲኦል ንጉሡ ጋኔን እየጮኸ ቀጥተኛ ትእዛዝ ሰጥቷል፦ *"የጌታ ቤተ ክርስቲያን ስትገቡ፣ በሌላ ቤተ ክርስቲያን ከምታደርጉት ይበልጥ በታላቁ መጠንቀቅ አለባችሁ። የመንፈሳዊ ዕይታ ሥጦታ ያላቸው ብዙ አባላት አሉ እና ብዙዎች የእኔ የበታች ተከታዮቼ እውነተኛ ማንነቶቻቸው ስለተጋለጠ ወዲያ ተባረዋል። ፓስተር ኪምን ለማጥቃት አሁን ትክክለኛውን ሰዓት መጠበቅ አለባችሁ። ያ ሞኝ የእነዚህ ችግሮች ምንጭ ነው። እሱን መጣል ከቻልን ሌላው ሁሉ በቀላሉ ይፈታል። ሂዱና ይህ እንዲሆን አድርጉ።"*

የጎረቤታችን ቤተ ክርስቲያን ፓስተር ሚስት አጋንንትን ወደራሷ የሚያቀርብ አይነት እምነት የላትም፣ አጋንንትንም አትከተልም። እኔ ከማውቀው፣ እርሷ በትጋት የምትጸልይ የጸሎት አርበኛ (የጸሎት ጀግና ወታደር) ናት። አጋንንቱ ማንነቶቻቸውን ለመሰወር እጅግ በከባዱ ሞከሩና የሚጠቀሙበት ምቹ መሣሪያ (መጓጓዣ) ፈለጉ። የፓስተሩ ሚስት ለመጎብኘት እንደፈለገች ሲያውቁ፣ እነሱ ውስጥ ድረስ ተከተሏትና የሰውን ልጆች ለርህራሄ ፍላጎት እንደ ዘዴ ተጠቀሙበት።

*"**ኢየሱስ** ሆይ፣ የአጋንንቱን ማንነት አሳየን። **ኢየሱስ**፣ እባክህን እነሱን ለእኛ ግለጻቸው።"* ሁላችንም ጸለይን። ከዛ አንድ ሰው ጮኸ፦ *"ዋው! አየኋቸው። ማየት እችላለሁ!"* እንደ ክብ ምስር ኬኮች የሚመስሉ 15 የሚሆኑ አጋንንት ነበሩ። እነሱ ብዙ ዓይኖች ነበሯቸው እና በአካሌ ዙሪያ ተጠቀለሉ። የተቀሩት የተለያዩ አይነት ቅርጽና መጠን ያላቸው አጋንንቶች ነበሩ። አንድ ግዙፍ ባለ መቶ እግር ትል፣ አንድ አባ ጨጓሬ፣ አንድ ጥቁር ጥላማ ጋኔን፣ አንድ ሴት ጋኔን፣ እና አንድ አንበሳ። እንዲከቡኝና የአካሌን የሚሠቃዩ ቦታዎች እየነኩ በቅንነት በልሳኖች እንዲጸልዩ በጭንቀትና ችኮላ የቤተ ክርስቲያኑን አባላት ጠየቅሁ። እነርሱም አካሌን መንካትና መጸለይ ጀመሩ።

አንድ ሰው ጮኸ፦ *"ፓስተር፣ አጋንንቱ እየተቀየሩ ነው! እነሱ አልተበታተኑም፣ ነገር ግን በሕብረት እየሆኑ ነው!"* እኔም መለስሁ፦ *"ያ እውነት ነው? በኃይልና ሥልጣን ጸልዩና አስወጧቸው!"* የቤተ ክርስቲያኑ አባላት በአንድ ድምጽ ጮኹ፦ *"በ**ኢየሱስ** ስም ከፓስተራችን አካል ውስጥ ውጡ! ወደ ሲኦል ተመልሳችሁ ሂዱ!"* ጁ-ኢዩን ጮኸች፦ *"እኚህ ክፉ አጋንንት እጆቻቸው በመተባበር ተቆላልፈው ውስጥህ ተቀምጠዋል። ኦህ፣ አይሆንም! ምን እናድርግ?"* እኔም በኃይል ጮህኩኝ፦ *"መጸለይ ቀጥሉ። ካቆማችሁ በትልቅ ችግር ውስጥ እንሆናለን።"* ሁሉም በታላቅ መሻት ጸለዩ። (ወደ ኤፌሶን ሰዎች 6:10-11) "በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ። የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ።"

እህት ቤይከ ጮኸች፦ *"ፓስተር፣ አጋንንቶቹ በድጋሜ ተለወጡ።"* እኔም ጠየቅሁ፦ *"አሁን ምንድን ነው?"* እርሷም መለሰች፦ *"አሰቃቂ ነው! በዚህ ጊዜ ወደ አንድ ጥቁር ባለ መቶ እግር ትል ተለወጠ። በሁለቱ ሹል የእባብ ጥርሶቹ አንገትህን እየነከሰህ ነው እና የውስጡን ሰውነትህን በእሾህ እየወጋህ ነው። ምን እናድርግ? ባለ መቶ እግሩ ትል ጀርባህ ላይ ተጣብቋል!"* ወዲያውኑ፣ ሊቋቋሙት የማይችሉት ሥቃይ ተሰማኝና የበለጠ ስቃይ እያስከተለብኝ ዘለልሁ። ከዛ ወደፊት ወደቅሁ።

በድጋሜ ጮህኩኝ:- “*ጌታ ሆይ፣ እባክህን እርዳኝ!*” ምንም ያህል በኃይል ብጣራም እርሱ አልመጣም። የቤተ ክርስቲያኑን አባላት አነሣሣሁ:- “*ፍጠኑና **ኢየሱስ**ን ጥሩ!*” እነርሱም በሕብረት እንዲህ ተጣሩ:- “***ጌታ** ሆይ የት ነው ያለኸው? እባክህን ፍጠንና ፓስተራችንን እርዳው!*” ከለመኑ በኋላ **ኢየሱስ** ከፊታችን ታየ።



**ኢየሱስ** ረዘም ያለ ጊዜ እንደወሰደ ተሰምቶኝ ስለነበረ ተናድጄ ነበር። እንዲህ አስቤ ነበር:- “*በጣም ረጅም ጊዜ የወሰደበት **ኢየሱስ** የት ሆኖ ነበር?*” **ኢየሱስ** መለሰልኝ:- ***“እኔ እረድሃለሁ። አትጨነቅ።”*** በመንፈሳዊ ዕይታቸው **ኢየሱስ** ወደ አካሌ ሲገባ የቤተ ክርስቲያኑ አባላት አዩ እና እርሱ አጋንንቶቹን ወዲያ አባሮ እያስወጣቸው እንደሆነ ተናገሩ። አጋንንቶቹ በድጋሜ በሕብረት ሆኑና የእጅ ላስቲኮች ወደሚመስሉ ነገር ተለወጡ።

**ኢየሱስ** ጎትቶ አወጣቸው። ከአንዱ ጎን ሲጎትታቸው ወደ ተቃራኒው ቦታ ሄደው ይጣበቃሉ እና ሳይወጡ ይዘረጋሉ። ሁሉንም የሚጣበቁ አጋንንት ለማስወጣት ብዙ ሰዓት ጠየቀ። **ኢየሱስ** እምነታችንን ለማለማመድ ሆን ብሎ ነው ጊዜውን ወስዶ የነበረው ብዬ አምናለሁ። (ያዕቆብ 4:7) “እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል፤”

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ **ኢየሱስ** ሲናገር አጋንንቶች በፍርሃት ይንቀጠቀጡና ለእርሱ እጅ ይሰጡ ነበረ። **ኢየሱስ** ጊዜውን ወስዶ የነበረበት አንድ ምክንያት መኖር አለበት። የቤተ ክርስቲያን አባላቶቻችንን ቶሎ ከችግሮች ማገገም ይችሉ እንደሆን ለመመርመር እና ለእኛም አጋንንትን ለማስወጣት የሕብረትን ጥረት እንድንለማመድ **ኢየሱስ** ፈለገ። የጸሎቱ ስብሰባ እኩለ ሌሊት ላይ ጀመረና እስከ ጠዋቱ 1 ሰዓት ድረስ ቀጠለ። ሰውነቴ አሁንም በሚያስጨንቅ ህመም ውስጥ ነበር እና የቤተ ክርስቲያኑ አባላት ጸሎቶቻቸውን ቀጠሉ።

የቤተ ክርስቲያኑ አባላት በጸሎት ከበውኝ እንዳለ ሆዴ በአየር ተሞልቶ አጉረመረመ። ሰውነቴ ታመመ እና ሆዴ በታላቅ ህመም ውስጥ ስለነበር ከዚህ የበለጠ ህመሙን ልቋቋመው አልቻልሁም። የቤተ ክርስቲያኑን አባላት ያስቸገረ አንድ በጣም መጥፎ ሽታ ከእኔ ነበር። በጣም አፈርሁ፤ ውስጤ እየበሰበሰ ያለ አንድ ነገር ከእኔ እየወጣ ያለ ይመስል ነበር።

አንድ ሰው እንዲህ አለ:- “*እባክህን ራስህን ተቆጣጠር።*” በዚህ ሁሉም ወደ ሳቅ ዘለው ገቡ። እኔም እንዲህ አልሁ:- “*ይህ ጊዜ ለመሳቅ አይደለም። ወደ **እግዚአብሔር** መጸለይ ቀጥሉ።*” እነርሱም ትህትና በተሞላበት አክብሮት ወደ ጸሎት ተመለሱ። “*ጆ-ኢዩን፣ **ጌታ** አሁንም አጋንንቶቹን ከእኔ እያስወጣ ነው?*” እኔ ጠየቅሁ። “*ፍጠኝና ተመልከቺ።*” ወዲያውኑ፣ ሦስት አባላት **ኢየሱስ** አጋንንቶቹን አንድ በአንድ እየያዘና እያሰራቸው እንደሆነ መግለጫ ሰጡ። የቀሩት ሁለቱ አጋንንት በቀላሉ እጅ አልሰጡም። **ኢየሱስ** በመጨረሻ ያዛቸውና እኔን ያሠቃዩኝን ሁሉንም አጋንንት አጥብቆ አሰራቸው። እነሱን እሳት ወደሚያመነጨው ጥልቅ ውስጥ ለመወርወር እርሱ ቃል ገባ።

ከቆይታ በኋላ **ኢየሱስ** እንዲህ አለ:- ***“ዋው! የጌታ ቤተ ክርስቲያን ‘ትንሾቹ በጎች’ ላሰባቸው የሚገቡ ናቸው! ለፓስተር ኪም የእናንተ ለቅሶዎችና ጸሎቶች፣ እና ስትጨነቁ፣ ስትጸልዩ፣ እርሱ ከአጋንንት ጋር እየታገለ እያለ በእርሱ በኩል ስትሆኑ በእውነት ስሜቴን ነክቶታል። ለጥቂት ረዘም ላለ ጊዜ ብቻ ቀጥሉ። የመንፈሳዊ ስጦታ ዕይታን ለፓስተር ኪም እከፍታለሁ እና መንግሥተ ሰማይ እና ሲኦልን በዝርዝር ለማየት ይችላል። እርሱ ከዛ እነዚህን ዕይታዎች በመጽሐፍ ይጽፋል እና እነርሱን ከአለም ጋር ይካፈላቸዋል። ብዙ የጠፉ ነፍሳት ይህን መጽሐፍ ያነባሉ፣ ይድናሉ፣ እና ወደ እኔ ይመለሳሉ።”***

እቤት ተመልሼ ለማረፍ ስተኛ፣ ከንክሻዎቹና ቡጨራዎቹ የሆኑት ቁስሎች ሊታገሷቸው የማይቻሉ ነበሩ። በጣም የሚያሠቃይ ህመም ስለነበረ ስተነፍስ ወይም ስተኛ በስቃይ እጮህ ነበር። ሚስቴ፣ ዮሴፍ እና ጁ-ኢዩን በትጋት መጸለይ ጀመሩ።

ጁ-ኢዩን እየጸለየች እያለ **ኢየሱስ** እንዲህ ሲል ሰማቸው፡- ***"ክፉ ኢጋንንቱ ትተዋችሁ ሲሄዱ፣ በፀጥታ ትተዋችሁ አይሄዱም። በዛ ፈንታ ለሚመጡት ብዙ ቀናት እንድትሰቃዩ ከአደጋው በኋላ ላይ የሚያሙ ንክሻዎችንና ቧጨሮዎችን ይተዋሉ። ሚስትህ የመፈወስን ስጦታ ስለተቀበለች በቁስሎችህ ላይ እጆቿን እንድታኖር አድርግና ትጸልይ።"*** ሚስቴ ወዲያውኑ እጆቿን በቁስሎቼ ላይ አደረገች፣ ነገር ግን ወዲያውኑ የሚፈለገውን ያህል አልፈወሰም። በሥቃይ መሬቱ ላይ ተንከባለልሁና ወደ **ጌታ** አቤቱታ በማቅረብ አመለከትሁ። *"**ጌታ** ሆይ፣ ሚስቴ የፈውስ ስጦታ አላት፣ ለምንድ ነው ግን እስከ አሁን የሚያስጨንቀውን ሥቃይ እየተሠቃየሁ ያለሁት?"* **ጌታ**ም የፈወስ ኃይሎቿ ደካማ እንደነበር አብራራ፣ ነገር ግን ቀስ በቀስ እየተሻለኝ እንደምመጣ አረጋገጠልኝ። ጉጉ እና መጠበቅ የማልችል በመሆኔ በአቅራቢያዬ ወደሚገኝ ዶክተር ለህክምና በጥድፊያ ሄድኩኝ፣ ነገር ግን ህመሙ ሀይለኛ ስለነበር ህክምናውን አቋረጥሁ። ሚስቴ እንዲህ አለች፡- *"በ 20 ዓመታት ጋብቻችን ውስጥ አንተን በእንዲህ አይነት ሥቃይና ህመም ውስጥ አይቼህ አላውቅም።"*

**እህት ቤይክ, ቦንግ-ንዮ**: **በመግሥተ ሰማይ ያሉት ቤቶቻችን*

ለፓስተሬ እየጸለይሁ እያለ **ጌታ** በመንግሥተ ሰማይ ውስጥ ያለውን የፓስተሬን ቤት አሳየኝ። (የጌታችንና የመድኃኒታችን የ**ኢየሱስ ክርስቶስ** ቅዱስ ወንጌል በዮሐንስ 14:2-3) የፓስተር ኪም ቤት ከ360 ወደ 370 ፎቆች ከፍ አለ እና የሚስቱ ቤት ከ270 ወደ 280 ፎቆች ከፍ አለ። የዮሴፍ ቤት አራት ፎቅ ነበረ እና አምስተኛው ፎቅ በመጠናቀቅ ላይ ነበር። የጁ-ኢዩን ቤት 12 ፎቅ ነበር እና 13ኛው ፎቅ በመገንባት ላይ ነበር። እንዲህ ብዬ ጠየቅሁ፡- *"**ጌታ** ሆይ፣ የፓስተሬና የሚስቱ ቤቶች በአንድ ጊዜ አስር ፎቆች እየተገነቡ እያለ የዮሴፍና የጁኢዩን ቤቶች በአንድ ጊዜ አንድ ፎቅ ብቻ ነው እየተገነባ የሚገኘው። ይህ ለምን ሆነ?"* ***"ፓስተሩ ስብከት ማዘጋጀትና በስብከቱ እናንተን መባረክ ብቻ አይደለም የሚያደርገው፣ ነገር ግን እርሱ ለእናንተ በትጋት ይጸልያል። የፓስተሩ ጸሎት ከእናንተ ጋር ሲነጻጸር በጣም ሀይለኛ ነው። ለቤተ ክርስቲያኑ አባላት የሚያደርገው የፓስተሩ አገልግሎት ቤቱ በፍጥነት እንዲገነባ ያደረገው ያ ነው። ደግሞ፣ የፓስተሩ ሚስት ካንግ ህዩን-ጃ ለቤተ ክርስቲያኑ አባላት ቀንና ሌሊት ምግብ ታዘጋጃለች። ያ ብቻ አይደለም፣ እርሷ በሳምንቱ ጊዜ በየቀኑ ቤተሰቦቻቸውን ትመግባቸውና ታለብሳቸዋለች። በመንግሥተ ሰማይ የእርሷ ሽልማት ታላቅ ይሆናል። ጁኢዩን ለመጮህና ተከራካሪ የመሆን ዝንባሌ አላት፤ በጣም ትንሹ ሁኔታ ግልፍተኛ ያደርጋታል (ያበሳጫታል)። እብሪተኛ (ትዕቢተኛ) እየሆነች ልትመጣ ትችላለች። ስለዚህ ትሁት አድርጋችሁ ጠብቋት። ዮሴፍ ጭምት በመሆኑ ብዙ ጊዜ ቁጡ ይመስላል። እኔ እንኳ ሳየው አስተያየቱ ወዳጃዊ አይደለም እና ያንን እንዲቀይር እኔ እፈልጋለሁ። ዮሴፍ ምን ላይ ማሻሻል እንደሚያስፈልገው ፓስተራችሁ በስብከቱ ውስጥ ሲጠቅስ፣ እርሱ በቀረበው አስተያየት ደስተኛ አይደለም። ዮሴፍ እኝህን ጠቃሚ ትችቶች በእምነት ተቀብሎ ታዛዥ እንዲሆን እፈልጋለሁ። ከዛ የእርሱ ቤት ወደ ላይ ይገነባል።"***

የህክ-ሱንግ ቤት አስር ፎቆች ከፍታ ነበረ እና ለ11ኛው ፎቅ ደጋፊ አምዶች በመገንባት ላይ ነበሩ እና የዩ-ክዩንግ ቤት ሰባት ፎቆች ነበሩት። የቤተ ክርስቲያናችን ምስጢር በፓስተርና በሚስቱ በመውጣቱ ከፓስተሩ ቤት 50 ፎቆችና ከሚስቱ ቤት 30 ፎቆች እንደተናዱ **ኢየሱስ** ነገረኝ።

ወደ ሌሊቱ አገልግሎት ስሄድ ፓስተር ኪም ደካማ ይመስል ነበር ለጥቂት ጊዜ እየጸለየና እያለቀሰ የነበረ ይመስላል። ዓይኖቹ አብጠውና በአግባቡ ለማየት እየታገለ ነበር። እኔ ወደ **ጌታ** ለመንሁ። *"**ጌታ** ሆይ፣ ፓስተራችን በጣም ብዙ ሥቃዮችን ከኢጋንንቶች ዛሬ ተሠቃይቷል። ጥንካሬን ስጠው።"* **ኢየሱስ** በርህራሄ መጣና አጽናናኝ፡- ***"እያንዳንዱ የሚያጽናኗቸው ብዙ የቤተሰብ አባላት አሏቸው፣ ነገር ግን የእኔ በጣም ተወዳጇ ቤይክ ቦንግ-ንዮ፣ አንቺ ማንምና ምንም የለሽም። እኔ አጽናናሻለሁ።"*** እርሱ ቀጠለ፡- ***"አንቺ ከሁሉም ነገር በላይ እኔን ትወጂኛለሽ እና ለዚህ ነው ከፍ ያለ ዋጋ በጣም የሰጠሁሽ!"***

ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ውብ የሆኑ ሁለት መላእክት ከመንግሥተ ሰማይ መጡ። እነርሱ ረጅምና መልከመልካም ነበሩ። ከእነርሱ አንዱ የማውቀው ሊቀመልአክ ሚካኤል ነበረ፣ ሌላኛው እንዲህ እያለ ራሱን አስተዋወቀኝ:- *"እህት ቤይክ ቦንግ-ንዮ፣ እኔ ገብርኤል ነኝ እና በ**እግዚአብሔር** ፊት እቆማለሁ። **ጌታ** እንዳጅብሽ አዘዘኝ፣ ስለዚህ መጣሁ።"* እኔም መለስሁ:- *"አሀ እሺ፣ አመሰግናለሁ።"* እነርሱ ወደ ህዋ ውስጥ ይወስዱኝ ጀመር። በድንገት አንድ በጣም ትልቅ የርኩስ አጋንንት ቡድን እኛን ለማገድ መጡ።

የአጋንንቶቹ ፊቶች በጣም የተለያዩ ነበር። የአንድ ዘንዶ ራስ፣ ትላልቅ እባቦች፣ እና የተለያዩ የእንስሳት መናፍስት አየሁ፣ እኛን ለማጥቃት ሁሉም ተዘጋጅተዋል። እነሱ ከሌሎች ርኩስ ሀይላት ጋር ተሰበሰቡ እና ቶሎ ጥንካሬያቸው እጅግ አደገ፣ ነገር ግን ገብርኤልና ሚካኤል በፍጹም ስጋት አልተሰማቸውም። በዛ ፈንታ የተረጋጉ ይመስላሉ። ሚካኤልና ገብርኤል እጆቻቸውን ሲያነሱ፣ አጋንንቶቹ በፍጥነት ጠፉ። (የዮሐንስ ራእይ 12:7-9)

አጋንንቶቹ ከጠፉ በኋላ በመንግሥተ ሰማይ ውስጥ ደረስን እና በርቀት ቆሞ **ኢየሱስ** ሰላም አለኝ። እርሱም እንዲህ ብሎ ጮኸ:- ***"እወድሻለሁ የእኔ ተወዳጅ ቤይክ ቦንግ-ንዮ። አፈቅርሻለሁ።"*** **ኢየሱስ**ና እኔ በመንግሥተ ሰማይ ሁሉ እየተጓዝን በደመናዎች ላይ ሄድን። በመንግሥተ ሰማይ ውስጥ ሁሉም ወርቃማ የሆኑ ብዙ ተራራዎች አሉ። በመንግሥተ ሰማይ ውስጥ ያሉ ሰማዮችን ሳይ ወደ ቤት የመመለስ ሀሳብ ከአዕምሮዬ ጠፋ።

**ሊ, ሀከ-ሱንግ:** **ኢየሱስ ከፓስተር ኪም ጋር አለቀሰ*

እየመሰከርን የ**ክርስቶስ ኢየሱስ**ን ወንጌል ለመስበክ ከቀኑ 10 ሰዓት እስከ 1 ሰዓት ድረስ ወጣን። በኋላ ላይ ለመጸለይ ወደ ቤተ ክርስቲያን አመራሁ። እጆቹን ወደላይ ዘርግቶ በጉልበቶቹ ተንበርክኮ ሲጸልይና ሲያለቅስ ፓስተራችንን አየሁት። **ኢየሱስ** ከፓስተሩ አጠገብ ቆሞ አየሁት። **ኢየሱስ** ከእሾኾች የተሰራ ዘውድ አድርጎ ነበር እና ፓስተራችን ላይ ወደ ታች አትኩሮ በመመልከት እያለቀሰ ነበር። የ**ኢየሱስ** ራስ በሀይል እየደማ ነበረ እና የእርሱ ደም በልብሱ ላይ ተንጠባጠበ። እርሱ በደም ርሶ ነበር። **ኢየሱስ** ፓስተር ኪምን አቀፈውና ማልቀሱን ቀጠለ። በመቅደሱ ውስጥ ሁሉም መብራቶች ጠፍተው ነበር፣ ከመሠዊያው አቅራቢያ ግን አንድ ደማቅ ብሩህ ብርሃን ከ**ኢየሱስ** ፈንጥቆ (ወጥቶ) እያበራ ነበረ። በጀርባ ስለ **ክርስቶስ** *ሥቃይ* 'ሦስቱ ሚስማሮች' የሚባል አንድ መዝሙር ያለማቋረጥ እየተዘመረ ነበር።

በዛ ምሽት ከቆይታ በኋላ፣ **ኢየሱስ** ይህን ነገረኝ:- ***"የአየር ሁኔታው ምንም ያህል ቀዝቃዛ ቢሆን ቀለል ያለ ልብስ ለብሳችሁ ተንበርክካችሁና እጆቻችሁን ቀጥታ ወደ ላይ ዘርግታችሁ መጸለይ ምርጥ ነው። ሲቀዘቅዛችሁ እሳት እልክላችኋለሁ፣ ስለዚህ አስቀድማችሁ አታስቡ። በጣም ግዙፍ ልብሶችን ከለበሳችሁ እየጸለያችሁ እያለ ትተኛላችሁ። ተረዳህ?"***

**ኪም, ጁ-ኢዩን:** **በአንድ ልብ ሆኖ በስምምነት ንስሐ መግባት*

በልሳኖች እየጸለይሁ እያለ፣ እጅግ በጣም የሚያስቀይም አንድ ባለ ሦስት ራስ ዘንዶ ዘለለብኝ። እኔን ለማስፈራራት ወደ ኋላና ወደ ፊት ይል ነበር፣ ነገር ግን እንዲህ በማለት አባረርሁት:- *"በ**ኢየሱስ ክርስቶስ** ስም፣ አንተ የቆሸሽህ ጋኔን ከእኔ ሽሽ!*



*ከእኔ ርቀህ ተወገድ!'*።

እኔም በልሳኖች መጸለዬን ቀጠልሁ። **ኢየሱስ** ከፊቴ መጣና በተለይ ፀጥ ብሎ ነበር። ምንም ቃል ሳይናገር ስቅስቅ ብሎ እያለቀሰ ለረጅም ጊዜ ከፊቴ ቆሞ ነበር። ብዙ ጥያቄዎችን ጠየቅሁ፣ እርሱ ግን እንባዎችን ብቻ አፈሰሰ። ዛሬ በምሽት አገልግሎት ላይ ፓስተር በሚያሳዝን ሁኔታ እያለቀሰ ተናዘዘ:- *"**ጌታ** ላይ በጣም ብዙ ሥቃይ ስላስከተልሁ እኔ በጥልቀት በጣም ተጎድቻለሁ። **ጌታ** ሆይ፣ በአንተ ላይ በጣም ኃጢአት አድርጌያለሁ።"* ሁላችንም በሕብረት በመዘመርና ንስሐ በመግባት ላይ ትኩረት አደረግን። **ኢየሱስ**፣ ፓስተሩ፣ እና ሁላችንም በአንድ ላይ አለቀስን። (1ኛ ዮሐንስ 5:4)

# ==== ቀን 18 ==== (1ኛ ጴጥሮስ 5:6-10)

**ሊ, ሀከ-ሱንግ:** **በአካል አጋንንቶቹን ማጥቃት!*

በምሽቱ ስብከት ላይ ፓስተሩ ይህን ነገረን:- *"አጋንንቶች ሲመጡ አትፍሩ፣ ነገር ግን ፊት ለፊት በድፍረት ተዋጉ! እነዛ የቆሸሹ አጋንንት ምንም ናቸው፣ ስለዚህ አትፍሯቸው። ወደ መንፈሳዊው ዓለም ውስጥ በጥልቀት ስትሄዱና በድፍረት ስትጸልዩ ተቃዋሚ ታገኛላችሁ [በአጋንንት መልክ/አይነት]። ሲታገኙ ያዟቸውና ወደ ቁርጥራጭነት ገንጥሏቸው፤ አጥፏት!"* ለራሴ ይህን አሰብሁ:- *"የሚያስፈሩት አጋንንት ላይ እንዲህ አይነት ነገር እንዴት ማድረግ እንችላለን? እርሱ እያጋነነ መሆን አለበት።"* ነገር ግን ፓስተሩ በቆራጥ ጽኑ እምነት እንዲህ ደግሞ ተናገረው:- *"ይህን ማድረግ እንችላለን፣ እኛ ስንጠቃ ነበር እና ብዙ ስድብና ሁከት አስተናግደናል። አሁን እነሱን ለመበቀልና ለማጥቃት የእኛ ተራ ነው።"* ከዛ እነሱን በአካል እንዴት እንደምናጠቃ በግልጽ አስተማረን።

*"በእውነት አጋንንትን መያዝ እንችላለን?"* እኔ አሰብሁ። እስከ አሁን፣ የ**ኢየሱስ**ን ስም እንደ ውጊያ መሣሪያ ለመጠቀም ችለን ነበር፣ አሁን ግን ከአጋንንት ጋራ የፊት ለፊት የእጅ ለእጅ አካላዊ ጦርነት ማድረግ እንደምንችል ተነገረን!

በኋላ ላይ፣ በልሳኖች እየጸለይሁ እያለ ከበፊት የነበሩ ሁለት አጋንንት ተመለሱ። አንዱ ጡንቻማ ጋኔን ነበር እና ሌላኛው በላዩ ላይ ሁለት ፊቶች ነበሩት። የፒኮክ ላባ ይዞ ነበር እና እንደበፊቱ የላባውን ለስላሳ ጫፍ የአፍንጫዬን ቀዳዳዎች ለመኮርኮር ተጠቀመበት። በምሽቱ አገልግሎት ላይ ፓስተሩ ያቀረቡትን ስብከት አስታወስኩ። (ያዕቆብ 4:7) ከጋኔኑ ላባውን እየወሰድሁ መስሎ እንዲታይ አካላዊ እጄን ዘረጋሁ። እንዲህ ብዬ አሰብሁ:- *"ኦህ፣ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ያ ላባ አሁን በእኔ እጅ ነው ያለው!"* ተአምራዊ ነበር።

በላባው ሹል ጠቋሚ ጫፍ ጋኔኑን ያለማቋረጥ እወጋው ጀመር። ጋኔኑም ጮኸ:- *"አውች!"* በፍጥነት ያለምህረት እየወጋሁት ዙሪያውን አጠቃሁት። እንዲህ እየጮኸ ወደ ላይና ወደ ታች ዘለለ:- *"አውች! አድኑኝ!"* ከቁስሎቹ አረንጓዴ ፈሳሽ ቀስ በቀስ ወደ ውጭ ፈሰሰ። ደሙ መሆን አለበት። ሌላኛው ጋኔን ይህን ሲያይ በጣም ስለደነገጠ ፍርሃት ተሞልቶ ሮጦ ሸሸ።

አጋንንቶቹ በአካሉ ላይ የተዉትን የሚያሰቃዩ ቁሥሎቹን ተቋቁሞ ፓስተር ኪም መጸይ ቀጥሏል። **ኢየሱስ** ቀረበውና ያለማቋረጥ በእጆቹ ቁስሎቹን ነካ። **ኢየሱስ** ወደ እኔ መጣና እንዲህ አለ:- ***"ሀከ-ሱንግ፣ ቢከብድም እንኳ እጆችህ ወደታች እንዲወርዱ አትፍቀድ። እጆች ወደ ላይ ከፍ ተደርገው (ተነስተው) የሚጸለየው ጸሎት የበለጠ በጣም ብዙ ኃይል አለው።"***

**ኪም, ጁ-ኢዩን:**

ዛሬ ያልተለመዱ የሚመስሉ በጣም ብዙ አጋንንቶች ነበሩ እና ያለማቋረጥ ከፊቴ መጡ። እኔም እንዲህ ብዬ በኃይል ጮህኩኝ:- *"እናንተ አጋንንቶች፣ በ**ኢየሱስ** ስም ከእኔ ሸሹ።"* እነሱም ጠፉ። እኔም መጸለዬን ቀጠልሁ። በድንገት አንድ በእውነት ጠንካራ የሚመስል ወንድ ጋኔን እያጉተመተመ ወደ እኔ ተራመደ:- *"ሄይ፣ መጸለይ አቁሚ። ለሕፃን ልጅ የሚበዛ በጣም ብዙ ጸልየሻል።"* በንዴት ጮህኩኝ:- *"ሄይ፣ አንተ ቆሻሻ ሰይጣን! በ**ኢየሱስ** ስም ከእኔ ሽሽ!"* ሰይጣኑም ጠፋ።

መጸለይ እንደቀጠልሁ፣ በምታምር ሴት መልክ አንድ ጋኔን መጣ። ይህ ጋኔን በጣም ለዛ ያለውና መልከመልካም ስለነበር ርኩስ ጋኔን እንደነበር ማሰብ አልቻልሁም። (2ኛ ቆሮንቶስ 11:14-15) የምታወራበት መንገድ እንኳ የጠራ ነበር። እሷም እንዲህ አለች:- *"እባክሽን አትጸልዩ። ለምንድን ነው የምትጸልዪው?"* ችላ አልኳት እና እሷ ተናደደች። *"ሄይ፣ ለምንድ ነው ምትጸልዪው? ስትጸልዪ የተለየ ነገር ታያለሽ?"* አለች እና ከዛ እንዲህ ብላ ጮኸች:- *"መጸለይ አቁሚ!"* እኔ እንዲህ ብዬ ጮህኩኝ:- *"በ**ኢየሱስ** ስም ከእኔ ሽሺ፣"* እና ወዲያውኑ ከራሷ ጀምሮ እስከ ታችኛው የወገቧ መለያያ ድረስ በግማሽ መሰንጠቅ ጀመረች።

ስላስጠላኝ እንዲህ እያልኩ ትከሻዬን ነቀነቅሁ:- *"ኢው፣ በጣም ይቀፋል!"* አካሏ በግማሽ ሲከፈል አንድ እርጉም አሰቃቂ ጋኔን ከውስጥ ታየ። አሁንም የጋኔኑ የውጫዊ ማንነቱ ከውስጣዊ ማንነቱ በጣም የተለየ የመሆኑን እውነታ መርሳት አልቻልኩም።

በኋላ፣ በአንገቱ ላይ መሀረብ ያለው አንድ ንፁህ ሕፃን ልጅ መስሎ የመጣ አንድ ጋኔን አየሁ። እርሱ ፀያፍ ተንኮል በዓይኖቹ የመጫወት ችሎታ ነበረው። በ**ኢየሱስ** ስም ወዲያ ላባርረው ሞከርሁ፣ ነገር ግን ይህ ጋኔን ተቋቋመና በቀላሉ አልተንቀሳቀሰም። እኔም ጥርሴን አጥብቄ ተጭኜ ያለማቋረጥ ጸለይሁ። ከዛ ጋኔኑ ጠፋ።

**እጅግ በትልቁ በኃይል እየበራ በሚነድ እሳት ውስጥ መጠመቅ*

እንዴት ብዙ የተለያዩ የአጋንንቶች አይነት እንዳሉ ተገነዘብሁ። ሌሎቹን አባላት እየነካሁ መሰከርሁ። አጋንንቶቹ ሳያቋርጡ ይመጡና ይሄዳሉ እና በፍፁም ግራ መጋባት በሥራ ተወጥረው ዙሪያውን ይንቀሳቀሱ ነበር። እየጸለይሁ እያለ ፓስተር ኪም እንዴት እያደረገ እንደነበር ተደነቅሁ። እርሱን ተመለከትሁት፣ ነገር ግን እርሱን በማየት ፈንታ በእርሱ ቦታ ላይ እጅግ በኃይል የሚበራ የእሳት ኳስ አየሁ። ተደነቅሁ፣ ያየሁትን ለማረጋገጥ ዓይኖቼን ከፈትሁ እና ፓስተር ኪም እንደ ሁል ጊዜው ቦታው ላይ ተሠይሞ እየጸለየ አየሁት። በድጋሜ ዓይኖቼን ስጨፍን እጅግ በኃይል የሚበራ አንድ ትልቅ የእሳት ኳስ አየሁ። አጋንንቶች እርሱን ለማጥቃት ሳይችሉ ከፓስተራችን አጠገብ ቆመው ነበር፣ ስለዚህ የቤተክርስቲያኑን አባላት ለማጥቃት ተንቀሳቅሰው ሄዱ።

በድንገት፣ አንድ ባለ ረጅም ጸጉር ሴት ጋኔን መጣችና ድራኩላ (Dracula) በሚመስል ረጃጅም ሹል ጥርሶቿ ግራ ክንዴን ነከሰችኝ። እኔም ወዲያ ልገፋት ብሞክርም አልቻልሁም። ህመሙ በጣም የሚያሠቃይ ስለነበረ ቀጥ አድርጌ ማሰብ አልቻልሁም። ከዛ፣ ሌላ ጋኔን አጠቃኝ። እኔም እንዲህ ተጣራሁ:- *"**ጌታ** ሆይ፣ **ጌታ** ሆይ፣ እርዳኝ። እባክህን እርዳኝ!"* ወደ ፓስተር ሚስት ተጠጋሁና እጆቼን ወደላይ አድርጌ መጸለይ ቀጠልሁ። 100 የሚሆኑ አጋንንት እኔን ከመጸለይ ለማዘናጋት መጡ። እኔም እንዲህ በመጮህ መልሼ አጠቃኋቸው:- *"እናንተ ቆሻሻ አጋንንት፣ ለምንድን ነው እንዲህ የምትኖሩት? ለምንድን ነው የምታስቸግሩኝ?"* ሹል የውሻ ክራንቻ ጥርሶች ያሉት አንዱ በመጣደፍ እንዲህ እየጮኸ ወደ እኔ መጣ:- *"አንቺን ወደ ሲኦል ለመላክ እንፈልጋለን።"* እኔም መለስሁ:- *"ምን? ሲኦል? በጣም የምትገርሙ ናችሁ! ሄይ እናንተ ቆሻሻ አጋንንት ከእኔ ሽሹ። **በኢየሱስ ስም** ከእኔ ሽሹ።"* በዛ ቅጽበት እያንዳንዳቸው ሸሹ። መንግሥተ ሰማይን መጎብኘት ከፈለግሁ ከክፋት ርኩስ ሀይላት ጋር በከባዱ መዋጋት እንደሚያስፈልገኝ ተገነዘብኩ።

**መንፈሳዊ የክህነት ግዴታዎቻቸውን የሚያቆሙ ፓስተሮች (ካህናት)*

ለረጅም ጊዜ መጸለይ ቀጠልሁ፣ **ኢየሱስ** መጥቶ እንዲህ እያለ በቀፅል ስሜ ይጠራኝ ጀመር:- ***"ሰሊጥ፣ የእኔ ተወዳጅ ሰሊጥ፣ ከፉ መናፍስትን በማስወጣት አንቺ በጣም ጎበዝ ነሽ!"*** እኔም መለስሁ:- *"**ኢየሱስ** ሆይ፣ አባቴ ሲጠይቅህ ስለፈለገ አንድ ነገር አሁን አስታወስሁ። ፓስተሮች መሆን አቁመው ወደ አለማዊ ስራዎች የተመለሱ ፓስተሮች አሉ። እነዛ ፓስተሮች ላይ ምን ይሆናል?"* **ኢየሱስ** ፈቃደኛ ባለመሆን እንዲህ መለሰ:- ***"ይህን ለአንቺ ለማብራራት በጣም ልጅ ነሽ፣ ነገር ግን በጥሩ ሁኔታ ስሚና የምነግርሽን በትክክል ለእርሱ ንገሪ።"*** እርሱም ቀጠለ:- ***"ከከባድ (ከኃይለኛ) ችግሮቹ የተነሳ ፓስተር መሆን የተዉ ፓስተሮች በሰማያዊው አባቴ በጥብቅ ይፈረድባቸዋል። ሰማያዊው አባት እንዲህ ይገስፃቸዋል:- 'ፓስተር መሆን ለምን አቆማችሁ። መንፈሳዊ የክህነት ግዴታዎቻችሁን እንድታደርጉ ተሰጥኦዎችን ሰጥቻችሁ ነበር። ነገር ግን እናንተ ለምን ያለ እኔ ፈቃድ ለማቆም ውሳኔዎችን አደረጋችሁ? እናንተ ትልቅ ስህተት አደርጋችኋል። እናንተ ንስሐ መግባት ኃጢአታችሁን መናዘዝ አለባችሁ!' ከዛ በቀሪው ምድራዊ ሕይወቱ እርሱ በመታዘዝ በመንገዱ እኔን መከተል አለበት። የጌታን ቀን ቅዱስ አድርገው ያልጠበቁ ሰዎችም ደግሞ አሉ እና የፈለጉትን ያደርጋሉ። ዳግም ያልተወለዱት እነሱ ቢዝነሶቻቸውን ይከፍታሉ። በእሁድ ማንኛውም የቢዝነስ ግብይይቶች መኖር የለባቸውም። ብዙዎች ድህነታቸውን በአፎቻቸው ያውጃሉ፣ ነገር ግን እነርሱ በጣም ተሳስተዋል። እነርሱ የእውን ከዳኑ ህይወቶቻቸው መዳናቸውን ማሳየት ነበረበት! በሰማይ ያለው አባታችን በሁላችሁም ላይ ንቁ ዓይን አለው። ለአባት እያንዳንዱ ነፍስ በጣም ክቡር ነው እና በራሳቸው ምርጫ ነፍሳት ወደ ሲኦል ሲሄዱ፣ ያ እርሱን እጅግ በጥልቀት ያሳዝነዋል (ያሳምመዋል)። እርሱ ብዙ እንባዎችን አፍስሷል!"***

*ፓስተሮችን የሚያባርሩ እነዛ (ያዕቆብ 3:16)*

እኔ ከዛ ጠየቅሁ፡- *“**ኢየሱስ**፣ አንዳንድ ጊዜ በቴሌቪዥን ቤተ ክርስቲያናኖች ከፓስተሩ ጋር ሲጣሉ አያለሁ እና ያ በእውን ቅር ያሰኘኛል። ለምንድን የቤተ ክርስቲያን አባላቶችና ፓስተሮቻቸው ይጣላሉ? በዛ ቅፅበት አንተ በማን ወገን ነህ?”* **ኢየሱስ** እንዲህ አለ፡- *“አንቺ በጣም ልጅ ነሽ፣ ሆኖም አንቺ ሁል ጊዜ እንደዚህ አይነት ጥያቄዎች ትጠይቂያለሽ።”* እኔም መለስሁ፡- *“**ጌታ** ሆይ፣ እኔ የፓስተር ሴት ልጅ ነኝ። ፓስተሩ ከቤተ ክርስቲያን ተባሮ ሲወጣ ማየት ያሳዝነኛል!”* **ኢየሱስ** እንዲህ መለሰ፡- ***“ፓስተሩ (ካህኑ) በተደጋጋሚ ስህተት ይሠራል እና ያ አንድ ችግር ነው። የበለጠ የሚጠቅመው፣ የቤተ ክርስቲያን አባላቶች ቅር ሲሰኙ እና ፓስተሩን (ካህኑን) ሲያባርሩ እነርሱ አንድ ግዙፍ ኃጢአት ይፈጽማሉ። በፊት አንድ ሰው ኃጢአት የሠራ ቢሆንም እነርሱ በግልጽ በመጸጸት ንስሃ ቢገቡና እግዚአብሔርን ቢከተሉ እነርሱ አሁንም መንግሥተ ሰማይ መግባት ይችላሉ። እነርሱ እንዲህ አይነት ኃጢአት በፍፁም መድገም የለባቸውም!”*** (ወደ ፊሊጲስዩስ ሰዎች 2:3)

እኔም ጥያቄዎችን መጠየቅ ቀጠልሁ፡- *“**ኢየሱስ** ሆይ፣ ሁላችንም በአንድ ላይ እየጸለይን ነው፣ ለምንድን ነው ግን እህት ቤይክንና ቤተሰዎቿን ብቻ መንግሥተ ሰማይን እና ሲኦልን እንዲጎበኙ የምትወስዳቸው? እኛ የፓስተር ቤተ ሰዎች ነን፣ ትክክል? ቤተሰቤ የበለጠ እምነት ያለው ይመስላል። **ጌታ** ሆይ፣ ግን ለምን አንተ ሀክ-ሱንግን፣ ዩ-ክዩንግን እና እህት ቤይክ ቦንግ-ንዮን ብቻ ታፈቅራለህ?”* **ኢየሱስ** በጥያቄዬ ወደ ሳቅ ዘሎ ገባና እንዲህ መለሰ፡- ***“የእኔ ተወዳጅ ጁ-ኢዩን፣ ያ እውነት አይደለም። እነርሱ ከበድ ያለ ህይወት አላቸው። ሀክ-ሱንግ እና ዩ-ክዩንግ በስነ ልቡና ይቸገራሉ፣ ትክክል? እህት ቤይክ ቦንግ-ንዮ ደግሞ በጀርባ ህመም እየተሠቃየች የአልጋ ቁራኛ ናት። እነርሱ የሚበሉት ጥቂት አላቸው እና የሚኖሩትም በአንድ ትንሽ ምድር ቤት ክፍል ውስጥ ነው፣ ነገር ግን እነርሱ ያለማቋረጥ ይጸልያሉ! እነርሱ ከቤት ተባረው ወደ መንገድ መቼ እንደሚወጡ አያውቁም፣ ሆኖም እነርሱ በመታዘዝ ወደ እግዚአብሔር ይጸልያሉ። በተለይ እነርሱን አፈቅራቸዋለሁ። ምክንያቱም ምንም እንኳ ገደብ ቢኖርባቸውም እነርሱ አሁንም በትጋት ይጸልያሉ! እነርሱ የእኔ ከለላ (ጥበቃ) ያስፈልጋቸዋል! አንቺ በጣም ብዙ የቤተሰብ አባላት አሉሽ፣ እነርሱ ግን አባት ወይም ባል እንኳ የላቸውም። ለዚህ ነው እነርሱ የእኔ ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው!”*** (ኦሪት ዘጸአት 33:19)

*“**ኢየሱስ** ሆይ፣ ፓስተራችን እነዚህን ሁሉ መንፈሳዊ ልምምዶች በአንድ መጽሐፍ ውስጥ እየመዘገበ ነው። መጽሐፉ ሲፈፀም ሁሉንም መንፈሳዊ ስጦታዎች መልሰህ ትወስዳቸዋለህ?”* **ጌታ**ም እንዲህ አለ፡- ***“ጁ-ኢዩን፣ ትንቢት የመናገር ስጦታ በቀላሉ የማይሰጥ በቀላሉም የማይወሰወድ እጅግ ጠቃሚ ስጦታ ነው። ትንቢት የመናገር ስጦታ የሚወሰደው ሰማያዊው አባትሽ ሲያዝ ብቻ ነው እና ያለበለዚያ እንዳለ ይተዋል።”***

**ሊ, ዩ-ክዩንግ:** **አጋንንቶች እምነታችሁን ይፈራሉ*

ዛሬ፣ ብዙ የተለያዩ መልኮችን ባሳየኝ አንድ በጣም በሚያስፈራራ ጋኔን ተጠቅቼ ነበር። በኋላ፣ ለ**ኢየሱስ** እንዲህ አልሁት፡- *“**ኢየሱስ** ሆይ፣ አጋንንቶቹ በጣም ያስፈራሉ!”* እርሱም እንዲህ መለሰ፡- ***“ዩ-ክዩንግ፣ አጋንንቶቹን ማሸነፍ ትችያለሽ። አጋንንቶች እምነትሽን ይፈራሉ፣ ስለዚህ አትጨነቂ። መላእክት አንቺን ለመጠበቅ ሁል ጊዜ እዚህ ናቸው።”***

**እህት ቤይክ, ቦንግ-ንዮ:** **ፓስተር ኪምን ያጠቁ ቅርጽ የሌላቸው አጋንንት ማንነት*

በልሳኖች በኃይል እየጸለይሁ ነበር፣ ነገር ግን ምንም ማየት አልቻልሁም ነበር። ሁሉም ነገር እንደ ጨለማ ጨልሞ ነበር። ወደ መንፈሳዊው ዓለም በጥልቀት ለመሄድ ሞከርሁ፣ ስለዚህ ጮክ ብዬ ጸለይሁ። ብዙ ክብ የሆኑ ነገሮች ዙሪያውንና በዙሪያ እየተሽከረከሩ አስተዋልሁ።

ፓስተራችንን ተንኮል ተሞልተው በአረመኔነት ያጠቁት አይነት አጋንንት መሆን አለባቸው ብዬ አሰብሁ። መልሼ ልከፍላቸው ስላሰብሁ በኃይል አተኮርሁ። እነሱ እኔን ለማዘናጋት በዙሪያዬ ተጠቀለሉ። እኔም ልብ በሚነካ ሁኔታ በኃይል ወደ **ኢየሱስ** ጸለይሁ፣ እና እርሱም እንዲህ አለ:- *“በጥንቃቄ እነሱን ተመልከቺ*። እነሱ እንደ ምስር ፓንኬኮች ይመስላሉ። ከእነሱ ወደ 20 የሚሆኑት እድል ያገኙ እንደሆን እየሰለሉ ቤተ ክርስቲያኑ ሁሉ ዙሪያ እየተጠቀለሉ ነበር። **ኢየሱስ** እንዲህ አለ:- *“ትናንትና ፓስተር ኪምን የነከሱና እጁን የጠመዘዙ እነዚህ መጥፎ የማይበቁ አጋንንት ነበሩ። እኔ ሁሉንም ወሰድኳቸውና የጋለው የሲኦል ጉድጓድ ውስጥ ወረወርኳቸው። እነሱ ግን አገልጋዮቼን ለማጥቃት ተመልሰዋል። ቦንግ-ንዮ በተለይ አንቺ መጠንቀቅ አለብሽ!”*

ንጉሡ ጋኔን እንዲህ ብሎ ምስጢራዊ ትእዛዝ ሰጥቶ እንደነበር ተነግሮኝ ነበር:- *“በጌታ ቤተክርስቲያን ውስጥ የመንፈሳዊ ዕይታ ስጦታ ያላት ‘ቤይክ ቦንግ-ንዮ’ የምትባል አንድ አባል አለች እና እኛ ማን እንደሆንን መለየት ትችላለች። ያቺን ሴት በማጥቃት ላይ አተኩሩ!”* እነዚህን አጋንንት የገለጠልኝ ጌታ ባይሆን ኖሮ እነሱን ለማየት በመንፈሳዊ ዕይታ ስጦታም እንኳ አስቸጋሪ ይሆን ነበር። በጥልቀት ስጸልይ ግልጽ ያልሆኑ እነዛን ክፉ መናፍስት ለማየት እንደምችል **ጌታ** ነግሮኛል። በኃይል ስጸልይ የአጋንንቶቹ ማንነት ይገለጣል እናም እነሱ ይጠፋሉ።

**ሊቀ መላእክት ሚካኤል እና ገብርኤል*

ወደ መንግሥተ ሰማይ እኔን ለማጀብ ሁለት ግሩም መላእክት መጡ። እነርሱ ሚካኤልና ገብርኤል ነበሩ። ከሌላ ከማንኛውም መላእክት ጋር ሊነፃፀሩ አይችሉም። *“የእኛ ተወዳጅ **ኢየሱስ** እህት ቤይክ ቦንግ-ንዮ እንድትታጀብ አዘዘ። ስለዚህም እኛ በግል መጥተናል።”* **ጌታ** እንደ እኔ አይነቱን በጣም አነስተኛ አንድ ሰው እንዴት ልዩ አድርጎ እንደተንከባከበ በማወቁ ራሴ ትሁትና ዝቅ ብዬ ነበረ። አጸፋውን እንዴት መግለጽ እንዳለብኝ አላወቅሁም ነበር። መደነቄን እንደምንም መሸከም ቻልሁና በጉጉት እነርሱን ተከተልኳቸው።

በመንግሥተ ሰማይ **ኢየሱስ** የኤደንን ገነት አሳየኝ፣ እጅግ በመድነቅ ትንፋሽ የሚወስድ ነበር። በንግግራችን **ኢየሱስ** ይህንን ነገረኝ:- *“ቦንግ-ንዮ፣ ትናንትና ፓስተር ኪም ውስጥ የነበሩትን አጋንንት ለማስወጣት አስቸጋሪ ነበረ። ደከምሽ መሆን አለበት። በፓስተሩ ውስጥ የነበሩት አጋንንት አንቺ ላይ እንደሚጣበቁና እንደማይለቁ ደም መጣጭ ተባይ አይነት ናቸው። እነዛ መርዘኛ ነብሳት ራሳቸውን ይደብቃሉ እና ለመዘርጋትና ተመልሶ ለመታጠፍ ራሳቸውን እንደ የእጅ ላስቲኮች ይለውጣሉ። ከስብሰባው በኋላ ፓስተር ኪም እህት ሺን ሱንግ-ክዩንግን ወደ ቤት ሊያደርሳት የታመመውን አካሉን ጎተተ። እነዚህ ልጅ የበግ ጠቦቶች ፓስተራቸውን ለመጠበቅ ልብ አላቸው። ይህንን ባየሁበት ቅጽበት በጥልቀት ስሜቴ ተነክቶ ነበር እና እነርሱን ለመተባበር ወሰንሁ።”* እርሱ ቀጠለ:- *“ፓስተር ኪም ውስጥ ተጣብቆ የነበረው የመጨረሻው ጋኔን እስከሚችለው ድረስ እርሱን ለማሰቃየት ቆርጦ ነበር። እሱን ለማስወጣት ኃይል መጠቀም ነበረብኝ። በሚያሳዝን ሁኔታ በቤተ ክርስቲያንሽ ውስጥ ልጅ ከሆኑት የበግ ጠቦቶች መሐል ሲኦልን ማየት የቻልሽው አንቺ ብቻ ነሽ። ላንቺ አስቸጋሪ እንደሆነ እኔ አውቃለሁ፣ ነገር ግን የበለጠ ታጋሽ ብትሆኚ መታገስሽን ኢደንቃለሁ። አሁን ፓስተርሽ ኪም ዮንግ-ዱ መጻፍና ጽሑፉን እንደ መዝገብ በደንብ መጠበቅ አለበት። ያየሽው የሲኦል ክፍል በሙሉ አይደለም፣ ነገር ግን የሲኦልን አንድ ትንሽ ከፊል ድርሻ ብቻ ነው። በዚህ ሥራ አማካኝነት ብዙ ነፍሳት ይድኑ ዘንድ የሰማያዊ አባታችን መሻት ነው። ያለማቋረጥ አንቺን ወደ ሲኦል መውሰዴ ልቤን እጅግ ያሳዝነዋል እና ያንቺም ልብ እንዲሁ እጅግ እንዳዘነ አውቃለሁ። ከአሁን ጀምሮ ጥቂት ብቻ አሳይሻለሁ፣ ስለዚህ በጥንቃቄ ተመልከቺና ለፓስተር ኪም ምን እንዳየሽ በትክክል ዘግቢ።”* እኔም እንዲህ አልሁ:- *“**ኢየሱስ** ሆይ፣ አንተ በኃይል ከጠየቅህ። እባክህን እናቴንና ታናሽ ወንድሜን አታሳየኝ። እነርሱን ሳይ ሥቃዩን መሸከም አልቻልሁም።”* **ኢየሱስ**ም እንዲህ መለሰ:- *“ያ ሊስማማ የሚችል አይደለም። ለማየት ላትወጃቸው የምትችውን ነገሮች ማየት አለብሽ፣ ስለዚህ እውነቱን መመስከር ትችያለሽ።”* እርሱ መናገር እንደጨረሰ **ጌታ** እጄን ያዘና ወደ ሲኦል መራኝ።

*ወደ ሲኦል መመለስ*

በሲኦል ውስጥ የሚያስፈራራ (የሚያስደነግጥ) ነው። ሁሉም መጥፎ በተቆለፈበት ቦታ ውስጥ እንዴት ጎጂ መጥፎ እንደሆነ አዕምሮዋችን ሊያስብ አይችልም። ሥቃይ፣ ማቃሰትና ጩኸት ብቻ ያለበት የተረገመ ቦታ ነው። **ጌታ** እና እኔ በአንድ ጠባብ መንገድ ላይ ነበርን። በእያንዳንዱ ክፍል (በኩል) ላይ በበዛ ሥቃይ ውስጥ ያሉ ነፍሳት ትዕይንቶች ነበረ። በመንገዱ ግራና ቀኝ በኩል ጥልቅ ገደል ወደነበረበት አንድ ቦታ መጣን። **ኢየሱስ** እንዲህ አስጠነቀቀ:- ***"ተጠንቀቁ!"*** ዓይናችሁን ለአንድ ሰከንድ ከመንገዱ ላይ ማንሳት ወደ ታች እንድትወድቁ ሊያደርጋችሁ ይችላል። በሁለቱም በኩል (በመንገዱ በቀኝም በግራም በኩል) እንደ ሰማይ ከፍታ ያህል ተከምረው የራስ ቅሎችን በገደሉ ውስጥ አየሁ።

የራስ ቅሎቹ አልሞቱም ነበረ፣ ነገር ግን በቀስታ ይንቀሳቀሱና ይጮኻሉ። ያ ለጆሮዎቼ የሚወጋ ነበር። አንዳንዶቹ ተንሸራተው ወደ ታች ሲወድቁ የራስ ቅሎቹ ወደ ተወሳሰበ ውጥንቅጥ ጠብና ጭቅጭቅ ውስጥ ይገባሉ። እነሱ ወደላይኛው ተመልሶ ለመውጣት እርስ በእርሳቸው ይገፋፋሉ። እርስ በራሳቸው ላይ እንዲህ እያሉ ያማርራሉ ይጯጯሃሉ:- *"አህ፣ እኔ እየታፈንኩ ነው! አንተ መጥፎ ዞር በል! ልትንቀሳቀስ ነው?"*

እኔ ጠየቅሁ:- "እባክህን **ጌታ** ሆይ፣ በጣም አጸያፊ ነው። የበሰበሰው ሽታ በመላ ዙሪያ አለ። ከዚህ መውጣት እፈልጋለሁ። ይህን ያህል የራስ ቅሎች እዛ እንዴት ሊኖሩ ቻለ*? እነሱ ምን አይነት የሰው ልጆች ነበሩ?"* በጣም የተለያዩ አይነት ሰዎች እንደነበሩ **ኢየሱስ** ነገረኝ፣ ***"ቤት ሰርስረው በመግባት የሚሰርቁ ሌባዎች እየሰረቁ እያለ በስህተት እሳት ሲለኩሱ በእሳቱ ውስጥ የሞቱ፣ በሆቴል ተኝተው እያለ በእሳት ውስጥ የሞቱ፣ ወንዶችን ለማመንዘር ያሳሳቱና በእሳት ውስጥ የሞቱ፣ በአካሎቻቸው መሥራት እየቻሉ በሱ ፈንታ ወደ ልመና በመዞር ልመናውን የተለማመዱ፣ በሸርሸር ጊዜ የሰጠሙ፣ ቤተሰቦቻቸውን የገደሉ፣ ረጅም የእግር ጉዞ ሲያደርጉ በአደጋ የሞቱ እና ከሁሉም ኑሮዎች ሌሎች ብዙዎች በዚህ አሉ።"***



ልቆጥራቸው ያልቻልኩ በጣም ብዙ የራስ ቅሎች ነበሩ። በአንድ ጎን አንድ ሰው እንዲህ ሲል ሰማሁ:- *"እናንተ መጥፎዎች፣ እዚህ በጣም ተጨናንቋል። አየር ያነሰው ይህ ቦታ እየገደለኝ ነው!"* ከታች የነበሩት የራስ ቅሎች እንዲህ እያሉ ነበረ:- *"ከላይ ያላችሁ እናንተ መጥፎዎች፣ እየጨፈለቃችሁኝ ነው! እኔን መጨፍለቅ አቁሙ!"* ከታች ያሉት እነዛ የራስ ቅሎች ብዙ የተበሳሱ የቁስል ቀዳዳዎች ነበሯቸው።

የበለጠ ወደፊት ስንራመድ የበሰበሱ ሬሳዎች ሽታ እየጠነከረ መጣ። *"**ጌታ** ሆይ፣ ያ በጣም መጥፎ ሽታ ምንድን ነው? እንደ በሰበሰ ሥጋ ነው የሚሸተው።"* **ጌታ**ም እንዲህ መለሰ:- ***"አዎን ትክክል ነሽ። በጥንቃቄ ተመልከቺ!"*** እየበሰበሱ ካሉት አካሎች የሚወጣ አንድ ፈሳሽ አስተዋልሁ፤ እንደ ውቂያኖስ በሁሉ ዙሪያ ነበረ። *"**ጌታ** ሆይ፣ እዚህ ምንም የራስ ቅሎች ወይም አጥንቶች የሉም። አንድም አካል እዚህ አላየሁም፣ ነገር ግን ለምንድን ነው መጥፎው ሽታ በጣም አስከፊ የሆነው?"* **ኢየሱስ** እንዲህ አለ:- ***"ሥጋና አጥንቶቹ በስብሰው አልቀዋል።"***

*የባህር ቁልቋል የሚመስለው ተክል*

እንደቀጠልን፣ ወደ አንድ ትልቅ ለጥ ያለ ባዶ መሬት መጣን። አንድ ግዙፍ የባህር ቁልቋል የሚመስል ተክል ነበረ፣ ነገር ግን ምንም የሚታዩ እሾኾች አልነበሩትም። ከፊለፊቱ የጥቃቅን ትሎች መንጋዎች ነበሩ እና አንድ ነገር በተክሉ ላይ እየሄደ ነበር።

**ኢየሱስ** በቅርበት እንድመለከት ነገርኝ እናም ወደ ተክሉ ስራመድ ታናሽ ወንድሜን ከማይቆጠሩ እርቃናቸውን ከሆኑ አካላት ጋር በአንድ ላይ አየሁት። የባህር ቁልቋሉ ላይ ሁሉም ተተብትበውና ተጣብቀው ነበር። ሰዎቹ በሥቃይ በመጮህ ላይ እያሉ ሥጋቸውን እየበሉ በነበሩ በጥቃቅን ትሎች እያንዳንዱ ተሸፍኖ ነበር።

በሁሉም የሥቃይ ጩኸቶች እንኳ የወንድሜን ድምጽ በግልጽ መስማት እችል ነበር። *"እህቴ፣ የእኔ ተወዳጅ ቦንግ-ንዮ እህቴ ለምንድን ነው በድጋሜ እዚህ ያለሽው? አውች! ይህ ሊቋቋሙት (ሊታገሡት) የማይቻል ነው። ይህ በጣም የሚያሠቃይ ነው!"* ሁሉም አይነት ትሎች ሲነክሷቸውና ወደ አካላቸው ውስጥ ሰርስረው በመግባት ሥጋቸውን ሲገነጥሉ እያንዳንዱ በሥቃይ ጮኸ። በጣም ብዙ ትሎች ሸፍነዋቸው ስለነበር አንድ ኢንች የሚያህል ቆዳ እንኳ ማየት አልቻልሁም።

**የስጋ ትል በተሞላ ጉድጓድ ውስጥ ቤተሰቤ*

ወደ ግራ ተመለከትሁ እና በጣም ብዙ በሆኑ (በማይቆጠሩ) ሰዎች ጥቅጥቅ ብሎ የተሞላ አንድ ግዙፍ ጉድጓድ አየሁ። ሁሉም እርቃናቸውን ነበሩ እና በስጋ ትሎች ተሸፍነው ነበረ። በሥጋና በስጋ ትሎች መኃል ለመለየት በጣም አስቸጋሪ ነበር። (**የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ** ወንጌል በማርቆስ 9:48) በድጋሜ ራሴን ስቼ እንደምወድቅ አስቤ ነበር። እናቴን አየኋትና በዓይኖቿ ውስጥ ተመለከትሁ። እርሷ ወደዚህ ጉድጓድ ውስጥ ለመወርወር እየጠበቀች ነበር። እናቴ ጮኸች፦ *"የእኔ ልጅ ቦንግ-ንዮ፣ ጤንነት አይሰማሽ እንደነበር ሰምቻለሁ፣ ነገር ግን ለምን በድጋሜ እዚህ መጣሽ?"* ከዚያም አነባች። *"እናቴ፣ ወደ ሲኦል መምጣት አልፈልግም፣ ነገር ግን **ጌታ** እኔን ወደ ሲኦል መልሶ ማምጣት ቀጥሏል። ምን ማድረግ እችላለሁ?"* እናቴም እንዲህ መለመን ጀመረች፦ *"**ጌታ** ሆይ፣ እርሷን እጅግ በጣም እየጎዳት እንደሆነ ኢያወቅህ ለምን ልጄ በሲኦል ሰሠቃይ እንድታይ ፈቀድህላት?"* እኛ በአንድ ላይ አለቀስን።

*"እናቴ፣ በጣም በብዙ ጭንቀት ውስጥ የማይሽ ቢሆንም እንኳ አንቺን ለመርዳት አንዳች ማድረግ አልችልም። በጣም ይቅርታ!"* አልሁኝ። እናቴም እንዲህ ለመነችኝ፦ *"እባክሽን ቦንግ-ንዮ፣ በፍጹም ዳግም ወደ ሲኦል ተመልሰሽ አትምጪ። እኔ ሞቻለሁ እና ለመሠቃየት ወደዚህ እንድመጣ ተደርጌአለሁ፣ አንቺ ግን እስከመጨረሻው ድረስ **ጌታን** መከተል መቀጠል አለብሽ። ፍጻሜሽ እንደ እኔ እዚህ እንዳይሆን፣ ነገር ግን ወደ መንግሥተ ሰማይ እንደምትሄጂ እርግጠኛ ሁኚ።"*

**ኢየሱስ**ን ለእርዳታ ለመንሁት፣ ነገር ግን እርሱ አንዳች ማድረግ አልቻለም። በሀይል ስጮህ ከፉዎቹ ኢጋንንቶች እናቴን ያለምህረት ወደ ጉድጓዱ ውስጥ ጣሏት። የትሎቹ መንጋ እግሮቿን ሸምቅቀውና በሥጋዋና አጥንቶቿ ውስጥ ሠርስረው በመግባት በፍጥነት ወረሯት። ሌሎቹ ሰዎች እያደረጉ እንደነበረው እርሷም በሥቃይ ጮኸችና በፍርሃትና ጭንቀት ዙሪያውን ዘለለች። ጩኸቶቿ በሁሉም ሰዎች ጩኸቶች ቶሎ እየተዳፈነ መጥቶ ነበር።

በቀኝ በኩል ታናሽ ወንድሜ ሲሠቃይ መስማት ጀመርሁ። እርሱም እንዲህ ጮኸ፦ *"እህቴ፣ አካሌ በህይወት ኢያለ ትሎቹ እየበሉት ነው። ኦህ፣ እኔ በጣም በብዙ ሥቃይ ውስጥ ነኝ! ታላቅ እህቴ፣ አሁኑኑ እንዲረዳኝ እባክሽን **ኢየሱስ**ን ለምኚው!"* ትሎቹ ወንድሜን ወጉት እና እርሱን ወደ ጥቁር በመለወጥ መርዝ በመላ ሰውነቱ ውስጥ ተሠራጨ። ወንድሜ ራስን መግደል ፈፅሞ ነበር። ነገር ግን ለእንደዚህ አይነቱ ድርጊት ቅጣቱ እንደዚህ በጣም መጥፎና ኃይለኛ ይሆናል የሚል ሀሳብ አልነበረኝም። እኔም **ኢየሱስ**ን ለመንሁት፣ እርሱ ግን በድጋሜ በጣም ዘግይቷል አለ። ወደ **ሰማያዊው አባቴ** እንኳን ሳይቀር ጮኼአለሁ፣ ነገር ግን እርሱም ደግሞ አይሆንም አለ። ቶሎ፣ የወንድሜ አካል አንድ ጥቁር አጽም ብቻ ሆነ፣ ነገር ግን እርሱ አሁንም እየጮኸ ነበር። *"እህቴ፣ ፍጠኝና ይህን ቦታ ለቀሽ ሂጂ። በፍጹም ወደዚህ ቦታ ተመልሰሽ መምጣት የለብሽም። ተረዳሽ?"*

**ጌታ** እዚህ ስላሉት ስለ አንዳንዶቹ ሰዎች ነገረኝ። ***"ከሁለትና ከሦስት ሴቶች ጋር የኖሩ ወንዶች፣ ጓደኞቻቸውን (በጋብቻ ውስጥና ከጋብቻ ውጭ) በመቀያየርና እዚህም እዚያም በመዞር የተኙ ሰዎች፣ ራሳቸውን የገደሉ፣ ቤተ ክርስቲያን ይገኙና ዝሙት የፈጸሙ፣ በተራራ ላይ የሞቱ፣ በውሻ ተገድለው የነበሩ፣ እና የሞቱ ሌሎች ብዙዎች እዚህ አሉ።"***

ከ**ኢየሱስ** ጋር በመቀጠል ላይ እያለሁ፣ ትልቅና የሚያስደነግጥ (የሚያስፈራራ) አንድ በጣም ረጅም ጠማማ እጀታና ስለት ያለው ማጭድ የሚመስል ተመለከትሁ። አንድ ግዙፍ ጋኔን ሰዎቹን ለመቁረጥ እየተዘጋጀ በጣም ረጅሙን ማጭድ ይዞት ነበር። **ኢየሱስ** እንዲህ አለ:- ***"ያ ጋኔን በሲኦል ውስጥ አስረኛው በጣም ግዙፍ ጋኔን ነው።"*** በመላው አካሉ ዙሪያ ብቅ ብቅ ብለው የወጡ ብዙ ራሶች አሉት። ሰዎቹን በተርታ መቆራረጥ ጀመረ እና የእነርሱ አስደንጋጭ ጩኸቶቻቸው በመላው የሲኦል ሁኔታ ውስጥ በመሄድ አስተጋባ።

በተንኮል የተሞሉ አረመኔዎቹ አጋንንቶች ሌሎችን በማሠቃየት ይደሰታሉ። የፓስተራችንን አባት መቁረጥ ጀመሩ። እርሱም እንዲህ ጮኸ:- *"አውች! አባካችሁ ኢድኑኝ። በጣም ይቅርታ። አባካችሁ አቁሙ! ይቅርታ ኢድርጉልኝ!"* አሰቃቂ ነበረ። በመሬት ላይ ሰዎች ራሳቸውን ይስቱ ወይም ይሞቱ ነበር፣ በሲኦል ውስጥ ግን ራስን መሳትም ሆነ መሞት አልነበረም፣ አሰቃቂ ጩኸቶች ብቻ ነበሩ። እዛ ሁሉም የስሜት ሕዋሳቶቻችሁ ንቁ ናቸው።

የፓስተሩ አባት እንዲህ አለቀሰ:- *"ወዮ እኔ ነኝ። በበሽታ ምትኩ እና ሰምት ሁሉም ነገር ከጭንቀትና ኃላፊነት ነፃ ይሆናል ብዬ አስቢ ነበር፣ ሥራ ሳይኖረኝ በሰላም አርፋለሁ ብዬ አስቢ ነበር። ነገር ግን ይህ እኔ የጠበቅሁት አይደለም!"* በምሬት ራሱን አነቃነቀ። የፓስተሩን አባት እግር ከቆረጠ በኋላ ጋኔኑ እንዲህ ጮኸ:- *"አሁን በአካልህ ላይ ልጀምር?"* ወደ ትንንሽዬ ቁርጥራጮች መቆራረጡን ቀጠለ። በጣም አሰቃቂ ሁኔታ (ትዕይንት) ነበረ። እያንዳንዱ ዝርዝር ግልጽ ነበር፤ ህልም አልነበረም። **ኢየሱስ** እና እኔ እየተመለከትን እንደነበር ጋኔኑ አውቋል፣ ነገር ግን ችላ አለንና በተንኮል የተሞላውን አረመኔያዊ ሥራውን ማድረጉን ቀጠለ።

ጋኔኑ በእጆቹ ራሱን ለሁለት ሰነጠቀውና ቀሪዎቹን በዘይት እየፈላ ወደነበረ ወደ አንድ ትልቅ የብረት ማሰሮ ውስጥ ወረወረው። ሰዎቹ ቀለጡና የቀረው ሁሉም አጥንቶች ብቻ ነበሩ። አሁንም አስጨናቂው ጩኸቶቻቸው አልደከመም ነበር። አጋንንቶች የግብዣ (የፓርቲ) አይነት እንደሆነ አድርገው በደስታ እየተንከተከቱ እዚህም እዚያም ዙሪያውን እየሮጡ ነበር።

*"አንዴ በድጋሜ ራሳችንን ማጨቅ እንችላለን። የምንበላው በጣም ብዙ አለን። በጣም ብዙ አዲስ ሰዎች ወደ ሲኦል ስለመጡ ዛሬ ጥሩ ቀን ነበረ። ስለዛ ነው ግብዣ (ፓርቲ) ያደረግነው እና እየጠበስናቸው ያለው።"* አሉ።

ማሰሮው ውስጥ የነበሩት ሰዎች እንዲህ እየጮኹ ነበረ:- *"ሄይ፣ እናንተ ጨካኝና ክፉ መጥፎዎች! ከዚህ አውጡኝ። ከነህይወቴ ኢያነደዳችሁኝ ነው! አሁኑኑ አውጡኝ! አንዳች ማየት አልቻልኩም። ሞቃት ነው! እዚህ እየሞትኩ ነው!"* እነሱ በድጋሜ እኔ መድገም የማልፈልጋቸውን እርግማኖች ብለዋል።

በኋላ፣ **ኢየሱስ** የሎጥ ሁለት ሴት ልጆች (ኦሪት ዘፍጥረት 19:31-38) በሀይል በሚነድ ጉድጓድ ውስጥ እጅግ በሃይለኛ እያለቀሱ ወዳሉበት አንድ ቦታ ወሰደኝ። **ኢየሱስ** እጅግ አዝኖና በጣም በብዙ ሥቃይ ተጎድቶ ስለነበር ወዲያውኑ ለቆ ለመሄድ ወሰነ። **ጌታ** እንዲህ አለ:- ***"ቦንግ-ንዮ በእነዚህ ሁለቱ ሴት ልጆች ልቤ ታሟል እና ቤተሰቦችሽን በሲኦል ውስጥ ስታዪ የአንቺን ሥቃይ አውቃለሁ። ነገር ግን አንቺ ስላየሽው ነገር በእርጋታ እንድታሰቢ እፈልጋለሁ።"*** ወደ ሲኦል ባመጣኝ በእያንዳንዱ ጊዜ ልቡ እጅግ በጣም እንደሚያዝን **ኢየሱስ** አካለፈ፣ እርሱ ግን ያንን ከእኔ ሰውሮታል። **ኢየሱስ** እንዲህ አለ:- ***"አሁን ከሲኦል እንሂድ (እንለይ)።"*** እርሱ ወደ ቤተ ክርስቲያን መልሶ አመጣኝ።

## ==== ቀን 19 ==== (ወደ ዕብራውያን 10:35-39)

**ሺን, ሱንግ-ክዩንግ:** **ዲያቆኒት ሺን ሱንግ-ክዩንግ መንፈሳዊ ዳንስ ደነሰች*

በልሳኖች እየጸለይሁ ነበረ እና አካሌ አንድ የሚነድ የእሳት ኳስ ተሰማው። ውጭ -10° ነበር እና ሁሉንም ማሞቂያዎችንም አጥፍተን ነበር። ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ቀዝቃዛ ነበር። ነገር ግን **መንፈስ ቅዱስ** በላያችን ላይ ስለነበረ **ጌታ** አካላችንን እጅግ በኃይል ወደ ሚነደ እሳት ስለለወጠው ብርቱው ቅዝቃዜ አላስቸገረንም። የክረምት ወፍራም ልብሶቻችንን ማውለቅ ነበረብን እና አጭር እጅጌ ያላቸውን ቀለል ያሉ ልብሶች ብቻ ለበስን።

በኃይል የሚበራ የፀሐይ ብርሃን ወደታች እያብለጨለጨ እንደሚያበራው እኔም በጸሎቱ እሳት ተመትቼ ነበር። በሞቃቷ ፀሐይ ስር ያለን ይመስል እኛ በላብ ርሰን ነበር። አብዛኛውን ጊዜ እስከ ጸሎቱ ፍፃሜ እንደ ምንም ንቁ በመሆን በብርድ እንቀጠቀጥ ነበር። ጸሎቶቼ በጥለቀትና በጥልቀት እየሄዱ እንደሆነ ተሰማኝ። ከአንድ ሰዓት በኋላ እጆቼ ያለውዴታ መንቀሳቀስ ጀመሩ። እንቅስቃሴዎቹ የተለያዩና በጣም ረጋ ያሉ ነበሩ።

እስከዛ ድረስ የፓስተሩን ሚስትና የእህት ቤይክ ቦንግ-ንዮን መንፈሳዊ ዳንስ መመልከት ብቻ እችል ነበር እና ይህንኑ ስጦታ ለመቀበል በጥልቅ ጓጉቼ ነበር። እኔም እንዲህ ለመንሁ:- *"**ጌታ** ሆይ፣ መንፈሳዊውን ዳንስ እንድደንስ እርዳኝ! ይህን መንፈሳዊ ስጦታ ናፍቄአለሁ። **ጌታ** ሆይ፣ እኔ ለስጦታው በግልጽ ጓጉቻለሁ። ይህ መንፈሳዊ ዳንስ በጠቅላላው ስለ ምን እንደሆነ እንደለማመደው እርዳኝ።"*

በክርስቲያናዊ ሕይወቴ በሙሉ ***መንፈስ**ን* ተለማምጄ ወይም በ***መንፈስ*** ተሞልቼ በፍጹም አላውቅም። በጣም ኃጢአተኛ ነበርሁ እና በ**ጌታ** ፊት ሁል ጊዜ አፍር ነበር። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በእሁድ አገልግሎት ካለው የበለጠ በሳምንቱ የጸሎት ጊዜያት የ***መንፈስ* ቅዱስ**ን ኃይል እየተለማመድሁ ነበር። የእሁዱ አገልግሎት ለሁለት ሰዓታት ብቻ ነው በዝማሬ፣ ጸሎት፣ ስብከት፣ እንዲሁም በማስታወቂያዎች ለ**እግዚአብሔር** የሚውል ነው። ይህም የበለጠ በመንፈሳዊ እንድፈልግ ተወኝ።

**ሊ, ዩ-ከዩንግ:** **በአምላካችን ዙፋን ፊት መግባት* (የዮሐንስ ራእይ 4:2-4)

ጸሎቴ እንደጀመረ አንድ ባለ ሦስት ቀንድ ጋኔን ታየ። እኔም እንዲህ ጮህኩ:- *"ጋኔን፣ በ**ኢየሱስ** ስም ጥፋ!"* እና ሄደ። እኔ እንዲህ ጮህኩኝ:- "***አባባ** ናፍቆሽኛል!"* **ኢየሱስ** እንዲህ እየተጣራ መጣ:- ***"የእኔ ተወዳጅ ዩ-ከዩንግ አባትሽን ጠራሽ?"*** እኔም በድፍረት መለስሁ:- *"አዎ።"* **ጌታ**ም ጠየቀ:- ***"ወደ አባትሽ ለመጣራት ፈልገሽ ነበር?"*** እኔም መለስሁ:- *"አዎን እጅግ በጣም እፈልጋለሁ"* ከዛ እርሱ ይህን ነገረኝ:- ***"ተጣሪ!"*** እኔም ያለማቋረጥ እንዲህ ጮህኩኝ:- *"**አባ! አባ!**"*

**ኢየሱስ** ወደ መንግሥተ ሰማይ ወሰደኝ። ለ**ኢየሱስ** ምስጋናዎችን እየዘመርሁ እና በባህር ዳርቻው ላይ ውሃ እየረጨሁ በመንግሥተ ሰማይ ሁሉ በደመናዎች ላይ መጓዝ እወዳለሁ። **ኢየሱስ** ይህን ጠየቀኝ:- ***"ዩ-ከዩንግ፣ ትላንት ያደረግሁልሽን ቃል ኪዳን ታስታውሻለሽ? አስታወስሽ?"*** እኔም መለስሁ:- *"አዎ **ኢየሱስ**። **እግዚአብሔር አብ**ን ልታሳየኝ ቃል ገብተህልኝ ነበረ።"* **ኢየሱስ** በታማኝነት ቃሉን ጠበቀና አባቱን ለመገናኘት ወሰደኝ። **አባታችን** ማሰብ ከምንችለው በላይ ግዙፍ (ትልቅ) ነው፣ የመንግሥተ ሰማይ ላይኛው ሰማያዊ ሰማይ ድረስ ይደርሳል እና ከፀሐይ የበለጠ ደምቆ ያበራል። እርሱ እጅግ በጣም ግዙፍ በሆነ አንድ ዙፋን ላይ ተቀምጦ ነበረ።

በ**እግዚአብሔር** ፊት ምስጋናዎችን እየዘመርሁ በደስታ ተሞልቼ ነበረ። *'ነፍሴ ሆይ **እግዚአብሔርን** ባርኪ'* ብዬ ዘመርሁ እና **እግዚአብሔር አብ**ም ስዘምር አደመጠኝ። እርሱም በደስታ ደነሰ እና እርሱ በተንቀሳቀሰ ቁጥር ሊረዱት የማይቻል የሚያምሩ የተለያዩ ብዙ የብርሃን ቀለም ጨረሮች በድምቀት ከእርሱ ይወጣሉ። ከ**እግዚአብሔር አብ** ፊት ለፊት ከአንድ ተራራ የሚበልጥ አንድ መጽሐፍ ነበረ እና እርሱም መጽሐፉን እየተመለከተው ነበረ።

የ**እግዚአብሔር** ግዙፍ እጅ ተዘረጋና በእርጋታ ራሴን አሻሸኝ። የእጆቹ መጠን ምን ያህል ግዙፍ እንደሆነ በቃላቶች ሊገለጽ አይቻልም። የላይኛው ክፍል የ**እግዚአብሔር** አካል ደመና በሚመስል የውሃ ጠብታዎች (በጉም) ተሸፍኗል። **ኢየሱስ** ምስጋናዎችን መዘመር እንድቀጥል ጠየቀ ስለዚህም ዘመርሁ። እጆቼን በአንድ ላይ በማጨብጨብና እጆቼን ይዞ ወደ ኋላና ወደ ፊት በመወዛወዝ **እግዚአብሔር** በምስጋናዬ ተደሰተ። ክንዶቼን ዙሪያውን ሁሉ በማወዛወዜ በጣም ደስተኛ ነበርሁ። **ኢየሱስ** እንዲህ አስጠነቀቀኝ:- ***"በአባታችን በእግዚአብሔር አብ ሕልውና ከቁጥጥር ውጭ አትወዛወዢ!"*** በአክብሮትና በትሕትና ራሴን በማጎንበስ እጆቼን ወደ ላይ ከፍ እንዳደርግ እርሱ አስተማረኝ። በኋላ፣ **ኢየሱስ** ወደ ቤተ ክርስቲያን መልሶ ወሰደኝ።

**ሊ, ሀኪ-ሱንግ:** **ኢጋንንቶቹን በእጃችችሁ ምቷቸው!*

ፓስተራችን ከባለፈው ሰይጣናዊ ጥቃት በሚያስጨንቀው ሥቃይ አሁንም እየተሰቃየ ነበረ። ዛሬ ምሽት በእጆቻችን አጋንንቶቹን መያዝ እንደምንችል ነግሮናል እና በአጋንንቶቹ ላይ አጸፋውን ለመመለስ እንድንዘጋጅ ጠየቀን። እኛም በመተባበር:- *"አሜን!"* ብለን ጮህን። የጸሎት አገልግሎት ሰዓት ስለነበረ በትጋት በልሳኖች ጸለይሁ።

**ኢየሱስ** በፀጥታ ቀረበ። እርሱም ከፓስተሩ ሚስት ፊት ለፊት ተቀመጠና ለረጅም ሰዓት ጸሎቶቿን አደመጠ። ከዛ ፓስተሩን ቀረበና እንዲህ ተናገረው:- ***"ፓስተር ኪም፣ የቱ ጋር ነው እየታመምህ ያለኸው?"*** አጋንንቶቹ ነክሰውትና ቧጭረውት የነበረበት ቦታዎች ላይ ፓስተር ጠቆመ። በእርጋታና በፍቅር ያለማቋረጥ ቦታውን እየነካ **ኢየሱስ** በፓስተሩ አንገትና ጀርባ ላይ አተኮረ።

**ኢየሱስ** ከሄደ በኋላ፣ በልሳኖች መጸለይ ቀጠልሁ። አምስት ርኩሳን መናፍስት በአንድ ጊዜ አጠቁ። የእጅ ለእጅ ውጊያን አስመልክቶ የነበረውን የፓስተሩን መልእክት አስታወስሁ። ከዘረጋሁ በኋላ እጄን ከፈትሁና አንድ ነገር ያዝሁ። በመንፈሳዊ ዓይኖቼ ስመለከት ነጭ ቀሚስ የለበሰች አንድ ሴት ጋኔን እንደነበረች አየሁ። እግሯ በመዳፌ ውስጥ በጥብቅ ተይዞ ነበር እና እሷ ራሷን መርዳት የማትችል ነበረች። (የጌታችንና የመድኃኒታችን **የኢየሱስ ክርስቶስ** ወንጌል በማርቆስ 3:15) ። እንደ ሄሊኮፕተር ውልብልቢት ዙሪያውን አሽከረከርኋት። ተአምራዊ ነበር። አሽከረከርኳትና ወደ አንድ ጥግ ወረወርኋት። አንገቷ በከባዱ ተመቶ ተሰበረ እና እንዲህ ጮኸች:- *"አውች! እየገደልከኝ ነው።"* የፓስተሩን መልእክት አስታወስሁ። *"ኢጋንንትን ስታዩ ያለምህረት ጨፍልቋቸው! ዓይኖቻቸውን አውጡና ላያቸው ላይ በመሄድ በከባዱ እርገጧቸው!"* በጡጫዬ መታኋቸሁና ረገጥኳቸው። እነሱም ጮኹ:- *"አህ፣ አንተ ሰው! አህህ! አድነን!"* እነሱ ሸሹ። አስደናቂ ነበር። ከእንግዲህ አልፈራም። አጋንንቶች ብዙ ሆነው የሚያጠቁ ቢሆንም እንኳ እነሱን ለመዋጋት ዝግጁ ነኝ።

ሌላ ጋኔን አሽከረከርሁኝና አርቄ ወረወርኩት። ጁ-ኢዩን የጠቀሰችው አንድ ጋኔን ነጫጭ ዓይኖቹን እያሽከረከረ ቀረበኝ። ቀረብ እስኪል ድረስ ይህን ጋኔን ጠበቅሁት። ጸሎቴን ለማወክ ልክ እንደሞከረ ያለምህረት ዓይኖቹን አወጣኋቸውና መሬት ላይ ደበደብሁት። እውር ሆኖ፣ መሬቱ ላይ እየፈለገ ተሳበ፣ *"አህ አይሆንም! ዓይኖቼ! ዓይኖቼ የት ናቸው? እንዳገኛቸው እርዱኝ።"* በመጨረሻ አገኛቸው። ነገር ግን ዓይኖቹ ይቀመጡበት የነበረ ቀዳዳዎች ውስጥ መልሶ ሊያስቀምጣቸው ሲሞክር ዓይኖቹ ላይ በጣም ብዙ ቆሻሻ ነበረ። በተሳሳተ ሁኔታ አስቀመጣቸውና ሮጦ ጠፋ።

አንድ ወንድ ጋኔን የተቀደደ አንድ ካናቴራ ለብሶ ከእኔ አንድ ምልክት የሚፈልግ እንደነበረ በመምሰል ቀረበ። እንደ ቦውሊንግ ኳስ ላሽከረክረው ፈለግሁ። የሚበቃ ያህል ሲጠጋ እጄን ዘረጋሁና ዓይኖቹ ውስጥ ሁለት ጣቶቼንና የዓፍንጫው ቀዳዳ ውስጥ አንዱን ጣቴን ከተትሁ። እንደ ቦውሊንግ ኳስ ወረወርሁት እና ከአንድ ከፍ ካለ ድንገተኛ ድምጽ ጋር ተንሸራቶ ወደቀና ጠፋ።

አንዴ በድጋሜ ረጅም ጸጉር ያለውና ልብስ (ጋውን) የለበሰ አንድ ጋኔን ታየ። ከዓይኖቿና ከንፈሮቿ እየደማች ስለነበረ ብርድ ብርድ የማለት መጥፎ ስሜት ተሰማኝ። ከኋላው ሮጥሁኝ፣ ያዝሁት፣ ፊቱን በጥፊ መታሁትና ዘልዬ ተከመርሁበት። በጣም አሸናፊነት ተሰማኝ! እኔም ነገርሁት:- *"እዚህ መምጣት አቁም በቃ! እናንተ ኢጋንንት አበሳጭ ናችሁ!"* ያለማቋረጥ ከነበረው ተደጋጋሚ ድብደባ በኋላ እየጮኸ ሮጠ። ይህ የሚደንቅ ነበረ። ቂል አጋንንቶችን በጥፊ በመምታት በጣም በብዙ እየተገረምሁ ነበር!

የብረት ጭምብል የለበሰ አንድ ጠንካራ የተሟላ ወንድ ጋኔን ሲቀርበኝ በልሳኖች መጸለዬን ቀጠልሁ። በጭምብሉ ውስጥ አንድ ዓይን ብቻ ነበር ይታይ የነበረው እና ያም ዓይን በትንንሽዬ ትሎች የተሞላ ነበረ። ልነካው ስላልፈለግሁ እንዲህ ብዬ በሀይል ጮህኩኝ:- *"በ**ኢየሱስ** ስም ከእኔ ሸሽ!"* እሱ ግን ተቋቋመና ከዛ በሚጠማዘዝ እንቅስቃሴ መደነስ ጀመረ።

እየደነሰ እያለ ባልታወቀ ሁኔታ በተደጋጋሚ ይታይና ይጠፉ ነበር። ጋኔኑ በድጋሜ እስኪታይ ድረስ ጠበቅሁና ያዝሁት ዙሪያውንም አሽከረከርኩት። ከዛ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ጀርባ ጋኔኑን ወረወርኩት እና አንዴ ጮኸና ጠፋ። በዛ ቅጽበት **ኢየሱስ** መጣና እንዲህ በማለት አጨበጨበ:- ***"የእኔ ተወዳጅ ሁ-ሱንግ፣ እነዚህን ኢጋንንት የማሠቃየት ደረጃን በስተመጨረሻ አሳድገሃል። እኮራብሃለሁ። በጣም እኮራብሃለሁ።"***

አንዳንድ ጊዜ በስብከቶች ጊዜ መላእክት በፓስተራችን ራስ ላይ አንድ የዘይት አይነት ሲያፈሱ አይቻለሁ እና የእርሱ ስብከቶች የበለጠ በኃይል ያስተጋባሉ። ስብከቶቹ ስለ አንዳንድ የኢጋንንቶች ማንነት ሲሆን እነዛ አጋንንቶች በምስጢር በአንድ ጥግ ይደበቁና በአስፈሪ አስተያየቶች በፍርሀት ይንቀጠቀጣሉ።

**ኪም, ጁ-ኢዩን:**

*'ክብር፣ ክብር፣ ሃሌ ሉያ እያልሁ እየዘመርሁ ነበረ እና አካሌ በእሳት ላይ ነበረ። ቤቱ ውስጥ በጣም ይቀዘቅዝ ነበር እኔ ግን እንደ እብድ እያላበኝ ነበር። ሀክ-ሱንግ ተዋግቶት የነበረው ያው ጋኔን፣ ዓይኖቹን በተሳሳተ ሁኔታ መልሶ ከቷቸው የነበረው እያማረረ ነበረ:- "አህ ሰው፣ በመጥፎው ሀክ-ሱንግ ምክንያት እየተሠቃየሁ ነው። እሱ ይህን አደረገ።"* እኔም መለስሁ:- *"ያ በጣም ጥሩ ነው! ይህን በመስማቴ ደስ ብሎኛል።"* ማልቀስ ጀመረና እንዲህ አለ:- *"አቁሚ! እባክሽን ያንን አቁሚ።"* እኔም እንዲህ በማለት ጮህኩኝ:- *"አንተ ቆሻሻ ጋኔን፣ በ**ኢየሱስ** ስም ከእኔ ሽሽ!" ጋኔኑም ሸሸ።*

አንድ ነገር ልብሶቼን መጎተት ጀመረ፣ እኔ ግን አንዳች ማየት አልቻልሁም። ደግሞም በጸጉሬ ላይ አንድ ጠንካራ ጉተታ እና በጎኔ ላይ አንድ መነካካት ተሰማኝ። ዙሪያውን የሚሽከረከር አንድ እንግዳ ነገር አስተዋልሁ። በእሱ እንዴት ተናድጄ እንደነበርኩ ለዚህ ጋኔን ነገርሁት፣ እና ጋኔኑም መለሰ:- *"በእውን? ጥሩ፣ በእኔ ምክንያት ተበሳጪ። እባክሽን እኔ ወደ ሲኦል ላመጣሽ እየሞከርኩ ነው። አንቺ ትንሽ ተባይ ለምንድን ነው በጣም ብዙ የምትጸልዪው? መጸለይ አቁሚ። ስትጸልዪ የምትበዪው አንዳች ታገኛለሽ? ለምንድ ነው የምትጸልዪው?"* እኔም ወዲያው መለስሁ:- *"ሂይ፣ ሰጸልይ ተአምራቶች ይሆናሉ እና እኔም ሽልማት አከማቻለሁ። አንተ ጋኔን ከእኔ ሽሽ!"* ወዲያውኑ ተጠቅልሎ ሄደ።

በኋላ፣ ሁለት ራሶች ባሉት አንድ ግዙፍ እባብ ደንግጬ ነበር። ከዘንዶ (ከአናኮንዳ) ይበልጥ ስለነበረና በድንገት ወደ እኔ መምጣት ስለጀመረ በፍርሀት እየተንቀጠቀጥሁ ደንግጬ ነበር። እኔም እንዲህ ጮህኩኝ:- *"**ኢየሱስ** ሆይ እርዳኝ! እባክህን ይህን አስከፊ እባብ እንዲጠፉ አድርግ!"* **ኢየሱስ** ወዲያውኑ መጣና እባቡን ያዘው። **ኢየሱስ**ም እባቡን በጣም በፍጥነት ያሽከረክረው ጀመረ እና አርቆ ወረወረው። እኔም **ኢየሱስ**ን አመሰገንሁት እና እርሱ እንዲህ አለ:- ***"የእኔ ተወዳጅ ሰሊጥ፣ ስሜን በጠራሽ ቁጥር ሁል ጊዜ እዚህ እሆንና እረዳሻለሁ፣ ስለዚህ አትጨነቂ። ማድረግ ያለብሽ ሁሉ በትጋት መጸለይ ነው።"***

**ወደ መንግሥተ ሰማይ ሊያመጣችሁ የሚችል ጸሎት*

ዛሬ ሁለት ውብ መላእክት በቀስታ ሲወርዱ አየሁ። እነርሱ ከሰዎች ይበልጥ በጣም ረጅሞች ናቸው እና በትህትና እንዲህ አሉ:- *"ሰላምታዎች፣ እህት ጁ-ኢዩን።"* በእጆቻቸው ውስጥ በጀርባው ላይ ክንፎች ያሉት አንድ የሚያምር በድምቀት የሚያበራ ልብስ ነበረ። *"እህት ጁ-ኢዩን ይህ ልብስ በጣም ያምራል፣ አይደለም እንዴ?"*



እኔም መለስሁ:- *"አሁን ልሞክረው እፈልጋለሁ።"* እነርሱም እቅፍ አድርገው በእርጋታ አለበሱኝ። መላእክቱ በሁለቱም ጎኖቼ በኩል ቆሙና ክንዶቼን ያዙ። በጥንካሬ ተሞልቼ ነበረ እናም ወደ ላይ ወደ መንግሥተ ሰማይ በረርን። ቶሎ፣ ህዋን ትተን ሄድን እና መሬት የበለጠ እየራቀ መጣ።

የሚልክ ዌይ ከዋክብቶች ዙሪያውን ሁሉ ተበታትነው ወደነበረበት አንድ ቦታ በረርን። እጅብ ድንቅ ውብ ነበረ። ሁለቱም ክንዶቼ ወደ ጎኔ ዘና አሉ እና ልብሴ ላይ ያሉት ክንፎች እርስ በእርሳቸውን እያማቱ ለመብረር ሲሞክሩ አየሁ። በሆነ ምክንያት ከዚህ በኋላ ወደ ፊት መሄድ አልቻልንም። እኔም እንዲህ ብዬ አሰብሁ:- *"መንገዱን ሁሉ ተጉዤ ወደ መንግሥተ ሰማይ መሄድ ፈልጌአለሁ፣ ነገር ግን እዚህ ምንድን ነው እየተደረገ ያለው?"* መላእክቱም እንዲህ አብራሩልኝ:- *"ምክንያቱ አንቺ የሚበቃ ያህል በኃይል ስላልጸለይሽ ነው፣ ስለዚህም እዚህ ድረስ ብቻ ነው መጓዝ የቻልነው።"* ቅር ተሰኝቼ ነበር እና ወደ ምድር መመለስ ጀመርን።

ምድር (መሬት) ከጠፈር ስትታይ በጣም ውብ ትመስላለች፣ ነገር ግን ይህን ያህል ትንሽ ፕላኔት እንደነበረች ላምን አልቻልሁም። ዛሬ በቀሩ አጋጣሚዎች ተሞልቶ ነበረ፣ እኔ ግን ስለ ጸሎት አንድ ጠቃሚ ትምሕርት ተማርሁ። በጸሎት ወደ መንግሥተ ሰማይ መንገዱን ሁሉ ለመጓዝ ጥንካሬዬን ሁሉ ወደ ጸሎት ውስጥ መሰብሰብ አለብኝ።

**እህት, ቤይክ ቦንግ-ንዮ:** **ከኢየሱስ ጋር ሽርሽር መውሰድ*

እየጸለይሁ እያለ **ኢየሱስ** ሲኦልን ለመጎብኘት ወሰደኝ። ቶሎ አንድ ግዙፍ አምድ ታየ፣ በላዩ ላይ ነገሮች ሲጓዙበት በደንብ ግልጽ ባልሆነ (በደበዘዘ) ሁኔታ ማየት ቻልሁ። በቅርበት ስመለከት የማይቆጠሩ ሺሆች ሰዎች ተጣብቀውበት እንደነበሩ አየሁ። እነሱ እርቃናቸውን ነበሩ እና መነቃነቅ (መንቀሳቀስ) እንኳ እስከማይችሉ በጣም በጥብቅ ታስረው ነበረ። ሰዎቹ በሥቃይ እንደ ጮኹ ነጫጭ ትኋኖች (ጎጂ ትሎች) የእነሱን ሥጋ በልተው እየጨረሱ ነበረ። ሁሉም ሥጋ አልቆ ከነበረና አጽም ብቻ ከቀረ በኋላ ሥጋቸው ይመለስ ነበረ እና አስደንጋጩ የመከራ ጊዜ (ሥቃይ) በድጋሜ ይደገም ነበረ።

እነዚህ ልዩ ሰዎች ምን አይነት ኃጢአት ፈጽመው እንደነበር **ጌታ**ን ጠየቅሁት እና እርሱ ይህን መለሰ:- ***"እነዚህ ሰዎች የማለዳውን አገልግሎት ለአጭር ጊዜ በግድ የለሽነት የተካፈሉና ወደ ዓለም ለመሄድና በዓለም ለመደሰት በፍጥነት ከአገልግሎቱ የሚወጡ ናቸው፣ በፍፃሜያቸው በመኪና አደጋ ለመሞት ብቻ። ደግሞ፣ ቤተ ክርስቲያን የተካፈሉ ነገር ግን ከዝግ በሮች በስተጀርባ የጠጡ አንዳንዴም ቡና ቤቶችን የጎበኙ ሰዎች አሉ፣ እንዲሁም ጌታን በፍፁም ሳይለማመዱት ቤተ ክርስቲያን እንደ ደንብ ማሟያ የተካፈሉ ሰዎች አሉ።"***

አስደንጮቹን ሁኔታዎች መሸከም ስላልቻልሁ **ኢየሱስ** ከቦታው እንዲወስደኝ ለመንሁት። እርሱም:- ***"ደህና፣ አሁን ወደ መንግሥተ ሰማይ እንሂድ?"*** አለ። እርሱ እጄን ያዘና በሰማያዊ ሰማዮች ውስጥ እየበረርን በዔድን ገነት ውስጥ ደረስን። **ኢየሱስ**ና እኔ በገነት ውስጥ ክንዶቻችንን በአንድ ላይ ቆላለፍን እና የሚበልጥ ደስ የሚል ጉብኝት ነበረን። እንዴት ደስተኛ እንደነበርሁ በማየት **ኢየሱስ** በእርጋታ እንዲህ አንሾካሾከልኝ:- ***"የእኔ ተወዳጅ ቦንግ-ንዮ፣ ጤናሽ በጣም ጥሩ አይደለም? አሁን የእውን ከባድ ነው፣ ነገር ግን አንቺ መጽናት አለብሽ።"*** የእርሱ ቃሎች ሁል ጊዜ ያጽናኑኛል እና ወደ ማንባት ይወስዱኛል። (2ኛ ቆሮንቶስ 1:5)

**ፓስተር, ኪም የንግ-ዱ:** **እንደ ኤሌክትሪክ ንዝረት*

ከባለፈው ቀን የአጋንንት ጥቃት አሁንም ድረስ በታላቅ ሥቃይ ውስጥ ነበርሁ። **እግዚአብሔር** ግን በደግነቱ ልቋቋም ከምችለው የሥቃይ መጠን ጋር ስብከቶችን እንዳቀርብና ምስጋናዎችን እንድዘምር አስቻለኝ። በሁሉም ጥንካሬዬ እጆቼ ወደ ላይ ከፍ ብለው ጸለይሁ። ከኤሌክትሪክ ጋር የተገናኙ ንዝረቶች (electrical shocks) በሁለቱም እጆች ውስጥ ሲገቡ ይሰማኝ ጀመረ። የኤሌክትሪክ ፍሰቱ ጠንካራ ነበረ እና በእያንዳንዱ የሰውነቴ ክፍል ውስጥ ያለማቋረጥ ጎረፈ።

**እግዚአብሔር** የቅባት ዘይት በላዬ ላይ አፈሰሰ፣ ነገር ግን አካላዊ ሥቃዬ እያነሰ አልሄደም። እጆቼ ወደ ላይ ከፍ ተደርገው መጸለይ የሚያሰቅቅ ከባድ ነበር። በመርፌ እንደ ተወጋሁ ሆኖ ድንገተኛ ሀይለኛ ሥቃይ የተማኝ ጊዜያት ነበሩ። ከዛ ክንዶቼን አወርድ ነበረ። ሥቃዩ ቀለል ሲል፣ ለመጸለይ እጆቼን መልሼ ወደ ላይ አነሳቸዋለሁ እና ይህን ብዙ ጊዜ እደጋግመዋለሁ።

እጆቼን ወደ ላይ ከፍ አድርጌ ለመጸለይ ወስኜና ቆርጬ ነበር። በድንገት ግራ መዳፌ በቀስታ ወደ ውጪ መንቀሳቀስ ጀመረ። ከዛ የበለጠ ተሰማኝ እና በአንድ ሰዓት ውስጥ ግራ እጄ ወደ ውስጥ ከመሆን ወደ ውጪ ሙሉ ለሙሉ ዞረ። ቀኝ እጄ ከውስጥ ወደ ውጫዊው ለመንቀሳቀስ ሦስት ሰዓታት ያህል ፈጅቷል። በእንደዚህ አይነት አኳኋን ረዘም ላሉ ሰዓታት ቆይቼ ነበር። ሁለቱም ክንዶቼና እጆቼ ደንዝዘው ነበረ እና በእንደዛ ሁኔታ ከአራት ሰዓታት በላይ ጸለይሁ። በጣም የሚያሰቃይ ነበር።

*እያንዳንዱን ኃጢአት መናዘዝ*

ይህ ሥራ የእውነት ከጌታ መሆኑን አላውቅም ነበር፣ ስለዚህም እንዲህ ብዬ ጮህኩኝ፡- *"ሰይጣን ከእኔ ተወገድ! ከእኔ ሂድ!"* **ኢየሱስ** ምንም ቃላት አላሰማም። በዛ ፈንታ እርሱ በሚንቀጠቀጠው አካሌ ውስጥ ደስታ፣ ሰላም፣ እና የ**መንፈስ ቅዱስ**ን እሳት አፈሰሰ። በህይወቴ የበፊቶቹን ኃጢአቶች ማስታወስ ጀመርሁ፣ ስለዚህ ንስሐ መግባት መናዘዝ ጀመርሁ። እንደ ፓስተር ተገቢ ያልሆነ ህይወቴንና ስፖርቶችን የመጫወት ሱሶቼን ተናዘዝሁ። ያ ኃጢአት በቸልተኛነት **ጌታ**ን እንዳገለግል አስከተለኝ። ስለ እያንዳንዱ ኃጢአት ንስሐ ለመግባት ሞከርሁ። ሁለቱም ክንዶችና እጆች ተጠማዘው ከሥቃዩ የተነሳ እስከወድቅ ድረስ ባለኝ ሁሉ መጸለይ ቀጠልሁ።

*"ነገር ግን እንደ ጥንካሬህና ንስሐ እንደማይገባ ልብህ የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ በሚገለጥበት በቁጣ ቀን ቁጣን በራስህ ላይ ታከማቻለህ።"* (ወደ ሮሜ 2:5)

ስፖርቶችን የእውነት እወዳለሁ እና ስጫወት ስለ **ጌታ** ፈፅሞ በመርሳት በጥልቅ እሳተፋለሁ። ይህ እርሱን ያሳዝነዋል። የእኔ ሱስ የቦውሊንግ ጨዋታ፣ የእግር ኳስ ጫወታ፣ እና በተለይም የባድሚንተን ጨዋታን በማካተት ሰፊ የስፖርት መስኮችን ይሸፍናል። ተስማሚ አቋም እንዲኖረኝ ከልብ እፈልግ ነበር፣ ነገር ግን እኔ በስፖርት በጣም ብዙ ጊዜ አጠፋሁ። ከሚነራል ስፕሪንግ ዋተር የመዝናኛ ቦታ (ከማዕድን ምንጭ ውሃ የመዝናኛ ቦታ) አጠገብ በሚገኘው የባድሚንተን መጫወቻ ቦታ በተደጋጋሚ ብዙ ጊዜ እሄድ ነበር። ጭንቀቴን ሁሉ እዛ እተዋለሁ። ስፖርቶችን መጫወት ስህተት አይደለም፣ ነገር ግን የምናደርጋቸው ብዙ ነገሮች አስቀድመው አዕምሮዋችንን ሊይዙ ይችላሉ። መንፈሳዊውን ዓለም በጥልቀት በተለማመድሁ ቁጥር ስፖርቶችን መውደዴ ሱስ ውስጥ እንዳስጠመደኝ ተገነዘብሁ። እነዚህ መሠናክሎች መጠራቀምና መንፈሳዊ እድገቴን መጉዳት ቀጠሉ። ስቅስቅ ብዬ አለቀስሁና ስለ ሁሉ ነገር ንስሐ ገባሁ።

በህይወቴ አንድ ጊዜ ሁሉም የቤተ ክርስቲያን አባላቶቼ ሌላ ቤተ ክርስቲያናት ለመካፈል ትተው ሄዱ እና ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የቀረ አንድ ሽማግሌ ሰው ብቻ ነበረኝ። በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያኑ እያደገ አልነበረም። እንደመታደል በደምብ የማውቀው አንድ ፓስተር ከሲዖውል (በደቡብ ኮሪያ የሚገኝ የአንድ ከተማ ስም ነው) በብዙ መቶዎች የሚሆኑ አባላት ላሉት አንድ ቤተ ክርስቲያን እንደ ዋና ፓስተርነት (ዋና ካህንነት) አንድ ቦታ አቀረበልኝ። *"ኦዎ ይህ በጣም ታላቅ ነው!"* ብዬ አሰብሁ፣ አቅራቦቱን ለመውሰድ ተዘጋጀሁ። ከመሄጃዬ በፊት በነበረው ቀን እየጸለይሁ እያለ **ኢየሱስ** ከመንግሥተ ሰማይ ላይኛው ጫፍ እስከ መሬት ድረስ የተዘረጋ አንድ እጅግ በጣም ረጅም ዘንግ ይዞ ታየ። **ኢየሱስ** እንድንበረከክና እንድሰግድ አዘዘኝ፣ ስለዚህም አክብሬ ታዘዝሁኝ። **ኢየሱስ** ያንን ረጅም ዘንግ ያዘና በታላቅ ኃይል መታኝ። አልጎዳኝም ነበር እና ለእኔ ያለውን የ**ጌታ**ን ፍቅር ተሰማኝ። ነገር ግን የእርሱ ፊት በሀዘን ተሞልቶና እንባዎች በፊቱ ላይ እየተንጠባጠቡ ነበረ። **ኢየሱስ** ጠየቀኝ፡- ***"የእኔ ተወዳጅ አገልጋይ፣ የቤተ ክርስቲያን አባላቶችህ በቁጥር እየበዙ ሲሄዱ ምን ማድረግ ትፈልጋለህ? ፓስተር ኪም ዮንግ-ዱ! ፓስተር ኪም ለመቅደሱ ምን አይነት መብዓ ታቀርባለህ?"*** ለ**ጌታ** አንድም መልስ መመለስ አልቻልሁም። መልሶቼ የአሣፋሪ ልቤን እውነት እንደሚያወጡ አውቄ ነበር።

ፓስተሮች በአንድ ላይ ሲሰባሰቡ እያንዳንዳችን ስለ *'ቤተ ክርስቲያን ፈጣን እድገት'*፣ *'ምን ያህል በቁጥር እንደተሰባሰቡ'*፣ *'ቤተ ክርስቲያን ለመገንባት ምን ያህል አመታት እንደሚወስድ'*፣ *'የትኛው ፓስተር ባልደረባቸው ፊተኛው ራጭ ሰው እንደሆነ'* እናወራለን። ደግሜ አሰማቸው የነበሩ አንድ አይነት መልሶች እነዚህ እንደነበሩ አውቅ ነበር። በ**ጌታ** ፊት ዝቅ ካለ ራሴ ጋር ጉልበቴ ተንበርክኮ፣ ራሴን ልቋቋመው አልቻልሁም እና በጣም አፍሬ ነበር። አንዳች ማድረግ ስላልቻልሁ አለቀስሁ። **ኢየሱስ** በእርጋታ ጀርባዬን አሻሸና በመልካም ልባዊነቱ አጽናናኝ።

*“የእኔ ተወዳጅ አገልጋይ፣ የግንባታ እርዳታ መብዓዎችህን ፈልጌ አውቃለሁ? ቤተ ክርስቲያንህ በቁጥር መሻሻል (መነቃቃት) እንዲኖረው ፈልጌአለሁ? እነዚህን ነገሮች በልብህ ውስጥ ኢታስቀምጥ፣ ነገር ግን እኔ የምሻውን እንድትከተል እፈልጋለሁ። የጠፉ በጎቼን እንድትፈልግና እንድታገኝ እፈልጋለሁ፣ እና ቁጥሩ ምንም ይሁን፣ አንድም ወይም መቶ በግ ይሁን። ታላቅ እንክብካቤ እንድታደርግላቸው እኔ እፈልጋለሁ። በጣም በትናንሽ ነገሮች ታማኝ ሁን። በዙሪያህ ባሉ በትላልቅ ነገሮች አትዘናጋ፣ ነገር ግን በትጋት ጸልይና በእኔ ጊዜ ጠብቅ። በመጨረሻ፣ ተስፋ የቆረጥህ አትሁን።”*

**የፓስተር ሚስት, ካንግ ህዩን-ጃ:** **ከተዋረደ መንፈስ የሆነ ጸሎት*

ፓስተራችን ላይ እንደሆነው ዛሬ የእኔ እጆች ደግሞ እየዞሩ (እየተጠማዘዙ) ነበረ። **ኢየሱስ** ያንን በጁ-ኢዩን ትንቢት የመናገር ስጦታ በኩል ለእኛ አብራራ። ለአንድ ፓስተርና ለሚስቱ መንፈሳዊ ዓይኖቻቸው እንዲከፈቱ የበለጠ አስቸጋሪ ይሆን ነበር፣ አንድ በጣም አስቸጋሪ ሂደት ነው። ብዙ የተለያዩ የጸሎት አይነቶች አሉ፣ ነገር ግን እጅግ በጣም ኃይለኛው የጸሎት አይነት ሂደቱን የሚያፋጥነው በእንባ ንስሐ መግባት (በሃዘን መጸጸት) አንዱ ነው።

ከሌሎች ጋር ሲነፃፀር፣ በጣም በተደጋጋሚ እንባዎችን አላፈስስም። በጠንካራው ማንነቴ (ስብዕናዬ) ምክንያት ሊሆን ይችላል። ምንም ያህል በህይል እየጸለይሁና ወደ **ጌታ** እየተጣራሁ የሞከርሁ ቢሆንም እንኳ ማልቀስ አልቻልሁም። ፓስተሩን ለእርዳታ ጠየቅሁ እናም የተዋረደ መንፈስ እንደጎደለኝ ነገረኝ። **ጌታ**ን የተዋረደ መንፈስ እንድጠይቀውም አበረታታኝ።

*“እግዚአብሔር ልባቸው ለተሰበረ ቅርብ ነው፣ መንፈሳቸው የተሰበረውንም ያድናቸዋል።”* (*መዝሙረ ዳዊት* 34:18)

ከሰዓት በኋላ ሁሉ በተዋረደና በተጸጸተ ልብ ጸለይሁ እና **ጌታ** የንስሐ እንባዎችን በረከት በእኔ ላይ አፈሰሰ። ***መንፈስ ቅዱስ*** በእንባዎችና በላብ ሸፈነኝ። መቆጣጠር በማይቻል መልኩ ሳለቅስ በእንባዎች ተሞልቼ ነበር። በጁ-ኢዩን በኩል እየተናገረ **እግዚአብሔር** የእንባ ንስሐዬ ለእርሱ ተቀባይነት እንደነበረው ነገረኝ።

እያደረግነው በነበረው በሁሉም *ሥራ*፣ ጠላት ለማጥቃት ሁል ጊዜ አጋጣሚ ይጠብቅ ነበር። መከላከያችንን በፍጹም ማውረድ አልቻልንም። ሰይጣናዊ ማንነቶች የዕይታ መንፈሳዊ ስጦታ ላላቸው ለታዳጊ አባላቶች መገለጽ ከጀመሩ ጀምሮ፣ በጸሎት በኃይል ራሳቸውን ማስታጠቅ ነበረባቸው። **ኢየሱስ** በእነዚህ በህይወትና ሞት ትግሎች እንድንዋጋ ለምን እኛን እንደመረጠን አናውቅም፣ በጣም የደከምን ከመሆናችን የተነሳ።

**ኢየሱስ** ይህን ነግሮናል:- ***“እናንተ የጌታ ቤተ ክርስቲያን ትንንሽ በጎች ከፉ መናፍስትን በመዋጋት ብቻ እምነታችሁን ማቆየት ችላችኋል። እመኑኝ። እጄን ያዙና ሂዱ። ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ስለምሆን አትጨነቁ።”***

## ==== ቀን 20 ==== (የሐዋርያት *ሥራ* 1:8) **ኪም, ጁ-ኢዩን አጋንንቱን አጠቃች!*

አጋንንትን እንዳንፈራ ነገር ግን በቀጥታ እንድናጠቃቸው ፓስተሩ ነግሮናል። እርሱ እንዲህ ጮኸ:- *“እርገጧቸውና እንዲሠቃዩ አድርጓቸው! ዓይኖቻቸውን አውጡና ፍጪቸው። ያዟቸውና በዙሪያው ሁሉ አንቀጥቅጧቸው።”* በጣም አስደሳች ነበር እና አንድ ድንገተኛ ሀይል ሰጠኝ። በቀላሉ የምፈራ ስለሆንኩ በፍጹም ፍርሀት እንዳላሳይ አለበለዚያ አጋንንት የበለጠ እንደሚያጠቁ ፓስተሩ ነገረኝ። ጠንካራ ለመሆንና መከራን ለመቋቋም ቆርጬ ነበር።

በመጀመሪያ ያየሁት ጋኔን በጣም የደነገጥሁበት ነበር። ነጭ ልብስ የለበሰች ሴት ጋኔን ነበረች። በሚያስደነግጥ ለቅሶ ስትመጣ ብጉር እንዲኖረኝ (እንዲወጣብኝ) አደረገች። ተደናግጬ ነበር ነገር ግን ጥንካሬዬን ሁሉ አሰባስቤ ጸጉሯን ያዝኩና በፍጥነት ሳብኩት። (የጌታችንና የመድኃኒታችን የአምላካችን የ**ኢየሱስ ክርስቶስ** ወንጌል በማርቆስ 9:23) ።

እሷም እንዲህ አለቀሰች፡- *“አውች! እንድሄድ ፍቀጂልኝ! እየጎዳሸኝ ነው። አሁኑኑ ልቀቂ! እየጎዳኝ ነው!”* ሁሉንም ጸጉሯን እስክነቅለው ድረስ ያለ ምህረት ሳብኩት። እርሷም እንዲህ አለቀሰች፡- *“ጸጉሬ! ጸጉሬ!”* ከዛ ጠፋች።

ትልቅ ራስ ያለው አንድ ወንድ ጋኔን ሊያስፈራራኝ ሞከረ። አፉን በሰፊው ከፍቶ ቀረበኝ። አፉን ገነጠልኩት፣ ዓይኖቹንም አወጣኋቸውና ረገጥኳቸው። ጋኔኑም እንዲህ ጮኸ፡- *“አውች! ዓይኖቼ! አፌ! የት ነው ያሉት? ፈልጊያቸው! ያሳምማል!”* በጭንቀትና በችኮላ መሬቱ ላይ ፈለገ፣ ነገር ግን ስላላገኛቸው ጠፋ።

በኋላ ማጭድ ቅርጽ (ግማሽ ጨረቃ) አይነት ዓይን ያለው አንድ ጋኔን መጣ። ወደ ቁርጥራጮች ገነጣጠልኩትና ጮህኩበት። ጋኔኑም የተገነጣጠሉ የአካል ክፍሎቹን ሰበሰበና እንዲህ እያለ ሮጠ፡- *“ወደ አንቺ እመለሳለሁ። ታያለሽ።”*

**ሰይጣናዊ ስብሰባዎች እና ለሰማያዊ የጦር እቃዎች የጸሎት መጠይቆች*

በኋላ፣ እየጸለይሁ እያለ ጥግ ላይ አንድ የአጋንንቶች ቡድን ሲያወሩ ሰማሁ። 30 የሚሆኑ አጋንንቶች ስብሰባ በማድረግ ክብ ሰርተው ተቀምጠው አየሁ። ትልቁ ማዕረግ ያለው ጋኔን እንዲህ እያለ ነበር፡- *“የጌታን ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ልንተወው ነው? ፍጠኑና ከጸሎት አምታቷቸው (አዘናጓቸው)። እናንተ መጥፎዎች አንድ ነገር አድርጉ!”* ሌላ ጋኔን እንዲህ አለ፡- *“ያቺን አስቀያሚ ሴት ልጅ ጁ-ኢዩንን ታውቋታላችሁ? ሰሊጥ የምትባለውን ያቺን ሴት ልጅ! እንደ እሷ ባለ መሸነፍ የሚያሳፍር አይደለም እንዴ?”* ሌላው እንዲህ ጮኸ፡- *“እኔስ? አፌ ተገንጥሎ ተከፍቶ ነበረ! በጣም እየደማሁ ነበር።”* ሌላውም እንዲህ ጮኸ፡- *“ሄይ፣ እናንተ የደረሰባችሁ ምንም አይደል! እኔ ሁሉንም ጸጉሬን አጥቻለሁ እና አሁን ፍፁም መላጣ ነኝ! አሁን ምን እናድርግ?”*

በኋላ፣ አንድ ራስ ቅል ጋኔን ስላጠቃኝ በፍጥነት እንዲህ ጸለይሁ፡- “***ጌታ** ሆይ! መጥረቢያ ስጠኝ!*” ወዲያውኑ ከአጠገቤ አንድ መጥረቢያ ነበረ። ጋኔኑ ሲቀርብ መጥረቢያውን ያዝሁና ወደ ቁርጥራጮች እስኪፈረካከስ ድረስ ተረከኩት።

**ሊ, ዩ-ክዩንግ:** **ዩ-ክዩንግ አጋንንትን አጠቃች!*

ዛሬ መጸለይ እንደጀመርሁ ነጭ ጋውን ለብሳ አንድ ሴት ጋኔን ብቅ አለች። የውሻ ክራንቻ የሚመስሉ ረጃጅም ሹል ጥርሶች ነበሯት እና በአፏ ዙሪያ ሁሉ ደም ነበራት። በተግሳጼ ስላልሸሸች ጸጉሯን ያዝሁና ዙሪያውን እያሽከረከርኋት በጣም በሀይል ጠመዘዝኩት። *“አውች! ጸጉሬን ልቀቂ። አሁኑኑ ልቀቂው! እባክሽን!”* አለቀሰች። በጣም የመደሰት ስሜት ተሰማኝ፣ እንዲህም አልሁ፡- *“አንተ ቆሻሻ ጋኔን እስከ አሁን ድረስ በጣም ስፈራህ ነበር! የሚገባህን ማግኘት የአንተ ተራ ነው!”* ጸጉሯን ሁሉ በመንቀል ያለማቋረጥ ዙሪያውን አሽከረከርኳት እና እሷም ጮክ ባለ ድምጽ እንዲህ እያለች ረዘም ላለ ጊዜ አለቀሰች፡- *“ስትሞቺ ወደ ሲኦል ውስጥ እንደምጎትትሽ (እንደማወርድሽ) እርግጠኛ እሆናለሁ!”* ከዛ ሄደች።

በኋላ አንድ ራሰ በራ የሆነ ወንድ ጋኔን ቀረበኝ። ያዝኩትና በጭንቅላቱ ወደ መሬት ጣልኩት። *“አውች! እኔ እዚህ እየሞትኩ ነው! እኔን በጭንቅላቴ መጣል አቁሚ!”* በማለት ጮኸ። እኔ በጣም በብዙ እየተደሰትኩ ነበር። በጣም በኃይል ስጫን ጋኔኑ ተንሰቅስቆ አለቀሰ። ከዛ ጋኔኑን በሙሉ ኃይል መታሁት እና ወደ ጥጉ ውስጥ ወደቀ።

መጸለይ እየቀጠልሁ እያለ **ኢየሱስ** ከፊቴ እንዲህ በማለት ታየ፡- ***“የእኔ ልባዊ ተወዳጅ ዩ-ክዩንግ፣ እምነትሽ እጅግ በጣም አድጓል። አሁን አጋንንቶችን በጡጫሽ የእውን መጉዳት ችለሻል።”*** እርሱ ፈገግ አለ። እኔም እንዲህ አልሁ፡- “***ኢየሱስ** ሆይ፣ ወደ መንግሥተ ሰማይ መሄድ እፈልጋለሁ!*” እርሱ ሲኦልን እንድንጎበኝ አጥብቆ ፈለገ።

ወደ ሲኦል ስንሄድ ከእሳቱ የተነሳ ግሎ ቀይ ወደ ሆነ አንድ ግዙፍ የብረት ማሰሮ ወዳለበት አንድ ቦታ መጣን። **ኢየሱስ** እንዲህ አለ፡- ***“ዩ-ክዩንግ፣ ማሰሮው ውስጥ በጥንቃቄ ተመልከቺና እዛ ማን እንዳለ እዩ።”***

እኔም በጥንቃቄ ተመለከትሁ እና አያቴን ከሌላ ሰው ጋር ውስጡ አየሁ። ሁለቱም እንዲህ እየጮሁ ወደላይና ወደታች እየዘለሉ ነበር:- *“አውች! እባካችሁ እዚህ በጣም ሞቃት ነው!”*

አያቴ ስታየኝ እንዲህ አለች:- *“ዩ-ክዩንግ፣ ይህን የሚያሰቃይ ሙቀት ከዚህ በላይ መቋቋም አልቻልኩም! እባክሽን ኢያትሽን እርጂ። ከዚህ ለመውጣት እንዲረዳኝ **ጌታ**ን ጠይቂው።”* ምን ማድረግ እንዳለባት አላወቀችም፤ በሀይል (በጣም በቁጣ) ዙሪያውን እየሮጠች ነበር። የእርሷ ነጭ ልብስ እንኳ እየተቀጣጠለ ነበረ። አያቴ እንዲህ ጮኸች:- *“ዩ-ክዩንግ፣ እዚህ በመሆንሽ ደስተኛ ነኝ። እባክሽን ከዚህ እንድታወጪኝ እለምንሻለሁ! ይህን እሳት ከዚህ በላይ መሸከም አልችልም።”* እኔም እጄን በመዘርጋት እርሷን ለማውጣት ሞከርሁ፣ ነገር ግን **ጌታ** ማድረግ እንደማልችል በጥብቅ አስታወሰኝ።

*“**ኢየሱስ** ሆይ፣ እርሷን በጣም በብዙ ሥቃይ ውስጥ ሆና ኢያየኋት ልቤ እጅግ ኢያዘነ ነው። ምን ማድረግ እችላለሁ?”* አለቀስሁ። **ኢየሱስ** በጥብቅ አቀፈኝና እንባዎቼን ሁሉ አበሰ። ትተን መሄድ ጀመርን ነገር ግን አንድ የሚያስፈራ ጋኔን ከፊታችን ታየ። **ኢየሱስ** እንዲህ ጮኸ:- ***“ጁ-ኢዩንን ወይም ዩ-ክዩንግን ብትረብሻቸው እኔ ወዲያውኑ በሲኦል ውስጥ ወደ እሳቱ ጉድጓድ ውስጥ እወረውርሃለሁ!”*** ጭንቅላቱን አዘነበለና ሸሸ። **ኢየሱስ** እጄን ያዘና መልሶ ወደ ቤተ ክርስቲያን መራኝ እና እርሱ ወደ መንግሥተ ሰማይ ተመለሰ።

**ሊ, ሀክ-ሱንግ:** **የብረት ጭምብል ውስጥ ያለው ጋኔን*

እየጸለይሁ እያለ ነጭ የብረት ጭምብል ያደረገ አንድ ጡንቻማ ወንድ ጋኔን አንድ ትልቅ ሰይፍ ያወዛውዝብኝ ጀመረ። አልፈራሁም። በዛ ፈንታ ሰይፉን ወሰድኩበትና የጋኔኑን ራስ በሰይፉ መታሁት። ብረት ከብረት ጋር እየተጋጨ ሲያቃጭል መስማት ችዬ ነበር። ጭምብሉን ገነጠልኩት እና ፊቱ ላይ ሁሉ አጸያፊ ትሎችን አየሁ።



ጭስ ከላዩ ላይ የሚወጣ ሌላ ጋኔን ብቅ አለ። ቶሎ ጭሱ የሰውን ቅርጽ ያዘ። በጭሱ ውስጥ ሰዎች ተጠምደው እርዳታ እየለመኑ ማየት ችዬ ነበር። ይህ ጋኔን ሰዎች እንደዋጠ አወቄአለሁ። ወደ **ኢየሱስ** እየተጣራሁ በልሳኖች መጸለይ ጀመርሁ። *“**ኢየሱስ** ሆይ እርዳኝ! ጋኔኑ ሊውጠኝ እየሞከረ ነው። ፍጠንና እርዳኝ!”* እንደተጣራሁ **ጌታ** ወዲያውኑ ታየና አጋንንቱን አጠፋቸው።

ከጥቂት ቆይታ በኋላ ዙሪያውን ቀንዶች ያሉት አንድ ጋኔን አንድ ትልቅ ጥቁር ሰሌዳ ተሸክሞ መጣ። እንዲህም አለ:- *“አመጻለይ አቁሚ። መጸለይ አቁሚ!”* ችላ አልኩትና በልሳኖች መጸለይ ቀጠልሁ። ጥቁር ሰሌዳውን መፋቅ (መቧጠጥ) ጀመረ። ያን ድምጽ መታገሥ አልቻልሁም። ጆሮዎቼን ደፈንሁና እንዲህ በማለት ጮህኩኝ:- *“ሰይጣን፣ በ**ኢየሱስ** ስም ጥፋ!”* እንዲህ እያለ ሰሌዳውን መፋቅ ቀጠለ:- *“ሄይ፣ ይህ አስደሳች ነው!”* እኔም እንዲህ አለቀስኩኝ:- *“**ኢየሱስ** እባክህን እርዳኝ። ይህ ክፉ ጋኔን እያሠቃየኝ ነው!”* **ኢየሱስ** በብርሃን ታየ እና ጋኔኑ ወደ ኋላ ሳይመለከት ሮጠ።

# ==== ቀን 21 ====

**ኪም, ጁ-ኢዩን:**

በልሳኖች እየጸለይሁ በእሳት ላይ ነበርሁ። ሶስት አስፈሪ ድራጎኖች ታዩ። የመጀመሪያው ድራጎን የተለያዩ ሁኔታዎችና ክብ ቅርፆች በቀይ አካሉ ዙሪያ ነበረው። ሁለተኛው ድራጎን ወደ እሱ ስመለከት የመመሰቃቀል ስሜት እንዲኖረኝ ያደረገ ቀይና ሰማያዊ ቋሚ መስመሮች በአንድ ላይ ተቀይጠው ነበረው። ሦስተኛው ድራጎን በአንድ ላይ የተቀየጡ ሰማያዊና ቢጫ ዝንጉርጉር አግዳሚ መስመሮች ነበሩት። እነሱ በሙሉ ሊውጡኝ እንደፈለጉ ሆነው መጡ፣ እኔ ግን በጥብቅ ሦስት ጊዜ እንዲህ ጮህኩኝ፦ "*በ**ኢየሱስ** ስም ከእኔ ሽሹ!*" እነሱም ሸሹ።

ዙሪያውን ስመለከት በርከት ያሉ አጋንንት ክብ ሰርተው ዙሪያውን በመቀመጥ ስብሰባ ይዘው ነበር። መሪው ለመላጣው ጋኔን እንዲህ አለ፦ *"አንተ፣ በዚህ ጊዜ ሂድና ሞክር!"* ወዲያውኑ ወደ እኔ መጣ፣ ነገር ግን እንደበፊቱ ራሱን ያዝኩትና ዙሪያውን በፍጥነት ሳብኩት። ዓይኖቹን አወጣኳቸሁ እና ከእኔ ሸሽቶ ሮጠ። ከዛ መቀስ ጣቶች ያሉት አንድ ጋኔን መጣ። ጋኔኑ አንድ ጥቁር ሰሌዳን ቧጠጠ። የቧጠጠውን ድምጽ ልታገስ ስላልቻልኩ የብረት ጣቶቹን ሰበርኳቸውና ፊቱን ፋቅሁት። *"ሄይ፣ ጣቶቼን መልሰሽ ስጪኝ! ለምንድ ነው ጣቶቼን የምትወስጂው! አንቺ ትንሽ ተባይ እኔ ጋር ጣልቃ አትግቢ (ከእኔ ጋር አትጣዪ) እምነትሽ እንዴት በጣም እየጠነከረ ሊመጣ ቻለ?"* በዛ (ያን በማለት) ጋኔኑ ጠፋ።

በኃይል መጸለይ ቀጠልሁ። አንድ ትልቅ እባብ በቁጡ አስተያየት ወደ እኔ እየተሳበ መጣ። ቆዳዎቹ ወደ ተለያዩ ቀለሞች ይለዋወጣል። ጭራውን ወደ ኋላና ወደ ፊት በፍጥነት በፊቴ ይወረውረዋል። እባቡን ያዝሁትና ግድግዳ ላይ ወረወርኩት። (የጌታችንና የመድኃኒታችን የ**ኢየሱስ ክርስቶስ** ቅዱስ ወንጌል በቅዱስ ማርቆስ 16:17-18) ።

ሙሉውን በፋሻ ተጠቅልሎ የነበረ አንድ ጋኔን ታየ። የቻይና ካርቱን ጋኔን ገጸ-ባህርህ *'ካንግ-ሺ'* ን አስታወሰኝ። ጋኔኑም እንዲህ አለ፦ *"ትንሿ ተመልከቺ፣ ይህ የእውን አስደሳች ነው!"* ፋሻዎቹን መተርተር ጀመረ። ከፋሻዎቹ በታች የማይቆጠሩ ትኋኖች (ትሎች)፣ መቶ እግር ያላቸው የትል ዝርያዎች፣ እና ባለ ሺ እግር ትሎች በሙሉ አካሉ ዙሪያ እየተሳቡ ነበር። አጸይፎኝ (አስጠልቶች) በአስቸኳይ **ኢየሱስ**ን ተጣራሁ፣ እና እርሱ መጥቶ ታየ፣ ጋኔኑንም ያዘና ወደ ታች ወረወረው። "***ኢየሱስ** ሆይ፣ ኢጅግ በጣም አመሰግንሃለሁ!"* እርሱም ፈገግ አለና በእርጋታ ራሴን መታ መታ አደረገ። ***"የእኔ ልባዊ ተወዳጅ ሰሊጥ፣ እምነትሽ ኢጅግ በጣም አድጓል! በትጋት ጸልዪ።"*** ዛሬ **ኢየሱስ** ደረቱ ላይ የተለያዩ ብርሃኖችን የሚፈነጥቅ አንድ ቀይ ልብ ያለው ልዩ ወርቃማ ልብስ ለብሶ ነበር።



**ኢየሱስ** ከሄደ በኋላ አንድ ጋኔን እንደ አዛውንት ሴት አያት መስሎ ብቅ አለ። እሷ ጥቁር ልብስ ለብሳ እና አንድ ረጅም መጥረቢያ ይዛ ነበር። *"አትጸልዪ! ሌላ ጊዜ አድርጊው። ዛሬ መጸለይ የለብሽም፣ ትክክል? ዛሬ መጸለይ ለምን በጣም ፈለግሽ? ነገ አድርጊው። ነገ ስትጸልዪ ኢየሱስ ያገኝሻል። በዛ ፈንታ ያንን አድርጊ።"* እሷ ጮክ በማለት ያንን ስለደገመችው እንዲህ በማለት ጮህኩኝ፦ "*ሄይ አንቺ አስቀያሚ አሮጊት፣ በ**ኢየሱስ** ስም ከእኔ ሽሺ።"* እሷም ጠፋች።

**ሊ, ዩ-ክዩንግ:**

እየጸለይሁ እያለ አንድ ጋኔን እንዲህ እያለ ቀረበኝ፦ *"አንቺ። ሄይ አንቺ! ይቅርታ ልትጠይቂኝ ኢያስፈልግሽም!"* የምሰማውን ማመን አልቻልኩም፣ ስለዚህ ያዝኩትና ፊቱን በጥፊ መታሁት።

ከዛ ግን እንዲህ በማለት ፊቴን በጥፊ መታኝ:- *"አንቺ ፊቴን በጥፊ ለመምታት ደፈርሺ? ወደዚህ ነይ። እገድልሻለሁ።"* እኔም በንዴት እየነደድኩ ስለነበር ዓይኖቹን አወጣኋቸውና ወደ ታች ወረወርኳቸው። ፊቴ ማበጥ ጀመረ እና ትንሽ መዘናጋት በጋኔን ፊቴን በጥፊ እንድመታ የማስከተሉን እውነታ ልረሳ አልቻልኩም።

ከቆይታ በኋላ አንድ ሴት ጋኔን ነጭ ልብስ ለብሳ ብቅ አለች። እንባ በእንባ ሆና ነበር። *"አግባብ አይደለም! ያ መጥፎ ሀክ-ሱንግ ደበደበኝ እና ያቺ ተባይ ጁ-ኢዩን በሁሉም አቅጣጫ (እያዟዟረች) በጥፊ መታችኝ።"* ቀረብ እስክትል ድረስ ጠበቅኳትና በጣቶቼ ዓይኖቿን አወጣኋቸው። እሷ በሥቃይ እላይና ታች ዘለለችና ጠፋች። ሌላ ሴት ጋኔን እንዲህ አለች:- *"ሄይ፣ አንቺ እኛን እንደዛ በመናገር (በመያዝ፣ በማስተናገድ) ማምለጥ የምትችዪ ይመስልሻል?"* ጸጉሯን በመያዝ ዙሪያውን ሁሉ አሽከረከርኳትና ከእኔ አርቄ ወረወርኳት። እኔ እንዲህ ጠየቅሁኝ:- *"**ኢየሱስ** ሆይ መጥረቢያ ስጠኝ።"* በመጥረቢያ ጭንቅላቷን በመምታት ብትንትኑን አወጣሁት። ራሷ ተቆርጦ ወደ እኔ መጣችና እንዲህ ጮኸች:- *"ሄይ አንቺ፣ ለእኔ ርህራኄ አይሰማሽም እንዴ?"* ጭንቅላቷን ለመፈለግ እንዲህ እያለች ዙሪያውን ተንከራተተች:- *"ጭንቅላቴ የት ነው ያለው? ፊቴ የት ነው ያለው?"*

በኋላ ላይ **ኢየሱስ**ን ለማየት ፈለግሁ። በሁሉም ኃይሌ ጠራሁት፣ *"አባ! አባ!"* **ኢየሱስ** በብሩህ ፈገግታ ሰላምታ አቀረበልኝ፣ ***"የእኔ ልባዊ ተወዳጅ ሰሊጥ፣ ትልቅ ነበርሽ። የእኔ ዩ-ክዩንግ ኢጋንንቶችን በራሷ በስኬት ማሸነፍ ችላለች።"*** እርሱ ደግሞ እንዲህ አለ:- ***"ዩ-ክዩንግ፣በስብከቱ ጊዜ ፓስተር ኪም 'ሰሊጥ' ብሎ ሲጠራሽ ጮክ በማለት መልስ ስጪው። ጮክ በማለት ማረጋገጥም ደግሞ እምነት ነው። ተረዳሺ?"*** እኔም መለስሁ:- *"አዎ **ጌታ** ሆይ። አሜን።"*

ቶሎ ብዙ መላእክት እንዲህ እያሉ መጡ:- *"እህት ዩ-ክዩንግ፣ ኢጋንንቶችን ድል ነስተሻል። አስደናቂ ነሽ። ቀጥዪበት! እና ኢጋንንት በድጋሜ ሲያጠቁ እስከ አሁን እንዳደረግሽው በድፍረት አሸንፊያቸው!"* ሁሉም አደፋፈሩኝ። **ኢየሱስ** መንግሥተ ሰማይን ለመጎብኘት ወሰደኝ። ወደ መንግሥተ ሰማይ የሚደረጉ ጉብኝቶችን ሁል ጊዜ እወዳለሁ እናም እደሰታለሁ። እዛ ስደርስ ዮ-ጂ እና እኔ በ**ጌታ** ፊት መደነስ (ማሽብሸብ) ጀመርን። እኛም እርሱን እንዲህ በማለት ጠየቅነው:- *"**ጌታ** ሆይ፣ የንስሐ እንባዎችን በዲያቆኒት ሺን ሱንግ-ክዩንግ ላይ እና በዮሴፍ ላይ እባክህን አፍስስ። ሁለቱም የንስሐን ጸሎት በሚያሳዝን ሁኔታ (ኢያነቡ) ለመጸለይ ይሻሉ ነገር ግን ማልቀስ አልቻሉም።"* **ጌታ** ግን እንዲህ መለሰ:- ***"ሰዎች በልቦቻቸው ለንስሐ ከልብ ሲጸልዩ ብቻ የንስሐን እንባዎች መስጠት እችላለሁ።"***

ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንመለስ ታጅበን ነበር። **ኢየሱስ** በጥፊ የተመታውን ፊቴን ነካውና እንዲህ አለ:- ***"ተወዳጅ ዩ-ክዩንግ፣ ጠንካራ ሁኚ። ተረዳሺ?"*** እርሱ በእጁ ሰላምታ አቀረበልንና ተሰወረ።

**ሊ, ሀክ-ሱንግ:** **ቼይንሶው (በሜካኒካል ሀይል የሚሰራ ስለታማ ጠርዞቹ ላይ ሠንሰለት ያለው መቁረጫ ማሽን) የያዘ ጋኔን*

በልሳኖች እየጸለይ እያለ ሦስት ኢጋንንት ሁሉም በአንድ ጊዜ አጠቁኝ። አንደኛው የሰው ፊትና የድራጎን አካል ነበረው። ሌላኛው የራስ ቅል ጋኔን ነበረ እና የመጨረሻው እላዩ ላይ የብረት ጭምብል ነበረው። በሚገርም ሁኔታ በጣም የሚጮህ ቼይንሶው ተሸክሞ ነበር እና እጆቼን ለመቁረጥ ሞከረ። በሙሉ ትኩረት መሆን ነበረብኝ። መከላከያዬን ለአንድ ሰከንድ ባወርድ እቆራረጥ ነበር። ልሸነፍ አልነበረም፣ ስለዚህ ዞር ብዬ አሳለፍሁና ጥቃቱን አመለጥሁ። በውጊያው ጊዜ ቼይንሶውን ነጥቄ ወሰድኩና የጋኔኑን እጅ ቆራረጥኳቸው። ጋኔኑ እየጮኸ ነበረ እና ሌሎቹ ሁለት ኢጋንንት በተስፋ መቁረጥ ከእኔ ርቀው ሮጡ።



በኋላ ሌላ ጋኔን ቀረበኝ።

እኔም እንዲህ በማለት በዘዴ ተጠጋሁት:- *“ሄይ ወደዚህ ና እና እኔ አስደሳች ነገር አስተምርሃለሁ። በዚህ በኩል! ፍጠን!”* ጋኔኑ ተጠራጥሮ ነበርና ለመምጣት እምቢ አለ። *“ሄይ! እዚህ የሚያስደስት አንድ ነገር የእውን ለአንተ አለኝ። እዚህ ና እና እይ!”* አልኩኝ፣ ነገር ግን አሁንም አላመነኝም። እንዲህ ብሎ ጠየቀኝ:- *“እኔን ላለመቅጣት ቃል ትገባለህ?”* እኔም እንዲህ መለስሁ:- *“እኔ ለምን እቀጣሃለሁ? የሚያስደስት አንድ ነገር ላካፍልህ ብቻ ነው የፈለግሁት፣ ስለዚህ እዚህ ና።”* ተደስቶ ወደ አጠገቤ በመቃረብ መጣ እና በምደርስበት ቦታ ውስጥ ሲሆን ክንዱን ያዝሁና በአየር ላይ አሽከረከረው ጀመር እና ግድግዳ ላይ ወረወርሁት።

ከትንሽ ቆይታ በኋላ የሰልፈኛ ወታደሮች የእግር ኮቶዎች ከፍተኛ ድምጽ በዙሪያዬ ሰማሁ። በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰልፈኞች በመተባበር ይመስላል። አንድ ግዙፍ የአጋንንቶች ቡድን ማዕበል ወደ እኔ ሲመጣ አየሁ። ሁሉም ወታደራዊ ዩኒፎርሞችን ለብሰዋል። እኔን ለማጥቃት እየመጡ የነበሩት አጋንንት ከበፊተኞቹ የበለጠ ፈጣኖች እየሆኑ እንደመጡ አውቄ ነበር። ነገር ግን፣ የ**ኢየሱስ**ን ስም ስጠቅስ ሁሉም ሸሹ።

**ኪም, ዮንግ-ዱ:** **ሁለቱም ክንዶች እንደ ተጠማዘዘ ፕሬትዝልስ (የቢስኩት አይነት) ዞሩ*

እጆቼ ወደ ላይ ከፍ ብለው ለ30 ደቂቃዎች ያህል ወደ **ጌታ** እየጮህኩ ነበረ። እጆቼ በተደጋጋሚ ክብ መስራት ጀመሩ። ግራ እጄ ከውስጥ ወደ ውጭ መንቀሳቀስ ጀመረ፣ ቀኝ እጄም የግራ እጄን እንቅስቃሴ በማስመሰል ተከተለ። በድንገት፣ ሁለቱም እጆቼ እንደ ፕሬትዝል ወደ ውጭ መዞር ጀመሩ እና በዛ አኳኋን ላይ ቆዩ። በጣም የሚያሠቃይ፣ የማይመች ለመታገሥ የሚከብድ አኳኋን ነበረ። ከዛ እጆቼ በድጋሜ በአንድ ሰከንድ ልዩነት ከውጭ ወደ ውስጥ በተቃራኒ ሁኔታ ዞሩ። መጀመሪያ ግራ እጄ ከዛ ቀኝ እጄ ወደ ውስጥ ዞረ እና ለተጨማሪ 30 ደቂቃዎች በዛ አኳኋን ሆኜ ነበር። ሂደቱ በጣም ዝግ ያለ ስለነበረ የማልታገስና ቁጡ እየሆንኩ ነበር።

እኔም አማረርሁ:- *“**ጌታ** ሆይ፣ ለምን በጣም እንድሠቃይ ታደርገኛለህ? ከውስጥ ወደ ውጭ ልታዞረኝ ከሆነ በፍጥነት አድርገው። አንተ ከእኔ ጋር እየተጫወትህ ያለህ ይመስላል። ምን እያደረግህልኝ ነው? እኔ ትዕግስት ያጣሁ (ችኩል) ነኝ። የሚያስፈልገኝን ሁሉ በአንድ ጊዜ አሁን ብትሰጠኝ ለሁለታችንም አጥጋቢና ቀላል አይሆንም እንዴ?”* **ጌታ**ን በምሬቶቼ ማጥቃት ጀመርሁ:- *“**ጌታ** ሆይ፣ በቅዱስ እሳትህ ብትመታኝና መንፈሳዊ ዓይኖቼን ብትከፍት ለሁለታችንም ጠቃሚ አይኖንም እንዴ? ለማግኘት ይህን ያህል ከባድ ካደረግኸው ማን መንፈሳዊ ስጦታዎችን መቀበል ይችላል?”*።

ለመንፈሳዊ ስጦታዎች ለመንሁ እና መንፈሳዊ ስጦታዎችን ፈለግሁ። በሀይሌ ሁሉ እየጮህኩ በጣም ጮህኩኝ፣ **ጌታ** ግን ክንዶቼን በማዞር የ**መንፈስ ቅዱስ** ሥራዎችን መድገም ቀጠለ። እርሱ ይህን ብዙ ጊዜአት አደረገ። እኔም እንዲህ ብዬ አሰብሁ:- *“ምን አይነት መንፈሳዊ ስጦታ ነው እርሱ ሊሰጠኝ እየሞከረ ያለው? ይህ ምን አይነት መንፈሳዊ ስጦታ ነው?”* በጣም ተናድጄ ነበር እና ለውጡ በፍጥነት እንዲሆን በአስቸኳይ ሻትሁ። ነገር ግን **ጌታ** የችኮላ ፍላጎቶቼን አልተካፈለም። በዛ ፈንታ፣ በእርምጃው (ዝግ በማለቱ) ተደናግጬ ነበር።

የእጆቼ መዞር ሲቆም ከአራት ሰዓታት በኋላ ነበር እና እጆቼ ከፊት ወደ ኋላ መንቀሳቀስ ጀመሩ። እጆቼን ዘና ለማድረግ ሞከርሁ፣ ነገር ግን ምንም ነገር ባደርግ ስልታዊው መንቀጥቀጥ ቀጠለ። በእርግጥ አስደሳችና አስገራሚ ነበረ። የፈውስ ስጦታና የተአምራት ኃይል የመቀበል ሂደት ላይ እንደነበርሁ በትንቢት ተነግሮኝ ነበረ።

**እህት, ቤይክ ቦንግ-ንዮ:** **ሌላ የሲኦል ጉብኝት*

መንፈሳዊውን ሽብሸባ (ዳንስ) እየተደሰትሁበትና በልሳኖች እየጸለይሁ ነበረ። እኔን ወደ **ኢየሱስ** ለመውሰድ አስር መላእክት ከመንግሥተ ሰማይ ወደ ታች መጡ።

ወደ **ኢየሱስ** ከመጣሁ (ከቀረብሁ) በኋላ እርሱ እንዲህ አለ፡- *"የእኔ ልባዊ ተወዳጅ ቦንግ-ንዮ፣ እንደምታውቂው ፓስተርሽ ስለ መንግሥተ ሰማይና ሲኦል መጽሐፍ እየጻፈ ነው። ፓስተር ኪምን ከእኔ ጋር ወደ ሲኦል ለመውሰድና ስለ ሲኦል ምን መጻፍ እንደሚያስፈልገው ላሳየው እፈልጋለሁ፣ ነገር ግን መንፈሳዊ ዓይኖቹ ገና አልተከፈቱም። የሲኦልን ሁኔታዎች በአግባቡ መዝግቦ ለመያዝ አንቺን ከመውሰድ በቀር ሌላ አማራጭ የለኝም። ለጉብኝት ልወስድ የምችለው ብቸኛዋ አንቺ ነሽ፣ ስለዚህ ለጥቂት ረዘም ላለ ጊዜ እንድትታገሺ እጠይቅሻለሁ። በአንድ ላይ ሄደን ሲኦልን እንጎብኝ።"*

በቶሎ (ከጥቂት ቆይታ በኋላ)፣ በሲኦል ውስጥ በአንድ መንገድ ላይ ወደ ታች እየተጓዝን ነበር። የበሰበሰው *ሥጋ* ክርፋት ሆዴን ገለበጠው እና እዛ ፍጻሜ የሌለው ጨለማ ነበረ። እኔም የ**ጌታ**ን እጅ በጥብቅ ያዝሁኝ። በሲኦል ለዘላለም *ሥቃይ* ብቻ አለ። ሰዎች እሳት በሚያመነጭና በጋለ ጉድጓድ ውስጥ ሆነው ለእርዳታ እየጮኹ ወዳለበት አንድ ቦታ መጣን። እሳቱ በጣም ኃይለኛ ነበር። እጅግ በጣም ግዙፍ በሆነ ከበሮ ውስጥ እርቃናቸውን ሆነው እየዘለሉና እየጮኹ ያሉ ለመቁጠር በጣም የሚበዙ (በጣም ብዙ) ሰዎች እዛ ነበሩ። አባቴን በድጋሚ አየሁት። ስቅስቅ ብሎ ማልቀስ ጀመረ፡- *"ቦንግ-ንዮ እዚህ ምን እያደረግሽ ነው? ባየሁሽ በእያንዳንዱ ጊዜ ይህን የልብ ህመም ልሸከመው አልቻልኩም። አንቺ ላይ ስላደረግሁብሽ ነገር በጣም ይቅርታ። ስላደረግሁት ነገር እዚህ እየከፈልኩ ያለሁትም ለዛ ነው ብዬ እገምታለሁ።"* አንድ ቃል መናገር አልቻልሁም፣ ነገር ግን ያለማቋረጥ አለቀስሁ። በሲኦል ውስጥ የሚሠቃየው *ሥቃይ* እኔ በምድር (በመሬት) ላይ ከአባቴ ከደረሰብኝ የጉዳት *ሥቃይ* ይልቅ በማይታሰብ ሁኔታ ይበልጣል። በመሬት ላይ የተለማመድሁት ምንም ማለት አይደለም።

አንድ በጣም ግዙፍ ጋኔን ረጅም ጠማማ እጀታና ስለት ባለው ማጭድ ሰዎችን መቆራረጡን እየተደሰተበት ነበረ። እሱ በደስታ እንኳን አንድ ዘፈን ያንጎራጉር ነበር። ጋኔኑ አባቴን መንጭቆ ወሰደውና ቤት ውስጥ የተሰሩ ፓስታዎችን በምንቆርጥበት መልክ (ሁኔታ) ይቆራርጠው ጀመር። *"አህህህህ! እባካችሁ ኢድኑኝ! እለምንሃለሁ! እባክህን ግደለኝ በቃ!"* የአባቴ የሚያሰቃዩ እንባዎችና አስጨናቂ ጩኸቶች እራሴን እንድስት አደረጉኝ። **ጌታ** አጠገቤ ባይሆን ኖሮ በተደጋጋሚ ብዙ ጊዜያት እራሴን በሳትኩ ነበር። በሲኦል ውስጥ ላሉት *ሥቃዮች* ፍጻሜ የላቸውም፤ በዘላለማዊ ፀፀቶች ተረግማችኋል። በፍጹም ምንም ተስፋ የለም። ወደ ሲኦል መሄድን ማስወገጃ ብቸኛው መንገድ **ኢየሱስ**ን እንደ አዳኛችሁ መቀበልና በታማኝነት መኖር ነው።

የአባቴን አስጨናቂ ለቅሶዎች ወደ ኋላ ትተን አልፈን ሄድን። ለጥቂት ጊዜ ተራምደን ከሄድን በኋላ ከፊት ለፊቴ አንድ ዛፍ አየሁ። እየቀረብሁ ስሄድ እናቴን፣ ታናሽ ወንድሜን፣ በህግ ወንድሜ የሆነውን እና የአጎቴን ልጅ እርቃናቸውን ሆነውና ከላይ ወደ ታች በመዘቅዘቅ ተንጠልጥለው ዛፉ ላይ በቁርጭምጭሚቶቻቸው ሲወዛወዙ አየሁ። ሌሎቹ የቤተሰብ አባላትም ደግሞ አዩና ለእኔ እንዲህ ጮኹ፡- *"ቦንግ-ንዮ፣ እኛን መርዳት ካልቻልሽ ለምን እዚህ ሆንሺ? በድጋሚ ለምን መጣሺ? እኔን በሥቃይ ውስጥ ሆኜ ማየት ያን ያህል ትፈልጊአለሽ?"*

**ኢየሱስ** ይህ ልዩ ጋኔን በሲኦል ውስጥ ሁለተኛው ግዙፍ ጋኔን እንደነበረ ነገረኝ። ጋኔኑ የሰዎቹን አካል መደብደብና *ሥጋ*ቸውን ልጦ መጨረስ ያስደስተው ነበረ። ጋኔኑ ከዛ ያለምህረት ሰዎችን ወደ እሳት ውስጥ ይወረውራቸው ነበር። እኔ ጋኔኑን ወደ ቁርጥራጮች ልገነጣጥለው ፈልጌ ነበረ።

ቤተሰቤ ተንጠልጥሎ ከነበረበት በታች ጥቁር ነብሳቶች (ኢንሴክትስ) የሞሉበት ጎድጓዳ ሣህን እንዲያስቀምጥ ከበታቾቹ አንዱን አዘዘ። እነዚህ ነብሳቶች የትል ቅርጽ ነበራቸው፣ ሾለው የሰሉ ጥርሶችና በደማቁ የሚያበሩ ዓይኖችም ነበሯቸው። ትሎቹ ቤተሰቤ ላይ ዘለው ወጡና ያለምህረት *ሥጋ*ቸውን ከመጠን በላይ በሉ። አካላቸውን በሙሉ ዓይኖቻቸውንና የአፍንጫ ቀዳዳዎቻቸውንም እንኳ ሰርስረው ገቡ። ሁሉም እንዲህ ሲጮኹ ሰማኋቸው፡- *"አህህህህ! እባክሽን ኢድኚኝ! ቦንግ-ንዮ! ትልቋ እህት! አውች! በህግ እህቴ! እባክሺን እርጂኝ! አክስቴ! እባክሽን እርጂኝ!"* በቶሎ ከጥቂት ቆይታ በኋላ ሁሉም *ሥጋ*ቸው ረገፈ እና ትሎቹ በአጥንቶቻቸው ውስጥ እንኳ ሰርስረው ገቡ። ይህ ለዘላለም እንደሚቀጥል ማወቁ ልቤን ሰበረው (እጅግ አሳዘነኝ)። **ኢየሱስ**ን ለእርዳታ በኃይል በጠየቅሁ ቁጥር እርሱ እንዲህ ብቻ ማለት ችሎ ነበረ፡- *"ያን ማድረግ አልችልም። በጣም ዘግይቷል።"*

**ኢየሱስ** ወደ አንድ ግዙፍ ተራራ ወሰደኝ። ሰዎች በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሆነው በዙሪያው እዚህም እዚያም ቆመው አየሁ። እነሱ በሀይል ከመደብደባቸው የተነሳ ፊፅሞ የደከማቸውና ያበጡ ይመስላሉ። ከሰዎቹ አጠገብ እንዲህ በማለት ሊያፌዝብኝ የጀመረ አንድ የሚያስፈራ ጋኔን ነበረ:- *“እኔ በተደጋጋሚ ብዙ ጊዜ ዓይቻለሁ። ለምንድን ነው እዚህ በድጋሜ ያለሺው?”* በጣም ተቆጥቼ ነበር፣ እረግመውም ጀመር። *“ሄይ፣ አንተ መጥፎ ነህ! ቤተሰቤ ላይ እንዳደረግከው አንተን መቦጫጨቅ እና ወደ እሳቱ ጉድጓድ ውስጥ መወርወር ብችል እመኛለሁ። አገኝሃለሁ!”* ጋኔኑ የበለጠ ጮክ በማለት እንዲህ አሾፈ:- *“አንቺ ስለፈራሺኝ ነው እያለቀስሽ ያለሺው። ያ እኔን ደስተኛ ያደርገኛል! ስለዚህ አንቺ ምን ልታደርጊ ነው?”* እኔም እንዲህ አልኩት:- *“**ኢየሱስ** ሆይ፣ ያን ጋኔን እንድትገድለው እፈልጋለሁ። ያን ጋኔን እጠላዋለሁ! ጌታ ሆይ፣ ለምንድን ነው አንዳች ሳታደርግ እዛ ጋር የቆምከው? የሆነ ነገር አሳያቸው!”* **ኢየሱስ** ቀኝ እጅን ከፍ አደረገና በፍጥነት አሽከረከረው። ወዲያውኑ የጋኔኑ አካል ሽባ ሆነና እንደ ድንጋይ ምሰሶ መንቀሳቀስ አልቻለም ነበር። ከትንሽ ቆይታ በኋላ ሁሉም ሰዎች ሥጋቸውን በሚበሉ በተለያዩ አይነት ነብሳት ተሸፈኑ። የሰዎቹ ጩኸት በመላ የሲኦል ሁኔታ ውስጥ አስተጋባ።

**የቀድሞውን የኮሪያ ፕሬዚዳንት መገናኘት*

እኛ ቀጠልን፣ **ኢየሱስ**ም እንዲህ አለ:- ***“ቀጥሎ የምትገናኚአቸው ነፍሳት በደምብ የምታውቂአቸው ስለሆነ ትኩረት አድርጊ (በትኩረት ተከታተዪ)።”*** እኔም የቀድሞውን የኮሪያ ፕሬዚዳንት አየሁ። በአካሉ ዙሪያ የተጠመጠመበት አንድ ትልቅ ነጭ እባብ ነበረ እና በርከት ያሉ ቀለሞች ያሏቸው እባቦች ከነጩ እባብ በላይ ነበሩ። እሱም እንዲህ አለ:- *“አህህህ! እኔን ማፈን አቁሙ! እባካችሁ አቁሙ! እባካችሁ አድኑኝ!”* ነገር ግን በዚህ ጭንቀት መኃል ውስጥ ሆኖ እንኳ እኔን ያነጋግረኝ ጀመር። *“አንቺ ማን ነሽ? ለምን እዚህ ሆንሺ? እኔ ከሁሉም ክብር ጋር የኮሪያ ፕሬዚዳንት ነበርኩ፣ አሁን ግን እኔ በሲኦል ውስጥ እየተሠቃየሁ ነኝ። ብዙ ፓስተሮች ቤተ ክርስቲያን እንድካፈል እኔን ለማግኘት ሞክረዋል፣ እኔ ግን ሁሉንም ችላ አልኳቸው። እነርሱ ስለ ሲኦል የነገሩኝን ችላ አልኩኝ እና እንዲህ አይነት ቦታ በእውን ይኖራል ብዬ በፍጹም አልሜ አላውቅም። ልጄ እስከ አሁን **ኢየሱስ**ን አያውቅም እና ስለዛ በጣም ተጨንቄአለሁ። ልጄ በህይወት እያለ **ኢየሱስ**ን መቀበል እና በመንግሥተ ሰማይ መኖር እንዲችል ድህነትን (መዳንን) መቀበል ያስፈልገዋል። አሁኑኑ ሄጄ ለልጄ ስለዚህ እውነት መንገር ብችል እመኛለሁ። እኔ አልችልም፣ ስለዚህ አሁን ምን ማድረግ አለብኝ? አህህህ! ልቤ እጅግ በጣም ታሟል።”* እሱ ወደ **ኢየሱስ** ለመነ፣ ነገር ግን **ኢየሱስ** አንድም ቃል ሳይናገር ዝም ብሎ አዳመጠ።

## ==== ቀን 22 ==== (1ኛ ጴጥሮስ 1:6-9) **አንድ ጋኔን ፒያኖ ተጫወተ*

**ሊ, ዩ-ክዩንግ:**

እየጸለይሁ እያለ አራት ዓይኖች ያሉት ባለ ጥቁር ፊት ጋኔን መጣና በፒያኖ ወንበር ላይ ተቀመጠ። ጋኔኑ ፒያኖውን ለመጫወት በመሞከር ነካካ። እኔም በጣም ተናድጄና ተቆጥቼ እንዲህ ጮህኩኝ:- *“ሄይ፣ በጣም ቆሻሻ ጋኔን! ለምንድን ነው በእህቴ በጁ-ኢዩን ፒያኖ የምትጫወተው? ያ ፒያኖ እርሷ በአምልኮ አገልግሎት ጊዜ የምትጠቀምበት ነው።”* ጋኔኑም ማለብኝና አፌን እንድዘጋ ስለነገረኝ በጣም መቆጣት ጀመርኩ። *“ምን? አንተ አሁን አቃለልከኝ? አንተ በጣም ምተህል!”* ከኋላው ሮጥኩኝና ያዝኩት። አንገቱን ጠመዘዝኩትና ራሱን መሬት ላይ መታሁት።

ተጨማሪ ሦስት አጋንንት ብቅ አሉ። አንደኛው ግንባሩ ላይ ዓንኖች ባሉት አንድ አጽም መልክ ታየ። እንደ የሌሊት ወፍ ክንፍ አይነት በሚመስሉት ክንፎቹ ዙሪያውን ይበር ነበር። የፒያኖው ወንበር ላይ አረፈና ፒያኖውን ሲጫወት መዝፈን ጀመረ። የዘፈኑ ድምጽ መጥፎ የፍርሃት ስሜት የሚያስከትል (የሚያስደነግጥ) ነበረ እና ሙዚቃው ከሪዘም (rhythm) ውጪ ነበረ።

*“ሄይ፣ ያ ፒያኖ የጁ-ኢዩን ነው። ለምንድን ነው የምትነካው? ጸሎቶቼ ላይ ትኩረት ማድረግ አልቻልኩም!”* በማለት ጮህኩኝ። እርስ በእርሳቸው እንዲህ እያሉ ሲነጋገሩ መስማት እችል ነበር:- *“ማተኮር አልቻለችም። የፈለግነውን ያህል እንጫወት።”*

ሁሉም በሀይልና በተደጋጋሚ የፒያኖውን ኪዎች ይመቱ ጀመር። ፒያኖው ይሰበር ይሆናል ብዬ ተጨንቄ ነበር። እኔም እንዲህ ነገርኳቸው፡- *“እንደማስተውለው በእርግጥ እናንተ የምትሰሙኝ አይደላችሁም።”* ወደ እነሱ ሮጥሁና ሁሉንም በአንድ ጊዜ ያዝኳቸው፣ ደበደብኳቸውና ዙሪያውን አወዛወዝኳቸው። አፍንጫዎቻቸው እየደማና ራሶቻቸው ተጎድቶ ጮኹና ርቀው ሮጡ (አመለጡ)።

በድጋሜ መጸለይ ጀመርኹ። ነጭ የለበሰ አንድ ጋኔን አፉ እየደማ ታየ። ጋኔኑ ዓይኖች የሌሉት የተበላሸ ስለሚመስል መሳለቂያ አደረግሁት። ጋኔኑም እንዲህ አለ፡- *“ሀክ-ሱንግ ዓይኖቼን አወጣቸው። ለዚህ ነው እንዲህ የሆንኩት። ለምንድን ነው አንቺ በጣም የምትስቂው?”* ጋኔኑ ከእኔ ጋር ጠብ ሊያነሳ (ጠብ ሊጭር፣ ሊጣላ) ሞከረ። እኔም እየጮህኩ እንዲህ አልሁ፡- *“ሲያቴ በአንተ ምክንያት በሥቃይ ውስጥ ናት! እርሷ ለምንድን ነበር ወደ ሲኦል ውስጥ የወረደችው?”* ጋኔኑ አሾፈብኝና አናደደኝ። *“እሷ በሲኦል ውስጥ መሆን ይገባታል፣ እሷ ሲኦል ይገባታል። እሷ የበለጠ ትሰቃያለች።”* እኔም እሳት ለብሼ እሳት ጎርሼ (እጅግ በጣም ተቆጥቼ) በሙሉ ሀይሌ የጋኔኑን ፊት ቧጠጥሁት። ጋኔኑም ከመጠን በላይ እየደማ ሮጠ።

አንዴ በድጋሜ በጸሎት ውስጥ እያለሁ በሌላ ጋኔን ተበሳጭቼ ነበር። ተናድጄና ልጋጠመው አልተመኘሁም ነበር። እንዲህ የማለት ስልጣኔን ለመጠቀም ወሰንሁ፡- “**የኢየሱስ ደም**”። ጋኔኑ ግን እንዲህ መለሰ፡- *“ደም? የማን ደም? የኢየሱስ ደም? አሀ፣ የአንቺ ደም?”* *“እሺ፣ ውጊያ ከፈለግህ ና፤ እንዋጋ!”* በማለት ጮህኩኝ። አጋንንቶች በቡድኖች ሆነው አጠቁ፣ ነገር ግን በሆነ ምክንያት ጡጫዬን ዙሪያውን ሳወዛውዝ እንደ ቡድን ሁሉም ይወድቁ ነበረ። አጋንንቶቹን ሆዳቸውን ከመታሁ ዓይኖቻቸው በድንገትና በሀይል ይፈጥ ነበር። አፍንጫዎቻቸውን ስመታ አፍንጫዎቻቸው መድማት ይጀምራሉ። እግሮቻቸውን ይገቹ ሳወዛውዛቸው እግሮቻቸው እንደሚለጠጡ የእጅ ላስቲኮች ይለጠጡ ነበር።

ምንም እንኳ አጋንንቱ ቢሸነፉም መታየትና እኔን መነዝነዝ ቀጠሉ። እነሱ የመጸለይ ተሰጥዎዬን እያስታጎሉ (እያደናቀፉ) ነበር። እኔም እንዲህ ብዬ አሰብሁ፡- *“እንዋጋና ማን እንደሚያሸንፍ እንይ።”* ወደ እኔ ከቀረበ ማንኛውም ጋኔን አፍንጫዎቻቸውን ወጋሁና የእነሱን ብዙ ጸጉርም ያዝሁ። እጆቼንና እግሮቼን እንደ ጦር መሣሪያዎች ተጠቀምሁ። እነሱን ማሸነፍ ስቀጥል ቁጥራቸው የሚጨምር ብቻ መሆኑ እንግዳ ነገር ነበር። ወደ መጨረሻ አካባቢ ለመቁጠር እጅግ ብዙ የሆኑ ብዙ አጋንንት ነበሩ። ሁሉም በአንድ ጊዜ መጡ። በአስቸኳይ እንዲህ ጮህኩኝ፡- *“እርዳኝ! **መንፈስ ቅዱስ** በፍጥነት! እርዳኝ!”* በአጭር ጊዜ ውስጥ **ጌታ** መጥቶ ታየ። **ጌታ** ሁሉንም አጋንንት ገሰጻቸውና እንዲህ በማለት አጽናናኝ፡- ***“ወይዘሪት ጠቃጠቆ! በብዙ ውስጥ እንደነበርሽ አውቃለሁ።”***

በፊት ሌሎች ቤተ ክርስቲያናትን ስካፈል አብዛኞቹ ሰዎች ብዙ ጊዜ አዘውትረው በጣም ብሩህ እንዳይደለሁ ይላሉ። ለመጸለይና ወንጌልን ለመስበክ እኔን በማስተማር ፈንታ ምግብ ብቻ ያቀርቡልኝ ነበር። እነርሱ በቁሳዊ ነገሮች ብቻ ሊረዱኝ ሞክረዋል። ስለዚህ፣ ማድረግ ያለብኝ ነገር ሁሉ ወደ አገልግሎት መጽሐፍ ቅዱሴን ይዤ መምጣት ነው ብዬ አስብ ነበር። ነገር ግን ከ**ጌታ** ቤተ ክርስቲያን ፓስተር መሪነት በልሳኖች መጸለይ ጀመርሁ። በልሳኖች መጸለይ እንደቀጠልሁ የጸሎት ጥልቅ ደረጃን ማግኘት ችዬ ነበረ። አሁን፣ አጋንንትን ለማየት ችያለሁ እና ከእነሱ ጋር ለመዋጋት ችያለሁ። እየተሸነፍሁ ወይም ከጦርነቱ የተነሳ እየደከመኝ እንደሆነ በተሰማኝ ቁጥር የማደርገው ሁሉ የ**ጌታ ኢየሱስ**ን ስም መጣራት ነው። እርሱ ሁል ጊዜ ይጠብቀኛል። በመጀመሪያ፣ የማይቆጠሩ (እጅግ ብዙ የሆኑ) የአጋንንቶች ጥቃት ያስፈራራኝ ነበር። አሁን ግን **ኢየሱስ** ከእኔ ጋር ስለሆነ በፍጹም አልፈራም። በእርግጥ በአጋንንቶች ላይ ድል መቀዳጀት (አጋንንቶችን ማሸነፍ) አስደሳችና አስደናቂ እየሆነ መጥቷል።

**ኪም, ጁ-ኢዩን:** **ራሰ በራ ጋኔን ታየ*

ዛሬ፣ አፏ በጣም እንደተከፈተ ሕጻን ልጅ መስሎ ሌላ ጋኔን መጣ። እኔም በጉንጮቿ አካባቢ እስኪያብጥ ድረስ ፊቷን የእውን በሀይል በጥፊ እየመታሁ ቁጣዬን በእሷ ላይ ተወጣሁ።

እኔም እንዲህ በማለት ጮህኩ፡- *"አንቺ የእህት ዩ-ክዩንግን ጉንጮች በጥፊ መተሻል፣ ትክክል? አንቺ ከዚህ በላይ ትቀጫለሽ። የበለጠ ልደበድብሽ ነው!"* እሷም እንዲህ በማለት አለቀሰች፡- *"ይቅርታ። ዩ-ክዩንግን በድጋሜ በፍጹም አልመታም። ከልብ!"* እኔም መለስሁ፡- *"ያ፣ ትክክል። አንቺ በተፈጥሮ (በባህርይ) ውሸታም ነሺ።"* ጸጉሯን በሙሉ ነቅዬ አወጣሁትና እሷን ወደ ፒያኖው ወረወርኋት። ከዛ ረጅም ነጭ ጸጉርና ብርቱካንማ ዓይኖች ያሉት አንድ የራስ ቅል ጋኔን አየሁ። እኔም ዓይኖቹን አወጣኋቸው እና ጋኔኑ እስኪሸሽ ድረስ በንዴት እየተንጨረጨረ እጅግ በሚያስቅ መልኩ በጣም ሀይለኛ በሆነ ሥቃይ ዙሪያውን ዘለለ።

**አሸናፊ ቤተ ክርስቲያናት*

መጸለይ እንደቀጠልሁ እንደ አባባዎች ደስ የሚል መአዛ በአየር ላይ ተሠማኝ። **ጌታ**ም ስለታየ እንዲህ ብዬ ጠየቅሁት፡- *"ይህ ጣፋጭ መአዛ ከአንተ ነው **ጌታ** ሆይ?"* **ጌታ**ም እንዲህ መለሰ፡- ***"አዎ ነው። መአዛውን ወደድሺው?"*** እኔም በደስታ እንዲህ በማለት መለስሁ፡- *"አዎ **ጌታ** ሆይ። የእውነት ጥሩ ይሸታል።"* **ኢየሱስ** ይህን ነገረኝ፡- ***"አንቺ ዛሬ በቀናኢነት እየጸለይሽ ነው። እኔ ልዩ የሆነ ነገር አሳይሻለሁ። የቤተ ክርስቲያንሽንና የኮሪያ ቤተ ክርስቲያናትን ሁኔታ በትኩረት ተመልከቺ።"*** **ጌታ** እጁን ወደ ላይ እንዳነሳ ራእይ ተሰጥቶኝ ነበረ።

ሁለት አጋንንት ከአጠገቧ ሆነው መሬትን ከቅርብ ርቀት እንዳይ ተደርጌ ነበረ፣ አንደኛው ጋኔን በመሬት በስተ ግራ ሌላኛው ጋኔን ደግሞ በመሬት በስተቀኝ በኩል ቆመው ነበረ። እንደ ገመድ ዝላይ ጨዋታ እየተጫወቱ እነሱ በአንድ ላይ በመላው ዓለም ዙሪያ አንድ ገመድ እያወዛወዙ ነበረ። በቅርበት በምመረምርበት ጊዜ ገመዱ በእውነቱ አንድ ረጅም እባብ እንደነበረ አየሁ። አጋንንቱ ሲያወዛውዙ፣ ገመዱ ወደ እነርሱ ሲመጣ ብዙ የኮሪያ ቤተ ክርስቲያኖች ሲዘሉ አየሁ። አንድ ዙር በመጣ ቁጥር ላለመጠለፍ (ላለመደናቀፍ)ና ላለመውደቅ እየሞከሩ አብያተ ክርስቲያናቱ ይዘሉና ይዘሉ ነበረ። አብዛኞቹ ቤተ ክርስቲያናት በመጀመሪያው አልወደቁም፣ ነገር ግን መወዛወዙ ሲቀጥል ተደናቀፉና ወደቁ። የእኛም ቤተ ክርስቲያን እንኳ ሲትዘል አይቻለሁ። እኛ በእባቡ አካል አልተጠለፍንም (አልተሳሳትንም) ነበረ።

ከጋኔን የሆነ እያንዳንዱ መወዛወዝ ልናሸንፈው የሚገባ ፈተና፣ ሙከራ እንደነበረ **ኢየሱስ** አብራራ። አንድ ቤተ ክርስቲያን ካልተደናቀፈችና ካልወደቀች፣ ቤተ ክርስቲያንዋ ሙከራውን በድል አሸንፋለች ማለት ነው። የ**ጌታ** ቤተ ክርስቲያን ከሁሉም ያነሰ አባላት አሏት። ሌሎች ቤተ ክርስቲያናት በጣም ብዙ አባላት ነበሯቸው፣ ነገር ግን እነርሱ ቶሎ በተደጋጋሚ ይደናቀፉና ይወድቃሉ። **ኢየሱስ** እንዲህ አለ፡- ***"የጌታ ቤተ ክርስቲያን በታላቁ አሸንፋለች። መጽናት ቀጥሉ እና የተለያየ መከራ ሲወድቅባችሁ ዝለሉ። ዛሬ፣ ሳታንቀላፊ ለረጅም ሰዓታት ጸልየሻል። ስለዚህ ይህን አሳየሁሽ። በቅንነት ጸልዪ።"***

**ሊ, ሀክ-ሱንግ:** **በአዝናኝ ኢንደስትሪ ውስጥ አጋንንትን የመሰሉ ገጸ ባሕርያት (ጠባዮች)*

እየጸለይሁ እያለ አንድ ጋኔን ቀረበኝ። አያቴን በሲኦል ውስጥ ካየኋት በኋላ በጣም ተቆጥቼ ስለ ነበረ ቁጣዬን በዚህ ጋኔን ላይ ተወጣሁ። ዓይኖቹን አወጣኋቸውና አርቄ ወረወርኋቸው። በዚህ ውጊያ ጊዜ ስለ ሰይፍ ማሰብ ጀመርሁ እና አንድ ሰይፍ በእጄ ውስጥ ሆኖ ታየ። እኔም ክንዶቹን ቆረጥኋቸው። የተለያዩ አይነት የጦር መሣሪያዎችን ለመጠቀም ባሰብሁ ጊዜ ወዲያው በእጄ ውስጥ ወይም ከአጠገቤ ይታያሉ። **ጌታ** በጠየቅሁት ጊዜ እነዚህን የጦር መሣሪያዎች ሰጥቶኛል። ለረጅም ጊዜ እየተዋጋሁ ነበረ እና ሳላገናዝበው ታላቅ ልምድን አግኝቻለሁ። ደግሞም ልበ ሙሉነትንና ድፍረትን አግኝቻለሁ።

ነጭ ልብስ ያደረገች ታዳጊ ሴት ልጅ መስሎ አንድ ጋኔን ቀረበኝ። እሷ ከሆረር የቴሌቪዥን ድራማ አንድ የታወቀ ሰው ( አንድ ገጸ ባሕርይ) ከሆነው ጋር በጣም ትመሳሰላለች። በአዝናኝ ኢንደስትሪው ከተፈጠሩት ጋራ እንዴት የእውን አጋንንት በጣም እንደሚመስሉ ተደንቄ ነበረ! ይሄኛው በታዋቂው የኮሪያ ቲቪ የሆረር ተከታታይ ፊልም ውስጥ ነፍሳት ከሞቱ በኋላ ወደ ሲኦል እንደሚያወርደው ጋኔን ነበረ። በራእይ፣ አንድ ሽማግሌ ሰው ከመሠዊያው በታች መሬት ላይ ተኝቶ እየደማ አየሁ። ሽማግሌውን ሰውዬ እያጠቃች፣ ጋኔኗ የሰውዬውን ደም ለመምጠት የሾሉ ስለታማ የውሻ ክራንቻ የሚመስሉ ጥርሶቿን ተጠቀመች። አንዴ ደሙ ከደረቀ በኋላ እሷ በፍጥነት እሱን መብላት ጀመረች።

*የጋኔን መርፌ ሹል መንደፊያ*

መርፌ በተሞላ አካል እንደ ጃርት ወይም ፖኪውፓይን (porcupine) መልክ ሌላ ጋኔን ታየ። እኔም ጡጫዬን አወዛወዝኩበት። ጋኔኑን ስነካ፣ በጋኔኑ መርፌዎች ጡጫዬ ስለተወጋ ታላቅ ሥቃይ ተሰማኝ። የጸሎታችን ስብስብ ጊዜ ካለቀም በኋላ እንኳ እጄ ቀልቶና በመርፌው ምልክቶች አብጦ በሥቃይ ውስጥ ነበር። አጋንንት በሰውነቴ ላይ አካላዊ ምልክቶችን ማኖርና (መተውና) አካላዊ ሥቃይ ማስከተል በመቻላቸው ተደንቄ ነበር።

**ፓስተር ኪም ዮንግ ዱ:** **የእጅ እንቅስቃሴና መንቀጥቀጥ (እንቅጥቃጤ)*

በትጋት በልሳኖች ስጸልይ እጆቼ በትንሽ ከፍታና ዝቅታ እንቅስቃሴዎች መንቀሳቀስ ጀመሩ። ከጥቂት ቆይታ በኋላ ሁለቱ መዳፎቼ ፊት ለፊት በአንድ ላይ ተጋጠሙና በኃይል ተንቀጠቀጡ፣ ጊዜውም በሄደ ቁጥር የበለጠ በኃይል እየተንቀጠቀጠ መምጣት ጀመረ። አንድ ፓስተር በፈውስ ሲያገለግል አስታውሳለሁ። የእርሱም እጆቹ ደግሞ እየተንቀጠቀጡ ነበረ። የእርሱ እጆች እየተንቀጠቀጡ እያለ ብዙ ተአምራት እየተደረጉ (እየሆኑ) ነበረ። የፈውስን ስጦታ በማሳደግ ሂደት ላይ መሆን አለብኝ ብዬ ደመደምሁ። ክንዶቼና እጆቼ በ**መንፈስ ቅዱስ** አቅጣጫ (**መንፈስ ቅዱስ** እንደመራቸው) በነፃነት ይንቀሳቀሱ ነበረ። ለማየት ዓይኖቼን ከፈትሁና እንቅስቃሴዎቹን ለማገድ ሞከርሁ፣ ነገር ግን ከፈቃዴና ከአሳቦቼ ውጭ መንፈስ ቅዱስ መራኝ [ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በፈቃዴና በአሳቦቼ ሳይቸገር መራኝ]። ፈቃዴና አሳቦቼ እንደአጋጣሚ (ጥቃቅን ጉዳይ) ብቻ ነበሩ።

**እህት ቤይክ, ቦንግ-ንዮ:** **ጌታ እምነቴን ፈተነ*

እየጸለይሁ እያለ **ኢየሱስ** መጣና እንዲህ አለ፦ ***"ቦንግ-ንዮ፣ ዛሬ፣ እምነትሽ ምን ያህል እንዳደገ ለማየት አንቺን ለመፈተን እፈልጋለሁ። ዝግጁ ነሺ?"*** እኔም በልበ ሙሉነት እንዲህ መለስሁ፦ *"አዎ ጌታ ሆይ። ዝግጁ ነኝ።"* እርሱም ተሰወረ እና መላእክት መጡ፣ ባለ ክንፋማ ልብስም አለበሱኝ። አልብሰውኝ እንደጨረሱ መላእክቱ ደግሞ በፍጥነት ጠፉ።

አብዛኛውን ጊዜ **ኢየሱስ** እና መላእክቱ ወደ መንግሥተ ሰማይ ወይ ወደ ሲኦል ይመሪኝ ነበር፣ በዚህ ጊዜ ግን እንደዛ አይደለም። ልብ በሚነካ ሁኔታ ወደ **እግዚአብሔር** መጮህ ጀመርሁ። ነፍሴ ባለ ክንፋማውን ልብስ ለብሳ ወደ መንግሥተ ሰማይ መብረር ጀመረች። ነገር ግን ምንም ያህል ልብ በሚነካ ሁኔታ ብጸልይም በጣም በቀስታ ነበር እየበረርሁ የነበረው። ተስፋ የሚያስቆርጥ ነበረ፣ ነገር ግን እኔ አላቆምሁም እና በትጋት መጸለይ ቀጠልሁ። ከጥቂት ቆይታ በኋላ (በቶሎ) ፈጽሞ ደከምሁ። አንዳች ማየት አልቻልሁም፣ ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ ብቻ።

**ጌታ** እምነቴን ለመፈተን እንደፈለገ ያለውን ስላስታወስሁ መጸለይ ቀጠልሁ። በሚያሳዝን ሁኔታ፣ ልታስቡት የምትችሉት እያንዳንዱ መሠናክል ደርሶብኛል። ራሴን የመጀመሪያ መነሻ ቦታ ውስጥ ተመልሶ አገኘሁት።

እስከ አሁን ድረስ፣በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በጸለይሁ ቁጥር **ጌታ** ወደ እኔ ይመጣና ሁሉንም ነገር ያሳየኛል። እኔ ሳላገናዝበው ትዕቢተኛ (እብሪተኛ) እየሆንሁ መጥቻለሁ። ከጥቂት ጊዜያት በፊት ባለክንፋማ ልብስ ሲያለብሱኝ የነበሩትን መላእክት የጠየቅኋቸውን ጥያቄ አስታወስሁ። **ኢየሱስ** የት እንደነበረ ጠይቄአቸው ነበር እና እነርሱ እንዲህ መለሱ፦ *"አሁን፣ እርሱ ሚልኪ ዌይ ውስጥ ሊገናኝሽ እየጠበቀሽ ነው።"* በሚያሳዝን ሁኔታ፣ በዛ ጊዜ፣ በጣም በዝግታ እየተጓዝሁ ስለነበረ ዘይግቼ ነበር። እምነቴ ብቻ ያን ያህል በከፍታ (በዛ ከፍታ ያህል) እንድበር አልፈቀደልኝም።

ለረጅም ሰዓት (ጊዜ) ከልብ ጸለይሁ፣ ነገር ግን አሁንም አንዳች ማየት አልቻልሁም። ብዙ አሳቦች በአዕምሮዬ ውስጥ ተመላለሱ እና ንስሃ መግባት ጀመርሁ። ከ**ኢየሱስ** እርዳታ ውጭ እኔ አንዳች ማድረግ አልችልም። ረግረግ ውስጥ ያለማቋረጥ እየሰመጥሁ እንደሆነ ተሰማኝ። የሆነ ነገር ውስጥ ተቆልፎብኝ እንደነበረ አይነት ስሜት እስኪሰማኝ ድረስ ያ የአዕምሮ ሁኔታ ቀጠለ።

አንዳንድ ነገሮች በፊቴ እየተንቀሳቀሱ ነበረ እና በአንድ ጨለማ ክፍል ውስጥ ተቆልፎብኝ በሲኦል ውስጥ እንደነበርሁ ተገነዘብሁ።

በዚህ ጨለማ ውስጥ ምንም አይታይም። የአጋንንቶች መንጋ በዙሪያዬ ነበር። የማይቆጠሩት አጋንንቶች እግሮቼን አጥብቀው ያዙና እኔን አንለቅም አሉ። እነሱ አነቁኝና በጠቅላላው መንቀሳቀስ እንዳልችል እጆቼን፣ እግሮቼንና አካሌን ጎተቱ። በልሳኖች መጸለይ ጀመርሁ፣ ነገር ግን በድንገት እርግማኖች ያለውዴታዬ ከአፌ ወጡ (ፈሰሱ) ።

*“ሄይ፣ እናንተ ቆሻሻ አጋንንት! ለምንድን ነው የምታስቸግሩኝ? እናንተ ከፉዎች ከእኔ ራቁ!”* መራገም ማቆም አልቻልሁም። **ኢየሱስ**ን ከማግኘቴ በፊት የተጠቀምኳቸው ቆሻሻ አነጋገሮች ሁሉ ከአፌ በፍጥነት ወጡ። አጋንንቱ ላይ በጣም ብዙ ብሳደብም ምህረት የለሽ (የማያቋርጥ) ጥቃታቸውን እኔ ላይ አላቆሙም። እኔም እንዲህ ብዬ ተጣራሁ፦ *“**ኢየሱስ** ሆይ እባክህን እርዳኝ!”*

ወደ **ጌታ** መጣራት ቀጠልሁ እና በትጋት በልሳኖች ጸለይሁ። ጎልቶ ከማይታይ (ከዘገየ) ጊዜ በኋላ፣ ባልታወቀ ሁኔታ ከሲኦል አመለጥሁና ወደ መንግሥተ ሰማይ እየበረርሁ ነበር። ስበር (እየበረርሁ እያለ) እየጸለይሁ ነበር። በህዋ ውስጥ ጠንካራና ሀይለኛ አጋንንቶች ያሳድዱኝ ጀመር። ከእነሱ ጀርባ ማለቂያ የሌለው የአጋንንቶች ሰልፍ በግልፅ ማየት ችዬአለሁ። ሲኦልን በማምለጤ አሁን ደህንነት አለኝ ብዬ አስቤ ነበር። በዛ ፈንታ፣ በጣም ጠንካራ የሆኑ (በጣም የጠነከሩ) አጋንንትን ከፊት ለፊቴ መጋጠም ነበረብኝ። እኔ በጥልቅ ችግር ውስጥ እንዳለሁ ተሰምቶኝ ነበር።

አሁንም **ኢየሱስ**ን ወይም ማንኛቸውንም መላእክት ማየት አልቻልሁም። እኔም እንዲህ ብዬ አሰብሁ፦ *“እነዚህን የአጋንንት የጦር ሠራዊቶች ብቻዬን መጋጠም አለብኝ!”* እንደዚህ ካለ ጦር ጋር በውጊያ (ለጦርነት) እጋጠማለሁ ብዬ በፍጹም አስቤ አላውቅም። አላማቸው የክርስቲያኖችን የጸሎት ሕይወታቸውን ለማደናቀፍ በመጣር ክርስቲያኖችን ማዘናጋት የሆነ፣ በህዋ ውስጥ የአጋንንት የጦር ሠራዊቶች እንደነበሩ አላውቅም ነበር። አንድ ሕፃን ልጅ የወላጁን እጅ ይዞ በደስታ አብሮት(ሯት) እንደሚሄድ፣ **ኢየሱስ** ሁል ጊዜ እጄን ይይዝና ወደ መንግሥተ ሰማይና ሲኦል ይመራኛል። እኔ በጣም ጥበብ የጎደለኝ (ገራገር) ነበርሁ እና ሁሉም ነገር ቀላል እንደሆነ አስብ ነበር። ያለ ጥንቃቄ ጸለይሁ።

አጋንንቶቹ ወደ ፊት እንዳልሄድ እኔን ለመከላከል እየሞከሩ በወሰድኳቸው በእያንዳንዱ እርምጃዎቼ ብዙ መሠናክሎችን አስቀመጡ። እኔም ከልብ በሆነ ቅን ጸሎት ጮህኩኝ። እንባዎችና ላብ ከሰውነቴ ፈሰሰ። አንድ ጋኔን እንዲህ በማለት ጮኸ፦ *“ሄይ፣ እዛ ጋር ተመልከቱ! ሌላ ጸሎት ከመሬት እየወጣ ነው!”* ከዛ ሌላው እንዲህ መለሰ፦ *“ሄይ፣ ያ ጸሎት ምንም ኃይልና ሥልጣን የለውም።”* አፕሎችን (ፖሞችን) አንስተው እንደሚበሏቸው ሁሉ፣ ከመሬት ወደ ላይ የወጡትን ጸሎቶች አጋንንቶቹ ያዟቸውና ጸሎቶቹን “በሏቸው”።

ከዛ እኔም ኃይል የሌላቸው ጸሎቶች ጥቅም እንደሌላቸው አወቅሁ። እያንቀላፉ የሚደረግ ጸሎት፣ ትኩረት የሌለው ጸሎት፣ በሰውኛ (humanistic፣ በሥጋ) መሻቶች የተሞላ ጸሎት፣ ራስ ወዳድ ጸሎቶች፣ የአካላዊ መሻቶች ጸሎት እና የሚወላውሉ ጸሎቶች ሁሉ ተፈላጊውን ውጤት የማያመጡ ናቸው። በሚገርም ሁኔታ፣ ከመሬት ወደ ላይ በመውጣት እያረጉ ያሉ የተለያዩ የጸሎት አይነቶችን መለየት ችዬ ነበረ። ተፈላጊውን ውጤት የማያመጡ የጸሎት አይነቶች የጋኔን ተወዳጅ “ፍሬዎች” ነበሩ እና ወዲያውኑ በፍጥነት ይበሉ ነበረ።

በህይወትና ሞት ሽረት (with life-and-death desperation) የተሞላ ጸሎት ብቻና ከልብ የሆኑ የእንባ ጸሎቶች ብቻ ሰማዩን ይበሱና ወደ መንግሥተ ሰማይ ይወጣሉ። ፓስተር በሚጸልይበት ጊዜ (ሲጸልይ) በኃይል የሚያለቅስበትንና በሚያሳዝን ሁኔታ የሚጮህበትን አንድ ምክንያት ተረዳሁ። እኔ እንዲህ ብዬ በማሰብ በተደጋጋሚ ብዙ ጊዜ በፓስተር እበሳጭ ነበር፦ *“እዚህ ብዙ ሰዎች የሉም። እርሱ ለምንድን ነው በጣም በኃይል የሚጮኸው? እርሱ ያን ያህል አብዝቶ መጮህ አለበት?”*

በእውነቱ፣ በፓስተር ከፍ ባሉ (ኃይለኛ) ለቅሶዎችና ጩኸቶች ብበሳጭም (ብቆጣም) እንኳ ራሴን ለጸሎት የማስገድድበት ጊዜያት ነበሩ። ብስጭቴንና ቁጣዬን መናዘዝ (መጸጸት፣ ንስሃ መግባት) ጀመርሁ። እንደዛ መጸለይ (እንድንጸልይ) ለእኛ የሚያስፈልግበትን ምክንያት በእርግጠኝነት አውቃለሁ።

ሰዓቱ መንጎዱን ሳላውቅ መጸለዬን ቀጠልሁ። እንደደከመኝና ምንም ጥንካሬ እንዳልቀረልኝ ሳስብ በደማቁ እያበሩ ብዙ ከዋክብትን ከሚልኪ ዌይ በርቀት አየሁ። ወዲያውኑ በውስጤ የቀረውን እያንደንዷን በጣም ጥቃቅን ጥንካሬ አሰባሰብሁና በልሳኖች መጸለይ ጀመርሁ። እኔም ፈጽሞ ደከሞኝ ሚልኪ ዌይ ላይ ደረስሁ፣ ነገር ግን እዛ የእኔ ተወዳጅ **ኢየሱስ** በደስታ ሰላም አለኝ (ሰላምታ አቀረበልኝ)።

**ኢየሱስ** እንዳየኝ በብሩህ ፈገግ አለና እንዲህ አለኝ፦ ***"ቦኒ-ንዮ፣ ታላቅ (በጣም ጥሩ) አድርገሻል። እኮራብሻለሁ!"*** በዛ ጊዜ በትንሹ ተቆጥቼ ስለነበረ በዚህ ሁኔታ **ኢየሱስን** ጠየቅሁት። *"**ጌታ** ሆይ፣ ይህን እንዴት ታደርግብኛለህ? ማስረዳት (ማብራራት) ትችል ነበረ። ያለ አንዳች ማስጠንቀቂያ እንዴት እንዲህ ልትተወኝ ቻልህ?"* ስጨርስ **ኢየሱስ** ሳቀ። እነዚህን ጥቂት ቃላቶች ብቻ ከ**ጌታ** ጋር ከተነጋገርሁ በኋላ እርሱ በድጋሜ ተሰወረ። በድንገት ሁሉም ነገር ጨለማ ነበር፣ እኔም በሲኦል በአንድ ገደል ጫፍ ላይ ቆሜ ነበር።

**ጌታ** እምነቴን ለመፈተን በተጨማሪ አንድ ጊዜ ትቶኝ ሄደ። በቶሎ ከጥቂት ቆይታ በኋላ ከዶልፊን ጋር የሚመሳሰል አንድ ጋኔን አፉን በጣም ከፍቶ ሹል ጥርሶቹን እያሳየ ሊያጠቃኝና ሊነክሰኝ ሞከረ። ልቢጭረው በሚመስል ሁኔታ ተንቀሳቀስሁና እንዲህ ጮህኩበት፦ *"ከቻልክ ና እና ያዘኝ።"* ጋኔኑም በቀላሉ ጠፋ።

ከፊት ለፊቴ አንድ ጠባብ መንገድ ነበረ። እኔም በዚህ መንገድ ላይ ወደ ፊት መራመድ ጀመርሁ እና የሆነ ነገር እየቀረበኝ እንደሆነ ከማወቄ በፊት ረዘም ላለ ጊዜ ተጓዝሁ። እየቀረበ ሲመጣ ራስ ብቻ ያለው ነገር ግን ዓይኖችና አፍንጫ የሌለው አጸያፊ መሳይ አንድ ጋኔን እንደሆነ ማየት ችዬ ነበረ። ፊቱ ላይ ከግራ እስከ ቀኝ ጆሮው ድረስ ሰፊ መቆረጥ ነበረ እና ጥርሶቹም እንደ ሻርክ ጥርስ የሰሉ (የሾሉ) ነበሩ።

ከዚህ ጋኔን ጋር ፊት ለፊት ስሆን እንዲህ አልሁ፦ *"ሄይ፣ ከአንተ በጣም የገዘፉ አጋንንትን ተዋግቼ አሸንፌአለሁ። አንተ ለእኔ ምንም ነህ። **በአምላክ ሥላሴ** የተፈጠረ እሳት በውስጤ አለ። አካሌን በነካህበት ቅጽበት ትነድና ወደ አመድነት ትለወጣለህ። መጥተህ እንድትዋጋኝ እዳፈርሃለሁ።"* ጋኔኑ በጣም ፈርቶ ነበረና በፍጥነት ሮጦ ጠፋ። ማለቂያ የሌለውን መንገድ ብቻዬን ተጓዝሁ። ወደ ሲኦል ጥልቅ ውስጥ በጥልቀት እየተጓዝሁ እንደሆነ ይመስል ነበረ። እኔም ደንግጬና በውስጤ እየተንቀጠቀጥሁ ነበር፣ ነገር ግን ፍርሃቴን ማሳየት ስላልፈለግሁ ተረጋግቼ መቆየትና ራሴን መሰብሰብ ነበረብኝ።

እኔም በመንገዱ ላይ መራመድ ቀጠልሁ። በህይወት ያለ የሚመስል አንድ ትልቅ ቅጠል አስተዋልሁ። ቅጠሉም በተደጋጋሚ ይከፈትና ይዘጋ ነበረ እና ሊውጠኝ ሞከረ። እኔ ግን እንዲህ በማለት ጮህኩኝ፦ *"ደህና! ለይቼ እዚህ የመጣሁት አንተን ልገድልህ ነው! ማን እንደሚተርፍ (እንደሚድን) እንይ!"* እኔም መልሼ በኃይል አጠቃሁ እናም ጋኔኑ በቶሎ ጠፋ።

እኔም ቀጠልሁ። በመንገዱ በሁለቱም አቅጣጫዎች እንደ ነብሳት (insects) የሆኑ የአጋንንት መንጋዎች ሊይዙኝ እየሞከሩ እንደሆነ ተገነዘብሁ። ብርድ ብርድ እንዲለኝ ያደረጉ የአጋንንቶችን አስደንጋጭ ጩኸቶች ሰማሁ። ብዙ የተለያዩ ጩኸቶችን ሰማሁ፣ እኔ ግን ችላ አልኳቸውና በኃይል ጮክ ብዬ በልሳኖች እየጸለይሁ ተጓዝሁ። እኔም እንዲህ በማለት ጮህኩ፦ *"**ሥላሴ አምላክ ሆይ**! ጥንካሬውን ስጠኝ! አካላዊና መንፈሳዊ ጥንካሬና ኃይልን ስጠኝ!"* በቅንነት ከልብ ጸለይሁ እና በቶሎ ቅዱሱ እሳት በውስጤ በኃይል በብሩህ እየተንበለበለ ነበረ።

ምን ያህል እንደተጓዝሁ ለማወቅ እየሻትሁ፣ የመንገዱን ፍጻሜ በርቀት አየሁ ብዬ አሰብሁ። በድንገት፣ አንድ ብሩህ ደማቅ አንጸባራቂ ከፊቴ ታየ እና እዛ **ኢየሱስ** ነበረ። እኔም በአድናቆት በጣም ተደንቄ ነበረ (እጅግ ተደንቄ ነበረ)። *"አዎ! **ጌታ** ሆይ፣ በመጨረሻ ዳንሁ!"* ወደ እርሱ ሮጥሁና አቀፍሁት። **ጌታም** በእርጋታ በክንዶቹ ያዘኝና እንዲህ አለ፦ ***"የእኔ ልባዊ ተወዳጅ ቦንግ-ንዮ፣ እዚህ ለመምጣት በብዙ ውስጥ አልፈሻል! ከአጠገቤ ተቀመጪ እኔም እረፍትን እሰጥሻለሁ።"*** እኔም በ**ጌታ** ክንዶች ውስጥ ቆየሁ እና ለማረፍም ዓይኖቼን ከደንሁ (ጨፈንሁ)።

*"በድጋሜ እየሆነ ነው?"* ዓይኖቼን ስከፍት **ጌታ** የትም ቦታ ሊገኝ አልቻለም። እኔም እንዲህ ብዬ አሰብሁ፦ *"እንዴት በሲኦል ጨለማ ክፍል ውስጥ ልመለስ ቻልሁ?"* ምንም ያህል ወደ **ጌታ** በኃይል ብጣራም ባዶነት ብቻ አስተጋባ። ወደ **ጌታ** ተጣራሁ፣ ነገር ግን እርሱ እዛ አልነበረም። **ኢየሱስ** አሳተኝ የሚል ስሜት ከተሰማኝ በቀር ልረዳ አልቻልሁም። **ኢየሱስ** በግልጽ እንዲህ ብሏል፦ ***"ቦንግ-ንዮ፣ ጥሩ አድርገሻል። ልትፈጽሚ ነው ስለዚህ ታጋሽ ሁኚና እዚህ እረፊ።"*** እርሱ እነዚህን ነገሮች ካለ በኋላና እኔ ደህንነት ሲሰማኝ፣ እርሱ በድጋሜ ፈተነኝ።

ቁጣዬ ያልተወሰነ ነበር። እንደ መካነ አራዊት እንስሳ በብረት ቤት ውስጥ ተቆልፎብኝ እንደነበረ ተገነዘብሁ። በተለያዩ መልኮች የማይቆጠሩ አጋንንት ቤቴን ከበው ሊጠይቁኝ ሲሞክሩ እያፈጠጡብኝ ነበር። እነሱ እያሾፉብኝና እየሳቁብኝ አፈጠጡብኝ። የራስ ቅል ባርኔጣዎችን ያደረጉ ብዙ ሺሆች የአጋንንት ሠራዊቶች እዛ ነበሩ።

በብረቱ ቤት ውስጥ ተቆልፎብኝ ሳለሁ አጋንንቶቹ እኔን በመከታተል (በመመልከት) ላይ አተኮሩ። እኔም እንዲህ በማለት ጮህኩኝ፦ *"ሄይ እናንተ መጥፎዎች፣ ማን ናችሁ? ከየት ነው የመጣችሁት?"* እነሱም እንዲህ መለሱ፦ *"እኛ ከዚህ ወደዚያ (እዚህም እዚያም) ከተዘዋወርን በኋላ መጣን። አንቺስ፣ ለምንድን ነው እዚህ የሆንሺው?"* **ኢየሱስ** ወደ ሲኦል እንዳመጣኝ፣ ነገር ግን እርሱ ትቶኝ እንደሄደ እናም ብቻዬን እዚህ የሆንሁበት ምክንያት ያ እንደሆነ አብራራሁ። እነሱም ይህን ከሰሙ በኋላ እንዲህ በማለት አፌዙብኝ (አላገጡብኝ)፦ *"ሄይ፣ ጌታሽ ሊመለስልሽ አልፈለገም። ይህ ላንቺ ፍጻሜሽ ነው!"*

እኔም ድምፄን ከፍ አድርጌ በልሳኖች መጸለይ ጀመርሁ። የራስ ቅል ባርኔጣ ያደረጉት የአጋንንት ዓይኖች ወደ ቀይ መለወጥ ጀመረ። እነሱ በቁጣ ወደ ታች አፈጠጡብኝ። በልሳኖች የመጸለይ ኃይል አጋንንቶቹን አስጨንቋቸው (ከብዶባቸው) ነበረ እና እነሱ ሲለወጡ ስላየሁ የበለጠ ድምፄን ከፍ በማድረግ ጸለይሁ። *"**አምላክ ሥላሴ** ሆይ፣ በብሩህ በኃይል ወደሚንበለበለው እሳትህ ለውጠኝ!"* ሁሉም አጋንንት ለማውደም በመፈለግ የብረቱን ቤት አጠቁት። ነገር ግን፣ በውስጡ በብሩህ እየተንበለበለ ያለው ቅዱሱ እሳት ነድዶ አቃጠላቸውና ሁሉንም ወደ አመድነት ለወጣቸው። የቤቱ የብረት ዘንጎች አልተበላሹም ነበር ነገር ግን ሳይጎዱ ቆዩ።

አንዴ በድጋሜ፣ የተለያዩ እንስሳት ጩኸቶችና የአጋንንቶች ድምፆች በመላው ጊዜ ሁሉ አስተጋባ እና ለወራቶች እዛ የነበርሁ ያህል ይሰማል። ምንም ያህል በትጋት ብጮህም ብራገጥም ብጮህም ከሲኦል ቤት ውስጥ መውጫ ምንም መንገድ አልነበረም። ቀስ በቀስ ነፍሴ በድካም መሠቃየት ጀመረች። **ጌታ**ን መጠበቁ ከልብ ከሆነ መናፈቅ ወደሚነድ የልብ ህመም ተለወጠ፣ ነገር ግን መጸለይ ማቆም አልቻልሁም።

እንዲህ ብዬ ጸለይሁ፦ *"**ጌታ** ሆይ፣ ጥንካሬ ያስፈልገኛል (እፈልጋለሁ)። ጥንካሬ ስጠኝ! ደግሞም የፈውስ ስጦታ ስጠኝ እና ከዚህ ለማምለጥ የብረቱን ቤት ማቅለጥ እንድችል በእሳቱ ሙላኝ።"* እኔም ዓይኖቼን ከፈትሁ እና አሁንም በቤቱ ውስጥ ተቆልፎብኛል። በሲኦል ቤት ውስጥ ምንም ህልም ወይም ተስፋ የለም። ምንም ያህል በብዛት ወደ **ጌታ** ብጣራም አሁንም በቤቱ ውስጥ ተጠምጃለሁ። ይህ ማለት በሲኦል ውስጥ ለዘላለም እሠቃያለሁ ማለት ነው? አንድ ጣት እንኳን ለማንሳት በውስጤ የቀረ በቂ ጥንካሬ አልነበረኝምና ወደ አንድ ጥግ ወደቅሁ። በቤቱ ውስጥ ለአራት ወራቶች ያህል የተጠመድሁ ይመስል ነበረ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ እንደገና መጮህ ጀመርሁ፦ *"**ጌታ** ሆይ፣ እርዳኝ! የት ነው ያለሽው?"* የ**ጌታ**ዬን ጥላ እንኳ አላየሁም። አጋንንቶቹ አካሌን መንተትና ማሠቃየት ቀጠሉ እና እኔም ለ15 ቀናት ከእነሱ ጋር ተዋጋሁ። በቤቱ ውስጥ ቀናቶች ሲነጉዱ በግልጽ ይሰማኝ ነበረ።

*"**ጌታ** ሆይ እርዳኝ! እባክህን አስወጣኝ። ከዚህ ቦታ እንዳመልጥ እርዳኝ!"* ለራሴ እየጸለይሁ ነበረ። አንድ ሰው ሲስቅ ሰማሁ። እኔም እንዲህ ብዬ ጮህኩኝ፦ *"ዋው! ይህ **የጌታ** ድምፅ ነው!"* **ጌታ** በብሩህ ደማቅ ብርሃን መሀል ውስጥ ታየና ጨለማውን ቤት እና በዙሪያዬ ያለውን አካባቢ አበራው።

**ኢየሱስ** የበለጠ ከፍ ባለ ድምፅ እንዲህ እያለ መሳቅ ጀመረ:- ***"ተወዳጅ ቦንግ-ንዮ፣ በሲኦል ውስጥ የነበረው ልምምድሽ እንዴት ነበረ?"*** እኔም **ጌታ**ን ጠየቅሁት:- *"**ጌታ** ሆይ፣ እንዴት ይህን ታደርግብኛለህ? እኔ እንድሠቃይ ለማድረግ ወሥነህ ነበር? ለምን ይህን አደረግህብኝ?"* ቅሬታዎቼን ሳቀርብ በጣም ተጨንቄ ነበረ እና **ጌታ** እንዲህ በማለት መለሰ:- ***"ይቅርታ። በግሌ አንቺን ለመፈተን ፈልጌ ነበረ፤ እምነትሽ ምን ያህል እንዳደገ!"*** ለዛ አንዳች ማለት አልቻልሁም።

**ጌታ** የት እንደነበረ ስጠይቅ እርሱ ብዙ ቤተ ክርስቲያኖችን ለመጠበቅና ተወዳጅ ምእመናኑን ለመምራት (ለመንከባከብ) በምድር ላይ እንደነበረ መለሰ። እጅግ የውስጥ ስሜቶቼን ለ**ጌታ** ተናዘዝሁና ምህረቱን ጠየቅሁ። *"**ጌታ** ሆይ፣ እኔ መራርና በዚህ በሲኦል ቤት ውስጥ ሳለሁ በጣም በብዙው ቅር ተሰኝቼብህ ነበርሁ። ማረኝ።"* የድምፄ ቃና በቅሬታዎች ተቀየረና ስሜቶቼ በድንገት ሲናደዱ ለራሴ ሀዘን ተሰማኝ። *"**ጌታ** ሆይ፣ ለአራት ወራት ያህል በቤቱ ውስጥ ተዘግቶብኝ ነበርሁ።"* ማንባት ጀመርሁ።

**ጌታ** ከፍ ባለ ድምፅ መሳቅ ቀጠለ እና እኔ እንዲህ በማለት ጮህኩኝ:- *"እኔ አዝኜና ተበሳጭቼ ስታየኝ ለምንድን ነው ደስተኛ የሆንከው? በሲኦል ውስጥ በጣም ብዙ ተሠቃይቻለሁ፣ ለምንድን ነው ግን አንተ እንደሚያስቅ ነገር እየሳቅህ ያለኸው። በሥቃይ ውስጥ ሆኜ ማየትህ የሚያስደስትህ ነው?"* እርሱም በርህራሄና በእርጋታ እንዲህ መለሰ:- ***"ቦንግ-ንዮ፣ ቤተ ክርስቲያን መካፈል ከጀመርሽ ሁለት ወራት ብቻ ነው፣ ነገር ግን እምነትሽ እጅግ በጣም አድጓል። ኮርቼብሻለሁ!"*** እርሱ በእርጋታ ጀርባዬ ላይ መታ መታ አደረገኝ።

**ኢየሱስ** በሲኦል ውስጥ ለብሼው የነበረውን ለጦርነት የሚለበሰውን ልብስ አወለቀና ክንፎች ባሉት በንፁህ የሚያበራ ልብስ በድጋሜ እንዲያለብሱኝ መላእክቶችን አዘዛቸው። እርሱ እንዲህ አለ:- ***"አንቺ ብዙ ጸንተሻል፣ ስለዚህ መንግሥተ ሰማይን እንጎብኝ!"*** እርሱ እጆቼን ያዘና ወደ መንግሥተ ሰማይ መብረር ጀመርን። በሕይወቴ ከተለማመድሁት በጣም ከባዱ ቀን ዛሬ ነበረ።

ከመሬት ወደ ሚልኪ ዌይ ለመድረስ ነፍሴን ሦስት ዓመታት ፈጅቶባታል እና እኔም በሲኦል ውስጥ 4 ½ ወራት አሳልፌአለሁ። 3 ½ ዓመታት በፍጥነት ያለፉ ይመስላል። በህዋ ውስጥ ያሉ አጋንንትና በሲኦል ውስጥ ያሉ ክፉ አጋንንት ሁሉ ከባዶችና ጠንካሮች ነበሩ። ከ**ጌታ** ጥበቃ ውጭ (ያለ **ጌታ** ጥበቃ) ለአንድ ደቂቃ ወይም አንድም ሰከንድ እንኳን ከአጋንንት ጋር በጦርነት ውስጥ መቆየትና አሸናፊ መሆን አልችልም ነበረ። መንግሥተ ሰማይ ውስጥ ስደርስ ብዙ መላእክቶች ፈገግ አሉና አጽናኑኝ። *"እህት ሆይ፣ ጥሩ አድርገሻል!"* የመላእክቱ ቃላት መንፈሶቼን አነሣ። ምን ጊዜም በመንግሥተ ሰማይ ስሆን በሲኦል ውስጥ የተለማመድሁት መከራ (ችግር) ሁሉ ይረሳል።

ቤተ ክርስቲያን መካፈል ከጀመርሁ ሁለት ወራት ብቻ ስለሆነኝ እኔ በጣም ብዙ አላውቅም። በአንድ ፊልምና በአንድ ስብከት ካየሁት ባህርን ስለከፈለ ሙሴ ስለሚባል አንድ ሰው ትንሽ ተምሬአለሁ። አንድ ጊዜ ብቻ ሙሴን እንዳገኘው ለ**ኢየሱስ** ጥያቄ አቀረብሁ። **ኢየሱስ** ወደ ወርቃማው የአሸዋ ባህር ዳርቻ መራኝ። መላእክቶች በእርጋታ ወደ ታች ወደ ዳርቻው አመጡኝ። **ኢየሱስ** ሙሴን በስም እንደጠራው እርሱ ቀረበኝና በትሕትና ሰላም አለኝ:- *"እንኳን በደህና ወደ መንግሥተ ሰማይ መጣሽ!"* ሙሴ በጣም ረጅምና መልከ መልካም ነበረ።

**የሙሴን ተአምራት በመንግሥተ ሰማይ ውስጥ ማየት*

**ኢየሱስ** እኔን ለሙሴ አስተዋወቀኝ። እኔ እንዲህ አልሁ:- *"ሙሴ ሆይ፣ ክቡር ሆይ፣ በጣም በበቂ ሁኔታ አላውቅህም። ነገር ግን ከፓስተሬ አንድ ስብከት ስላንተ ስለሰማሁ በጣም ትንሽ አውቃለሁ።"* እርሱም መለሰ:- *"ኦህ በእውነት? እህት ሆይ፣ እዚህ በመሆንሽ ደስተኛ ነኝ!"* እኔ ቀጠልሁ:- *"በመሬት ላይ ሳለህ ውቅያኖሱን ከፍለህ እና ብዙ ተአምራት አላደረግህም (አላከናወንህም)?"* ሙሴ በትሕትና እንዲህ መለሰ:- *"እኔ አንዳች አላደረግሁም፣ ነገር ግን **እግዚአብሔር** ነበረ ጥንካሬውን የሰጠኝ እና እኔ ያደረግሁት ነገር ሁሉ መታዘዝ ነበረ።"* እኔም እንዲህ አልሁ:- *"እኔ ቤተ ክርስቲያን የተካፈልሁት ለሁለት ወራቶች ብቻ ነው፣ ስላንተ በሰማሁበት ቅጽበት ግን አንተን ለመገናኘት ፈለግሁ።*

*ነገር ግን፣ **ጌታ** አብዛኛውን ጊዜ ሲኦልን እንድጎበኝ ይወስደኛል፣ ስለዚህ አንተን መገናኘት የማይቻል ነበረ። ከተአምራቶችህ አንዳንዶቹን ለማየት እመኛለሁ። አንዳንድ ልታሳየኝ ትችላለህ?"*

**ኢየሱስ** ሙሴን አንድ ግዙፍ ተራራ በወርቃማ አሸዋ እንዲገነባ ፈቀደለት። በዓይን ቅፅበት ሁለት የተራራ ጫፎች እዛ ነበሩ። እኔም አንድ ባለ 600 ፎቅ ቤት እንዲገነባ ለማረጋገጥ ጠራሁት። እርሱ እጆቹን በቀላሉ ወደ ላይ አነሳና አንድ ጊዜ አሽከረከረው እና አንድ ባለ 680 ፎቅ አፓርትመንት ሕንጻ ከፊቴ ታየ። በአግራሞት መንገጭላዬ ወረደ። እርሱ ከመሬት ወደ መንግሥተ ሰማይ የተዘረጋ አንድ ወርቃማ ደረጃዎች ሰራልኝ። ሙሴ በቃላት ሊብራሩ የሚችሉ ብዙ ሌሎች ተአምራት አከናወነ። እኔ እንዲህ አልሁ፦ *"ሙሴ ሆይ፣ ክቡር ሆይ፣ ላልጠነከረው እምነቴ ይቅርታ እጠይቃለሁ። በጣም ብዙ ስለፈተንሁህና በጣም ብዙ ጥያቄዎችን ስለጠየቅሁህ አዝኜና ቅር ተሰኝቼአለሁ (አፍሬአለሁ)።"* እርሱም እንዲህ መለሰ፦ *"ስለ አንዳች አትጨነቂ እና አሁንም ጥያቄዎች ካሉሽ ለመጠየቅ አታመንቺ።"*

ይህ (የውቅያኖስ መከፈል) የእውነት በጣም አስደናቂ የሆነ አስደንጋጭ ልምምድ መሆኑን በማየቴ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንደተጻፈው የውቂያኖስን መከፈል ለማየት ጠየቅሁ። **ኢየሱስ** ከአጠገቤ ሆኖ በጸጥታ እየተመለከተ ነበረ። *"**ኢየሱስ ሆይ**፣ ሙሴ ሆይ፣ እኔ አዲስ አማኝ ነኝና ብዙ አላውቅም፣ ስለዚህ በጥያቄዎቼ በጣም ፈጣን እንደነበርሁ አሰብሁ። እባካችሁ ይቅርታ አድርጉልኝ። ይቅርታ። ወደ ቤተ ክርስቲያን ስመለስ ያየሁትን እጽፍና ዓለም እንዲያውቅ ማድረግ እንዲችል ለፓስተሬ አካፍለዋለሁ።"* **ኢየሱስ**ና ሙሴ ሁለቱም ደስታቸውንና ጥልቅ ስሜታቸውን ገለፁ። **ኢየሱስ** እንዲህ አለ፦ ***"ሙሴ፣ እህት ቤይክ ቦንግ ንዮ ወደ ምድር መመለስ ስላለባት ደህና ሁኚ በላት።"*** ሙሴ በትሕትና ራሱን ዝቅ አደረገና *"ደህና ሁኚ እህት ሆይ።"* አለ።

**ኢየሱስ** ለእኔ እንዲህ በማለት አብራራልኝ፦ ***"በመንግሥተ ሰማይ እንኳ ሙሴ ሁል ጊዜ ባተሌ (ሥራ የበዛበት) ነው። እርሱ በመንግሥተ ሰማይ ዙሪያ ሁሉ ይጓዛል እና የሚጠብቃቸው ብዙ ነገሮች አሉት።"*** በመንግሥተ ሰማይ ሙሴን መገናኘቴን (መተዋወቄን፣ ማግኘቴን) በፍጹም አልረሳውም። **ኢየሱስ** ወደ ቤተ ክርስቲያን መልሶ መራኝ እና እኔም ጸሎቶቼን ፈፀምሁ።

## ==== ቀን 23 ==== (1ኛ ዮሐንስ 3:7-10)

**ፓስተር ኪም ዮንግ ዱ:** **ወይዘሮ ካንግ, ህዩን ጃ ያለ መከላከያ ተያዘችና በአንድ ጋኔን ተጠቃች*

ከሌሊቱ 5 ሰዓት ላይ ሚስቴ፣ ዮሴፍ፣ ጁ ኢዩን፣ እና እኔ ከሕብረት ድርጅት የግብርና ማህበር (Cooperative Agricultural Association) ሕንጻ ባሻገር ከሚገኘው አንድ ሬስቶራንት ፊት ለፊት ቆመን ነበር። ሚስቴ ወደ ፊት ስትራመድ ተመታችና መሬቱ ላይ ወደቀች። በበረዶ ላይ እንደምትንሸራተት እርሷ በጠንካራው አስፋልት መንገድ ላይ ከቁጥጥር ውጭ ወደ አምስት ሜትሮች ያህል ርቃ ተንከባለለች። ይህ በጣም በፍጥነት ስለሆነ ወድቃ እንዲህ ስትሆን እርሷን ለመያዝ አንድም እድል አልነበረንም። እርሷ በሥቃይ ጮኸች እና እንድትነሳ ለመርዳት እኛ ሁላችንም ሮጥን። መዳፎቿ ሁሉ ተከፍተው፣ የጣቶቿ ጥፍሮች ተሰብረው፣ እና እጆቿ በደም ተሸፍነው ነበር።

እንዲህ ሀይለኛ ውድቀት ሊያስከትል የሚችል አንዳች ነገር ለማግኘት በመንገዱ ዙሪያ ፈለግን። ነገር ግን መንገዱ በጣም ንጹህ፣ ለጥ ያለ፣ እና በተስተካከለ ጥሩ ቅርፅ ላይ ነበረ። ይህን ሊያስከትል የሚችል ምንም ቁሳዊ ማስረጃ አልነበረም።

በኋላ ላይ ጁ-ኢዩን **ኢየሱስ**ን ስለዚህ ነገር ጠየቀችው። የእለት ተእለት እንቅስቃሴያችን ከቤተ ክርስቲያን መሄድ፣ ከመጸለይ፣ እና ወደ ቤት ከመሄድ የተውጣጣ ስለሆነ እኛ የመዝናኛ ሰዓት እንደሌለን **ኢየሱስ** አብራራ። እርሱ ቀጥሎም የመዝናኛ ምንም ሰዓት ስለሌላችሁ ክፉ መናፍስት እናንተ ደካማ የምትሆኑበትን ለማግኘት ትንሽ አጋጣሚ ነው ያላቸው በማለት አብራራ። ነገር ግን ዛሬ፣ በረጅም ጊዜያት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ትንሽ የመዝናኛ ሰዓት ለመውሰድ (ለመዝናናት) ቤተ ሰቤ ከመንፈሳዊ የእለት ተእለት እንቅስቃሴ ወጣ። ከተለመደው የእለት ተእለት ሁኔታ ውጭ አንድ ክፉ መንፈስ እርሷን መታትና ወደቀች።

**ኢየሱስ** የሚስቴን የቆሠሉ መዳፎች ነካ። እኔም ደግሞ ሚስቴን ማጽናናት ጀመርሁ። *"የእኔ ተወዳጅ ሚስት ሆይ፣ **ለእግዚአብሔር** ምስጋና እናቅርብ። መከላከያችንን ስላወረድን ንስሐ መግባትና **ለጌታ** ምስጋና ማቅረብ አለብን። እርሱ የሚልቅ ጸጋ ያቀርብልናል። እስከ መጨረሻው እንጽናና ድል እናድርግ።"* ሳጽናናት (ሳበረታታት) በጉልበቶቿ ተንበረከከችና የቆሠሉ እጆቿን ወደ ላይ ከፍ አድርጋ ለጌታ ምሥጋና አቀረበች (ሰጠች)።

ክፉ መናፍስት ሁል ጊዜ ስለሚያጠቁንና ስለሚያደናቅፉን፣ ሁል ጊዜ ንቁ እና ጥንቁቅ መሆን እንዳለብኝ ወሰንሁ። መከላከያችንን ባወረድንበት ጊዜ ክፉ መናፍስቶች ያጠቃሉ። የጸሎት ቀን ካለፈን (አንድ ቀን ሳንጸልይ ከቀረን) አዕምሮአችን ይደክምና ለጥቃት እንዳረጋለን። ክፉ መናፍስቶች ለደካማ ጊዜያት በጉጉት ይጠባበቃሉ። ስለዚህ ሁል ጊዜ ሙሉ በሙሉ መታጠቅ አለብን።

የጸሎት ስብሰባችን አንድ ተጨማሪ ሳምንት ብቻ ነበረው እና ጥቃቶቹም የበለጠ የማያቋርጡ (ያልተቆጠቡ) እየሆኑ መጥተዋል። ሁላችንም መንፈሳዊ ዓይኖቻችን አንድ በአንድ እየተከፈቱልን ነው። ጠላት ይህን ያለቅጥ (በጣም) ፈርቷል፣ ጥቃቶቹ ግን የደከሙ ነበሩ። ጸሎቶቻችን እየጠነከሩ ሲመጡ እምነታችን አደገ። በጣም የጠነከሩ ክፉ መናፍስት ይላኩ ነበርና ጦርነቶቻችንም (ውጊያዎቻችንም) የማያቋርጡ ነበሩ።

በኋላ፣ የሚያሠቃይ ኪንታሮት የነበረውን የዮሴፍን እግር መረመርሁ። እኛ ለፈውስ በኃይል ጸልየን ነበረ። ባየሁት ነገር ደንግጬ ነበር። ቆዳው ውስጥ የነበረው ኪንታሮት፣ አሁን ጥቁር ስሮቹን በውጭኛው እግሩ ላይ ገልጧል። በመንፈሳዊ ዓይኖቼ **ኢየሱስ ደሙን** በዮሴፍ እግር ላይ በየቀኑ ሲያደርግ ማየት ችዬአለሁ። እኔም እንዲህ አልሁ፡- *"ዋው! ይህ በጣም ታላቅ ነው። ዮሴፍ፣ የቆዳ ዶክተር ጋር ሄደህ ምስክርነትህን መስጠት ይገባሃል።"*

በኋላ፣ ሚስቴ አክታ እስከታወጣ ድረስ ማሳል ጀመረች። ዮሴፍ፣ ጁ-ኢዩን፣ እና እኔ እጃችንን አንገቷ ላይ አደረግንና ከልብ ጸለይን። ረጅም ፀጉር ባላትና ነጭ ልብስ በለበሰች ወጣት ሴት ልጅ መልክ አንድ ጋኔን ራሱን ለእኛ ገለጠልን። ጋኔኑ ለሚስቴ መውደቅ ሃላፊ ነበረ፣ አሁንም እንድትሠቃይ፣ እንድታስልና አክታ እንድታወጣ እያደረገ የሚስቴን አንገት እያጠቃ ነበረ።

እኔም እጄን በአንገቷ ላይ አደረግሁና ስጸልይ ሌላኛውን እጄን አወዛወዝሁ። በቶሎ ክፉው መንፈስ እንዲህ በማለት ጮኸ፡- *"ፓስተር ኪም፣ እጅህን አንሳ! በዚህ ቅጽበት እጅህን አንሳ! መጸለይ አቁም! ኦህ፣ በጣም ይሞቃል። ላብድ ነው ብዬ አስባለሁ!"* ጋኔኑ ጮኸና ጠፋ።

**ኢየሱስ** መጣና እንዲህ አለ፡- ***"ልጆቼ ሆይ፣ ክፉው መንፈስ ሸሽቷል። ነገር ግን ክፉው መንፈስ ቀሪ የሥቃይ ውጤቶችን (ጥፋቶችን) ስለተወ ለጥቂት ጊዜ መቋቋም ይኖርባችኋል። ያለማቋረጥ ከጸለያችሁ በፍጥነት ትፈወሳላችሁ። አትጨነቁ።"***

**ኪም ጁ ኢዩን:**

"***ኢየሱስ** ሆይ፣ በመንግሥተ ሰማይ ውስጥ ቤቶቻችንና ግምጃ ቤቶቻችን ምን ያህል ትልቅ ናቸው?"* በማለት ጠየቅሁ። **ኢየሱስ** እንዲህ መለሰ፡- ***"ለምን ጸልየሽ ለራስሽ በመንግሥተ ሰማይ ኢታዩውም? እኔ በዚህ ጊዜ ላይ ላሳይሽ አልችልም። በእምነትሽና በትጋትሽ መንፈሳዊ ዓይኖችሽ እስኪከፈቱ ድረስ መልሱን ለማወቅ እሺ። አንጄ ያ እንደሆነ ወደ መንግሥተ ሰማይ ነዪና መልሱን አግኚ።"***

"***ኢየሱስ** ሆይ፣ የአባቴ ጸሎቶች ምን ያህል በመሻሻል ተንቀሳቅሰዋል?"* **ጌታ**ም እንዲህ መለሰ፡- ***"ፓስተር ኪም ሲጸልይ መንፈስ ቅዱስ ይገለጸል። የፓስተሩ እጆች የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ያደርጋሉ። ይህ ማለት የፈውስ ስጦታ እርሱ ላይ መጥቷል ማለት ነው። ነገር ግን፣ ይህ የፓስተር ኪም የመጀመሪያ ልምምድ ስለሆነ እርሱ በጸሎት ጊዜ ዓይኖቹን መክፈት ቀጥሏል።***

*ስለዚህ የእርሱ ጸሎቶች ወደ ፊት ወደ ዙፋን እየሄዱ አይደለም፣ ነገር ግን ጋላክሲ ውስጥ ቀርተዋል። እርሱ መጸለይ ቢቀጥልና ስለ ኢጆቹ መንቀሳቀስ ባይጨነቅ እርሱ በቶሎ በመንፈሳዊ ይከፈትና መንግሥተ ሰማይን መጎብኘት ይችላል።"*

**ጌታ** በተጨማሪ የወንድም ዮሴፍ ንስሐ (ጸጸት) በጣም ደካማ እንደነበረ ተናገረ። **ጌታ** ከልብና በቅንነት ንስሐ እንዲገባ ነግሮታል። ነገር ግን፣ **እግዚአብሔር** በእናቴ እንባ በተሞላ ንስሐ እና ርኅራኄ በሚያሳዩ ጸሎቶቿ ረክቷል።

*እኔ እንዲህ አልሁ:- "**ኢየሱስ** ሆይ፣ የአባቴ እናት ዲያቆኒት ናት፣ ነገር ግን እርሷ በጣም ብዙ ስትጠጣ ትታያለች።"* **ጌታም** እንዲህ መለሰ:- ***"በአያትሽ ውስጥ አንድ የአልኮል ሱሰኛ ክፉ መንፈስ አለ። ምን ጊዜም ፓስተር ኪም ለመጸለይ ጊዜ ሲኖረው ሊጸልይላት ይገባዋል። ለደህንነትና እምነት ማረጋገጫ ንስሐ እንድትገባ (ኃጢአቷን እንድትናዘዝ፣ እንድትመሰክር) ደግሞ እርሱ ሊመራት ይገባዋል።"***

**ፓስተር ኪም:** (የያዕቆብ መልእክት 4:4-5) **ዝሙት የሚፈጽሙ ፓስተሮች እና የቤተ ክርስቲያን አባላት*

ምን ጊዜም አገልጋዮች መነጋገሪያ (አርእስተ) ዜና ሲሆኑና ቆሻሻ ምስጢራቸው በቲቪ ሲጋለጥ ልቤ ይታመማል። ቤተ ሰዎቼ የዚህን ጭምጭምታ ይሰማሉ (ያውቃሉ) በሚል ፍርሀት ቲቪውን አጠፋዋለሁ ወይም ጋዜጣውን እቀደዋለሁ። እንደ አገልጋይ እኔ በጣም አፍር እና ቅር እሰኛለሁ። እኔ ግራ ተጋብቻለሁ፤ ምን ማድረግ እንደሚገባኝ አላውቅም። አገልጋይ ስለሆንሁ እኔ እንደተጋለጥሁ ያህል ነው የተሰማኝ። ሌሎች የወደቁ አገልጋዮችን ቆሻሻ ድብቅ ምስጢሮች ለመወያየት ወይም ለማጋለጥ ምንም መሻት የለኝም። ነገር ግን **ጌታ** በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ዝርዝሮቹን እንድጽፍ ተጫነኝ።

የዝሙት ኃጢአትን ፈጽሞ መፈፀም እንደሌለብን **ኢየሱስ** አዘዘ። ወደ ሲኦል ከሚሄዱት ከማይቆጠሩት ሰዎች መሀል ብዙዎቹ አመንዝራዎች ናቸው። **ጌታ** እንዲህ በማለት አስታወሰን:- ***"የቤተ ክርስቲያን አባላቶቻችሁ አመንዝራዎች በሲኦል ውስጥ ሲሠቃዩ አላዩምን? ዝሙት ንስሐ ለመግባት በጣም የሚያስቸግር ኃጢአት ነው።"*** **ጌታ** የእርሱ ሕዝብ መንፈሳዊ ዝሙት ሲፈጽሙ ይጠላል፣ ነገር ግን እርሱ ደግሞ አካላዊ ዝሙትን የሚፈፅሙትን ሰዎች የበለጠ ይንቃል።

ብዙ አገልጋዮችና የቤተ ክርስቲያን አባላት **የኢየሱስን ስም** በመጠቀም ኃጢአታቸውን ከተናዘዙ ብቻ በፍፁም ይቅርታ እንደተደረገላቸው በማሰብ ራሳቸውን ያሞኛሉ። በውጤቱም፣ ያንኑ ኃጢአት መፈፀም ይቀጥላሉ፣ በድጋሚ ይናዘዛሉ እና በጸጋ እንደተሸፈኑ ያስባሉ። እነርሱ ጸጋን ይረጋግጣሉ እና ያንኑ የዝሙት ኃጢአት ደግሞ ደጋግሞ ለመፈፀም አያመነቱም። **ጌታ** በከንቱ ስሜታቸው ቅር ተሰኘ። (የዮሐንስ ራእይ 2:21-23) ። አንድ ሰው ወደ **ኢየሱስ** ከመምጣቱ በፊት ካለማወቅ ክፉ ያደርጋሉ። ሰዎች እርሱን እንደ **ጌታ** ተቀብለው ነገር ግን ያለማመንታት በተደጋጋሚ ኃጢአትን ማድረግ በመቀጠላቸው **ኢየሱስ** በጣም ተቆጥቷል። **ጌታ** በቁጣ እንዲህ በማለት ጮኸ:- ***"በምስጢር ዝሙት ለፈፀሙ አገልጋዮች ይቅርታ ለማድረግ በጣም አስቸጋሪ ይሆናል። እነርሱ ከልብ ንስሐ ካልገቡ (ከልብ ኃጢአታቸውን ካልተናዘዙ) ፍጻሜአቸው በሲኦል ውስጥ ይሆናል!'***

*እኔም በርኅራኄ እንዲህ ለመንሁ:- "**ጌታ** ሆይ፣ እነርሱ የሰው ልጆች ናቸው፤ እነርሱ ሥጋ ናቸው። እነርሱ አሁንም ይወድቁና ስህተቶችን ያደርጋሉ፣ ትክክል? አንድ ሰው ከሞተ፣ እርሱ / እርሷ ንስሐ ለመግባት አጋጣሚ አይኖራቸውም። በህይወት እያሉ ግን እርሱ / እርሷ ከተናዘዙ (ንስሐ ከገቡ) አይማሩም እንዴ? አንድ ሰው ንስሐ ከገባ (ከተጸጸተ፣ ኃጢአቱን ከተናዘዘ) አንተ ይቅርታ እንደምታደርግ የሚናገሩ (የሚጠቅሱ) ብዙ ጥቅሶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ።"* **ጌታም** እንዲህ መለሰ:- ***"አገልጋዮች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን ቃላት በጣም በደንብ ያውቃሉ እና እነርሱ ዝሙት ከፈፀሙ በኃይለኛ (በከባድ) ይፈረድባቸዋል። ምህረትን ለማግኘት ለእነርሱ አስቸጋሪ (ከባድ) ይሆንባቸዋል።"***

እኔ ለምህረት ያለማቋረጥ ወደ **ጌታ** ለመንሁ እና ለማፈግፈግ እንቢ አልሁ። አብርሃም እንዳደረገው ለመንሁ። "**ጌታ ሆይ**፣ ትክክል ብትሆንም፣ ለቀደመው ኃጢአታቸው ያለ ይቅርታ ወደ ሲኦል ከሰደድኻቸው አግባብ አይመስልም (ሚዛናዊ ያልሆነ ይመስላል)። ከዛ ቡድን መሐል ብዙ ነፍሳትን ወደ አንተ የመሩ ምናልባት አንዳንዶች ይኖራሉ። ቤተ ክርስቲያናቸውን በአግባቡ እየመሩ ያሉ አንዳንድ አገልጋዮች ምናልባት ይኖራሉ። እንደነዚህ ካሉ አንዳንዶቹ በአምንዝራዎች ቡድን ውስጥ አይደሉምን?" **ጌታ** በአስፈሪነት (በጣም በኃይል) እንዲህ በማለት ገሰጸኝ፦ ***"እንደ ፓስተር፣ የመጽሐፍ ቅዱስህን ቃል አታውቅምን?"*** **ኢየሱስ** (ወደ ፊልጶስዩስ ሰዎች 2:12)ን እንዳስታውስ ረዳኝ፣ ***"መዳንህን በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ ለመፈጸም (መፈጸም) ቀጥል።"***

**ጌታ** ቢገስጸኝም ከእርሱ ጋር መከራከርና መከራከር ቀጠልሁ። *"የኔ ተወዳጅ* ***ጌታ*** *ሆይ፣ እነዛ አገልጋዮች ሕይወታቸውን በሙሉ ለአንተ መሥዋዕት አድርገዋል። በምድር ላይ አንተን ለማገልገል ጊዜአቸውን አሳልፈዋል። ንስሐ እንዲገቡ አጋጣሚዎችን ልትሰጣቸው እንደሚገባ አታስብም። ፓስተሮች ወደ ሲኦል ሄዱ ብዬ ብል (ብወስድ) ማን ያምነኛል?"*

የጸጥታ (የዝምታ) ጊዜ ነበረ። **ጌታ** ከዛ በፀጥታና በክብር እንዲህ ተናገረ፡ ***"እግዚአብሔር አብ ከእኔ ጋር ተስማምቷል። ዝሙት የፈጸሙ አገልጋዮች በፍርሃት ከልብ ንስሐ ከገቡ ይማራሉ (ምሕረትን ያገኛሉ)። ነገር ግን፣ እነርሱ ወደ ክፉ መንገዶቻቸው ከተመለሱ እና ከተጸጸቱ በኋላ ያንኑ ኃጢአት ከፈጸሙ እግዚአብሔርን ኢያፌዘበት (ኢያላገጡበት) ነው! ትንሽም ሆነ ወይም በጣም ግዙፍም ሆነ ወይም ታላቅ (ጽኑ) ወይም ደካማ አገልግሎቶችን መምራታቸው ለውጥ ኢያመጣም፤ እግዚአብሔር አብልጦ የሚጠላውን ኃጢአት እነርሱ ይፈጽማሉ። አንተ ያንን ማስታወስና ትኩረት መስጠት ይኖርብሃል።"***

በአንድ ራእይ ውስጥ፣ በቤተ ክርስትያኑ ውስጥ ከአንድ ወጣት እህት ጋራ በፍቅር የወደቀ አንድ ልዩ ፓስተርን **ጌታ** አሳየኝ። እነርሱ የግብረ ሥጋ ግንኙነቶችን ለማድረግ በተደጋጋሚ ብዙ ጊዜ ይገናኛሉ። ውሎ አድሮ ጉዳያቸው ለፓስተሩ ሚስት ተጋለጠ። እርሷ እጅግ በመደንገጧ የጭንቀት መጠኗ እጅግ በጣም ከፍ ብሎ ነበረ እና አስጊም (አደገኛ) እንኳ ነበር። ሚስትየው ንስሐ እንዲገባ ልታግባባው ሞከረች፣ እርሱ ግን አላዳመጠም። ሚስትየዋ ከእንግዲህ በኋላ ሥቃዩንና ድንጋጤውን ልትቋቋመው አልቻለችም፣ ስለዚህ በጣም እየተጨናነቀች (እየተከፋች) መምታት ጀመረች። የማያምኑት የሚመርጡትን ምርጫ ራስን ማጥፋት ፈጸመች። አሁን፣ እርሷ በሲኦል ውስጥ እና በታላቅ ሥቃይ ውስጥ ናት።

**ጌታ** እንዲህ አለ፦ ***"ምን ጊዜም ያችን ልጅ ሳያት ልቤ ይቀደዳል (ይከፈላል፣ ይሰነጠቃል)። እንዴት ነው ያን ፓስተር ወደ ሲኦል የማልልከው? ያ ፓስተር አሁንም በአገልግሎት ውስጥ ነው። ንስሐው ከልብ የመነጨ (እውነተኛ) አልነበረም። ዛሬም እንኳ እርሱ የከንቱ ስሜትና ራስን የማሳሳት (የማጭበርበር) ህይወት እየኖረ ነው። የአስተሳሰብ መንገዱ የተዛባ (የተበከለ፣ የተበላሸ) ነው። ማንም በፍጹም (ምን ጊዜም) እኔን ሊያታልለኝ አይችልም። ማንም በፍፁም (ምን ጊዜም) እውነቱን በውሸት ሊሸፍን አይችልም።"***

**ስሞችን ከሕይወት መጽሐፍ መደምሰስ*

አንድ ጊዜ በቤተ ክርስትያናችን ውስጥ አንዲት ዲያቆኒት ነበረች። እርሷ በታማኝነት እየኖረች እያለ ከ**መንፈስ ቅዱስ** ብዙ ስጦታዎችን ተቀብላለች። ነገር ግን፣ ስጦታዎቹ ሁሉም ተመልሰው ተወሰዱ። ከትንሽ ቆይታ በኋላ አዘውትራ መጠጣትና ማጨስ ጀመረች። ከዚህም በላይ፣ ከአንድ ሰው ጋር በየቀኑ በስልክ ታወራና በምስጢር ታገኘው ነበር። ያን ሰው ከመቅጠር እንድታቆም ያለማቋረጥ እርሷን ለማግባባት ሞከርሁ። እርሷ ላይ ጮኼባትማለሁ ነገር ግን እርሷ ሰውየውን ዘወትር ማግኘት ቀጠለች። **እግዚአብሔር** ሰዎችን ይታገሳል። ነገር ግን፣ ሰዎች ንስሐ ካልገቡ ወደ እርሱ ቁጣ ይገደዳሉ (ተላልፈው የመጣሉ)። ስሟን ከሕይወት መጽሐፍ እርሱ እንደደመሰሰው (እንደፋቀው) **እግዚአብሔር** በራእይ አሳየኝ። እኛ ይህን ስናውቅ ሁላችንም በፍርሃት ተንቀጠቀጥን (ደነገጥን)።

**እግዚአብሔር** አንድ እድል ሲሰጠን፣ ምንም ይሁን ምን እኛ እድሉን መውሰድ አለብን። **ኢየሱስ** እንዲህ አለ፦ ***"ያቺ የተለየች ቅድስት እግዚአብሔርን አፌዛበታለች (አላግጣበታለች) እና መንፈስ ቅዱስን አስቸግራለች። ስለዚህ፣ እርሷ ካልተጸጸተችና ከልብ ንስሐ ካልገባች መንግሥተ ሰማይ አትገባም።"***

*የቤተ ክርስትያን አባላት ፍርድ ከባድ ከሆነ፣ ዝሙት የፈጸሙ ፓስተሮችን ምን ያህል በጣም አብልጬ እፈርድ ይሆን? አገልጋዮች እስከ ሞት ጫፍ ድረስ ንስሐ መግባት አለባቸው። የዛሬ አገልጋዮች እግዚአብሔርን እያፌዙበት (እያላገጡበት) ነው። እነርሱ፡- 'እነዚህ የጸጋ ቀናት ናቸው እና ወንጌል ነፃ አውጥቶናል። ንስሐ ግቡ ብቻ እና አንድ ሰው ያለገደብ ይማራል።' ይላሉ። እነዚህ ቀናት አንድ ሰው ከብሉይ ኪዳን ቀናት ይልቅ በፍርሃት ሊሆንባቸው የሚያስፈልገው ናቸው።"* ለሠራናቸው ሥራዎች ሁላችንም መልስ የምንሠጥበት ቀን እየመጣ እንደሆነ **ጌታ** አስጠነቀቀን።

ይህን ምዕራፍ ስጽፍ፣ ብዙ ሰዓታት መጨነቅና አለመስማማት አጋጥሞኝ ነበር። **ኢየሱስ** እንዲህ አለ፡- *"ታዲያ እኛ በዚህ እምነት ሕጉን እንሻረው። በፍጹም አይሆንም! ይልቅ ሕጉን እንጠብቀዋለን (እንደግፋለን)።"* (ወደ ሮሜ ሰዎች 3:31) ። በእርግጥ፣ የእለት ተእለት ኑሮአችንን በ**ጌታ** አስደናቂ ጸጋ ውስጥ ነው እየኖርን ያለነው። ነገር ግን፣ በእርሱ ጸጋ ውስጥ መኖር ማለት ኃጢአቶቻችን ጠፉ በቃ ማለት አይደለም። እኛ ንስሐ ካልገባን የ**እግዚአብሔር**ን ጸጋ እያወከን (እየሰደብን) ነው። የእለት ተእለት የንስሐ ሕይወት ወደ **እግዚአብሔር** ምህረትና ርኅራኄ በጣም ፈጣኑና አጭሩ መሄጃ ነው።

**ፓስተሮችን የሚቃወሙ ሰዎች (መንፈሳዊ ሥልጣን) / *የፓስተሮችን (መንፈሳዊ ሥልጣን) የሚቃወሙ ሰዎች*

እኔ ራሴ ፓስተር ስለሆንሁ ይህን መጽሐፍ ከፓስተር እይታ አንጻር የምጽፈው መስሎ ይታይ ይሆናል። ነገር ግን እኔ የሌሎች ፓስተሮችን ድርጊቶች ለመከላከል ምንም መሻቶች በልቤ ውስጥ የለኝም። እየመዘገብሁ እና እየጻፍሁ ያለሁት ስለታዘዝሁኝ ነው። በአንዳች አድልኦ መጻፍ አልፈልግም።

**ጌታ** እንዲህ ብሎ ነበረ፡- *"እኔ አገልጋዮቼን ስነስርአት አስይዛለሁ (እቀጣለሁ)።"* ከዚህም በላይ፣ ፓስተራቸውን ለመቅጣት (ስነ ስርአት ለማስያዝ) የቤተ ክርስቲያኑን አባላት እንደማይጠቀም **ጌታ** ተናግሯል። **ኢየሱስ** በምስጢር ኃጢአቶችን የሚያደርጉትን በጣም ይፈርድባቸዋል እና ስነ ስርአት ያስይዛቸዋል (ይቀጣቸዋል)።

**ጌታ** (1ኛ ሳሙኤል 4:11-22)ን ሰጠ። አንድን ፓስተር ለመቃወም ወይም ለማስወጣት (ለማባረር) በቡድን ሆነው የሚያሴሩ የቤተ ክርስቲያን አባላትን እንደማይቀበል ወይም እንደማይታገስ **ጌታ** ደግሞ ተናገረ። እርሱ በቆሬን በዳታንና በአቤሮን እንዳደረገው ሰዎቹን በጣም ይቀጣል (ኦሪት ዘኍልቁ 16:26-35)።

*እኔም በድጋሜ **ጌታ**ን ለመንሁ፣ "**ኢየሱስ** ሆይ፣ አንዳንድ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን አባላት ከአላዋቂነት የተነሳ ቡድን ይመሠርታሉ እና የመነሻ እቅዳቸው ቤተ ክርስቲያኑን ለማሻሻል ይሆን ይሆናል። ጉዳዩ ያ ከሆነ እነርሱ ለምን ይፈረድባቸዋል?"* **ኢየሱስ** እንዲህ መለሰ፡- *"ያ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲመጣ፣ አንድ ሰው ይህን በሰው (በሰውኛ) መንገድ ሊፈታ አይችልም። ያ በፍጹም ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም።"*

**ጌታ** በተጨማሪ አንድ ቅዱስ / ቅድስት በቀድሞ ወይም በአሁኑ ጊዜ አንድን ፓስተር በመቃወም መንፈሳዊ ሥልጣንን በግዴለሽነት ካቀለለ / ካቃለለች፣ እርሱ/እርሷ በፍርሀት ንስሐ መግባት አለበት / አለባት። ያለበለዚያ እርሱ/እርሷ ወደ ሲኦል የመሄድ አደጋ (ፍርድ) ላይ ይሆናል / ትሆናለች። ከዛ በኋላ እርሱ/እርሷ በታማኝነት፣ በእውነት፣ እና በጥንቃቄ መኖር አለበት / አለባት አለ።

የቤተ ክርስቲያን አባላት መንፈሳዊ ሥልጣንን በግዴለሽነት እንዲያቃልሉ የሚፈቅዱ ፓስተሮች ደግሞ ከቤተ ክርስቲያኑ አባላት በላይ በጣም ንስሐ መግባት አለባቸው። አባላቱና ፓስተሮች የግድ ሁሉም በፍርሀት ንስሐ መግባት እንዳለባቸው **ጌታ** አጽንኦት ሰጠ። እነርሱ ወደ **ኢየሱስ** ጸልየው ብቻ ከሆነ፣ እርሱ ሁሉንም ችግሮቻቸውን ለመፍታት ጣልቃ ይገባ ነበረ።

(የዮሐንስ ራእይ 2:1) *ጌታ በዓለም ሁሉ ያሉ ቤተ ክርስቲያኖችን ጎበኘ*

**ጌታ**ን መጠየቄን ቀጠልሁ:- *"**ጌታ** ሆይ፣ በዓለም ሁሉ ባሉ አብያተ ክርስትያናት በሙሉ አንተ በአንድ ጊዜ መገኘት እንደምትችል አንድ ሰው ተናግሮ ነበር። ይህ እውነት ነው?"* **ጌታ**ም መለሰ፡ ***"እኔ መንፈስ ስለሆንሁ በዚህ ዓለም ፊዚክስ አልታጎልም (የምታጎል አይደለሁም)። እኔ በሁሉም ቦታዎች ላይ፣ በማንኛውም ጊዜ ላይ፣ በማንኛውም ቤተ ክርስቲያን ወይም በአምልኮ ዝግጅት ውስጥ ባሉ በማንኛውም ቤተ ክርስትያኖች መገኘት እችላለሁ። እኔ በአንድ ጊዜ በአንድ ልዩ ቤተ ክርስትያን ላይ ብቻ አይደለሁም። እኔ በዓለም ሁሉ ያሉ ቤተ ክርስትያኖችን እየተመለከትሁ (እየተቆጣጠርሁ) ነው። መንፈስ (ቅዱስ) አንድ እና ያው ነው። መንፈስ በፍጹም አይደከምም ወይም እየዛለ አይሄድም። በማንኛውም ቤተ ክርስቲያን አንድ ሰው ሲጸልይ፣ እኔ ወዲያውኑ ጸሎታቸውን እሰማለሁ። እኔ በአንድ ጊዜ ሁሉንም መስማትና ከእያንዳንዱ ልጆቹ አጠገብ መሆን እችላለሁ። አንድ ሰው በከፍተኛ ፍላጎት (በቀናኢነት) ከጸለየ፣ ያ ሰው መንፈሳዊ ዓይኖቹ ይከፈቱለታል (ያ ሰው መንፈሳዊ ዓይኖቹ ተከፍተውለት ማግኘት ይችላል) እና በአንዳንድ ጊዜያት ላይ እኔ ያን ሰው መንግሥተ ሰማይን እና ሲኦልን ላሳየው እችላለሁ። ፓስተር ኪም፣ አንተና ሚስትህ ለመንፈሳዊ ዓይኖች ያለማቋረጥ ጠይቁ። አንተ እና ሚስትህ ደግሞ ራሳችሁን ለእኔ አስደሳች አድርጋችኋል። በብዙ ጊዜያት ላይ በእንባዎች ስለጮኻችሁና መንፈሳዊ ዓይኖችን በጉጉት ስለሻታችሁ እናንተ መንግሥተ ሰማይን እና ሲኦልን እንድታዩ ልዩ መብት ልሰጣችሁ እኔ እያሰብሁ ነው። ልብ በሚነካ ሁኔታ ጸልዩ። በመነሻ፣ አንተና ሚስትህ በመንፈሳዊ እንድትነቃቁ (እንድትቀሰቀሱ) እግዚአብሔር አብ አልፈቀደላችሁም ነበር። ነገር ግን አንተና ሚስትህ እጅግ በጣም ስለሻታችሁት እና የአምልኮ አገልግሎቶች በየቀኑ ከምሽቱ መጀመሪያ እስከ ቀጣዩ ቀን ጠዋት ድረስ ስላላችሁ እግዚአብሔር አብ በጣም ተገርሞ (ተደንቆ) ነበረ። እናንተ እጅግ በጉብዝና በተጨማሪም እንኳ ጮኻችኋል። እግዚአብሔር አብ እንዲህ ብሏል:- 'እንደ እነርሱ አንዳች ሌላ ቅዱሳን በፍጹም አይቼ አላውቅም።' እርሱ መንፈሳዊ ዓይኖቻችሁን እንደሚከፍት ተናግሯል።"***

ሁለት አይነት መንፈሳዊ መቀስቀሶች (መነቃቃት) አሉ። የመጀመሪያው ከመንፈሳዊ ዓይኖች መከፈት ጋር ነው እና ሌላኛው መንፈሳዊ ዓይኖች ሳይከፈቱ ነው። አብዛኞቹ ቤተ ክርስቲያኖች መንፈሳዊውን ግዛት ማየት ሳይችሉ በመንፈሳዊ ተነቃቅተው ነበረ። ሁሉም ቤተ ክርስቲያኖች ማለት ይቻላል ይህን አይነት መንፈሳዊ መነቃቃት አላቸው። ይህን ዓይነት መንፈሳዊ መነቃቃት (መቀስቀስ) **መንፈስ ቅዱስ** ለአንድ ቅዱስ (ቅድስት) እንዳስፈለገው (እንዳስፈለጋት) የሚሰጠው አሳብ (ስሜት)፣ የፀና እምነት፣ እና ቃላት ነው።

የአንድ ሰው መንፈሳዊ ዓይኖች ሲከፈቱ **ከኢየሱስ** ጋር ጭውውት (ንግግር) ማድረግ ይችላሉ። በኮሪያ፣ ከ**ጌታ** ቤተ ክርስትያን ሌላ፣ ይህ ተሰጥኦ ያላቸው ትንሽ ብዛት ያላቸው ቅዱሳን አሉ። እነዚህ ቅዱሳን **ኢየሱስ ክርስቶስ**ን ሲፈልጉትና ሲጠሩት ከ**ኢየሱስ ክርስቶስ** ጋር መወያየት ችለዋል። በ**ጌታ** ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ መንፈሳዊ ዓይናቸው የተከፈተላቸው ሰዎች ከ**ጌታ** ጋር ብዙ ጊዜያት ለመወያየት አጋጣሚ እንዳላቸው **ኢየሱስ** ተናገረ።

**ኪም ጁ ኢዩን**: (መጀመሪያይቱ የሐዋርያው ዮሐንስ መልእክት 5:1-5) *የተለያዩ ኢጋንንትን መዋጋት*

በአምልኮ አገልግሎታችን ላይ ልብ በሚነካ ሁኔታ **እግዚአብሔር**ን ሳመሰግን አንድ ጋኔን እንደ አንዲት ወጣት ሴት ልጅ መስሎ ከፊት ለፊቴ መጣ። አካላዊ ዓይኖቼ ተከፍተው፣ ጸጉሯን ለመያዝ በፍጥነት ወደ ፊት ሄድሁና ያለምህረት ዙሪያውን አወዛወዝኳት። እሷ መጮኺን ቀጠለች እኔም ወደ ቤቱ ጥግ ወረወርኳት። ከዛ አንድ ጋኔን በጥላ መልክ ቀረበኝ። በመጀመሪያ አላስተዋልሁትም ነበር፣ ነገር ግን በ**ጌታ** እርዳታ ልይዘው፣ ላሽከረክረው፣ እና በእግሮቼ እላዩ ላይ ልቆምበት ቻልሁ።

ቀጣዩ ጋኔን በእይታዬ ውስጥ ሲመጣ ሮጥሁና እግሩን ያዝሁ፣ አንገቱን ጠመዘዝሁ፣ ቀጠቀጥኩት፣ እና በእግሮቼ ረጋገጥኩት። ጋኔኑ በመሬቱ ሁሉ ደማ። ከማረፌ በፊት (ማረፍ ከመቻሌ በፊት) ሌላ ጋኔን ስለመጣ ሆዱን በቡጢ መታሁት። ጋኔኑም አለቀሰና እንዲህ እያለ መሬት ላይ ተቀመጠ:- *"አውች! ሆዴ!"* እኔ የጸጉሩን ቁራጭ በብዛት ያዝሁና ለእህት ዩ ከዩንግ አቀበልሁ። እኔም እንዲህ አልሁ:- *"እህቴ ሆይ፣ እዚህ ጋር አጥብቀሽ ያዢ!"* እህቴም እንዲህ መለሰች:- *"እሺ፣ ላየው ችዬአለሁ!"* እርሷም አወዛውዛው በሩቁ ጣለችው።

ዛሬ በሙሉ ጉልበት እየተጠቃን የነበረ ነው የሚመስለው። አብዛኛውን ጊዜ (የተለመደው)፣ በማህበር አንድ ላይ ለመጸለይ ስንጀምር ኢጋንንቶች ይታያሉ፣ ዛሬ ግን ስልታቸውን እንደቀየሩ ታየ እና በአገልግሎታችን መጀመሪያ ላይ ሊያደናቅፉን (ሊያስታጉሉን) ሞከሩ። በሆነ ምክንያት፣ በወጣት ሴቶች ልጆች መልክ ብዙ ኢጋንንቶች ዛሬ እያጋጠሙን ነው። ከእነሱ አንዱ በድጋሜ ሲቀርበኝ ያዝኩትና ሁለቱንም ጉንጮቹን በጥፊ መታሁ እና ፊቱን ቧጨርሁት። እሷም ጮኸች፦ *“አውች! ያማል!”* እሷም መልሳ ቧጨረችኝ፣ ደነቀኝም። የጥፍሮቿ ምልክቶች በጀርባዬ ላይ የት ቦታ እንደነበሩ በግልፅ ማየት ችዬ ነበር። ይህን ለፓስተር እና ለቤተ ክርስቲያን አባላት በአካላዊ ዓይናቸው እንዲያረጋግጡት አሳይቻቸዋለሁም።

**ሲ ዩ ክዩንግ:** በአምልኮ አገልግሎት ጊዜ **ጌታ**ን ሳመሰግን፣ ፊቱ ላይ ሁለት ቀለሞች ያሉት አንድ ጋኔን ቀረበኝ። የፊቱ አንድ ጎን ነጭ ነበረ እና ሌላኛው ጎን ጥቁር ነበረ። ሰማያዊ ፊት ያለው ሌላ ጋኔን ተቀላቀለው። እኔ ባንዳፍታ ሁለቱን ጋኔኖች ያዝኳቸውና ያለምህረት አወዛውዛቸው ጀመር። ባለ ሁለት ቀለም ፊት ያለውን ጋኔን አርቄ ወረወርሁት። ሰማያዊ ፊት ያለው ጋኔን መወዛወዙን አልቻለምና በቁጣ የእጄን ጀርባ ቧጨረው። የእጄን ጀርባ ከቧጨረ በኋላ ቆነጠጠኝና ነከሰኝ። እኔም በሥቃይ ጮህኩኝ። በጣም ቁጡ መሆን ጀመርሁና የቻልሁትን ያህል አርቄ ወረወርሁት። ጋኔኑ የት ላይ እንደቧጨረኝና እንደነከሰኝ ስመለከት ቆዳዬ ተገሸልጦ ነጭ የተቧጨሩ ምልክቶች አስተዋልሁ። ከንክሻው ምልክት የተነሳ ጣቴ ማበጥ ጀመረ። የቤተ ክርስትያኑ አባላት አካላዊ ምልክቱን አይተዋል እና በጣም ደንግጠው ነበር። ከጋኔኑ የደረሱብኝ ምልክቶችና ቁስሎች በጣም የሚያሠቃዩ ነበሩ። እኔም ስቃዩን ለመቋቋም ስሞክር ማልቀስ ጀመርሁ።

**ሲ ሀክ ሱንግ:** **የሴፍ በእባብ ተነደፈ*

ዩ ክዩንግ፣ ጁ ኢዩን እና እኔ መንፈሳዊ ዓይኖቻችን ተከፍተዋል እና የኢጋንንትን እና/ወይም የክፉ መናፍስትን እንቅስቃሴዎች ለማየት ችለናል። ነገር ግን ዮሴፍ እንደኛ ይህ ተሰጥኦ ስለሌለው በጥቂቱ እንደደከመው ይታያል። ከ**መንፈስ ቅዱስ** ሥራ የተነሳ በጸለየ ቁጥር አካሉ እንደ እሳት ሙቀት እንደሚሰማው ዮሴፍ ተናገረ። በአገልግሎት ጊዜ እርሱ ሁል ጊዜ ከአጠገቤ ነው የሚቀመጠው። በውጤቱም፣ በጸለይሁ ቁጥር ስለ እርሱ ልዩ ልመናዎችን አደርጋለሁ።

ከዮሴፍ ጋር **ጌታ**ን ሳመልክና ሳመሰግን፣ አንድ ጋኔን በእባብ መልክ በጸጥታ እየተሳበ ወደ እኛ ቀረበ። ጋኔኑም ዮሴፍ ጋር ቀረበና የዮሴፍ እግሮች ላይ ራሱን ጠመጠመ። እኔም እንዲህ ጮህኩኝ፦ *“ዮሴፍ ሆይ፣ አንድ እባብ በአካልህ ዙሪያ እየተጠቀለለ ነው!”* እርሱም እንዲህ በማለት መለሰ፦ *“ምን? እኔ አንዳች አላይም።”* እኔም እባቡን አንገቱን ያዝሁና ለዮሴፍ አቀበልሁት። እኔም በታላቅ መደነቅ (ጉጉት) እንዲህ በማለት ጮህኩኝ፦ *“በጥብቅ ያዘውና ወደ መሬት አወዛውዘው!”* እርሱ እኔ የማየውን ማየት ስላልቻለ ዮሴፍ ግራ የተጋባ ሆኖ ታየ። እርሱ የእባቡ እውነታ ሊገባው አልቻለም። እርሱም እንዲህ አለ፦ *“ወንድም ሀክ ሱንግ፣ አንዳች ማየት አልቻልሁም!”* እኔም ያልሁትን ደግሜ፦ *“ዮሴፍ፣ ወደ መሬት አወዛውዘው!”* እርሱም እባቡን ያዘና ያወዛውዘው ጀመር።

ይህን ሁኔታ እያየ የነበረ ማንኛውም ሰው ዮሴፍ አንድ ነገር የያዘ በማስመሰል ክንዱን አየር ላይ እያወዛወዘ ብቻ እንደሆነ ይገምት ይሆናል። ነገር ግን፣ አንድ ሰው መንፈሳዊ ዓይኖች ካሉት፣ ዮሴፍ አንድን እባብ አንገቱ ላይ ይዞት እያወዛወዘው እንደሆነ ያያል። አንድ ሰው ይህንን ድርጊት ከመንፈሳዊ ዓይኖች ውጭ በአካላዊው ግዛት ሊያብራራ የሚችልበት አንዳች መንገድ የለም።

ዮሴፍ እባቡን ማየት ስላልቻለ እጆቹን ላላ አድርጎ በአየር ላይ አወዛወዘ። በውጤቱም እባቡ በጉልበት ተጽዕኖ መፍጠር ቻለና በዮሴፍ ክንድ ላይ መጠምጠም ጀመረ። እባቡም እጁን ነደፈው። እውን እንደነበረ ዮሴፍ አሁን ተረዳ። በእጁ ጀርባ ላይ ከእባቡ የሆነ አንድ ግልፅ የንክሻ ምልክት ታየ።

ከእባቡ ጥርሶች የሆኑ የሁለት ትንንሽ ጥርሶች ምልክቶች ነበሩ እና ክንዱ መድማት ጀመረ። ፓስተሩ እየሆነ ያለውን ነገር ተገንዝቦ ከእባቡ ጋር ወደ ላይ ወደ መሠዊያው እንድንመጣ ጠየቀን።

እጁን አንስቶ ፓስተሩ ጮኸ። *"**በኢየሱስ ስም!**"* በእነዚያ ቃላት፣ እባቡ ለግማሽ (ለሁለት) ተከፈለ (ተሰነጠቀ) እና ራሱ ፈነዳ። ሁኔታውን ሳይ መንገጭላዬ ወረደ።

ዛሬ ክፉ መናፍስትን ስንዋጋ ብዙ ሰዓታት አሳልፈናል። እኛ በመከላከል ወይም በማጥቃት ለጦርነት ተሰማርተናል። እኛ አጋንንትን ለማሸነፍ እነሱን በማሳደድና በማባረር ታላቅ (ኃይል) የኃይል ጉዳይ አውጥተናል። ነገር ግን፣ እኛ እነሱን መያዝ ስንችልና ወደ ፓስተሩ ስናመጣቸው ክፉ መናፍስቱ በእርሱ ይደከማሉ። ፓስተሩ የቅዱስ ነበልባላዊ እሳት ስጦታ አለው እና በእርሱ ትዕዛዛት ቅዱሱ እሳት ክፉ መናፍስትን ለማቃጠል ከአካሉ ይወጣል እና እነሱ አቧራ ይሆኑና ይጠፋሉ።

**አጋንንትን ማደን*

ሁሉንም አጋንንት ስናይ እንይዛቸውና ፓስተሩ ወደቆመበት ወደ መሠዊያው እናመጣቸዋለን። እርሱ በቅዱስ ነበልባላዊ እሳት ያጠፋቸዋል። በጣም አድካሚ ነበረ እና እኛ በሙሉ ጉልበት (ሀይል) እንደተጠቃን ይመስላል። ልንቆጥራቸው እንኳ ያልቻልናቸው በጣም ብዙ ክፉ መናፍስት እዛ ነበሩ። ምንም ያህል ብዙ አጋንንት ብናባርርም (ብናስወጣም) ወይም ብናሸንፍም ብዙ የክፉ አጋንንት ቡድኖች መጥተው ታዩ። እኛ ስንዋጋ **ኢየሱስ** ከመሠዊያው በአድናቆት ተመለከተን። **ኢየሱስ** ከመስቀሉ ፊት ቆመ ነበር። በአገልግሎት መሐል ጊዜ፣ አጋንንትን አሳደድንና ተዋጋን። እኛ አዘባርቀን ነበር እና አገልግሎትን መጨረስ አልቻልንም ነበር። አጋንንትን አድኖ ለመያዝ ሁላችንም በአንድ ላይ ትብብር አደረግን።

በጦርነቱ ጊዜ፣ ዮሴፍ በሦስት የተለያዩ ቦታዎች ቆሠለ፣ ሁለቱ ከእባብ ንድፊያዎች እና ሌላኛው ከቧጠጠችው ወጣት ሴት ጋኔን ነው። ሁሉም ቁሥሎቹ እየደሙ ነበር። ቧጨሮዎቹንና የንድፊያ ምልክቶችን በግልፅ ማየት ችዬ ነበረ፤ የቧጨሮዎቹና የንድፊያ ምልክቶቹ በሁለቱም እጆቹ ጀርባ ላይ ነበሩ። ዮሴፍ በጣም የተጎዳ ስሜት እንዳይሰማው የዮሴፍን ቁሥሎች አነስተኛ ግምት ለመስጠት ሞከርን። እኛ ሁላችንም የማበረታቻ ቃላት ተናገርን እና እነዛ የክብር የጦርነት ጠባሳዎች እንደሆኑ ነገርነው።

**ካንግ ህዩን ጃ:**

በአገልግሎት መሐል ጊዜ ሀክ ሱንግ፣ ዩ ክዩንግ፣ ጁ ኢዩን፣ እና ዮሴፍ እንዲህ በማለት ጮኹ:- *"ፓስተር! ወይዘሮ ካንግ ህዩን ጃ! በቡድኖች ሆነው የሚያጠቁ ብዙ አጋንንት አሉ። ምን እናድርግ?"* ፓስተሩም:- *"አትጨነቁ። **ሥላሴ አምላክ** ከእኛ ጋር አለን። ሁላችሁም በውጊያ ልታሸንፏቸው ትችላላችሁ።"* ብሎ ነገራቸው። ልጆቹም በመደነቅ ጮኹ:- *"ዋው! ታላቅ! ቆሻሻ አጋንንት! ዛሬ ሁላችሁም ሞታችኋል!"* ሁሉም አጋንንትን እየተዋጉ በቤቱ ሁሉ ሮጡ።

በአካላዊ ዓይናችን ሕጻናቱ እጆቻቸውና ክንዶቻቸው በአየር ላይ እየተወዛወዙ እዚህም እዚያም ሲሮጡ ብቻ ነው ለማየት የቻልነው። በመንፈሳዊ ዓይኖች ግን፣ የእውነት እየተካሄደ ያለውን ለማየት ችለናል። በድካም ጊዜ እንዲህ ብዬ አሰብሁ:- *"እየተካሄደ የነበረውን ከሌላ ቤተ ክርስቲያን የሆኑ ሰዎች ቢያዩስ? እንግዶቻችን ወይም አዲስ አባላቶቻችን ቢሆኑስ?"* ነገር ግን፣ ይህ አሁን ሊያሳስበኝ ለእኔ ጠቃሚ አይደለም። ልጆቹ አጋንንትን እያባረሩ እዚህም እዚያም እየሮጡ እያለ፣ ልብ በሚነካ ሁኔታ በልሳኖች ጸለይሁና በመንፈስ አሸበሸብሁ። የቀኝ እጄ በጥንካሬ ሲሞላ ተሰማኝ እና አንድ ነገር እንደያዝሁ ተረዳሁ። እጄም እንደ ዊንድሚል (የነፋስ ወፍጮ) በክብ መልክ መንቀሳቀስ ጀመረ። የክብ እንቅስቃሴዬ በፍጥነትና በኃይል መጨመር ጀመረ። *"ምን እየሆነ ነው ያለው?"* ብዬ አሰብሁ።

እየሆነ ስለነበረው ነገር ለማሰብ ጊዜ አልነበረኝም። እጄና ክንዴ በበለጠ ኃይል እየፈጠነ እየፈጠነ በክብ ተንቀሳቀሰ። አላቆመም። እዛ ቁጭ ብዬ ብቻ ይህ እንዲሆን ማድረግ አልቻልሁም። በእግሮቼ ቆምሁና ዙሪያውን መሮጥ ጀመርሁ። ነገር ግን እጄ አሁንም የክብ እንቅስቃሴዎችን እያደረገ ነበረ። ወደ እህት ቤይክ ቦንግ ንዮ በጨረፍታ አየሁ እና እርሷም ደግሞ ይህንኑ ነገር እያደረገች ነበረ። ባልተጠበቀ ሁኔታ እጄ የአንድን ወንበር ጠርዝ መታ። ከአካላዊ አመለካከት (አስተያየት) እየተደረገ የነበረውን ልረዳ አልቻልሁም።

መንፈሳዊ ዓይናቸው የተከፈተላቸውን ልጆች ጠየቅሁ፦ *"ጆ ኢዩን፣ የእናትሽን ክንድ ተመልከቺ። ለምንድር ነው እጇና ክንዴ የክብ እንቅስቃሴዎችን የሚያደርጉት? ለምንድን ነው የማይቆመው?"* በድንጋጤ አስተያየት እርሷ እንዲህ መለሰች፦ *"እናቴ፣ በእጅሽ አንድ ጋኔን ይዞሻል! ጋኔኑን መዘረር እንድትችዪ ጋኔኑን ማወዛወዝሽን ቀጥዪ።"* ሁኔታውን በአዕምሮዬ መቆጣጠር ባልችልም የበለጠ በኃይል ለማወዛወዝ ሞከርሁ። ፓስተሩ እንዲህ አለ፦ *"ወይዘሮ ካንግ ህዩን ጃ፣ ማወዛወዝሽን እንደቀጠልሽ (እየቀጠልሽ) ወደ መሠዊያው ነዪ።"* እኔም ወደ መሠዊያው ተራመድሁ እና ፓስተሩ እንዲህ ጮኸ፦ *"ቅዱስ እሳት!"* እጄም በተፈጥሮ (በተፈጥሯዊ መልክ) ቆመ እና ጋኔኑም ወደቀ። ጋኔኑ በቅዱስ እሳት ተቃጥሎ ነበር፤ ጋኔኑም አቧራ መሆን ጀመረ።

ያ በእውነት አስገራሚና አስደናቂ አድራጎት (አጋጣሚ) ነበረ። ስመለከት ሁሉም አጋንንት ሙሉ በሙሉ ተሸንፈዋል። መንፈሳዊ ተሰጥኦዋችን ምን ያህል ኃይለኛና ታላቅ እንደሆነ በድጋሜ አንድ ጊዜ ተገነዘብሁ።

**ኪም ጁ ኢዩን:** **አጋንንት የፓስተሩን አካል ሲነኩ ወደ አመድነት ይፈረካከሳሉ*

ከምሽት አገልግሎት በኋላ በልሳኖች ስጸልይ አንድ ጋኔን ቀረበኝ። በ**ኢየሱስ** ስም ሥልጣን አሸነፍሁት። ነገር ግን በጣም ብዙ የአጋንንት ቡድኖች ታዩ። ሁሉም ነጭ ልብሶች በለበሱ ወጣት ሴቶች ልጆች ተመስለዋል። እዛ የማይቆጠሩ በጣም ብዙ በመኖራቸው ተደንቄ ነበር። በአራት ወይም በአምስት ቡድኖች በወታደራዊ ሰልፍ ሄዱና በማዕረጋቸው ተሰለፉ። እንደ ወጣት ሴቶች ልጆች ቢታዩም ፊታቸው በመልክ ተመሳሳይ አልነበረም፣ ነገር ግን እያንዳንዱ የተለየ ነው።



ተከብቤ ሳለሁ፣ በአቅራቢያዬ ያለ ማንኛውንም ለመያዝ፣ ለመደብደብና ለመቧጨር ወሰንሁ። እነሱ ለመሸሽ ቢሞክሩም፣ በቀላሉ እይዛቸውና ከልብስ እንደተሰሩ አሻንጉሊቶች ዙሪያውን አወዛውዛቸዋለሁ። በእሳት እየተንበለበለ ወደነበረው ፓስተር እወስዳቸዋለሁ። እነሱ እርሱን ይጠሉታል እና በጣም ይፈሩታል። ወደ ፓስተሩ ሳመጣቸው አካሉን ብቻ በመንካት ይቃጠሉ ነበረ። ይጮኹና ወደ አመድ ይቀየሩ ነበረ። ፓስተሩ ይህ እየሆነ እንደነበረ አያውቅም እንኳ ነበር። እርሱ መጸለዩን ብቻ ይቀጥላል።

በውጊያው መሐል በጣም መናደድ ጀመርሁና እንዲህ ብዬ አሰብሁ፦ *"ዛሬ ለመጸለይ ተዘጋጅቼና ቆሬጬ ነበረ እና **ጌታ**ን መንግሥተ ሰማይን መጎብኘት እችል እንደሆን ጠየቅሁት። ነገር ግን፣ አጋንንት አስታጎሉኝና ትኩረት ለማድረግና ጥያቄዎቼን ለማሳወቅ አልቻልሁም ነበር። ዛሬ መንግሥተ ሰማይን መጎብኘት አልቻልሁም ነበር። ይህ መልካም ነው። መንግሥተ ሰማይን ዛሬ መጎብኘት ካልቻልሁ ቁጣዬን አጋንንቱ ላይ እወጣለሁ!"* በእይታ ውስጥ የመጡትን ሁሉንም አጋንንት አሸነፍኳቸው።

በመንፈሳዊ፣ ከመቶ በላይ የሆኑ አጋንንትን በመገጣጠም አስቸጋሪ ቀን ነበረኝ። ከረጅም ቆይታ በኋላ **ኢየሱስ** መጣና ፓስተሩ እየጸለየበት ወደነበረው ወደ መሠዊያው ሄደ። ፓስተሩ ከጥቂት ቀናት በፊት አጋንንት ካደረሱበት ከሚያውቃየው ህመሙ እስከ አሁን ሙሉ በሙሉ አላገገመም ነበር። ምንም እንኳ ሥቃይ ቢኖርበትም እርሱ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎትና አምልኮ መምራት ቀጠለ። በጸሎት ጊዜ እንኳን እርሱ በሥቃይ ውስጥና በጣም ተዳክሞ ነበር።

**ኢየሱስ** ከአጠገቡ ቆመና በፍቅር ራሱን፣ ጀርባውን፣ እና አካሉን በተለይም ቁሥሎቹ በነበሩበት ቦታ በእጁ አሻሸው። **ጌታ** ፓስተሩን ባየ ቁጥር እርሱ በጣም አስደናቂ (ተጫዋች) መሆን ይጀምራል። **ኢየሱስ** ከፓስተር ጋር መሆን ይወዳል። **ኢየሱስ** አንድ ዝማሬን እንኳ ዘመረ:- ***"ምንም እንኳ ብትቆሥልም፣ አንተ አሁንም ልብ በሚነካ ሁኔታ እየጸለይህ ነው። ታላቅ እያደረግህ ነው!"*** **ጌታ** በጣም ደስ ተሰኝቶ ነበረ።

ይህን እየተመለከትሁ እያለ በጣም ለጥቂት ጊዜ መከላከያዬን አውርጄ ነበር እና አንድ የማይታይ ጋኔን ቀኝ ክንዴንና እጄን መጠምዘዝ ጀመረ። የጋኔኑ ቀዝቃዛ ሀይል ከጣቶቼ ጫፍ እስከ ክንዴ ድረስ በዝግታ ተሠራጨ። እኔም ቀዝቃዛውን ሀይል ከመሠራጨት ለማስቆም ወዲያውኑ ቀኝ እጄን መነጨቅሁ። እንዲህ ብዬ ጮህኩ:- *"በ**ኢየሱስ** ስም አዝሃለሁ፣ አንተ ቆሻሻ ጋኔን ከእኔ ተወገድ! ተወገድ!"* ቀዝቀዛው ሰይጣናዊ ሀይል በዝግታ መበታተን ጀመረ። ስጸልይ ቀኝ እጄንና ክንዴን በድጋሜ ጤናማ እስኪሆን ድረስ በተደጋጋሚ በኃይል መታሁት።

**የዩ ክዩንግ ኢጋንንትን ለማደን የጭንቀት ሙከራ*

ጥቁር ፊትና አምስት የተዋሀዱ አካላት ያለው አንድ ጋኔን ቀረበኝ። የ**ኢየሱስ**ን ስም በቅንነት እየጠራሁ ያዝሁትና አወዛወዝሁት። ሌላ ጋኔን ነጭ ልብሶች በለበሰ ሰው መልክ ታየ። ይህ ጋኔን በጣም ረጅም ነበረ፣ ሰማይን መንካት የሚችል ይመስል ነበር። ኢጋንንቶቹን አወዛወዝኳቸውና በልሳኖች መጸለይ ጀመርሁ። ስጸልይ፣ ራሱ ላይ ሹል ቀንድ ያለው አንድ ጋኔን ፒያኖ ላይ እንደተቀመጠ ይሳለቅብኝ ጀመር። ይህ ጋኔን ረጅም ጭራ ነበረው እና ቀፋፊ ይመስላል። ይህንንም ጋኔን ደግሞ ለመያዝ ችዬ ነበር እና በጣም አስደንጋጭ ነበር። ጋኔኑም የሌሊትን ወፍ ክንፎች የሚመስሉ ክንፎቹን በማርገብገብ ለመሸሽ ሞከረ። ነገር ግን እኔ ወደ መሬት ላወርደውና ልረጋግጠው ቻልሁ። እኔም ያለምህረት በድንገት አጠቃሁት።

ጋኔኑን እየደበደብሁ እያለ **ጌታ** ከአጠገቤ መጣ። ***"አሀ፣ ዩ ክዩንግ፣ ታላቅ ሥራ እያደረግሽ ነው። አንቺ ጋኔኑን እያሸነፍሺው ነው። እኔ ወደ መንግሥተ ሰማይ ልወስድሽና ዙሪያውን ላሳይሽ እያቀድሁ ነበረ፣ ነገር ግን አንቺ ኢጋንንትን በመዋጋት ሥራ በዝቶብሻል። ምን ታስቢያለሽ?"*** እኔም እንዲህ መለስሁ:- *"**ኢየሱስ** ሆይ፣ መንግሥተ ሰማይን በኋላ መጎብኘት እችላለሁ። አሁን ሁሉንም ኢጋንንት ማሸነፍ አለብኝ!"* **ጌታ**ም እንዲህ አለ:- ***"መልካም፣ ኢጋንንትን ድል ንሺና አሸናፊ ሁኚ።"*** **ጌታ** ከአጠገቤ ቆመና ተመለከተ። ኢጋንንቱ **ኢየሱስ**ን ሲያዩ የበለጠ ፈርተው ነበርና ለመሸሽ ሞከሩ።

**ኢየሱስ** ፓስተሩ እየጸለየበት ወደነበረው ወደ መሠዊያው ተራመደ። እርሱ የፓስተሩን ራስ አሻሸና በእርጋታ መታ መታ አደረገ፣ በተለይም በራ (መላጣ) የሆነበትን ቦታ። **ጌታ** ወደ ዮሴፍ ሄደና በእርጋታ እግሩንና አካሉን ነካ። **ኢየሱስ** የታመሙ ቦታዎችን (ሥቃይ የነበራቸውን ቦታዎች) እየነካ ነበረ። **ኢየሱስ** ከጎኔ ሲሄድ በጣም ደስተኛ አልነበርሁም። ጮክ ብዬ *"**አባ፣ አባ!**"* በማለት ጮህኩኝ።

አንዴ **ኢየሱስ** ከሄደ በኋላ፣ መሠዊያው ላይ አንድ ጋኔን ታየና ወደ እኔ መጣ። በአሽሙራዊ አስተያየቶቹ ተናድጄ ነበር። ችላ ልለው ሞከርሁ፣ እሱ ግን ሊያሾፍብኝና የዘለፋ ቃላትን ይናገረኝ ቀጠለ። ፀባዬ እየተፈተነ ነበር። በጣም ቁጡ መሆን ጀመርሁ። ያዝሁትና አወዛወዝሁት። ጋኔኑም እንዲህ በማለት አማረረ:- *"እየዞረብኝ ነው። በጣም ዞሮብኛል! ልቀቂኝ!"*

ጋኔኑ በዓይኑ ውስጥ ዓይኖች እንዳሉት አስተዋልሁ። ሁለቱም የውስጣዊ ዓይኖቹ እያፈጠጡብኝ ነበር። ያ በጣም የሚያስደነግጥ ነበር። እኔም በሀይለኛ ድምጽ እንዲህ አልሁ:- *"እንዴት ብትደፍር ነው የምታፈጥብኝ!"* የጋኔኑን ዓይኖች በጣቴ ወጋኋቸው። ጋኔኑ በዓይኑ ውስጥ ብዙ ዓይኖች ስለነበሩት በርከት ላሉ ጊዜያት መውጋት ነበረብኝ። *"አሀ! ዓይኖቼ፣ ዓይኖቼ!"* ጋኔኑ በሀይለኛ ፍርሀት (ሽብር) ጮኸ፣ ነገር ግን እኔ አልለቀቅሁትም። ዙሪያውን እና ዙሪያውን አወዛውዘው ቀጠልሁ። እሱም እንዲህ ጮኸ:- *"ብቻዬን ተዪኝ! ተዪኝ! ካልለቀቅሽኝ እነክስሻለሁ!"*

ሲያስፈራራኝ፣ በላቀ ኃይል አወዛወዝሁት። ጋኔኑ በሁሉም ጥንካሬው እጄን ነከሰኝ። አንዴ እንደ ነከሰኝ አጥብቄ መያዜን አጣሁና በርቀት ወረወርኩት። **ኢየሱስ** በቅርበት ወደ ጎኔ መጣና በሚያበረታቱ ቃላት አመሰገነኝ። ***"አህ፣ የእኔ ዩ ክዩንግ አጋንንትን በማሸነፍ ታላቅ ናት። አንቺ በጣም ብሩህ ነሽ!"*** እርሱ በእርጋታ እጄን ያዘና እኔን ማበረታታት ቀጠለ። ***"ዩ ክዩንግ፣ ሌላ ጋኔን ሲቀርብሽ አያለሁ። አሸንፈው!"*** **ጌታ** ቆመና ከጋኔኑ ጋር ስዋጋ (ተጋድሎ ሳደርግ) ተመለከተ።

አንድ ጋኔን በአጽም መልክ መጣና እንዲህ ጮኸ፡- *"ከእኔ ጋር ወደ ሲኦል ነዪ!"* ከጎን ወደ ጎን ራሴን ሳነቃንቅ *"አይሆንም! አይሆንም!"* አልሁ። እኔም ያዝሁትና በታላቅ ኃይል መሬቱ ላይ ወረወርሁት። ጋኔኑም ጮኸና ጠፋ። **ኢየሱስ**፣ ከአጠገቤ ቆሞ አጨበጨበና እንዲህ አለ፡- ***"ዋው! የእኔ ዩ ክዩንግ ታላቅ ሥራ እያደረገች ነው! እምነትሽ የእውነት (ከልብ) በጣም (በብዛት) አድጓል።"*** እርሱ እያበረታታኝ ከእኔ ጋር ለትንሽ ጊዜ ቆየ።

**ኢየሱስ** ወደ መንግሥተ ሰማይ ተመለሰ። እኔም ለትንሽ ረዘም ላለ ጊዜ በልሳኖች ጸለይሁ። የዛን ቀን ወደ 50 የሚሆኑ አጋንንትን ተዋግቼ አሸንፌአለሁ ብዬ አስባለሁ።

**በመንፈስ ቅዱስ ቅባት የሀክ ሱንግ መለወጥ*

የአጋንንት ቁጥር ቀስ በቀስ መጨመር ቀጠለ። እነሱ በቡድኖች ሆነው ያጠቁናል። ዓይኖቻቸውን ወጋሁ፣ ዓይናቸውን ቀድጄ አወጣሁ፣ ረጋግጬ ቀጠቀጥኳቸው፣ እና ዙሪያውን አወዛወዝኳቸው። ሁለት እጆች ብቻ ስለነበሩኝ አጋንንቱን ሳጠቃቸው ራሴን መከላከል አልቻልሁም ነበር። እነሱ በጣም ብዙ ነበሩ። ጥንካሬዬ መዳከም ጀመረ እና እንዲህ ብዬ አሰብሁ፡- *"ቅዱስ ሰይፍ ብቻ ኖሮኝ ቢሆን በእርግጠኝነት ሁሉንም ለማሸነፍ እችል ነበረ።"*

በጦርነቱ መሐል ስለዚህ በተደጋጋሚ አስብ ነበር። የ**እግዚአብሔር**ን ኃይል ለመቀበል የበለጠ መጸለይ ይገባኛል። ደግሞም በትጋት የእርሱን ቃል ማንበብና ማጥናት አለብኝ። እኔ እነዚህን ሁሉ ባደርግ የ**መንፈስ ቅዱስ**ን ሰይፍ ለመቀበል እችላለሁ።

ዛሬ ከአጋንንት ጋር ስዋጋ ብዙ ነገሮች አገናዘብሁ። ይበልጥ ባሸነፍኳቸው ቁጥር በብዛት ሆነው ይመጡና በብዛት ሆነው ያጠቃሉ። የት እንደሚደበቁ ምንም አሳብ የለኝም (አላውቅም)። አጋንንት ለማጥቃት መምጣታቸውን ብቻ አይደለም አውቅ የነበረው፣ ነገር ግን በዮሴፍ፣ በጁ ኢዩን፣ እና በዩ ክዩንግ አንዴ ተሸንፈው የነበሩት ይመለሱና ያጠቃሉ። እነሱ በአገልግሎት ሰዓታት ጊዜ እና በጸሎት ሰዓት ጊዜ አስታጉለውናል። በጸሎት ሰዓት ጊዜ በሚያጠቁን አጋንንት ፍፁም ቁጥር (ብዛት) ተገርመን ነበር።

እንደ ጥንብ አንሣ፣ በብዛት ሲሰባሰቡ በወረራቸው ዙሪያ ክብ ይሠራሉ። ለመብላት ጊዜ ሲሆን ጥንብ አንሣዎች በታላቅ ቁጥር (በጣም በብዛት ሆነው) በወረራቸው (አድነው ሊበሉት ባሉት) ላይ ዘለው ይከመራሉ። አጋንንትም ሁሉም በአንድ ጊዜ በተመሳሳይ መልክ ያጠቃሉ እና ይታዩ ያልነበሩት ከየትም ቦታ ወጥተው ይታያሉ። የተደበቁት ተስማሚ ጊዜ ሁል ጊዜ እየጠበቁ ነው። ደግሞም በሲኦል ውስጥ ሰይጣንን ማየት ችዬ ነበር። የበታቾቹ ማጥቃቱን ለመቀላቀል በመሰማራት ላይ እያሉ እሱ የበታቾቹን በጩኸት እያዘዛቸው ነበር። እጅግ ብዙ ከሆኑ አጋንንት ጋር የተካሄደ ጦርነት በፍፁም ተለማምጄ (አጋጥሞኝ) አላውቅም። ዛሬ፣ የቤተ ክርስትያኑ ጣሪያና ግድግዳዎች ላይ የተጣበቁ የአጋንንት መንጋዎች ነበሩ። እጅግ ብዙ ስለነበሩ ከአጋንንቱ በቀር ሌላ ምንም የሚታይ አልነበረም።

እኔም ቅዱስ እሳት እንዲሰጠኝ ወደ **እግዚአብሔር** ጮህኩ፡- *"**ሥላሴ እግዚአብሔር** ሆይ፣ እባክህን ቅዱስ እሳት ስጠኝ! አጋንንትን የሚያቃጥለውን እሳት!"* እግዚአብሔር በፍጥነት ደረቴ ውስጥ የገባ አንድ የእሳት ኳስ ሰጠኝ።

ቅዱሱ እሳት በሰውነቴ ውስጥ እንደተቀመጠ አጋንንት እኔን መሸሽ ጀመሩ። እሳቱ ሰውነቴ ውስጥ ከመግባቱ በፊት በጣም እየደከመኝ ነበርሁ። ነበልባላዊው እሳት ከገባ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጥንካሬዬ ተመለሰ። አጋንንትን ለማደንና ለማሸነፍ ችዬ ነበር። ሁሉንም አጋንንት ካሸነፍኩ በኋላ የምስጋና ጸሎት ለጌታ አልሁ። እኔ ለሁሉም ነገር በጣም አመስግኜ ነበረ። ከዛ፣ የፓስተሩን ልብ እጅግ አሳዝኜ የነበረበትን ቀናት አስታወስሁ እና በእነዛ አሳቦች፣ እንባዎች ዓይኖቼን ይሞሉት ጀመር።

በአገልግሎት መሐል ጊዜ፣ ፓስተሩ *"ሳም?"* በማለት ተጣሩ፣ እኔም ወዲያውኑ አሜን በማለት መለስሁ። ፓስተሩ እጅግ በጣም ኃይለኛ የሆነ አገልግሎት ይመራሉ። ነፍሴና መንፈሴ በፍጥነት እያደገና እየተቀየረ እንደሆነ አስተዋልሁ። ከሁለት ወራት በፊት ከነበርኩት ሰው ሙሉ በሙሉ በጣም የተለየሁ ሰው ነኝ። ከዚህም በላይ፣ እኔ በመንፈሳዊ ተነቃቅቼአለሁ እና ትንቢት ለመናገር፣ መናፍስትን ለመለየት፣ በልሳኖች መጸለይ፣ እውቀትን ማግኘት፣ ጥበብን ማግኘት ችዬአለሁ፣ እና በእምነት በጣም ጠንካራ ነኝ። ከ**ኢየሱስ** ጋር ስወያይ፣ የ**አብ**ን ዙፋን በተደጋጋሚ አያለሁ።

***መንፈስ ቅዱስ*** አንድ መንፈስ ቢሆንም፣ በመንፈሳዊ ዓይኖቼ እርሱን ለማየት ችዬአለሁ። እኔ ወደ ቤተ ክርስትያን መምጣት እወዳለሁ፤ አስደሳችና የሚያስደንቅ ነው። ሌሊቱን ሁሉ በሆነ አገልግሎት ላይ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ። ወንጌል ስሰብክና ስጸልይ የተለማመድሁትን ደስታ ለመግለጽ ይከብደኛል። አገልግሎቱ የሚደረገው ከምሽት እስከ ንጋት ጠዋት ጊዜ ድረስ ነው፣ አብዛኛውን ጊዜ እስከ ጠዋቱ 12 ሰዓት ወይም 1 ሰዓት ድረስ ነው። ከጸሎት ሕብረት በኋላ፣ እስከ ጠዋቱ 11 ሰዓት ድረስ እርስ በራሳችን እንመሰክራለን። ሩዝ ለመብላትም ደግሞ እንሰበሰባለን። አንዴ የማለዳ ጠዋት ምግባችንን ከተመገብን፣ ፀሐይዋ ማብራት እስክትጀምር ድረስ ለጥቂት ረዘም ላለ ጊዜ እንጸልያለን። አንዴ የጸሎት ስበሰባችን ከተፈጸመ፣ ፓስተሩ ወደ ቤታችን በመኪና ያደርሰናል። ወደ ቤት በሚደረገው ጉዞ ላይ **ኢየሱስ** ያጅበናል። ሃሌ ሉያ!

**እህት ቤይክ ቦንግ ንዮ**: **የመስቀል ሥቃይ በሲኦል ውስጥ ይጠብቃል*

ልብ በሚነካ ሁኔታ በልሳኖች ስጸልይ ኢየሱስ መጥቶ ታየ። እርሱ ወደ ሲኦል ሊወስደኝ እንደሆነ ወዲያውኑ ተሰማኝ። ጉዞዬን ለመግለጽ **ጌታ** ጥቂት ያመነታ ይመስላል። **ጌታ** አንድ ጥያቄ እኔን ለመጠየቅ ከመቻሉ በፊት እኔ ጠየቅሁት። *"**ኢየሱስ** ሆይ፣ ለምንድን ነው የምታመነታው? ሲኦልን እንድጎበኝ በድጋሚ ወደ ሲኦል ልትወስደኝ እንደሆነ አውቃለሁ፣ ትክክል?"* **ጌታ** የማይመች አስተያየት ሰጠኝ፡ ነገር ግን፣ **ጌታ**ን አለመታዘዝ አልችልም። *"**ኢየሱስ** ሆይ፣ ቤተ ሰዎቼ በሥቃይ ውስጥ ሆነው ካላሳየኸኝ እስከ ሲኦል መጨረሻዎች ድረስ እከተልሃለሁ። ወላጆቼ በሥቃይ ውስጥ ሆነው በቃ ማየት አልፈልግም።"* **ጌታ** እጄን ያዘ እና አንድም ቃል አልተናገረም።

እንደተለመደው፣ አንዴ **ጌታ** እጄን እንደያዘ በሲኦል ውስጥ ነበርን። እኛ በጠባብ መንገድ በኩል መራመድ ጀመርን። በአጭር ጊዜ ውስጥ የበሰበሱ ራሣዎች ሽታ አየሩን ይሞላው ጀመር። እኛም አንድ ሰፊ ሜዳ ላይ ደረስን። ያልፍፃሜ የተሰለፉ መስቀሎች እዛ ነበሩ። ሁሉም መስቀሎች መሬቱ በጥልቀት ተቆፍሮ ገብተው ነበር። መስቀሎች ላይ የተሠቀሉ በጣም ብዙ ሰዎች ነበሩ እና ብዙዎች በረጅም መስመሮች ተሰልፈው ለመሠቀል እየጠበቁ ነበረ። መስቀል ላይ ለመቸንከር ተሰብስበው እየጠበቁ ከነበሩት ብዙ ሰዎች መሐል እናቴ ነበረች። እሷ ካልተያዙት መሥቀሎች ከአንዱ በታች ቆማ ነበረ።

አንድ ግዙፍ አስፈሪ ፍጥረት መሥቀሎቹን ይጠብቃቸዋል። የእናቴ ተራ ሲሆን፣ ፍጥረቱ እናቴን መሥቀል ላይ አሰራትና ለመቸንከር አዘጋጃት። ፍጥረቱ በጨረፍታ ተመለከተኝና ወደ እርሷ ሲዞር ተናገረ። *"ወደ ቤተ ክርስትያን እንዳትሄድ እና በዚህ ቅጽበት **ኢየሱስ**ን ማመን እንድታቆም ልጅሽን ተናገሪ። ያለበለዚያ አንቺ ዛሬ የእውነት ትሞቺያለሽ!"* እናቴ በጣም የፈራች መሰለች። ፍጥረቱ ወደ እኔ ተመለከተና እንዲህ ጮኸ፡- *"አንቺ በ**ኢየሱስ** ማመን እንደምታቆሚ ከተናገርሽ እኔ እናትሽን አተርፋታለሁ እና አላሠቃያትምም። በፍጥ! ማመን እንደምታቆሚ ተናገሪ!"* ጋኔኑ ከእኔ ጋር ለመስማማት ሞከረ። *"አሁን በፍጥ! ቃል ኪዳንሽን አድርጊ! ፍጠኚ!"* በማለት ፍጥረቱ አስገደደ። ሁኔታው በጣም የተወጠረ ነበር።

ፍጥረቱ የፈረስ ራስ እና የሰው አካል ያለው ነበረ። አሰቃቂ ነበረ። በቀጥታ ዓይኑን ማየት አልቻልኩም ነበር።

የፈረስ ጭንቅላት ያለው ፍጥረት አንድ ግዙፍ ደማቅ ሰይፍ ነቀነቀና የበታቾቹን አዘዛቸው። የበታቾቹም በፍጥነት ታዘዙ። ከዛ ፍጥረቱ እናቴን ገፋፋት። *"በፍጥነት ለልጅሽ ተናገሪ! አሁን! በአንቺ ልጅ ምክንያት ሲኦል በትርምስምስና ግራ መጋባት ውስጥ ናት። ልጅሽ እየተካፈለችበት ያለችው ቤተ ክርስትያን ሌሊቱን ሁሉ ትጸልያለች። እኛ በሁሉም ፊና ተደናቅፈናል። ወደ ሲኦል ይመጣሉ ተብለው የታሰቡ ሰዎች (የሰው ልጆች) ወደ ቤተ ክርስትያን እየሄዱ ናቸው እናም እኛ ፈርተናል። በፍጥነት! ልጅሽን አሁን ጠይቂ! ፓስተሯ የእኛን ማንነት እና ሲኦልን የሚያወጣ (የሚገልጽ) አንድ መጽሐፍ እየጻፈ ነው። ያን መጽሐፍ እንዳይጽፍ እኛ እሱን የግድ ማስቆም አለብን። አሁን በፍጥነት ልጅሽን ጠይቂ!"*

እናቴ ስትመለከተኝ እንባዎቿ በጉንጮቿ ላይ ያለማቋረጥ ፈሰሱ። **ኢየሱስ** ከአጠገቤ ስለቆመ እናቴ አንድም ቃል ለማለት አልቻለችም። እርሷ በቃ አንገቷን ደፋችና ማልቀሷን ቀጠለች። ፍጥረቱ ትዕግስቱ አለቀና በቁጣ ቱግ አለ። እናቴ ልብሷ ተገፍፎ መስቀል ላይ ተሰቅላ ነበር። እነሱ በገመድ በጥብቅ ሰቀሏት። በአጭር ጊዜ ውስጥ ትንሹ ወንድሜንና የወንድሜን ልጅ አመጧቸውና ልብሳቸውን ገፈፏቸው። እነሱም እንደዚሁ መስቀሎች ላይ ተሰቀሉ። ክፉው ፍጥረት ያለምህረት መስቀሎች ላይ ሁሉንም በምስማር ይቸነክራቸው ጀመር። ፍጥረታቱ (ክፉዎች አጋንንት) ሥጋቸውን (የሰዎቹን) ይቆራርጡ ጀመር።

ሥጋቸው ከራሳቸው አናት ጀምሮ እስከ እግሮቻቸው ጣቶች ድረስ ተቆራርጠው ነበር። አካላቸው እስከ አጥንቶቻቸው ድረስ ተቆርጦና ተቆራርጦ ነበር። የቤተ ሰዎቼ ሥጋ የሚፈላ የዘይት ማሰሮ ውስጥ ተወረወረ። ማሰሮው እጅግ በጣም በሚንበለበል እሳት ግሎ (ሞቆ) ነበር። የእኔ እናት፣ ትንሹ ወንድሜ፣ እና የወንድሜ ልጅ በአፅማቸው ቅርፅ ላይ ዓይናቸውና ጆሮዋቸው ብቻ ነበር የቀረው። የተቀረው ሁሉም ተቆራርጧል። በሚያሳዝነው ቅርፃቸው እነርሱ አሁንም እንዲህ በማለት መጮህ ችለው ነበር:- *"ቦንግ ንዮ፣ በፍጥነት ሂጂ! ከእንግዲህ በኋላ እንዳትመጪ ብለን ነግረንሽ ነበር። ለምንድን ነው መምጣት የቀጠልሽው? በሥቃይ ውስጥ ሆነን ስታዩን አትሠቃዩም እንዴ? እባክሽን ተመልሰሽ አትምጪ!"*

እኔም እየተነፋረቅሁ እንዲህ በማለት ጮህኩ:- *"እናቴ ሆይ፣ ድሃዋ እናቴ! ከሦስት ተጨማሪ ጉብኝቶች በኋላ ብመኝ እንኳ ወደ ሲኦል መምጣት አልችልም። አንዴ ሶስተኛው ጉብኝት ከተፈጸመ ከዛ በኋላ እዚህ እንደማያመጣኝ* ***ኢየሱስ*** *ነግሮኛል። አንቺን በሥቃይ ውስጥ ሳይሽ ልቤ በታላቅ ሥቃይ ውስጥ ናት!"* ፍጥረቱ አቋረጠንና በሀይለኛ ድምጽ አንዴ በድጋሜ ጮኸ:- *"እኔ ለመጨረሻ ጊዜ እጠይቅሻለሁ! ይህ የመጨረሻ እድልሽ ነው! አንቺ ልጅሽን በ**ኢየሱስ** እንዳታምን ትነግሪያታለሽ። በፍጥነት! መጸለይና ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ እንድታቆም አስገድጃት! በፍጥነት!"* ፍጥረቱ እናቴን ሲጨቀጭቃት፣ እኔ በእናቴ ቦታ ሆኜ ተናገርሁ። *"አንተ፣ ክፉ ፍጥረት! የምትለው አንዳች ካለህ ከእኔ ጋር ተነጋገር። ለምንድን ነው እናቴን የምታስፈራራት? ከያዝኩህ አንተ ትሞታለህ (ምተሀል)!"* ፍጥረቱን ስገስጸው እሱ ወደ እናቴ በታላቅ ፍጥነት እንደ ጥይት ሮጠ። ፍጥረቱ የእናቴን አናት ገሸለጠው፣ ጆሮዎቿን ቆራረጠ፣ እና ዓይኖቿን አወጣቸው። እናቴ በሥቃይ ጮኸች:- *"እርዱኝ! እባካችሁን!"* ከእንግዲህ በኋላ እናቴ በሥቃይ ውስጥ ሆና ማየትን መታገሥ አልቻልሁም። ይህን አሳዛኝ ሁኔታ ሊገልጹት (ሊያብራሩት) የሚችሉ ምንም ቃላት የሉም! ትንሹ ወንድሜ እና የወንድሜ ልጅም እንደ እናቴ ያው ሥቃይ ደረሰባቸው። ፍጡሩ ቀሪዎቹን የሰውነት ክፍሎች ወደ ሚፈላው የዘይት ማሰሮ ውስጥ ወረወራቸው። ከሚፈላው ማሰሮ ውስጥ በሥቃይ ውስጥ የሆኑትን የቤተ ሰዎቼን ጩኸቶች መስማት እችል ነበር።

የፍጡሩ ቁጣ አልረካም ነበር። በዚህ ጊዜ፣ እሱ አንድ ጎድጓዳ ሣይን በነብሳት ሞላና ከቤተ ሰዎቼ በታች አስቀመጠው። ነብሳቱ በታላቅ ፍጥነት በቤተ ሰዎቼ አካላት ላይ ራሳቸውን አጣበቁ። ነብሳቱ ወደ አጥንታቸው ውስጥ በመግባት ቆረጣጠሙና አኘኩ። ቤተ ሰቤ በጣም ጮኸ። እናቴ የላቀ ሥቃይ እየደረሰባት እንደሆነ ታየ።

እናቴ እንዲህ በማለት ጮኸች:- *“ሰይጣን፣ እኔ ሞቻለሁ እኮ! ለምንድን ነው የሞተን ሰው የምታሠቃየው? ሰይጣን፣ እነዚህን ነብሳት ውሰዳቸው! ይህን ሥቃይ አቁም! እባክህን!”* ይህ የማይቻል እንደሚሆን ባውቅም እንኳ እንዲህ በማለት ጠየቅሁ:- *“**ኢየሱስ** ሆይ፣ የሥቃያቸው ፍጻሜ መቼ ነው የሚሆነው?”* ለረጅም ጊዜ በጣም እያለቀስሁ ነበረ። **ኢየሱስ** እንዲህ አለ:- ***“አንዴ ሲኦል ከገባሽ በፍጹም ማምለጥ ወይም ሌላ እድል ሊኖርሽ አትችዪም። ለዘላለም በሥቃይ ውስጥ ትሆኛለሽ።”***

**ጌታ**ን አጥብቄው ይዤው እያለቀስሁ ለመንሁት:- *“**ኢየሱስ** ሆይ፣ እናቴ በሲኦል ውስጥ ለዘላለም በሥቃይ ልትሆን ነው። ታድያ እኔ እንዴት ነው በመንግሥተ ሰማይ ውስጥ በደስታ የምኖረው? እኔ ከእንግዲህ የእናቴን መከራ (ሥቃይ) ማየት አልችልም። እባክህን እርሷ መዳን እንድትችል እኔ የእናቴን ቦታ እንድወስድ አድርገኝ!”* **ኢየሱስ** በፍጥነት መላእክትን ጠራ።

በሁኔታው ድንጋጤ የተነሣ ልሞት ደርሼ ነበር። በ**ጌታ** ትዕዛዝ ሊቀ መላእክት ሚካኤል እና አንዳንድ ሌሎች መላእክት መጡና ወደ **ጌታ** ቤተ ክርስትያን መለሱኝ። **ኢየሱስ** ሙሴን እንኳ ጠራውና እንዲያጽናናኝ ጠየቀው። **ኢየሱስ** እና ሙሴ እጅግ አዝነው ነበር። እነርሱ ወደ ደረታቸው አስጠጉኝና እንባዎቼን አብሰው አጽናኑኝ። እንባዎቼ ሲወርዱ ሲያዩ እነርሱ ከእኔ ጋር አዘኑ።

# ==== ቀን 24 ====

**ኪም ዮሴፍ:** (2ኛ ጢሞቴዎስ 3:1-5)

በልሳኖች ስጸልይ በድንገት የንስሐ እንባዎችን አለቀስሁ። የእውነት በእንባዎች የሆነ ንስሐዬን ለመስማት (ለማግኘት) እኔ ረጅም ጊዜ ጠብቄአለሁ።

አካሌ የእሳት ኳስ እየሆነ መጣ፣ ስለዚህ አንድ ክፉ መንፈስ በእባብ መልክ ሲመጣ ያዝሁትና በአየር ላይ አወዛወዝሁት።

**ሊ ዩ ክዩንግ:**

ልብ በሚነካ ሁኔታ ስጸልይ ጥላቻን የሚያስከትል አንድ ክፉ መንፈስ መጣና በላዬ ላይ በረረ። በሌሊት ወፍ ክንፎቹ ከፊቴ አንዣበበ። እንቁራሪት የሚመስሉ ዓይኖች፣ ቀይ አፍንጫ እና ረጅም ምላስ አሉት። እኔ ላይ የጥላቻ ድምፅ በማሰማቱ ተናድጄ ስለነበር ያዝኩት፣ ክንፎቹን ገነጠልኳቸሁና ወደ አየር ላይ ወረወርኩት። ከተጎዱት የአካሉ ቦታዎች ደም ይንጠባጠባል።

በዛው ጊዜ፣ አንድ ጨለማ አስቀያሚ ጥቁር እባብ ቀረበኝ። እኔ እባቦችን እጅግ እፈራለሁ እነሱ ጥላቻን የሚፈጥሩ ፍጥረታት ናቸው። ወደ እኔ ሲቀርብ እንዲህ በማለት ከመጮህ በቀር አንዳች ለማድረግ አልቻልሁም ነበር:- *“**ጌታ** ሆይ! በጣም ፈርቻለሁ! እዚህ አንድ እባብ አለ!”* **ኢየሱስ** ከመቅጽበት መጣ፣ እባቡን ያዘው እና በርቀት ወረወረው።

**ጌታ** እንዲህ በማለት ጠየቀ:- ***“ዩ ክዩንግ፣ ደህና ነሺ? አትፍሪ! (ስጉ አትሁኚ!) ሄደን መንግሥተ ሰማይን እንጎብኝ።”*** እጁን ያዝሁ እና ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመሄድ ቦታውን ለቀቅን። በጉዞአችን ጊዜ በከዋክብቶች ክምችት ውስጥ በማለፍ ላይ እያለን **ኢየሱስ** የምስጋና መዝሙሮችን እንድዘምር ጠየቀኝ። እኛም *“ምስጋና ሆይ! ነፍሴ!”* በማለት ብዙ ጊዜያት ዘመርን። መንግሥተ ሰማይን ከጎበኘን በኋላ ወደ **ጌታ** ቤተ ክርስቲያን ተመልሰን መጣን እና እኔም መጸለዬን ቀጠልሁ።

**ኢየሱስ** ፓስተር ኪምን ቀረበው እና እርሱ ሲጸልይ በትኩረት አዳመጠ። **ኢየሱስ** ለረጅም ጊዜ እያዳመጠ ነበር እና ፓስተር ሥቃይ ይሰማው የነበረ ቦታ ላይ ነካ። ሥቃዩ ክፉው መናፍስት ነክሰውት በነበረበት ቦታ በጀርባው ላይ ነበረ።

**ኢየሱስ** ዮሴፍን ቀረበውና እንዲህ ጮኸ፡- ***“ንስሐ ግባ! የበለጠ፣ የበለጠ፣ የበለጠ! ረዘም ላለ ጊዜ አልቅስ! ስትጮህ ብቻ ነው የመንግሥተ ሰማይ በሮች የሚከፈቱት!”*** ዮሴፍ ዛሬ ብዙ አልቅሷል፤ እርሱ የንስሐ እንባዎችን እየቀመሰ ነበር።

**ኢየሱስ** ተመልሶ ወደ እኔ መጣ እና አንዳንድ መላእክት ታዩ። **ጌታ** በድፍረት እንዲህ ተናገረ፡- ***“ዩ ክዩንግ፣ አትታመሚ፤ ሁል ጊዜ ጤናማ ሁኚ። ተበረታቺ! (ተጽናኚ!)”*** መላእክቱ እንኳ እንዲህ ጮኹ፡- *“ቅድስት ዩ ክዩንግ! አትታመሚ!”*

**ጌታ** ***“ተጽናኚ!”*** አለ። እኛ ከዛ ስንብቶቻችንን አልን።

**ሊ ሀክ ሱንግ፡** **በመላእክት የሚቀርብ ተከላካይ ድራቢ*

ስጸልይ በበሩ በኩል ብዙ መላእክት መጡ። መላእክቱ ተከላካይ ድራቢ በመሆን ከበቡኝ። እኔም ምን እያደረጉ እንደነበረ መላእክቱን ጠየቅኋቸሁ። እነርሱም በተከላካይ ድራቢዎች እየከበቡኝ እንደነበረ ነገሩኝ። መላእክቱ በተከላካይ ድራቢዎች ሲሸፍኑኝ ቅዱስ ተንበልባይ እሳት መታኝ። አንድ ክፉ መንፈስ ከተከላካዩ ድራቢ ውጭ ቆሞ አየሁ። ክፉው መንፈስ አንድ ቢላ ይዞ ነበረ እና ከሆረሩ ፊልም ቸኪን አስታወሰኝ። እሱ ከመላእክቱ ወደ አንዱ ቀረበና መልአኩን ወጋው፣ ነገር ግን ቢላው ወዲያውኑ ቀለጠ እና እጁ በእሳት ተያዘ። ሌላ ክፉ መንፈስ ሲቀርብ አየሁ። በጣም ያረጀ ዛፍ ይመስላል። በዝግታ ወደኔ ሲንቀሳቀስ እጁን ዘረጋና ተከላካዩን ድራቢ ነካው። ተከላካዩን ድራቢ አንዴ እንደነካ ክፉው መንፈስ በእሳት ተያዘና ሙሉው ዛፍ በእሳት ተዋጠ። ዛፉ ሲሸሽ ጮኸ።



መላእክቱ ተከላካይ ድራቢዎች እየጸለየች በነበረችው በዲያቆኒት ሺን ዙሪያም ደግሞ እያስቀመጡ ነበረ። መላእክቱ ወደ 200 ይቆጠሩ ነበር። እነርሱ ተከላካዩን ድራቢ በቤተ ክርስትያኑ አባላት ዙሪያ ለማድረግ ሁሉም እየሠሩ ነበረ። አንድ ክፉ መንፈስ ደብዛዛ ቢጫ ሰው መስሎ ከእኔ ተከላካይ ድራቢ ውጪ ሆኖ አስተዋልሁ። እሱ ወደ እኔ እየመጣ ነበር። ክፉው መንፈስ ተከላካዮቹን ድራቢዎች አልፎ ለመግባት ሞከረ፣ ድራቢዎቹ ግን እንደ ነበልባላዊ እሳት በጣም ሞቃት (የጋሉ) እየሆኑ መጡ። ክፉው ጋኔንም መግባት ተወ። ክፉው መንፈስ ከዛ ወደ ዲያቆኒት ሺን ሄደ። እንደ እድል ሆኖ፣ እርሷ በተከላካይ ድራቢዎችና በእሳት ተሸፍና ነበር። ክፉው መንፈስ ወደ ድራቢዎቿ ውስጥ ጥሶ ለመግባት አልቻለም። ክፉው መንፈስ ወደ እናቴ ሸሸ። ወደ እናቴ ሲጠጋ በእሳት ተያዘና ጠፋ።

በድንገት አንድ ግዙፍ ብሩህ ብርሃን ከመንግሥተ ሰማይ ወደ ታች አበራ። አንድ ግዙፍ ረጅም መልአክ ነጭ ፈረስ እየጋለበ ወደ ቤተ ክርስትያን ሲመጣ አየሁ። ዕይታው አስደናቂ ነበረ። ልቤ በጣም በፍጥነት እየመታ ነበር። መልአኩ ወደኔ መጣና እንዲህ በማለት ራሱን አስተዋወቀ፡- *“ሄሎ፣ እኔ ሊቀ መላእክት ሚካኤል ነኝ።”* ሊቀ መላእክት ገብርኤል የሚባል ሌላ በብሩህ የሚያበራ መልአክ ከሚካኤል ኋላ እየተከተለ ነበር። ገብርኤል ከአንድ ምሰሶ ጋር የተያያዘ አንድ ግዙፍ ሰንደቅ አላማ ይዞ ነበር። ሊቀ መላእክት ሚካኤል ክፉ መናፍስትን ሲያሸንፍ ሊቀ መላእክት ገብርኤል የአሸናፊነትን (የድልን) ሰንደቅዓላማ ከጎን ወደ ጎን እንደሚያወዛውዝ እነርሱ አብራሩልኝ።

ሊቀ መላእክት ሚካኤልና ገብርኤል ተመሳሳይ ቁመት አላቸው። ፓስተሩ እየጸለየ እያለ እነርሱ በእርጋታ ቆመው ተመለከቱ። ይህን አስደናቂ ዕይታ ሳይ በጣም ተደንቄ ነበረ። እያለምኩ ወይም እውን የሆነ አንድ ነገርን እያየሁ እንዳለሁ ለመለየት ለእኔ አስቸጋሪ ነበር።

**ኪም ጁ ኢዩን:** **ብዙ ክፉ መናፈስት በቡድኖች ሆነው ተጣደፉ ነገር ግን የእኛ እምነት እየጠነከረ መጣ*

የመጨረሻ ጊዜ የጸለይሁ ጊዜ አንድ ክፉ መንፈስ በግማሽ ጨረቃ መልክ እየተጠቀለለ ወደኔ መጣ። ዛሬ አንድ ክፉ መንፈስ ዓይኖች ባሉት በሙሉ ጨረቃ መልክ ወደ እኔ እየተንከባለለ መጣ። ክፉው መንፈስ በቅርበት ወደኔ ሲመጣ ዓይኑ ውስጥ ወጋሁትና ዓይኑን አወጣሁት። ጣቴን በዓይን ማኖሪያ (በዓይን ጉድጓድ) ውስጥ አዞርሁ። እንዳጠቃሁት ክፉው መንፈስ በሁሉም አቅጣጫዎች በደም ተጥለቅልቆ ቁግ አለ። ቶሎ ከዛ በኋላ፣ አንድ ክፉ መንፈስ እንደ አንድ ወጣት ሴት ልጅ መስሎ ታየ እና እንደ አሻንጉሊት የላይኛው ክፍል ራሱ ላይ እየተሽከረከረ ነበር። እኔም ጸጉሯን በብዛት ያዝሁ፣ አንቀጠቀጥኳት፣ ብዙ ጊዜያት አወዛወዝኳት፣ እና በርቀት ወረወርኳት። **ኢየሱስ** ቀረበኝና አድራጎቶቼን እንዲህ በማለት አመሰገነ፡- ***"ጠቃጠቆ፣ ታላቅ ሥራ!"***

**ኢየሱስ** ቀጠለ፡- ***"ጠቃጠቆ፣ ዛሬ በተለይ ቆንጆ መስለሻል! ጸጉርሽን ማን ነው የነካካው?"*** እኔም *"ዲያቆኒት ሺን አደረገችው!"* በማለት መለስሁ። **ጌታ** እንዲህ በማለት አመሰገነ፡- ***"የእውነት? እርሷ ታላቅ ሥራ አድርጋለች!"*** ዲያቆኒት እስካሁን በመንፈሳዊ የተነቃቃች ስላልሆነች፣ **ኢየሱስ** አጠገቧ መጥቶ እንደነበረ አላወቀችም። ብዙ መላእክት **ኢየሱስ**ን አጀቡት። መላእክት **ኢየሱስ**ን ሲያጅቡ ሁል ጊዜ አያለሁ፣ ነገር ግን በዚህ ጊዜ በጣም ብዙ መላእክት ነበሩ። በማላእክቱ ውስጥ አንዳንዶቹ ከሚጸልዩት የቤተ ክርስትያን አባላት አጠገብ ለመቀመጥ ጥንድ ይሆናሉ። መላእክቱ አናት ላይ ሰፊ ክፍተት የነበረውን ወርቃማውን ጎድጓዳ ሣህን ለማልበስ እጃቸውን ይጠቀማሉ እና ጎድጓዳውን ሣህን በቀናኢነት ተሞልተው (በከፍተኛ ፍላጎት) በቅዱሳኑ ጸሎቶች ሞሉት።

አንዴ በድጋሚ፣ አንድ የክፉ መናፍስት ቡድን በቤቱ ጥግ ላይ ታየ እና እነሱ ወደ እኛ መጡ። ሲቀርቡ፣ እህት ዩ ክዩንግ ክፉ መናፍስቶቹን ያዘቻቸው፣ አወዛወዘቻቸው፣ እና በርቀት ወረወረቻቸው። እኔም ደግሞ አንዳንድ ክፉ መናፍስትን ያዝሁ፣ አወዛወዝኳቸሁና በርቀት ወረወርኳቸሁ። ወንድም ሀክ ሱንግ እና ወንድም ዮሴፍም ደግሞ ክፉ መናፍስቱን እየተዋጉ ነበር፤ እነርሱ ክፉ መናፍስቶችን ያዙ፣ አወዛወዟቸው፣ እና አርቀው ወረወሯቸው። እኛ ሁላችንም ይህንን ዘዴ ብዙ ጊዜያት ደጋገምን።

በግድግዳዎችና በመሬት ዙሪያ እንደወደቁ ሲንከታከቱ የክፉ መናፍስትን ድምጾች ለመስማት ችዬአለሁ። ያ በጣም ጫጫታ የሚያበዛ ነበረ። በጸሎቱ ስብስብ ፍፃሜ ሲቃረብ (አካባቢ)፣ በእኛ ላይ ተጨማሪ ብዙ ጥቃቶች እንዳሉ አስተዋልን። ነገር ግን፣ እያንዳንዱ ጥቃት ውጤቱ እምነታችን እየጠነከረ እየጠነከረ እንዲያድግ አድርጎታል።

**እህት ቤይክ ቦንግ ንዮ:** **ፓስተር ኪም **ኢየሱስ** እንዲስቅ አደረገ (ፓስተር ኪም **ኢየሱስ**ን አሳቀው)*

እኔ ብዙ መንፈሳዊ ነገሮችን አይቻለሁም ተለማምጃለሁም። በዚህ ልዩ መብት፣ ብዙ ሥቃይ እንድችል ተደርጌአለሁ። **ኢየሱስ** በመንግሥተ ሰማይ ውስጥ በሚገኘው የአበባ መናፈሻ ቦታ (የአበባ አትክልት ቦታ) እኔን በመውሰድ አስደንቆኛል። እርሱ በአትክልት ቦታው ውስጥ ደስታን በመስጠት የብርታት (የጉልበት፣ የመነቃቃት) ጊዜ ፈቀደልኝ። በአትክልት ቦታው ውስጥ ያሻሁትን ያህል ብዙ ጊዜ ለማሳለፍ ችዬአለሁ። በአትክልት ቦታው ውስጥ ከመላእክት ጋር እንደ ሕፃን ልጅ ተንከባለልሁ፣ ዘለልሁ፣ እና ተጫወትሁ። በመንግሥተ ሰማይ ውስጥ ያለው የአበባ አትክልት ቦታው ሊታሰብ በማይቻል መልኩ ግዙፍ እና ውብ ነው። የአበቦቹ ጣፋጭ መአዛ በጣም የከበረ ስለነበረ በሙሉ ዓለም አልቀይረውም ነበረ። ሰውነቴ የደከመና ደካማ ስለነበረ፣ ወደ **ጌታ** ቤተ ክርስትያን ከተመለስሁ በኋላ አረፍሁና ጋደም አልሁ። በጠዋቱ አገልግሎት ጊዜ፣ **ኢየሱስ** በቅርበት እየተከተለው ፓስተሩ ሲሰብክ ከጎን ወደ ጎን ይራመድ ነበር።

ፓስተራችን በጣም አስቂኝ ስለሆነ ስለ እርሱ ሳስብ ወዲያው ፈገፍ እልና እስቃለሁ። ከማወቅ ፍላጎት የተነሣ ፓስተርን አንድ ጥያቄ እንዲህ ብዬ ጠየቅሁት፦ *"ፓስተር፣ ይህን ቤተ ክርስትያን መካፈል ከመጀመሬ በፊትም እንዲህ አስቂኝ ነበርህ?"* ፓስተርም እንዲህ በማለት መለሰ፦ *"ቤተ ክርስትያናችን በአንፃራዊነት አዲስ ነው። አስቂኝ ይሆናል ብዬ የማስበው ምንም ኢጋጣሚ የለም። በስብሰባችን ጊዜ አስቂኝ የሆነን አንዳች ነገር ማሰብ አልቻልሁም። ሁል ጊዜ እጅግ አዝኜ ነበረ። ከባድና አሳዛኝ ተሰምቶኛል።"* እኔም ጠየቅሁ፦ *"እንዴት በጣም ተቀየርህ?"* ፓስተሩም እንዲህ አለ፦ *"በትክክል አላውቅም። እኔ በዚህ የጸሎት ስብሰብ ጊዜ ተቀይሬአለሁ! የእውነት ምን እየተደረገ እንደሆነ አላውቅም። እኔ እንዴት እንዲህ መሆን እንደጀመርሁ እና ማን ወይም ምን እንደቀየረኝ ከጠየቅሽኝ፣ አስደሳች ሁኔታን (አካባቢን) የፈጠረው **ጌታ** ነው ማለት አለብኝ።"*

ፓስተራችን ሁሉንም አይነት ሰዎች የማስመሰል ልዩ ተሰጥኦ አለው። በእርግጥ፣ ሰዎችን ብቻ አይደለም፤ እርሱ እንስሳትንና ግዑዝ ነገሮችን ጨምሮ ሁሉንም አይነት የተለያዩ ነገሮችን ማስመሰል ይችላል። **ኢየሱስ** ፓስተሩን እያስመሰለና በጣም (ከፍ አድርጎ) እየሳቀ ነበር። በስብከት ጊዜ፣ ሁለት መላእክት ፓስተሩ የሰበከውን እያንዳንዱን ቃል እየጻፉ ነበረ። መላእክቱ ከመስቀል አጠገብ በመሠዊያው ላይ ተቀምጠው በግዙፍ መጽሐፍ ውስጥ እየጻፉ ነበር። መላእክቱ የፓስተሩን ቃላት መመዝገብ ይጠበቅባቸው ነበረ። ነገር ግን፣ እነርሱ አልፎ አልፎ የፓስተሩን አንድ አኳኋን ይመለከታሉ። መላእክቱ በጣም በኃይል ከመሳቃቸው የተነሣ ይዝለፈለፉ እና የፓስተሩ አንዳንድ ቃላት ያመልጣቸው ነበር። መላእክቱ ጽሑፍ ሲያመልጣቸው (ሲስቱ) **ኢየሱስ** ገሰጻቸው። ***"ወደ ፓስተሩ አትመልከቱ፤ ብቻ ከልብ ጻፉ!"***

**ኢየሱስ** ፈገግ ባለ ቁጥር ወይም በሳቀ ቁጥር፣ ሁሉም መላእክት በእርሱ ደስተኛ ሁኔታ ተካፋይ ይሆኑ ነበረ። ነገር ግን፣ **ኢየሱስ** ሲያዝን መላእክት ጸጥተኛ ይሆናሉ። በስብከቱ መሐል ጊዜ፣ ፓስተሩ እኔን አንድ ጥያቄ ጠየቀኝ። *"እህት ሆይ፣ አሁን **ኢየሱስ** የት ነው ያለው?"* እኔም እንዲህ በማለት መለስሁ፦ *"እርሱ ከአጠገብህ ቆሟል።"* ፓስተሩም የቂል ፈገግታ ፈገግ አለና እንዲህ አለ፦ *"ኦህ፣ ምን ማድረግ አለብኝ? እኔ ፈስቻለሁና የማያስደስት ይሸታል። ለማንኛውም ሰው ለመታገሥ አስቸጋሪ ይሆናል። **ጌታ** ከኔ የወጣውን ጋዝ በሚያሸትበት ቦታ ከአጠገቤ በመሆኑ ለእርሱ በጣም ሀዘን ተሰምቶኛል። ምን ማድረግ አለብኝ?"* **ጌታ**ም በሳቅ እንዲህ ተናገረ፦ ***"እኔ መንፈስ ስለሆንሁ ያ የማይረባ ነው። ያ ምንም አይደል።"*** እርሱም የፓስተርን ራስና ጀርባ መታ መታ አደረገ።

***ፓስተር ኪም ዮንግ ዱ:*** የቤተ ክርስትያኑ አባላት አብዛኛውን አካላዊ ጥንካሬያቸውን በጸሎት ጊዜ ጨርሰዋል። በማቆም ፈንታ፣ እነርሱ ጥርሳቸውን ነክሰው ልብ በሚነካ ሁኔታ መጸለይ ቀጠሉ። **ጌታ** በእንዲህ አይነት ታማኝነት (ፍቅር) እየጸለይን ሲያይ ተገርሞ (ተደንቆ) ነበር። እኔ ሊታገሡት በማይችሉት ሥቃይ ውስጥ ነበርሁ። ሥቃዩ የተከሰተው በክፉ መናፍስት በርካታ ጥቃቶች አማካኝነት ነበር። እንዲህ አይነት ቁስል በጣም በዝግታ ነው የሚፈወሰው። የማያቋርጠው ሥቃይ አሠቃየኝ። እጆቼን ወደ ላይ ከፍ አድርጌ ለረጅም ጊዜ ለመጸለይ ለእኔ ከባድ ሆነብኝ። ነገር ግን፣ በሥቃዩ መሐል **መንፈስ ቅዱስ** እጆቼንና ክንዶቼን በተለያዩ መልኮች ያንቀሳቅስ ነበር። የክንዶቼና የእጆቼ እንቅስቃሴዎች በጥሩ ሁኔታ በደንብ ተቀናጅተው ይሄዱ ነበር።

ሁለቱም እጆቼ ሳያቋርጡ ይንቀሳቀሱ ነበረ። እነርሱ በተራ ይንቀሳቀሳሉ። በድንገት፣ እጆቼ በኃይለኛው ይንቀጠቀጡ ጀመር። እኔም እንዲሁ ሊታገሡት በማይቻል መልኩ ሞቁ ነበር። **ኢየሱስ** ነጭ ልብስ (ጋውን) ለብሶ ከፊት ለፊቴ ከጎን ወደ ጎን ሲራመድ አየሁት። ፊቴ ለስለስ ያለ የበጋ ሞቃት ንፋስ ተሰማው። የእርሱ ጠንካራ መገኘት (መኖር) ተሰማኝ። በሚያሳዝን ሁኔታ፣ መንፈሳዊ ዓይኖቼ አሁንም አልተከፈቱም ነበረ። **ጌታ** ሁኔታችንንና አፀግበሮታችንን (አፀፋችንን) እየተከታተለ (እየተመለከተ) እንዳለ መስሎ ታየ። እርሱ እየገመገመን ነበረ።

## ==== ቀን 25 ==== (ማቴዎስ 16፡13-19)

**ኪም ጁ ኢዩን፡** **ሰሊጥ የገነትን ኩኪሶች በላች*

በልሳን እየጸለይሁ፥ ብዙ እርኩሳን መናፍስትን እየተዋጋሁና እያሸነፍኳቸው ነበር፡፡ እየጸለይሁ ሳለ፥ አፌ በሆነ ነገር መሞላት ጀመረ፡፡ ማኘኬን ስቀጥል ከሽከሽ የሚል ድምጽ ይሰማኛል፡፡ ምን እያኘኩ ወይም እይበላሁ እንደነበር አላውቅም፡፡ የማላውቀውን ምግብ በልቼ እንደጨረስሁ፥ ለራሴ እንዲህ አልኩ፥ *"ይገርማል! ምንድ ነው ይሄ? በጣም ጣፋጭ ነው፡፡ አንድ ነገር እንዴት እንደዚህ ሊጣፍጥ ይችላል?"* ውዱ **ጌታ**ዬ፥ **ኢየሱስ**፥ መጣ፡፡

የእኔን ስም ጠራና ያናግረኝ ጀመር፥ ***"ጠቃጠቆ፥ ይህን ትሞክሪዋለሽ?"*** እኔም *"**ኢየሱስ**፥ ምንድ ነው?"* ብዬ ጠየቅሁት፡፡ **ጌታ**ም መለሰ፥ ***"እነዚህ ከገነት ላንቺ ያመጣሁልሽ ብስኩቶች ናቸው፡፡ ሀ በይ፤ አፍሽን ክፈች፡፡"*** አፌን ከፈትሁና **ጌታ** አፌ ውስጥ ብስኩቶቹን አስቀመጠልኝ፡፡

ብስኩቱ ምላሴን እንደነካ፥ ወዲያው በልስላሴ ቀለጠ፡፡ በዓለም ላይ ብዙ ጣፋጭ ብስኩቶች አሉ፥ ነገር ግን **ጌታ** የሰጠኝ ግን ከአእምሮዬ በላይ ነው የሆነው፡፡ ቁራሽ የሚያክሉት ብስኩቶች ነጭና ክብ ቅርጽ ነበራቸው፡፡

ጮክ ብዬ፥ *"ኦ፥ **ኢየሱስ** ሆይ፥ ብስኩቱ በጣም ነው የሚጣፍጠው! ሌላ ብዙ መብላት እፈልጋለሁ፡፡ እባክህ ተጨማሪ ልትሰጠኝ ትችላለህ?"* **ጌታ**ም፥ ***"አይሆንም፥ አሁን ከዚህ ተጨማሪ መብላት የለብሽም፡፡"*** አለኝ፡፡ እኔም ተገርሜ ጠየቅሁት፥ *"ምን ነበር?"* **ጌታ**ም እንዲህ አለኝ፥ ***"ይህ ቅዱሳን በገነት የሚበሉት ምግብ ነው፡፡ ሌላ ተጨማሪ እንደምትፈልጊ አውቃለሁ እናም ገነትን ስትጎበኚ፥ በብዙ እጋብዝሻለሁ፡፡ ስለዚህ አጽንተሽ ጸልዩ፡፡"*** **ጌታ**ን በእንባ ጠየቅሁት፥ *"**ኢየሱስ** ሆይ፥ እባክህ ገነት ውሰደኝ!"* ሆኖም፥ ገና ንግግሬን ሳልጨርስ **ጌታ** ሄዶ ነበር፡፡ የሚታየኝና የሚሰማኝ የመሄዱ ቅሬታ ብቻ ነበር፡፡ ደማቅ አንጸባራቂ ብርሃን ሲያበራ ለስላሳ ረጋ ያለ እስትንፋስ ተሰማኝ፡፡

**ኢየሱስ** የሰጠኝ ሰማያዊው ብስኩት ለዘላለም በህሊናዬ ውስጥ ይኖራል፡፡ አስደናቂውን ጣዕም መቼም አልረሳውም፡፡ ዛሬ በጣም የተባረከ ምሽት ነው፥ በቃላት ልገልጸው አልችልም፡፡ ከርቀት፥ **ኢየሱስ** በትህትና ሲናገር ሰማሁት፥ ***"ጠቃጠቆ፥ በቅርቡ፥ ወደ ገነት እወስድሻለሁ ስለዚህ አትጨናነቂ፡፡ ደኅና ሁኚ፡፡"*** ከዛም? ሙሉ በሙሉ ተሰወረ፡፡

ብርታቴን በድጋሚ ካገኘሁ በኋላ፥ መጸለይ ጀመርሁ፡፡ ስጸልይ ሳለሁ፥ እርኩሳን መናፍስት ወደ እኔ ሲመጡ አየሁ፡፡ ብዙ አጥንቶች እና የራስ ቅሎች ከሁሉም አቅጣጫ ወደ እኔ ሲሰባሰቡ አየሁ፡፡ በገጽታቸው መሳቅ ጀመርሁ፡፡ እርኩሳን መናፍስቱ በሁኔታዬ በንዴት በገኑ፡፡ ጮክ ብዬ፥ *"እናንተ አጥንቶች ሁላ፥ አስቂኝ ነው የምትመስሉት፡፡ በ**ኢየሱስ ስም**፥ አሁኑኑ እንድትሄዱ አዝዛችኋለሁ!"* ሁሉም ጠፉ፡፡

**ሊ ዩ ክዩንግ፡** **የርኩሱን መንፈስ ልብስ መቀዳደድ*

ስጸልይ ሳለሁ፥ እርኩስ መንፈስ ነጭ ልብስ የለበሰች አንድ አስቀያሚ ሴት ልጅን ተመስሎ አየሁ፡፡ ሁሉም ጸጉር እስኪነቃቀል ድረስ ጸጉሯን ይዤ አሽከረከርኳት፡፡ ነገር ግን ልብሷን ከቀዳደድሁት በኋላ እራቁቱን ወደ ሆነ ወንድ ተለወጠች፡፡ ሙሉ እርቃን ሰውነቱ ሁሉ ይታዩኛል እናም ይጸዳዳብኝና ይሸናብኝ ጀመር፡፡

በጣም ተናደድኩ፥ አንገቱን ያስኩት፥ *"አስቀያሚ እርኩስ መንፈስ! ለምንድ ነው የምትሸናብኝ?"* ፊቱን በጥፊ መታሁት እናም እንዲህ አለኝ፥ *"ይቅርታ! እባክሽ ይቅር በይኝ፡፡ ሁለተኛ ወደዚህ ላልመጣ ቃል እገባለሁ፡፡"* በጥፊ መምታቴንና መደብደቤን ቀጠልሁ፡፡ ዛሬ በእሳት ተጥለቅልቆ ወዳለው ወደ ወንድም ሀክ ሱንግ ወረወርሁት፡፡ እርኩሱ መንፈስ ልክ ከወንድም ሀክ ሱንግ ጋር ሲጋጭ ወደ አመድነት ተለወጠ፡፡

ጸሎቴን ስቀጥል፥ ሁለት ትላልቅ ዓይኖች ያሉት ሌላ እርኩስ መንፈስ መጣ፡፡ ግማሹ የፊቱ ገጽታ የወንድ ሲሆን ግማሹ የፊቱ ገጽታ ደግሞ የሴት ነበር፡፡ በጣም አጭር ጸጉር ነበረው፡፡ ይህ እርኩስ መንፈስ የሆነ

ሆረር ፊልምን አስታወሰኝ፡፡ ሲናገር፥ ሁለት ዓይነት ድምጽ ነበረው፡፡ የወንድና የሴት ድምጽ ከአፉ ይወጣ ነበር፡፡ ጸጉሩን ሁሉ ነጫጨሁና ልብሱን ከላዩ ቀዳደድሁበት፡፡ እርኩሱ መንፈስ እርቃኑን ቆመ፡፡

እርኩሱ መንፈስ በምላሹ እንዲህ አለኝ፥ *“ለምንድ ነው ልብሴን የገፈፋችሁኝ? ማነው ልብሴን የገፈፈኝ?”* እኔም በድፍረት መለስሁለት፥ *“እኔ ነበርሁ፥ እኔ ነኝ ያደረግሁት! ለምን ትጠይቃለህ? ክብርህ እንደተነካ ተሰማህ?”* እርኩሱ መንፈስ አለቀሰና ተለማመጠ፥ *“እባክሽ አልብሽኝ፡፡ እባክሽ ፍጠኝ! በጣም በርዶኛል፡፡ እባክሽ የሆነ ልብስ ስጪኝ!”*

እርኩሱ መንፈስ ቆሞ እያየኝ፥ ልብሶቹን በጫጭቆ ከጥቅም ውጭ አደረግኋቸው፡፡ እርኩሱ መንፈስ ማማረሩን ቀጠለ፥ *“ማነው ልብሴን መግፈፍ ትችያለሽ ያለሽ? ለምንድነው ልብሴን ያበላሸሽው?”* እርኩሱ መንፈስ አሰለቸኝ፡፡ *“ትርኪ ሚርኪ ነው የምታወራው፡፡ ሞተሀል!”* አልሁት፡፡ ወርውሬ ከመሬት ጋር አጋጩሁትና እደበድበው ጀመር፡፡ መጮህ ጀመረ፥ *"አ፥ እርዱኝ! ያማል! እንደማሸንፍሽ አውቃለሁ ነገር ግን እንዴት በኃይል ልትበልጭኝ እንደቻልሽ አላውቅም፡፡ ፈርቻለሁ!”* የእርኩሱን መንፈስ አቤቱታዎች መስማት አልፈለግሁም፡፡ እግሩን ሰበርኩትና ከእኔ አርቄ ወረወርሁት፡፡ የክፍሉ ጥግ ላይ ወደቀና ደቀቀ፡፡ ውጊያው ድል ከሆነና ከተጠናቀቀ በኋላ፥ **ጌታ** ተገለጠ፡፡

*ዩ ክዩንግ የገነትን ፍሬ በላች

**ኢየሱስ** ደማቅ አንጸባራቂ ካባ ለብሷል፡፡ እየቀረበ ሲመጣ፥ በእጁ ክብ ነጭ ነገር እንደያዘ አስተዋልሁ፡፡ **ኢየሱስ**ም፥ ***“ዮ ክዩንግ፥ ይህን ሞክሪው፡፡ የገነት ፍሬ ነው፡፡ በቅንዓት ስለጸለይሽ ሽልማት ነው ያመጣሁልሽ፡፡ እርኩሳን መናፍስትን የማሸነፍ ብቃትሽ በማይታመን ሁኔታ ጨምሯል፡፡ ፍሬው በጣም ጣፋጭ ነው፡፡ ፍጠኝ፥ ሞክሪው!”*** አለኝ፡፡ **ጌታ** በፍቅር ንግግር ተናገረኝ በመሆኑም ደስ ብሎኝ መለስሁለት፡፡ *“**ጌታ** ሆይ፥ በጣም አመሰግናለሁ!”* አልሁት፡፡ የመጀመሪያውን እንደገመጥሁ፥ በእርካታ ጮህኩ፡፡ ፍሬውን በፍጥነት ጨረስኩት፡፡

**ጌታ**ም አለ፥ ***“ዮ ክዩንግ፥ ገነትን እንጎብኝ፡፡”*** በቅጽበት፥ ክንፎች ያሉት ልብስ ለበስሁ፡፡ በመስቀሉ በኩል ወደ ሰማይ በሚመራ በር ወጣን፡፡ በሰማይ ስንበር፥ ቶሎ ገነት ደረስን፡፡

ገነት ስንደርስ፥ ዬህ ጂን አገኘኋት፡፡ (Yeh Jee) ዬህ ጂ እና እኔ በ**ጌታ** ፊት ለረዥም ሰዓት ደነስን (ዘመርን)፡፡ በአቅራቢያችን ከወርቅ የተሠራ ፒያኖ አስተዋለሁ፡፡ ፒያኖው በጣም ረዥም ነበር፡፡ ለተወሰነ ሰዓት ፒያኖው ላይ አፈጠጥሁ፤ በጣም የሚመስጥ ነበር፡፡

ሳሽበሽብ ሳለ፥ **አብ** በዙፋኑ ሆኖ ዚወዛወዝ አየሁት፡፡ ከዙፋኑ ላይ፥ **አብ** አንጸባራቂ ደማቅ ብርሃንን ይመስላል፡፡ **እግዚአብሔር** ብርሃን ነው፡፡ ላየው አልቻልሁም፡፡ ብዙ መላእክት ነበሩ እናም ሁሉም በዙፋኑ ፊት በተደረደሩ መጻሕፍት ላይ የሆነ ነገር በመጻፍ ተጠምደዋል፡፡ **እግዚአብሔር አብ** እጅግ ግዙፍ ነው፡፡ ማንም ቁመቱን ወይም ስፋቱን ሊገምተው አይችልም፡፡ አንድ ሰው **እግዚአብሔር አብ**ን ለማየት ቢሞክር እንኳ፥ ከደማቁ ብርሃን የተነሳ የማይቻል ነው የሚሆነው፡፡ ብርሃኑ ለማየት በጣም ከባድ ነው፡፡ የ**አብ** ካባው በጣም ረዥም ከመሆኑ የተነሳ ቁርጭምጭሚቱ ጋር ይደርሳል፡፡ እግሩን ብቻ ነው ለማየት የቻልሁት፡፡ (1ዮሐ.1:5 ከእርሱም የሰማናት ለእናንተም የምናወራላችሁ መልእክት። **እግዚአብሔር** ብርሃን ነው ጨለማም በ**እርሱ** ዘንድ ከቶ የለም የምትል ይህች ናት።)

**እግዚአብሔር አብ** በሚያስተጋባ ድምጽ ተናገረኝ፡፡ ***“ዩ ክዩንግ፥ በእዚህ መሆን ግሩም አይደል? በትጋት መጸለይሽን ከቀጠልሽ፥ ደጋግሜ አመጣሻለሁ፡፡ ስለዚህ፥ ያለማቋረጥ በትጋት ጸልዩ፡፡”*** ሰገድሁና ፥ *“እሺ **ጌታ**ዬ፥ አሜን፡፡”* ብዬ መለስሁ፡፡ ከተናገርሁ በኋላ፥ ግዙፍ እጁ ከብርሃኑ ወጥቶ ጭንቅላቴን ነካ ነካ አደረገኝ፡፡ ከዛም **ኢየሱስ** እንዲህ አለ፥ ***“ዩ ክዩንግ፥ ተመልከችኝ!”*** **ኢየሱስ**ን ለማየት ስዞር፥ በጣም አዘንኩ ልቤም ተሰበረ፡፡ ላለቅስ ደረስሁ፡፡ በእጁ ላይ በሚስማር የተቸነከረበት ግዙፍ ምልክትን አየሁ፡፡ እንዲሁም በእግሩ ላይ ያሉትን ምልክቶች፡፡ **ጌታ**ም ቀጠለ፥ ***“ደሜ ሲፈስ፥ ስለአንቺ ሞትሁ፡፡ ሁል ጊዜም እኔን አስቢኝ!”***

ደጋግሜ **ጌታን** በገነት ያለውን ቤቴን እንዲያሳየኝ ጠየቅሁት፡፡ *"በገነት ያለውን ቤቴን ማየት እፈልጋለሁ!"* **ጌታም**፥ "***መልካም፥ ቤትሽን አሳይሻለሁ፡፡***" ብሎ ፈቀደልኝ፡፡ **ጌታ** ወደ ቤቴ ወሰደኝ፥ ሙሉ በሙሉ ከወርቅ የተሠራ ነበር፡፡ ቤቱ ባለ አስራ ሁለት ፎቅ ነበር፡፡ መላእክቱ ቤቴን በመሥራት ተጠምደዋል፡፡ ደስታና ፍስሐ ስለተሰማኝ እንደ ጥንቸል ዘለልሁ፡፡ በደስታ መዘመር ጀመርሁ 'ነፍሴ ሆይ፥ አወድሺ፡፡' ስዘምርና ሳወድስ፥ **ጌታ** ተናገረ፡፡ "***ውድ ዩ ከዩንግ፥ ከአንቺ ጋር የጋብቻ ስነ-ስርዓት እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ፡፡***" (ኤፌሶን 5፡21-33፡- **ጌታ** ለዩ ክዩንግ የሚነግራት ጋብቻ በምድር ወንድ ሴትን እንደሚያገባው አይደለም፥ ነገር ግን **ክርስቶስ** ከቤተክርስቲያን ጋር ያለውን ቁርኝትና ጥልቅ ፍቅር ለማሳየት ነው፡፡ ኢሳይያስ .54፡5፤ *ፈጣሪሽ ባልሽ ነው፥ ስሙም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው፤ የእስራኤልም ቅዱስ ታዳጊሽ ነው፥* እርሱም የምድር ሁሉ አምላክ ይባላል።)

ዩ ጂ በሄድሁበት ሁሉ ትከተለኝ ነበር፡፡ "*እህት፥ **ኢየሱስ** አፍቃሪ ነው፡፡ ብዙ ምግብና ብዙ ፍቅርን ይሰጠኛል፡፡ እዚህ በመሆኔ በጣም ደስተኛ ነኝ! እህቴ፥ እባክሽ በአበባዎቹ ግቢ እንጫወት፡፡*" ዩ ጂ እና እኔ ወደ አበባው ግቢ ሄደን ራሳችንን አስደሰትን፡፡ በአበባዎቹ ላይ ተንከባለልን ጥሩ ጊዜም አሳለፍን፡፡ በጊቢው ጥሩ ጊዜ አሳለፍን፡፡ **ጌታም**፥ "***ዮ ክዩንግ፥ አሁን የመሄጃሽ ጊዜ ነው፡፡ ከዩ ጂ ጋር ተሰነባበቱ፡፡***" አለኝ፡፡ እህት ዩ ጂም "*እህት፥ ጤናማ ሁኚ እናም ደግመሽ ጎብኚኝ፡፡*" አለችኝ፡፡ እርስ በእርሳችንም ተቃቀፍንና ተለያየን፡፡

**ሊ ሀክ ሱንግ፡** *በ**ኢየሱስ ደም** ከተሸፈንኩ በኋላ እርኩሳን መናፈስቱ ሊቀርቡኝ እንኳ አልሞከሩም



ስጸልይ ሳለሁ፥ ***መንፈስ ቅዱስ*** በሰውነቴ ላይ ከቅዱሱ እሳት መጨመሩን ቀጠለ፡፡ ሰውነቴ የእሳት ኳስ ሆነ፥ የማይቋቋሙት ሙቀት፡፡ ብዙ ዓይነት እርኩሳን መናፍስት ሊያጠቁኝ ጀመሩ፥ ሆኖም ገና ሰውነቴን ሲነኩ፥ በእሳት ይያዙና አመድ ይሆናሉ፡፡ ሁሉም ቀልጠው ጠፉ፡፡ በእንጨት ዱላ ላይ ጠምጥሜ ለኮስኩት፡፡ አጭር ጸጉር ያለው፥ ነጭ የለበሰ ክፉ መንፈስ ሊያጠቃኝ ሞከረ፥ ነገር ግን ይገፔ በእሳት አቃጠልሁት፡፡ ሌሎች መናፍስት ወደ እኔ መቃረብ ጀመሩ፥ ነገር ግን ከሰውነቴ ከሚመነጨው ቅዱስ እሳት የተነሳ ሸሽተው ጠፉ፡፡ በመጨረሻ እርኩሳን መናፍስቱ ወደ መጋቢ ለምን እንደማይቀርቡ ተረዳሁ፡፡ በሚጸልይበት ጊዜ ሁሉ፥ ሰውነቱ የእሳት ኳስ ይሆናል፥ ስለዚህ ከእርሱ ለመራቅ ይሞክራሉ፡፡ መጋቢውን ሲሸሹት ማየት ያዝናናል፡፡

የኤሌክትሪክ ፒያኖው '**በመንፈስ ቅዱስ** አጥምቅ' (Baptize by the Holy Spirit) የሚለውን መዝሙር ማጫወት ጀመረ፡፡ ስለዚህ በመንፈስ በዜማና በቅኝት መደነስ ጀመርሁ፡፡ በዳንሴ ውስጥ እርኩሳን መናፍስትን እዋጋቸውና አሸንፋቸው ነበር፡፡ እጅግ አስደሳች ነበር፡፡ **ኢየሱስ**ም ረክቶ አስተያየት ይሰጠኝ ነበር፡፡ "***ጥሩ ሥራ ነው ወዳጄ ሳም!***" የ**ጌታ** አበረታች ቃላት ደስታ እንዲሰማኝ አደረገኝ፡፡



የኤሌክትሪክ ፒያኖው 'ሦስቱ ችንካሮች' (Three nails) የሚለውን መዝሙር አጫወተ እና እኔም በንስሐ እንባ ታጠብሁ፡፡ **ኢየሱስ** እንባዬን አብሶ በሚያጽናኑ ቃላት አረጋጋኝ፡፡ እየጸለዩ ከነበሩት የቤተክርስቲያን አባላት መሐል ያልፍ ነበር እናም ጭንቅላታቸውን ይዳስሳቸው ነበር፡፡ መጋቢ ጋር እንደደረሰ፥ ጭንቅላቱን ብዙ ጊዜ ዳሰሰው፡፡

**ጌታ** መላእክቱን፥ ጮኸ ብሎ አዘዛቸው፥ "***መላእክት፥ ደሜን በ 'የጌታ ቤተክርስቲያን' (ዘሎርድስ ቸርች) መግቢያዎች ላይ ቀቡ፡፡ እርኩሳን መናፍስቱ በዚህ ሕንፃ ዙሪያ እንዲንቀሳቀሱ አትፍቀዱላቸው፡፡ ደሜን በአየሩም ላይ አድርጉ፡፡***" መላእክት በቅጽበት መጡና ትእዛዙን በታላቅ ፍጥነት ፈጸሙ፡፡ መጀመሪያ፥ በቤተክርስቲያኑ መግቢያና በኮርኒሱ ላይ መከላከያ ሽፋንን አደረጉ፡፡ በመግቢያው ላይ፥ በሩና ሁለቱ ቋሚዎች መከላከያ ሽፋን ተደረገላቸው፡፡ ከመከላከያው ሽፋን በላይ፥ መላእክቱ አብዝተው በ**ጌታ** ደም መቀባት ጀመሩ፡፡ የ**ጌታ** ደም ከተደረገ በኋላ፥ እርኩሳን መናፍስቱ ግራ ሲጋቡና ወደ የ**ጌታ** ቤተክርስቲያን ለመግባት እርስ በእርሳቸው ሲጣሉ አየሁ፡፡ ደሙ እየከለለን፥ ምንም ያህል እርኩሳን መናፍስት ቢኖሩ አይገደንም፥ አንዳችም ወደ ቤተክርስቲያን ሊገቡ አልቻሉም፡፡ ስለዚህ ጸሎቴን በሰላም ጨረስሁ፡፡

**እህት ቤይክ ቦንግ ንዮ፡** *በ**እግዚአብሔር** ጥበቃ፥ በሲዖል ስቃይ ምንም ህመም አልተሰማኝም

ስጸልይ ሳለሁ፥ **ጌታ** ከሁለት መላእክት ጋር ተገለጠ፡፡ መላእክቱ አጅበው ወደ ከዋክብት ዓለም ወሰዱኝ፡፡ የምንሄድበት ከደረስን በኋላ፥ **ጌታ** ወደ እቤታችን ወደ ገነት እንድንመለስ አዘዘ፡፡ ከዚያ በኋላ **ኢየሱስ**፥ "***ቦንግ ንዩ፥ ሲዖልን እንጎብኝ***" አለኝ፡፡ ልክ የ**ጌታ**ን እጅ እንደያዝሁ፥ ሲዖል ተገኘን፡፡

በጠባብ መተላለፊያ መሄድ ጀመርን፡፡ ማለፊያው ጠባብ ከመሆኑ የተነሳ በሩዝ እርሻ መሀል በተሠራ መደብ ላይ የማልፍ ነው የመሰለኝ፡፡ ከሁለቱም የመተላለፊያው ግራና ቀኝ፥ ወደታች መጨረሻውን ማየት አልቻልሁም፡፡ ገደሉ ጥልቀቱ መጨረሻ የለውም፡፡ ሚዛኔን ስቼ ቢሆን፥ ከመንገዱ እወድቅ ነበር፡፡ የጬኸትና የሰቆቃ ድምጽ ከታች ሲያስተጋባ ይሰማኛል፡፡ የሚጮኹት ሰዎች በብዙ ስቃይ ያሉ ይመስላል፡፡ አየሩን የሞላው ክርፋት የማይቋቋሙት ነው፡፡ የበሰበሱ ሬሳዎችና የሚቃጠል ሥጋ ይሸተኛል፡፡ ጥቁር ጭስ ሳያቋርጥ ወደ ላይ ይወጣል፡፡ ሚዛኔን መጠበቅ ለእኔ በጣም አስቸጋሪ ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ ፊትለፊት ራሱ የቱ እንደሆነ መለየት አልቻልሁም፡፡

አንድ ጊዜ በሲዖል ሳለን ከ**ጌታ** ጋር መለያየት አጋጥሞኝ ነበር፡፡ እናም አሁን ይህ እንዳይፈጠር ፈርቻለሁ፡፡ እጁን አጥብቄ ለመያዝ ወሰንሁ፡፡ ወደ ውስጥ ይበልጡን መሄድ ቀጠልን፡፡ ጠባቡ መተላለፊያ የባሰ እየጠበበ መጣ፡፡ በቀጭኑ መንገድ ሚዛኔን ለመጠበቅ ስጣጣር፥ የ**ጌታ**ን እጅ መልቀቅ ነበረብኝ፡፡ **ጌታ** ወደ ፊት መሄዱን ቀጥሏል እናም እኔ የልብሱን ጫፍ ይዤ ከኋላ ከኋለው እከተላለሁ፡፡ ከሁለቱም የመንገዱ አቅጣጫ፥ የማያቋርጥ ጩኸት ይሰማኛል፥ *"እርዱኝ! አድኑኝ! ያቃጥላል! እባካችሁ እርዱኝ!"* በሚሊየን የሚቆጠሩ ድምጾች እንደሚጮሁ ከታች ድምጾቹ ያስተጋባሉ፡፡ ጩኸቶቹ ኃይለኛና ብዙ ነበሩ፥ ጆሮዬ ላይ የሚጮሁ ዓይነት ነበር የተሰማኝ፡፡

የሆነ ሰው ከኋላ እንደሚከተለን ተሰማኝ፡፡ እንዲሁም የሆነ ሰው ልብሴን ሲይዘው ተሰማኝ፡፡ ከዛም፥ በዙሪያችን ሰዎች እንዳሉ ተሰማኝ፡፡ በቅጽበት  መረበሽና ፍርሀት ያዘኝ፡፡ ራሴን አዘጋጀሁና ድፍረቴን ለመጨመር ሞከርሁኝ፥ በሀሳቤ፥ "***ኢየሱስ**ን ብቻ ተመልከች፡፡ ስለ**ጌታ** ብቻ አስቢ፡፡ ዝም ብለሽ ወደ ፊት ተራመጅ፡፡"* እያሰብሁ ሳለ፥ በጣም የፈራሁት ነገር ተከሰተ፤ **ጌታ** ተሰወረ፡፡ መላው ሲዖል ጨለማ ነው እናም ለማየት ፈጽሞ አስቸጋሪ ነው፡፡ ሆኖም ግን፥ የብርሃን ጭላንጭል ማየት ይቻለኝ ነበር፥ ነገር ግን ለአፍታ ብቻ ነው፡፡

ብርሃኑን በድጋሚ ሳየው፥ ከመሰወሩ በፊት **ጌታ** እንደነበር ተረዳሁ፡፡ ከአሁን በኋላ በዙሪያዬ በየትም በኩል አይታየኝም፡፡ *"አ፥ ምን ማድረግ ይሻለኛል? እንዴት **ኢየሱስ**ን በሲዖል አጣዋለሁ? **ጌታ** ግን ርኅራኄ የለውም፡፡ የት ሊሆን ይችላል? እንዴት ሙሉ በሙሉ ብቻዬን ይተወኛል?"* ብዬ አሰብሁ፡፡ ተስፋ ማጣት ተሰማኝ፡፡ "***ኢየሱስ**፥ ወዴት ነህ? እባክህ ተመለሰህ ና! እርዳኝ! ተረብሻለሁ! **ጌታ** ሆይ!"* ጠራሁት ሆንም፥ **ጌታ** ፈጽሞ በአቅራቢያዬ አልነበረም፡፡ ምንም እንኳ ወደ ፊት ለመሄድ ባስብም፥ ከጨለማው የተነሳ ተሳነኝ፡፡

ሌላ ርምጃ መራመድ አቅቶኝ ደንዝዤ ቆምሁ፡፡ ምንም እቅድ የለኝም እናም ግራ ተጋባሁ፡፡ በድንገት፥ የሆነ ነገር በእግሬ ላይ ሲጠመጠም ተሰማኝ፡፡ በእግሬ ላይ የተጠመጠመው ምን እንደሆነ ስረዳ፥ በድንጋጤ ለጥቂት ራሴን ስቼ ነበር፡፡ አራት ጥቋቁር እባቦች እግሮቼን አጣብቀው እየተጠመጠሙ ወደ ላይ ይወጡ ነበር፡፡ ከ**ኢየሱስ** ጋር በነበርሁ ጊዜ፥ እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ፈጽሞ አልተከሰተም፥ ሆኖም ግን ልክ **ጌታ**ን እንዳጣሁ፥ እባቦቹ በላዩ እየተጠመጠሙ ነበር፡፡

ወዲያው ቀልቤን ሰበሰብኩና *"እንዴት ብትንቁኝ በላዩ ትጠመጠማላችሁ?"* ብዬ ጮኽኩ፡፡ እባቦቹ ላይ እየጮህኩባቸው፥ ይዤ አርቄ ወረውራቸው ነበር፡፡ በጨለማው ውስጥ ወደ ፊት መሄድ ጀመርሁ፡፡ በእግሬና በእጄ እየዳሰስሁ ቀስ ብዬ ሄድሁኝ፡፡ በጣም እየተንቀራፈፍሁ ስለሆነ የምሄደው፥ እባቦቹ ደረሱብኝ፡፡ እንደደረሱብኝ፥ በሰውነቴ ላይ መጠምጠም ጀመሩ፡፡ እንደገና ይዤ ወረወርኳቸው፡፡ ወደ ፊት መሄዴን ቀጠልሁ እናም እባቦቹ እንደገና ደረሱብኝ፡፡ አሁንም ወረወርኳቸው፡፡ የሆነ ቅዠት ውስት ተመሳሳይ ታሪክን እየደጋገምሁ ነው የመሰለኝ፡፡ የሚገርመው ነገር ይህ ነው እባቦቹ አልነደፉኝም፡፡ በጣም ረዥም ወይም ትልቅ አልነበሩም፡፡ መካከለኛ መጠን ያለቸውና የተለያየ ቀለም ነበራቸው፡፡

ለተወሰነ ጊዜ ከእባቦቹ ጋር ከታገልሁ በኋላ፥ ወደ ፊት ለመሄድ ቻልሁ፡፡ በመጨረሻ በአጥንቶችና የራስ ቅሎች የተሞላ ቦታ ደረስሁ፡፡ አጥንቶቹና የራስ ቅሎቹ እንደተራራ ተከምረዋል እናም ህይወት ነበራቸው እንዲሁም ይንቀሳቀሳሉ፡፡ የሆነ ሰው የቀሚሴን ጫፍ ሲይዘኝ ተሰማኝ፡፡ ማን ወይም ምን ልብሴን እንደያዘ ለማየት ዞር አልኩ፡፡ አንድ የራስ ቅል ቀሚሴን ነክሶት ነበር እናም ልመነጭቀው ስሞክር ታገለኝ፡፡ አጽሙ ምንም እጅ የለውም፥ ሆኖም ግን የልብሴን ጫፍ በጥርሱ ይዞታል፡፡ ያናግረኝም ጀመር፥ *"እባክሽ እኔንም ውሰጂኝ! እባክሽ!"* በዚያ ቅጽበት፥ ቤተሰቦቼን አስታወስሁ፥ በስቃይ የነበሩት

ታናሽ ወንድሜ፣ የወንድሜ ልጅ፣ እናም የአማቼ ልጅ፡፡ ስለቤተሰቤ ሳስብ፥ በጣም ተናደድሁና ሳላውቀው ጸያፍ ቃላትን ተናገርሁ፡፡

*"አሁን ራሴን እንኳ መቆጣጠር አልቻልኩም፡፡ እንዴት ቀሚሴን ትይዘኛለህ! መውጫ መንገድ በመፈለግ ተጠምጃለሁ እናም እቸኩላለሁ! የተረገመ! ከመንገዴ ዞር በል! ልብሴን ልቀቀኝ!"* እየጮኽኩ፥ አጽሙን መታሁትና ደቀቀ፡፡ በዚህ ጊዜ፥ የአጥንት እጅ የቀሚሴን ጫፍ ይዞ ተጣበቀ፡፡ ላራግፈው ሞከርሁኝ፥ ሆኖም ታገለኝ፡፡ ብዙ አጥንቶችና የራስ ቅሎችን መታገል ነበረብኝ፥ ሁሉንም ላሸንፋቸው አልቻልም፡፡ ጮክ ብዬ፥ *"እናንተ አስቀያሚ አጥንቶች! ሰውነቴ በቅዱስ እሳት ይንበለበላል እናም **አምላኬ ሥላሴ** በውስጤ ይኖራል፡፡ በነካችሁኝ ቅጽበት፥ ተቃጥላችሁ ትቢያና አመድ ነው የምትሆኑት! ልትነኩኝ ከተገዳደራችሁ፥ በሉ ንኩኝ!"* አልኳቸው፡፡ ከዛ በኋላ አጥንቶቹና የራስ ቅሎቹ አልቀረቡኝም፡፡ ወደ እኔ የተጠጉት አመድ ሆኑ፡፡ አጥንቶቹ እኔን ማሰቸገር እንዳቆሙ፥ ያለምንም መሰናክል ወደ ፊት መሄድ ቻልኩ፡፡

በፊት **ኢየሱስ** ከእኔጋር እያለ፥ በሲዖል መጓዝ ቀላል ነበር፡፡ **ጌታ** ብርሃን ነው ስለዚህ ብርሃንን ይሰጣል፡፡ ያለ **እርሱ** መሄድ በጣም አስቸጋሪና ግራ የሚያጋባ ነው፡፡ እየተደናበሩ ወደ ፊት መሄድ አድካሚ ነው፡፡ ከጨለማው ጋር እየተከራከርሁ ለመሄድ የአዕምሮዬን ጥንካሬ እጠቀም ነበር፡፡ በጣም ተዳከሜና ሳላስብ ቁጭ አልኩ፡፡ ከልብሴ ጋር ተያይዘው የነበሩት ክንፎች ተጎድተዋል፡፡ የከፋ ሆኗል እናም አሁን መብረር እንኳ አልችልም፡፡

ሀሳቤን ሰብስቤ ብርታቴን አገኘሁ፡፡ ወደ ፊት ሄድሁ፥ በዳዴ ሄድኩ፡፡ በጣም ከመሰላቸቴ የተነሳ እንቅልፍ ሊወስደኝ ነበር፡፡ ለአፍታ ያህል ራሴን ሳትኩ እናም ስነቃ ራሴን በእስር ክፍል ውስጥ አገኘሁት፡፡ የእስር ክፍሉ ጭራሮአማና ለአንድ ሰው ብቻ የሚበቃ ነው፡፡ አሁንም በጣም ጨለማና ምንም ማየት አልችልም፡፡ ከዚህ የባሰ አይመጣም ብዬ ሳስብ፥ የሆነ ፍጥረት ሰውነቴንና ጸጉሬን ሲጎትት ተሰማኝ፡፡ የሆነ አስጠሊታ አሰቃቂ ድምጽ እያሰማ ነበር፡፡ በንዴት በግኜ፥ ጸያፍ ቃላት በድጋሚ ከአፌ መውጣት ጀመረ፡፡ መውጫ ቀዳዳ መፈለግ ጀመርሁ፥ ሆኖም ተስፋ የሌለው ነበር፡፡ ልፋቴ በከንቱ ነበር፡፡ ባለሁበት ሁኔታ ስታገል፥ ከሁሉም አቅጣጫ ብዙ እጆች ሲጎትቱኝና ሰውነቴን ሲያናውጡት ተሰማኝ፡፡ ላሸንፋቸው አልቻልሁም ስለዚህ በንግግሬ በጣም ስድብን አበዛሁ፡፡

*"የሁላችሁንም እጅ ነው የምሰባብረው! እጃችሁን አትሰበስቡም? የጽድቅ ህይወት ኖራችሁ ቢሆን ኖሮ፥ በዚህ ባልሆናችሁ ነበር፡፡ ሁላችሁም አትረቡም!"* እንደገናም *"እኔ የሲዖልን ንጉስ፥ ሰይጣንን፥ ላሸንፈው ነው እዚህ የመጣሁት፥ የዚህ ስፍራ ገዢ የሆነውን፡፡ ምንም ይሁን ምን የኢጋንንትን ንጉስ አሸንፈዋለሁ! በሰውነቴ ውስጥ፥ የሚንበለበለው የ**አምላኬ ሥላሴ** ቅዱስ እሳት በውስጤ አለኝ፡፡ ሰውነቴን ብትነኩ፥ ሁላችሁም ሟች ናችሁ! በ**ኢየሱስ** ደም ተሸፍኛለሁና የሚነካኝ ወይም ልብሴን የሚይዝ ቢኖር አመድና ትቢያ ነው የሚሆነው፡፡"* ስላቸው፥ ሁሉም በፍርሀት ወደ ኋላ አፈገፈጉ፡፡ በሰከንዶች ውስጥ፥ በስልጣን ሦስተኛ እርከን ላይ ያለው ሰይጣን ተገለጠ፡፡ ከዚህ በፊት ያገኘሁት መሰለኝ፡፡ ወደ ህምሳ ጭንቅላቶችና እግሮች ነበሩት፡፡ ጋኔሉ እግሬን ያዘና ልብሴን ገፈፈኝ፡፡ እራቁቴን ነበርሁ፡፡



በነንድጓድ ድምጽ ጮህኩ፡፡ *"በኢጋንንት ንጉስ ልብሴን ልትገፍ ተልከሀል፡፡ ከደፈርክ ሁሉንም ግፈፈው! ምንም ያህል ልብሴን ብትገፍ፥ ዓይኔን እንኳ አላርገበግብም፡፡ አልፈራችሁም፥ ኢጋንንት! በውስጤ የሚኖረው **አምላኬ ሥላሴ**ና የሚንበለበለው ቅዱሱ እሳት አለኝ፡፡ አልፈራችሁም! የፈለገ ልታስፈራሩኝ ብትሞክሩ፥ ኢታናውጹኝም፡፡ በእናንተ ላይ አንድ ነገር አለኝ፡፡ ቤተሰቦቼ በሲዖል እየተሰቃዩ በመሆናቸው እውነታ ልቤ ይታመማል፡፡ ቤተሰቦቼ ሊቀበሉት ስለሚገባቸው ስቃይ የኢጋንንት ንጉስ ተጠያቂ ነው፡፡ የፈለገ ቢሆን አገኘዋለሁ እናም ስለቤተሰቦቼ*

*እበቀለዋለሁ፡፡ አንተ እኔን ለመጋፈጥ በጣም ደካማ ነህ፥ እናንተ ጅሎች ከእኔ ዞር በሉ! የኢጋንንትን ንጉስ አምጡልኝ! ፍጠኑ! ከእኔ ተሰወሩ!"*

ጋኔሉ በንዴት መልሶ ጮኸ፥ "*ዛሬ ልትጋፈጭ የሚገባሽ እኔን ነው፡፡ ወንድሜ፥ ሰይጣን፥ ልብስሽን ስገፍና ዓይንሽን ጠንቁዬ ሳወጣም መስማት እንደሚፈልግ ነግሮኛል፡፡ ሥጋሽን ከአጥንትሽ እገፍፈዋለሁ፡፡ እንዲሁም ትሎቹ ሰውነትሽን እንዲበሳሱትና እንዲበሉት እንዳደርጋቸው ነግሮኛል፡፡ ዛሬ ምትን ትቀምሻለሽ! ሃሃሃሃ፥*" ሳቀ፡፡

እርሱ ካስፈራራኝ በኋላ፥ *"ምን? አንተ የማትረባ ጋኔል፥ እንደምኞትህ አድርግ! **ጌታ** በውስጤ ስለሚኖር፥ ሥጋዬን መግፈፍና ዓይኔን መጠንቆል ቢቻልህ እንኳ ምንም ህመም አይሰማኝም! ቅዱስ የሚነበለበለው እሳት በውስጤ ስላለ ብትጠነቀቅ ነው የሚሻልህ! አውቄሀለሁ፡፡ ብዙ ጊዜ ቤተክርስቲያናችን እየመጣህ አስቸግረኸናል፡፡ መጋቢ መጽሐፉን እንዳይጽፍ*

*አስቸግረሽዋል፥ አይደል? መልካም፥ እንደተመኘህ አድርግ!'* ብዬ መለስሁለት፡፡ ጋኔሉ ቢላውን አሳየኝ፡፡ ጥቁር ሰማያዊ የሚመስልና በጣም ስለታም ይመስላል፡፡ *ሥጋዬን እንደ አሳ መተልተል ጀመረ፡፡* ምንም ህመም ስላልተሰማኝ፥ ዓይኔን እንኳ አላርገበገብሁም፡፡ *"አ፥ ይህ በጣም የሚያነቃቃ ነው፡፡ በጣም ደስ ይላል፡፡ ከፈለግህ ሁሉንም ሥጋዬን ግፈፈው፡፡ **አምላኬ ሥላሴ** በውስጤ ስለሚጠብቀኝ አልፈራም፡፡ ጨመር አድርገህ ሥጋዬን ግፈፍ!'* በድፍረት ጋኔሉን አበሳጨሁት፡፡ **ሁሉንቻዩ አምላክ** እየጠበቀኝ ነበር እናም ኃይሉ በውስጤ ይሰማኛል፡፡

ዓይኔ ተጠንቁሎ ሲወጣ፥ ምንም ህመም አልተሰማኝም፡፡ የሆነ ሰው የበላኝን እያከከለኝ ነው የሚመስለው፡፡ ተነቃቃሁ፡፡ ምንም *ሥጋ* አልነበረኝም፤ አጽም ነበርሁ፡፡ ባለ ሀምሳ-ራሱ ጋኔል በባልዲ ሙሉ ትሎችን ይዞ መጣና በላዬ ላይ አፈሰሳቸው፡፡ ትሎቹ አጥንቶቼን መሰርሰርና መቅኔየን ሙብላት ጀመሩ፡፡ እንዲሁም የተዘለዘለውን ሥጋዬን ይበሉ ነበር፡፡

አጥንቴን ሲያግበሰብሱ፥ በ**እግዚአብሔር** ልዩ ጥበቃ ውስጥ ስለነበርሁ ምንም አልተሰማኝም፡፡ አጽንቼም በልሳን መጸለይ ጀመርሁ፡፡ እየጸለይሁ፥ አስፈሪውን አቋሜን አየሁት፡፡ የትሎች መንጋ በመላአጽሜ ላይ ነበሩ፡፡ ያ ምንም አልመሰለኝም ነበር፥ የጎዳኝ ነገር በስቃይ ውስጥ ያለችው የእናቴ ሀሳብ ነበር፡፡ ማልቀስ ጀመርሁ፡፡ ደረቅ አጽም የሆንኩ የማልረባ ኃጢአተኛ ነኝ፡፡ ምንም እንኳ ጋኔሉ ስቃይና መከራን ሊያበዛብኝ ቢሞክርም እንኳ ይጠብቀኝ ለነበረው ለ**ጌታ** ምስጋናን አቀረብሁ፡፡ የሰላም ጊዜዬ አጭር ነበረች፡፡ በድጋሚ፥ በስቃይ ውስጥ ከሚኖሩት ቤተሰቦቼ ሀሳብ የተነሳ በጣም ተናደድሁ፡፡ በአጋንንት ላይ ፍጹም ጥላቻ አደረብኝ፡፡

### *ሰይጣንን መጋፈጥ፥ የሲዖል ንጉስ

ቤተሰቦቼን ሳስብ፥ ደሜ ከአጥንቴ ተሚጦ እንዳለቀ ያህል ይሰማኛል፡፡ ሰይጣንን አግኝቼ በቤተሰቦቼ ፋንታ ስለስቃያቸው ልበቀለው ፈለግሁ፡፡ ቤተሰቦቼን እንዲያሰቃዩአቻው ለአጋንንት ትእዛዝ የሚሰጣቸው ሰይጣን ነው፡፡ ሆኖም ላገኘው ስላልቻልሁ፥ ትንፋሽ እስኪያጥረኝ ድረስ ተጨናነቅሁ፡፡ ስለዚህ ትኩረቱን ለማግኘት በሁሉም አቅጣጫ መሳደብ ጀመርሁ፡፡

የሲዖልን ንጉስ፥ ሰይጣንን አየሁት፥ በንዴት በገንሁ፡፡ በአጠቃላይ፥ ሰዎች አጋንንትን ወይም እርኩሳን መናፍስትን ሲያዩ፥ አልያም የሰይጣንን ድምጽ ሲሰሙ ተፈጥሯዊ ምላሻቸው መሸበር ወይም ግራ መጋባት ነው፡፡ ነገር ግን እኔ በጸሎት ሰዓት እርኩሳን መናፍስትን ስዋጋ ስለነበር፥ ፍርኃትን ለምጄዋለሁ፡፡ ባየሁት ጊዜ፥ ፈጽሞ ምንም አልመሰለኝም፥ የዓይኔ ሽፋን እንኳ አልተርገበገበም፡፡ በድንገት ጮህኩኝ፥ *"ስማ፥ አንተ የውሻ ቆሻሻው ነህ፥ ሰይጣን? የአጋንንት ንጉስ? አንተ @#%$#!'* (ጸያፍ ቃላት)

*አላቋረጥሁም፥* ነገር ግን መሳደቤን ቀጠልሁ፡፡ *"ቤተሰቦቼን በሲዖል ባለ መስቀል ላይ እየሰቀልካቸው ያለኸው አንተ ነህ፥ የምታሰቃያቸው፥ እናም ወደ እሳቱ የምትጥላቸው፡፡ አንተ ነህ ቤተሰቦቼን የምታሳርራቸው፥ በሚንተከተክ የዘይት ማሰሮ ውስጥ የምትከታቸው፥ አይደል? ይሄን ሁሉ መንገድ የመጣሁት አንተን እዚህ ለመገናኘት ነው፡፡ በሰላም አልመለስም! ሲዖልን ሳላገለባብጣት ከዚህ አልሄድም! ሰዎችን ከማሰቃየት የተሻለ የምትሠራው የለህም? ሰዎች እንዲሞቱና ወደ ሲዖል እንዲመጡ*

*አዲጋዎቹንና መጥፎ ገጠመኞችን እየፈጠርህ ያለኸው አንተ ነህ ብዙዎችን ወደ ሲዖል በመንተትህ ተጠያቂ ነህ! ከውሻ አትሻልም!'*

### *የሰይጣን ገጽታ

የሰይጣንን፥ የሲዖልን ንጉስ፥ ገጽታ ሳይ ይሄ የመጀመሪያዬ ነበር፡፡ የሰይጣን አቋም ከማስበው በላይ ነበር፡፡ **እግዚአብሔር አብ**ን ለመምሰል ነው የሚሞክረው፡፡ አካሉ በጣም ግዙፍ ነበር፡፡ ወደ ላይ ቀና ስል፥ መላ ቁመናውን ማየት አልቻልሁም፡፡ የሰይጣን ቁመቱ የሲዖል ጣሪያ ጋር ደርሷል፡፡ ስፋቱ በሁለቱም አቅጣጫ ከሲዖል ጥግ እስከ ጥግ ይደርሳል፡፡ የሰይጣን ዙፋኑም እንዲሁ ግዙፍ ነበር፥ እናም ከአዕምሮዬ በላይ ነበር፡፡



የሰይጣን ክንፎች የሌሊት ወፍ ክንፍ ነው የሚመስሉት እናም በዝግታ ነው የሚወዛወዙት፡፡ አንገቴን ወደ ኋላ ለጥጬ ሰይጣንን ለረዥም ጊዜ ተመለከትሁት፡፡ ነገር ግን አንገቴን ስላመመኝ ከፊቱ ለመተኛት ወሰንኩ፡፡ በጀርባዬ ስተኛ፥ መላ ሰውነቱን ለማየት ቻልኩ፡፡

ከፊለፊቱ ስተኛ፥ ሰይጣን ምንም ቃል አልተነፈሰም፥ ነገር ግን እኔ ላይ ከማፍጠጥ ውጪ። ሆን ብዬ ላበሳጨው ፈለግሁ፥ ስለዚህ መሳደብ ጀመርሁ።

*"ጋኔል፥ ምንድ ነው ይሄ አስቀያሚ ገጽታህ? እንደዚህ አስቀያሚ ሆነህ እንዴት እንደ ንጉስ እንደምትንቀሳቀስ ማሰብ አልቻልም። ዓይኖችህን ተመልከታቸው! እስከ አናትህ ድረስ ተሰንጥቀዋል። እኔን ተመልከተኝ! እዚህ ዘና ብዬ በጀርባዬ ተንጋልያለሁ።"* እርሱን ማንቋሸሼን ቀጠልሁ፥ ሆኖም ምንም አልጠቀመም። ምንም አልተንቀሳቀሰም፥ ዓይኑን እንኳ አላርገበገበም።

ሰይጣን ራሱን ወደ ተለያየ መልክ መቀያየር ይችላል፥ ሆኖም በፊቴ እንደ ትልቅና ሰፊ ነገር መቆሙን ቀጠለ። ሲያዩት ያቅለሸልሻል። በጣም አስቀያሚ ገጽታ አለው። ሰውነቱ ከሰው ጸጉር ጋር ይመሳሰላል። በሰውነቱ ላይ ጸጉር ታራርቆ ይገኛል። በጣም ወፍራም ነበር። መንቀሳቀስ የሚፈልግ አይመስልም። የኢጋንንት ንጉስ ምንም አይረበሽም፥ ስለዚህ በድጋሚ ልጮህበት ወሰንሁኝ።

"አንተ፥ እኔ ከአንተ በጣም ጠንካራ ነኝ! የማገለግለው **አምላክ ሥላሴ** ነው። እገዳደርሀለሁ!" በመጨረሻ፥ ሰይጣን ተናገረ፥ *"አንቺ ትንሽ ነገር እንዴት ብትደፍሪ እዚህ መጥተሽ ትጃጃያለሽ!"* እኔም አጸፋውን፥ *"ከዚህ በፊት መቼም አይተኸኝ አታውቅም! እንዴት በንቀት ትናገረኛለህ?"* ብዬ መለስሁለት። ይህ ዓይኑን በሰፊው ከፍቶ ከዓይኑ ቀይ የሚያበራ ኳስ እስኪወጣ ድረስ አበሳጨው።

ሰይጣን በእኔ ስቆ እንዲህ አለ፥ *"ስሚ፥ አንገትሽን አላመመሽም?"* ጮኽኩበት፥ *"ለምንድ ነው አንገቴን የሚያመኝ? ላሽንፍህ ነው የመጣሁት። አንገቴ ደህና ነው። @#%$#! አንተ በጣም ወፍራም ስለሆንክ መተኛት አንኳ አትችልም! የሆነ ነገር እንደሆንክ ታስባለህ? ሰውነትህ አስጠሊታና እንሽላሊት ነው የሚመስለው። ሰውነትህ ራሱ የተመጣጠነ አይደለም። ራስህን አታምኝ! ወደዚህ ውረድ!"*

ጮኽኩኝ፥ ነገር ግን በውስጤ፥ በልሳን እየጸለይኩና **አምላኬ ሥላሴ**ን ብርታት እንዲሰጠኝ እየጠየቅሁ ነበር። ከ**መንፈስ ቅዱስ** ቅዱሱን እሳት እየለመንኩኝ ነበር። ሰይጣንን በዘለፋ እየተናገርኩት ሳለ፥ ያሾፍብኝና ያንኮራፋብኝ ቀጠለ። አልተረታሁም። እርሱን ማበሳጨቴን ቀጠልሁ። *"ሰይጣን፥ ብላኝና ዋጠኝ! ብትበላኝ፥ ሆድህ ውስጥ ገብቼ ቤተሰቦቼን ከምታሰቃያቸው ብዙ እጥፍ ጊዜ ነው የማሰቃይህ። ውስጥህን መተልተል እችላለሁ! ምላስህን አፈናጥሬ አውጥቼ ነው የሲዖል እሳት ውስጥ የምከትልህ። ፍጠን! ና ወደ ታች!"* ሰይጣንም መልሶ፥ *"እኔ ለምን ወደ ታች እወርዳለሁ? አንቺ ወደ ላይ ነይ!"* በጣም ተናድጄ ነበርና ቁጣዬ ገነፈለ። ምንም እንኳ **ኢየሱስ**ን ባላየውም ወደ **እርሱ** (**ኢየሱስ**) መጸለይ ጀመርሁ።

*እህት ቤይክ፥ ቦንግ ንዮ ሰይጣንን ስታጠቃ

*"**ኢየሱስ** ሆይ፥ ላይህ አልችልም፥ ነገር ግን **አንተ** ሁል ጊዜ ከእኔ ጋር እንዳለህ አምናለሁ። **ኢየሱስ**፥ ሰይጣንን ልደበድበው እፈልጋለሁ። ሆኖም፥ ለእኔ በጣም ትልቅ ነው። ልደበድበው አልቻልኩም! እባክህ*

*ጭንቅላቱ ድረስ ወጥቼ እንዳጠቃው መሰላልን ስጠኝ!"* በ**ጌታ** ትእዛዝ፥ ሊቀ መላእክት ሚካኤል ከገነት ትልቅ ረዥም መሰላል ይዞ መጣ። መሰላሉ ትልቅ ከመሆኑ የተነሳ ከወለሉ እስከ ሲዖል ጣሪያ ይደርሳል።

በሊቀ መላእክት ሚካኤል እርዳታ፥ መሰላሉን በሰይጣን ላይ አስደገፍኩትና መሰላሉ ላይ መውጣት ጀመርን። በጣም ረዥምና አስፈሪ ነበር። ያለ ሊቀመላእክት ሚካኤል እርዳታ ወደ ጫፍ መውጣት ባልቻልኩ ነበር። እኛ በመሰላሉ ላይ ወደ ላይ ስንወጣ ሰይጣን ምንም አለመንቀሳቀሱ የሚገርም ነው። በመሰላሉ ጫፍ ስንደርስ፥ ከመሰላሉ ላይ ወደ ሰይጣን ትከሻ ላይ ዘለልሁ። በጥፍሬ ቆዳውን ቦጫጨኩት፥ ግን ምንም ለውጥ የለውም። ሰይጣን ምንም አልተንቀሳቀሰም። ትኩረትም አልሰጠኝ፥ ለእርሱ እንደምንም እንደሆንኩ ዓይነት። የሰይጣን ጀርባው እንደ አለት ጠንካራ ነበር። በጥፍሮቼ ተጠቅሜ ቆዳውን ለመቦጫጨር ምንም ብጣጣር፥ ጥቅም አልነበረውም። በመላው አቅሜ እየጮህኩ መቦጫጨሬን ቀጠልኩ። *"አንተ አስቀያሚ ጋኔል፥ እንካ ይሄንን!"* ለራሴ በልሳን ጸለይሁ፥ *"**አምላኬ ሥላሴ** እባክህ ብርታትን ስጠኝ! ኃይልን ስጠኝ!"* እል ነበር። ከዛም፥ መቧጨሬን ስቀጥል፥ በመጨረሻ ምልክት ለመፍጠር ቻልኩ።

በተቧጨረው በኩል አጥብቄ ሞነጨርኩት፥ ሆኖም የሰይጣን ቆዳ ጠጣር ነበርና በአንድ ግዜ ትንሽ ብቻ ነበር መቧጨር የቻልኩት። ለራሴ *"ይህ ለምን ከባድ ሆነ?"* ብዬ አሰብሁ።

በዚያ ቅጽበት፥ ጥበብ ወደ እኔ መጣና ወደ **መንፈስ ቅዱስ** ጮህኩ፥ *“**መንፈስ ቅዱስ**፥ አባክህ ቅዱሱን ሠይፍ ስጠኝ! አባክህ አሁን ስጠኝ!”* ስጸልይ ሳለ፥ ግዙፍ ወርቃማ ሠይፍ ወረደ:: ሠይፉ ወደ እኔ ሲቀርብ ያስኩትና የሰይጣንን ጀርባ ወጋሁት:: ደጋግሜ ጀርባውን ወጋጋሁት:: ያለኝን ኃይል ሁሉ ተጠቅሜ እንዳገኘሁ ጀርባውን ወጋጋሁት:: ጀርባውን ስገሸላልጠው የሥጋ ቁርጥራጮች ወደ መሬት መውደቅ ጀመሩ::



ቀጥዬ፥ ወደ ሰይጣን ጭንቅላት ላይ ወጣሁና ያለ ርኅራኄ አንዱን ዓይኑን ወጋሁት:: ሰይጣን በዓይኖቹ ውስጥ ሌሎች ዓይኖች አሉት:: ወደ ጀርባው እንደገና ተመለስኩና አንዱን ክንፉን ገንጥዬ ጣልሁት ከዙፋኑ ዘሎ ተነሳና በኃይል ጮኸ:: እኔም፥ *“ጋኔል፥ አፍህን ክፈት! ወደ ሆድህ ወርጄ እጨርስሀለሁ! አንጀትህን ዘነጣጥዬ አነድዳቸዋለሁ!”* ብዬ ጮህኩ::

ልክ ሰይጣንን በድጋሚ ላጠቃ ስል፥ ደማቅ ብርሃን ከላይ ፈሰሰና **ጌታ** ተገለጠ:: እንዲህ አለ፥ ***“ቦንግ ንዮ፥ ትልቅ ሥራ ነው የሠራሽው! አሁን፥ ነይ ውረጅ:: ለዛሬ ይበቃል:: አሁን እንሂድ::”*** ወዲያው **ጌታ**ን በመቃወም፥ *“**ጌታ** ሆይ፥ መሄድ አልፈልግም! ቁጣ እስካሁን ውስጤ እየነደደ ነው:: ተጨማሪ ሰዓት እፈልጋለሁ:: ቤተሰቦቼስ? በኢጋንንት እየተሰቃዩ ነው:: አሁን ልሄድ አልችልም! አሁን ከሄድኩ፥ ቤተሰቦቼ ያለርኅራኄ በድጋሚ ይሰቃያሉ:: ይህን እያወቅሁ እንዴት እሄዳለሁ? አሁን ልሄድ አልችልም?”* አልሁት::

**ጌታ**ም አለ፥ ***“ቦንግ ንዮ፥ ዛሬ ያደረግሽው ከበቂ በላይ ነው፤ ጥሩ ነው! ሌላ ሰው ቢሆን ኖሮ፥ በፍርሀት በደነዘዘ ነበር:: ሰይጣንን ይፈራውና አይገዳደረውም ነበር:: ነገር ግን አንቺ በድፍረት ስለጸለይሽ፥ ይህን የኢጋንንት ንጉስ እንድታጠቂው በውስጥሽ ነበርሁ:: እርግጠኛ ነኝ ትንፋሽ ጨርሰሻል:: እንሂድ:: ቦንግ ንዮ፥ የማይቆጠሩ ሰዎችን ሲዖልን እንዲጎበኙ አምጥቻቸዋለሁ፥ ነገር ግን ለማጥቃት የተገዳደረ ማንም አልነበረም፥ ሥጋውን መቦጫጨቅና ዓይኑን መጠንቆል! አንቺ ያልተለመድሽ ቅድስት ነሽ! አሁን ይበቃል:: እንሂድ! የኢጋንንት ንጉስ አሁን ተጎድቷል::”*** **ጌታ**ና እኔ በሊቀ መላእክት ሚካኤል አጃቢነት ወደ ገነት ተጓዝን::

*እህት ቤይክ፥ ቦንግ ንዮ በገነት ምንጭ ውኃዎች ገላዋን ታጠበች

በገነት ከሆንን በኋላ፥ ሰይጣን በቀሉን በቤተሰቦቼ ላይ ያደርጋል በሚል ሀሳብ ልቤ አስካሁን ከብዶብኛል:: *“እስከ መጨረሻው መዋጋት ነበረብኝ እናም ሰይጣንን ወደ ሲዖል እሳት መጣል ነበረብኝ:: ያኔ እርካታ ይሰማኝ ነበር::”* ብዬ አሰብሁ:: ገነት በጣም ውብ ናት፥ ከአዕምሮ በላይ:: **ጌታ** በወርቅ ወደ ተሠራ ረዥም ሰገነት ላይ አወጣኝ:: በሰገነቱ ውስጥ ኩልል ያለ የምንጭ ውኃ ይፈሳል:: ወደ ሰገነቱ ውስጥ አስገብቶ

ተንከባከበኝ:: ተከፍቼ ስለነበር በተደጋጋሚ ያቅፈኝና ያበረታታኝ ነበር:: **እርሱም**፥ ***“ቦንግ ንዮ፥ በህመም እንዳለሽ አውቃለሁ፥ ወደ ሲዖል ስትሄጂ በስቃይ እንዲሁም በፍርሀት:: ሆኖም፥ በገነት በመሆንሽ ሀሴት አይሰማሽም?”*** አለኝ:: እኔም መልሼ፥ “ልክ ነህ፥ **ጌታ** ሆይ” አልኩት::

**ጌታ**ም ቀጠለ፥ ***“ቦንግ ንዮ፥ ዛሬ የኢጋንንትን ንጉስ ስትዋጊ አቅምሽን ሳትጨርሺ አልቀረሽም:: በሊቀ መላእክት ሚካኤልና ገብርኤል እርዳታ ሂጂና ገላሽን ታጠቢ:: የሰይጣንን ገላ ስተቦጫጭሪና ስትቀዳድጂው፥ የሰውነቱ ፈሳሽ በሰውነትሽ ላይ ሆኗል:: በዚህ ሁኔታ ወደ ምድር ብትሄጂ፥ ሰውነትሽ ያብጥና ትሞቻለሽ:: መላእክቱ መርዙን ከገላሽ ላይ አጽድተው ንጹህ ያደርጉሻል::”*** ገላዬን እየታጠብኩ፥ ሌሎች መላእክት ክንፍ ያለው ለስላሳ ልብስ አዘጋጅተው ከዳር ይጠብቁኝ ነበር::

በመላእክቱ እርዳታ፥ እንደ ብርጭቆ በጠራው ውኃ ገላዬን ታጠብሁ:: ውኃው በሊቀ መላእክቱ ወገብ ድረስ ነው:: ሆኖም ግን፥ ለእኔ አንገቴ ድረስ ነው:: እንዲሁም እንደብርጭቆ በጠራው የምንጭ ውኃ ውስጥ ዋኘሁ:: ከምንጩ አጠገብ ወዳለው መልበሻ ክፍል ሄጄ ልብሴን ቀየርሁ:: መላእክቱ ወደ ደመናው እንድወጣ አገዙኝ:: በጣም ተዳክሜ ነበር:: ሊቀመላእክቱ ሌሎች መላእክት ወዳሉበት ቦታ ወሰዱኝ:: በገነት ሰማዮች ደመናት የተሠሩበት ትንሽ ቀዳዳ አለ:: የእውነት ድንቅና የሚያስደምም ነበር::

*የሚንበለበለው ቅዱሱ እሳት ሸለቆ

**ኢየሱስ** የሚንበለበለው ቅዱሱ እሳት ወደሚገኝበት ሸለቆ ወሰደኝ:: የምናየው ከርቀት ቢሆንም፥ ሙቀቱ ግን ይሰማኛል:: ሸለቆው ለብዙ ነፍሶች ከገደብ ውጭ ነው:: **ጌታ**ን ጠየቅሁት *“በሸለቆው አስገብተህ ቶሎ ታወጣኛለህ?”*

**ጌታ** ከዛ አብራራልኝ፥ *"ማንም ሰው ሸለቆው ውስጥ ቢገባ፥ ያ ሰው እስከመጨረሻው መሄድ አለበት፡፡ የእሳቱ ሸለቆ የማይቋቋሙት ሞቃት ነው፡፡ አስፈሪ ቦታ ነው፡፡ ማንም በገባበት መመለስ አይችልም! ምንም እንኳ ወደ ዋሻው እንድትገቢ ብፈልግም፥ የሰውነትሽ ብረታት ተዳክሟልና በዚህ ሰዓት ልትቋቋሚው አትችይም፡፡ ዋሻው አንድ ሰው በሚንበለበለው እሳት የሚጠመቅበት ነው፡፡ በመደበኛ ሁኔታ ማንም ሊቋቋመው አይችልም፡፡ አንድ ሰው ሙቀቱንና ወላፈኑን ለመቋቋም የሰውነት ኃይል ያስፈልገዋል፡፡"*

*"አንድ ሰው አንዴ ዋሻው ውስጥ ገብቶ በቅዱሱ እሳት ከተጠመቀ፥ የጌታን ሥራ በሚሠራበት ወቅት የእሳቱ ታላቅ ሥራ ይገለጥበታል፡፡ ሸለቆው በጣም ኃይለኛ ነው፡፡ አንድ ሰው ደካማ ልብ ሊኖረው አይገባም፡፡ ካልሆነ፥ ለልብ ድካም ይጋለጣል፡፡ ስለዚህ፥ ብዙ መጸለይና ለመበርታት ሰውነትሽን መንከባከብ ይኖርብሻል፡፡ ያኔ፥ ወደ በኋላ ላይ እንድትገቢ እፈቅድልሻለሁ፡፡ መጋቢ ኪም፥ ዮንግ ዱ መጽሐፎቹን እየጻፈ ስለሆነ፥ በመጀመሪያ እርሱን በእሳቱ ውስጥ አሳልፈውና በሚንበለበለው እሳት እንዲጠመቅ አደርገዋለሁ፡፡ ነገር ግን እርሱ ራሱ ከአቅም ውጭ ስለሆነ ሰውነቱ ሙሉ ሙሉ እንዳገገመ በሸለቆው ውስጥ አስገባዋለሁ፡፡ ቀጣዩ ሰው የምትሆነው ቅድስት ካንግ፥ ህዩን ጃ፡፡ አንቺ ሦስተኛዋ ሰው ትሆኛለሽ፡፡ መጋቢው የመጀመሪያው ይሆናል፡፡ አንቺና ካንግ፥ ህዩን ጃ በተመሳሳይ ጊዜ ይሆናል የምትገቡት፡፡ ራስ ወዳድ አትሁኚ፥ ነገር ግን እስከዚያ ሰዓት ድረስ በትእግስት ዝለቂ፡፡ ሁሉም የቤተክርስቲያኑ አባላት ከጸሎት የተነሳ ተዳክመዋል፡፡ እኔና መላእክቱ መናፍስት ነን ስለዚህ አይደክመንም፡፡ ለመንቀሳቀስ ለቀንና ለምሽት የተገዛን አይደለንም፡፡ ነገር ግን የእናንተ ሥጋዊ ሰውነታችሁ ለቁሳዊው ዓለምና ለገደቦች የተገዛ ነው፡፡ እነዚህን ሁሉ ለማሳለፍ መንፈስሽ አሁን ከሰውነትሽ ውጭ ነው፡፡ መንፈስሽ ተመልሶ ወደ ሰውነትሽ ሲገባ፥ የማይቋቋሙት ድካም ያገኝሻል፡፡"*

**ጌታ** በሚንበለበለው ቅዱሱ እሳት ዋሻ ካለፍኩ በኋላ፥ ከእሳቱ አዲስ ኃይልን እንደምቀዳጅ ነገረኝ፡፡ በዚህ አዲስ መረጃ፥ **ጌታ**ን በዋሻው ውስጥ እንድከተት ለመንኩት፡፡ ነገር ግን **ጌታ** የ**አብ** ፈቃድ እንደሚያስፈልገኝ ነገረኝ፡፡ ሰዓቱ ገና እንዳልሆነ ነገረኝ፡፡

ከመጓጓቴ የተነሳ፥ **ጌታ**ን "*ጌታ ሆይ፥ ዋሻው ረዥምና ፍጻሜ የሌለው እንደሚመስል ተናግረህ ነበር፡፡ ርዝመቱ ምን ያህል ነው?*" ብዬ ጠየቅሁት፡፡ **ጌታ** ይህንን በምድራዊ አገላለጽ ተረጎመልኝ፥ ከኢንኮን ከተማ እስከ ሶል ከተማ ይደርሳል፡፡ (27 ኪ.ሜ) አንድ ሰው ሲገባ፥ ብቻውን ገብቶ ብቻውን መውጣት

ይኖርበታል፡፡ አንድ ሰው ከገባ በኋላ፥ በገባበት መመለስ አይችልም፡፡ ወደ ፊት መሄድ ነው ያለበት፡፡ ከዛም **ጌታ** መላእክቱ ወደ ቤተክርስቲያን መልሰው እንዲያመጡኝ አዘዛቸው፡፡ በጣም ተዳክሜ ነበር፡፡ **ጌታ** ወደ ሌላ ጉዳይ ሄደ፡፡

500 መላእክት ያህል አጅበው ያመጡኝ ነው የሚመስለው፡፡ መላእክቱ እየሸኙኝ፥ በሚያጽናኑ ቃላት ያናግሩኝ ነበር፡፡ "*ቅድስት ቦንግ ንዮ፥ ሰይጣንን ባትፈጽሚው እንኳ፥ በሳስተሽ፥ ቀዳደሽ፥ በሠይፍ ወግተሸዋል፡፡ ታላቅ ሥራ ነው የሠራሽው! አሁን፥ ከኀዘንሽ ተጽናንተሽ ተደሰቺ!*" እርስ በእርሳችን ተሳስቀን ተሰነባበትን፡፡

# ==== ቀን 26 ====

(ማርቆስ 9፡23-24)

**ሊ ሀከ ሱንግ፡**

ልክ መጸለይ እንደጀመርሁ፥ ስምንት እግሮች ያሉት እርኩስ መንፈስ መጣ፡፡ ሊያጠቃኝ ወደ ፊት ተወነጨፈ፡፡ እርኩስ መንፈሱ፥ ቀለሙን እንደ እስስት ይለዋውጣል፡፡ ከአረንጓዴ ወደ ግራጫ፣ ወደ ቀይ፣ እናም ወደሌሎችም ይለዋውጣል፡፡ ወደ እኔ ሲወነጨፍ፥ አጸፋውን ለመስጠት እጆቼን አጠነከርሁ፡፡ በጣቶቼ ዓይኑን ልጠነቁለው ሞከርሁ፥ ነገር ግን እርኩስ መንፈሱ የአጸፋ ምላሼን ሲሸልት አፍንጫውን ወጋሁት፡፡

እርኩስ መንፈሱ እራሱን ወደ ዳይኖሰርነት ለወጠ፡፡ አንድ ትልቅ ዓይንና ብዙ ቀዳዳዎች በሰውነቱ ላይ ነበሩ፡፡ ዳይኖሰሩ ረዥም አስፈሪ ጭራ ነበረው፡፡ ወደ እኔ ቢያወናጭፈው በቅጽበት እንደምሞት አመንኩ፡፡ ዳይኖሰሩ በጣም አስፈሪ ነው የሚመስለው፡፡ እጆቼን ዘረጋሁና ጮኽኩኝ፥ "*ቅዱሱ እሳት!*" ከእጆቼ ውስጥ፥ የእሳት ኳስ ወደ ዳይኖሰሩ ተወረወረ፡፡ የእሳቱ ኳስ ዳይኖሰሩን መሬት ላይ ዘረረው፡፡ መሬት እንደወደቀ፥ ዳይኖሰሩ የአዞ ጥርሶቹን ሊያሳየኝ አጉረመረመ እናም ደምመጣጭ የውቃ ውስጥ ትሎች ከሰውነቱ ውስጥ ወጡ፡፡



*ሊ. ሀክ ሱንግ የገነትን ወይኖች በላ

**ኢየሱስ** ተገለጠና *"ሀክ ሱንግ፥ ገነትን እንጎብኝ"* ብሎ ጠየቀኝ፡፡ እኔም መልሼ፥ *"**ኢየሱስ** ሆይ፥ ዲያቆን ሺን ከእኛ ጋር መሄድ ትችላለች?"* ብዬ ጠየቅሁት፡፡ **ጌታ**ም በአንድ ጊዜ ለአንድ ሰው ብቻ ነው ለጉብኝት የምፈቅደው ብሎ መለሰልኝ፡፡ እኔም፥ *"እባክህ፥ መጀመሪያ ዲያቆን ሺንን ልትወስዳት ትችላለህ?"* **ጌታ** ጥያቄዬን ከለከለኝ፡፡ *"**የዲያቆን ሺን ጸሎቶች ገና ጠንካራ አይደሉም፡፡ አሁን አልወስዳትም፡፡**"* በመሆኑም፥ እኔና **ጌታ** ብቻ ገነትን ጎበኘን፡፡

በገነት ስንደርስ፥ **ጌታ** እንዲህ አለ፥ *"**ልጅ ሀክ ሱንግ፥ ገነትን እየጎበኘህ ስለሆነ፥ የሚጣፍጥ ነገር ልጋብዝህ እፈልጋለሁ፡፡**"* **ጌታ**ም ወይን የሚመስሉ ፍራፍሬዎችን አመጣልኝ፡፡ ፍራፍሬዎቹን ተቀብዬ በላኋቸው፡፡ ጣዕሙ ትንፋሽ የሳጥራል! ለእኔ የገነትን ፍራፍሬና በምድር ካሉት ፍራፍሬዎች ጋር ለማወዳደር አይቻለኝም፡፡

**ጌታ** ከ**አብ** ዙፋን ፊት አቀረበኝ፡፡ **አብ** በጣም ታላቅና ግዙፍ ነው፡፡ የሆነ ወንበር ነገር ላይ የተቀመጠ ይመስላል፡፡ ከላይ



ከሚፈነጥቀው ደማቅ ብርሃን የተነሳ፥ ወደ ላይ ለማየት አልቻልኩም፡፡ በድንገታዊ ቅጽበት **እግዚአብሔር አብ**ን ያየሁት መሰለኝ፡፡ **እግዚአብሔር አብ** በእርጥበታማ ደመና ወይም ጉም በሚመስል ተሸፍኗል፡፡ ሆኖም፥ የ**አብ**ን ፊት በጨረፍታ ለማየት ቻልኩ፡፡ ብዙ የተገለጡ መጽሐፍት የተዘረጉበት ጠረጴዛ በፊቱ ነበረው፡፡ ከመጻሕፍቱ ወርቃማ ቀለም ያንጸባርቃል፡፡ በ**እግዚብሔር አብ** ፊት እንደቆምኩ፥ መላእክት በቡድን ሆነው ወደ ገነት የብርጭቆ ባሕር ዘንድ ሊወስዱኝ መጡ፡፡ (ራዕይ 4:6) ለረዥም ሰዓት ከዋኘሁ በኋላ ወደ *'**የጌታ** ቤተክርስቲያን'* ተመለስሁ፡፡

*የ**ኢየሱስ** መላ ሰውነት በደም ተሸፍኖ

ወደ ቤተክርስቲያን ከተመለስኩ በኋላ፥ ወዲያው መጸለይ ጀመርሁ፡፡ በጸሎቴ ውስጥ፥ **ኢየሱስ** ሲሰቃይ የሚያሳይ እይታ በፊቴ ተገለጠ፡፡ በምስሉ ውስጥ፥ **ኢየሱስ** መስቀሉን ተሸክሞ እየሄደ ነበር፡፡ ሲሄድም፥ በጅራፍ ይገርፉት ነበር፡፡ **ጌታ** መስቀሉን በጀርባው እንደተሸከመ ዳገቱን መውጣቱን ቀጠለ፥ ነገር ግን በጣም ደክሞት ነበር፡፡



**ኢየሱስ** እኛ ከምናስበው በላይ ነው ተወግቶ፣ ቆስሎ የሞተው፡፡ **ኢየሱስ** ሲሰቃይ ማየቱ ከባድ ነበር፡፡ በጣም አለቀስሁ፡፡ **ጌታ**ም ቀረበና አጽናናኝ፡፡ እንባዬንም አበሰልኝ፡፡ *"**ሀክ ሱንግ፥ አታልቅስ፡፡**"* **ኢየሱስ** ከእኔ ከተሰወረ በኋላ፥ ብዙ እርኩሳን መናፍስት ተገለጡ፡፡ ሁሉንም እርኩሳን መናፍስት ተዋግቼና አሸንፌ ጸሎቴን ጨረስሁ፡፡

**ኪም ጁ ኢዩን፡** *በትንኞችና በትሎች የተሞሉት እርኩሳን መናፍስት

በጸሎቴ ጊዜ፥ ብዙ ዓይነት አስቀያሚ እርኩሳን መናፍስት ተገለጡ፡፡ አንደኛው እርኩስ መንፈስ በሁለቱም ዓይኖቹ ዳር ላይ ጥቁር ቡጉር አለበት፡፡ ነጭ ልብስን የለበሰ ወንድ ይመስላል፡፡ ዓይኖቹ እንደ እንቁራሪት ሆነው ወደ እኔ በኀሪጥ ይመለከታሉ፡፡ እርኩሱ መንፈስ ሐመርማ ቀለም ሲኖረው ግንባሩ የተጨማደደ ነው፡፡ በሽል ውስጥ ያለን ትል ነው ያስታወሰኝ፡፡ እጭና ትናንሽ የመቶ እግር ትሎች ከሰውነቱና ከፊቱ ይወጡ ነበር፡፡ ብዙ ትሎች በመላ ፊቱ ላይ ይርመሰመሳሉ፡፡

እርኩሱን መንፈስ ለመያዝ ፈለግሁ፥ ዘግናኝና ጸያፍ ገጽታው እንዳልነካው አገደኝ፡፡ አንገቱን አንቄ አንገጫገጭኩት፡፡ ቢሆንም፥ እርሱን እያንገጫገጭኩት እኔ ለጥቂት ራሴን ስቼ ነበር፡፡ *"ትሎች እጆቼ ላይ እየተጣበቁብኝ ነው!"* ጮኽኩኝ፡፡ እርኩሱን መንፈስ ወደ እህት ቤይክ ቦንግ ንዮ ወረወርኩት፡፡ እርኩሱ መንፈስ ወደ እርሷ ሲቀርብ ወደ አመድነት ተለወጠ፡፡ በቅጽበቱ እሳት ተሸፍና ነበር፡፡

ትንሽ ቆይቶ፥ ረዥም እባብ ወደ እኔ እየተሳበ መጣ፡፡ የሚያቅለሸልሸው ገጽታው በጭራው በኩል እንድይዘውና አስገደደኝ እናም ብዙ ጊዜ አሽከርክሬ ወደ ወ/ሮ ካንግ ህዩን ጃ አቅጣጫ ወረወርኩት፡፡ በመንፈስ እየደነሰች ነበር፡፡ እባቡ ወደ እርሷ እየተሳበ ሊነድፋት አፉን ከፈተ፥ ነገር ግን እባቡ አፉን እንደከፈተ፥ እሳት ከወ/ሮ ካንግ ህዩን ጃ ወደ እባቡ ተወነጨፈ፡፡

እባቡ ቶሎ ብሎ ወደ እህት ቤይከ ቦንግ ንዮ አቅጣጫውን ቀየረ። እንዳጋጣሚ፥ እርሷም በቅዱሱ እሳት ተሸፍና ነበር። ከዛም እባቡ አቅጣጫውን ቀየረና ወንድም ሀከ ሱንግን አጠቃ። ወደ ወንድም ሀከ ሱንግ እንደደረሰ፥ አጥብቆ በሰውነቱ ላይ ተጠመጠመ።

ከዚያ፥ በድንገት፥ ያልተገመተ ነገር ተከሰተ። እባቡ ማውራት ጀመረ፥ *"ይህ ከአንተ ጥንካሬ በላይ ነው ሀከ ሱንግ፥ አንተ አመጸኛ፥ መቼ ነው እንደዚህ ጠንካራ የሆንከው? በአንተ ላይ ለመጠምጠም አስቸጋሪ ሆኖብኛል።"* እየተበሳጨ፥ ቀጥሎ ወደ እህት ዮ ከዮንግ ሄደ፥ ነገር ግን የእባቡን ጭንቅላት ነክሳ ልትገነጥለው ሞከረች። እባቡ ወደ እኔ ተመልሶ መጣ። *"አንተ ዘግናኝ እርኩስ መንፈስ! ለምንድ ነው ማህበሩን እየደጋገምክ የምታውከው?"* ብዬ ጮኽኩኝ። እጄን እንደ ሠይፍ አድርጌ ለሁለት ቆረጥኩት። እባቡ ለሁለት ተሰንጥቆ ጮኸ። ይህ አጋጣሚ ታላቅ ነበር።

ቆዳውን ገፍፌ እንደ አትክልት ከታተፍኩት። ቁርጥራጩን በእንጨት አደረኩና በእሳት እጠብሰው ጀመር። እርኩሱ እባብ እየጮኸ ተሰወረ፥ *"ገላዬን፥ ገላዬን!"* እንዲሁም ዓይኑን በእንጨት በስቹ ጠበስኩት። የሚገርመው ነገር ይህ ነው፥ ቢላ ስፈልግ አጠገቤ ቢላ ይመጣል። እውነታው፥ ያሰብኩት ወይም የተመኘሁትን ሁሉ፥ **ጌታ** ሰጥቶኛል።

ያን ሁኔታ በኋላዬ ትቼ፥ ትኩረቴን ወደ ጸሎት መለስኩ። ሆኖም ግን፥ በጸሎቴ ጊዜ፥ ትንሽ ልጅ የሚመስል አስቀያሚ እርኩስ መንፈስ በድጋሚ ወደ እኔ መጣ። በዚህ ጊዜ፥ ጸጉሯ ፐርም እንደ ተቀባ ለስልሷል።

ዓይኗ ከሌሎቹ ቀናቶች በበለጠ ያንጸባርቃል። በራሳችን ላይ በርራ አለፈች። በጣም ተነቃቅቼ ስለነበር፥ ወደ **ጌታ** ተጣራሁ፥ *"**ኢየሱስ** ሆይ፥ ያቺ ርኩስ መንፈስ ተመልሳ መጥታለች! **ጌታ** ሆይ፥ እርዳኝ!"* ስጮህ፥ ልጅቷ ጮኸችብኝ፥ *"አ፥ ዝምበይ! በጣም እየረበሸሽ ነው! በሽተኛ ውሻ!"* ገሰጽኳት፥ *"ምን፥ እኔ ምንም ችግር የለብኝም! አንቺ ውሻ!"* በጸያፍ ቃላት ተናገርኩ።

እርኩሷ መንፈስ መልሳ፥ *"አ! ይህቺን አመጸኛ ተመልከቷት። ከእኔ የባሰ ጸያፍ ቃላትን እየተጠቀምሽ ነው።"* እጇቿን ወገቧ ላይ አድርጋ *"አንቺ፥ የምርሽን ነው? እንዴት እደዚህ ለማድረግ ተደፋፈርሽ?"* እርኩሷ መንፈስ በሁኔታዬ ግራ ተጋብታለች። ወደ እርሷ ሮጬ ጸጉሯን ያስኩና አሽከርክሬ ወደ ፒያኖው ወረወርኳት። በንዴት፥ *"ምን ስለሆነ? ለአንቺ እነደዚህ መሆን እችላለሁ!"* አልኳት። እርኩሷን መንፈስ ካሸነፍኳት በኋላ፥ **ኢየሱስ** እንዲህ እያለ ወደ እኔ መጣ፥ ***"ጠቃጠቆ፥ እንዴት ነሽ?"*** እኔም፥ *"**ኢየሱስ** ሆይ፥ አሁን ለምን ትመጣለህ? ምን ያህል እንደናፈቅኸኝ ታውቃለህ?"* ብዬ መለስሁለት። **ጌታ**ም አለ፥ ***"እሺ ጠቃጠቆ፥ ይቅርታ። ትንሽ አረፈድሁ? አሁን እዚህ ነኝ፥ ነይ እንጫወት።"*** **ጌታ** የሰውነቴን የተለያየ ቦታ በጣቱ ወጋ ወጋ አደረገኝ። ጸጉሬን እያሻሸ ሲንከባከበኝ፥ ጸጉሬ አንድ በአንድ ወደ ፊት መምጣት ጀመረ። ሲዳስስ እጅግ ደስ ይል ነበር።

**ኢየሱስ**ን በጣም ስለምወደው፥ ጭንቅላቴን በጉልበቶቹ ውስጥ እቀብር ነበር። ጭንቅላቴንና ፊቴን ጉልበቱ ላይ አሻሻቸዋለሁ። እንዲህ እያደረግሁ፥ በለሆሳስ፥ *"**ኢየሱስ** ሆይ፥ ጉልበቶችህ ለስላሳና ምቹ ናቸው፥ ካባህ እንዴት እንደዚህ እጅግ ሊለሰልስና ምቹ ሊሆን ቻለ? ሲነኩት ደስ ይላል።"* አልሁት። **ጌታ**ም መልሶ፥ ***"እንደዛ ነው? በሚቀጥለው ጊዜ ወደ ገነት ስትመጪ፥ እንደዚህ ዓይነት ልብስ እንደፈለግሽ መልበስ ትችያለሽ።"***

*ጄ ኢዩን የገነትን ፍሬ በላች

ዛሬ፥ **ኢየሱስ** ባዶ እጁን ሊጎበኘኝ አልመጣም። አንዳንድ ፍራፍሬዎችን ይዞልኝ መጥቷል። ሲሰጠኝ እንዲህ አለ፥ ***"ጠቃጠቆ፥ ሞክሪው።"*** እኔም *"**ኢየሱስ** ሆይ፥ ምንድ ነው?"* አልኩት። **እርሱ**ም መልሶ፥ ***"እነዚህ ቅዱሳን የሚበሏቸው የገነት ፍሬዎች ናቸው። ሞክሪው፤ ፍሬው በጣም ጣፋጭ ነው።"*** ትንሽ ቀመስኩና፥ *"ዋው! **ኢየሱስ** ምን ዓይነት ፍሬ ነው እንደዚህ ጣፈጭ ሊሆን የሚችለው? የእውነት በጣም ጣፋጭ ነው።"*

የሰማዩ ፍሬ የምድሩን አፕል ያክላል። ሆኖም፥ ቀለሙ፥ ነጭ እናም ፍሬው ጣፋጭና ኮምጠጥ ያለ ቃና ነበረው። ፍሬው ወደ አፌ ሲገባ፥ ለስለስ ብሎ ቀለጠ። በጣም ጣፋጭ ነበረ በመሆኑም ማንኛውንም ዓይነት ምድራዊ ፍሬ ላነጻጽርበት አልቻልኩም፥ የምድር ፍሬ እኔን አያረካኝም።

**ጌታ** ስበላ እያየኝ ፈገግ አለ። በአንድ ጊዜ ሁሉንም ፍሬዎቹ በላኋቸው። **ኢየሱስ**ም፥ ***"ጠቃጠቆ፥ በጣም ጣፋጭ አይደል? በየቀኑ ከገነት ፍራፍሬዎች እንዳመጣልሽ ትፈልጊያለሽ?"*** ብሎ ጠየቀኝ። ወዲያውኑ መልሼ፥ *"አዎ፥ እባክህ በየቀኑ አምጣልኝ! ለሁሉም የቤተክርስቲያኑ አባላትም ልታመጣላቸው ትችላለህ?"* አልኩት።

*የጁ ኢዩን የሲኦል ጉብኝት

**ጌታ** በድንገት ተገለጠና ምንም ቃል ሳይናገር ወደ ሲኦል ይዞኝ ሄደ፡፡ በሲኦል ስንደርስ፥ ረዥም ወንበር ያለበት ጨለማ ክፍል ውስጥ ቆምን፡፡ ወንበሩ በራስ ቅሎች ተጊጦና ረዥም ጸጉር ያለው ፍጥረት ተቀምጦበት ነበር፡፡ አስቀያሚ መልክ ያለው አጽም ነበር፥ ትናንሽ ዝንቦች በፊቱ ይርመሰመሳሉ፡፡ በደምብ በጥንቃቄ ስመለከት፥ በፊቱ ላይና በመላ ሰውነቱ ላይ የሚመላለሱት አባጨጓሬና ትሎች ነበሩ፥ ወንበሩን ሁሉ ሸፍነውታል፡፡



"***ጌታ** ሆይ፥ አስቀያሚ ነው!*" ብዬ ጮኽኩኝ፡፡ **ኢየሱስ**ም ስለታም መጥረቢያን ሰጠኝ፡፡ መጥረቢያውን በእጄ ያስኩና አጽም ወደሚመስለው ፍጥረት ተጠጋሁ፡፡ እርሱና ዝንቦቹ በእሳቱ ተበታተኑ፡፡ **ጌታ**

አጨበጨበና አበረታታኝ፡፡ "***ጠቃጠቆ፥ እምነትሽ በጣም ስላደገ፥ አሁን ሊጋንንቱን ማሸነፍ ችለሻል፡፡ ሁል ጊዜም እምነትሽ ይኑርሽ እንዲሁም ደፋር ሁኚ፡፡***" በድንገት፥ ወደ '**ጌታ** ቤተክርስቲያን' ተመለስሁኝ፡፡

በኋላ ላይ፥ ስጸልይ ሳለ፥ ሁለት እግሮች ያሉት እርኩስ መንፈስ መጣ፡፡ ወደ እኔ እየቀረበ፥ በረዥም ምላሱ እንደ እባብ ያደርግ ነበር፡፡ ምላሱን ያስኩና ፍጥረቱን ወደ ጥግ ወረወርኩት፡፡ ከግድግዳው ጋር ሲጋጭ፥ በህመም ጮኸ፥ "*አውች! ያማል!*" ካገገመ በኋላ፥ በእግሩ ዘሎ ቆመና ወደ ወንድም ዮሴፍ ሄደ፡፡

"*አ፥ እንዴት ይጣፍጣል! በጣም ጣፋጭ ነው!*" እያለ በአስቀያሚ ምላሱ የዮሴፍን ፊት መላስ ጀመረ፥ ወንድም ዮሴፍ ምን እየተፈጠረ እንደሆነ እንኳ ያወቀ አይመስለኝም፡፡ ዮሴፍ በትጋት መጸለዩን ቀጠለ፡፡ በድንገት ጮኸ፥ "*የ**ኢየሱስ** ደም! የ**ኢየሱስ** ደም!*" በመንፈስ ገና ንቁ አልሆነም ነበር፥ ስለዚህም እርኩሳን መናፍስት ሲፈታተኑት ለማወቅ ለእርሱ ከባድ ነበር፡፡ የ**ጌታ**ን ደም መጥራት ሲጀምር፥ ደም ከአፉ መፍሰስ ጀመረ፡፡ ደሙ በቅጽበት የእርኩሱን መንፈስ ምላስ አቀለጠው እናም መንፈሱ ወደ ሐመር ሰማያዊ መልክ ተለወጠ እናም በጣም ፈራ፡፡ "*ይሄ ምን ዓይነት ደም ነው?*" ብሎ እየጮኸ ሸሸ፡፡

**ሊ ዮ ክዩንግ፡** *ዮ ክዩንግ በፍጥነት ከብዙ ዓይነት እርኩሳን መናፍስት ጋር ትዋጋ ነበር

በጸሎቴ መሐል፥ ሸለምጥማጥ የመሰለ እርኩስ መንፈስ መጣ፥ ምላሱን እንደ እባብ እየመዘዘ ወደ እኔ ቀረበ፡፡ ፈርቼ ነበርና በፍጥነት አንገቱን ያዝኩት፥ ወደ ወንድም ሀክ ሱንግ ወረወርኩት፡፡ ሀክ ሱንግ ይዞ አርቆ ወረወረው፥ ነገር ግን አገገመና ወደ እኔ ተመለሰ፡፡ ስለዚህ እንደገና ይዤ የባሰ አርቄ ወረወርኩት፥ ጮኬም፥ "*እርኩስ መንፈስ! በ**ኢየሱስ ክርስቶስ ስም**፥ ዞር በል!*" አልኩት፡፡ ወዲያውም ተሰወረ፡፡

ነገር ግን ሸለምጥማጡ እንደሄደ፥ አስቀያሚ ሴት ልጅ የመሰለ እርኩስ መንፈስ መጣ፡፡ ግማሽ ፊቷ ነጭ ነበር፥ ሌላኛው ግማሽ ደግሞ ጥቁር ነበር፡፡ በጥፍሮቿ ጥቁር ሰሌዳ እየቧጠጠች ልታበሳጨኝ ሞከረች፡፡ "*ይህን ድምጽ መስማት አልፈልግም! እርኩስ መንፈስ፥ በ**ኢየሱስ** ስም፥ ጥፊ!*" ብዬ ጮህኩ፡፡ ሆኖም ግን፥ አልተሰወረችም፥ ይልቁን የባሰ ልታበሳጨኝ ሞከረች፡፡ በጣም ስለተበሳጨሁባት ወደ እርሷ እሮጥኩና ጸጉሯን አፍሼ ይዤ ወደ መሬት ጣልኳት፡፡ መሬት ላይ እንደ ወደቀች፥ ተሰወረች፡፡

ወደ በኋላ፥ ስጸልይ ሳለ፥ ስለ **ኢየሱስ** እያሰብኩ ማልቀስ ጀመርሁ፡፡ ነገር ግን ዛሬ፥ በቶሎ አልመጣም እናም እርኩስ መንፈሷ ትንሽ ልጅ ተመልሳ መጣች፥ አሾፈችብኝ፥ "*ስሚ፥ ለምንድ የምታለቅሺው? **ኢየሱስ** ወደ አንቺ ስላልመጣ ነው የምታለቅሺው? በሽተኛ መስለሻል፡፡*" ማበሳጨቷን ቀጠለች፥ ስለዚህ፥ "*ልትደባደቢኝ ትፈልጊያለሽ?*" አልኳት፡፡ መልሳ ጮኸች፥ "*ነይ፥ የመጀመሪያውን ሰንዝሪ፥*" እናም እራሷን ወደ ደንዳና ሰውነትና አጭር ጸጉር ወዳለው ወንድ ለወጠች፡፡

"*የ**ኢየሱስ** ደም! የ**ኢየሱስ** ደም!*" እያልኩ ስጮህ፥ ሳቀብኝ፡፡ "*ምን? የ**ኢየሱስ** ደም? ቀጥይ፥ ደም!*" በጣም ተቆጣሁና **አምላኬ ሥላሴ**ን ደጋግሜ መጣራት ጀመርሁ፡፡ መንፈሱም እንዲህ አለኝ፥ "***ሥላሴ** ማነው? የት ነው **ሥላሴ**? ያን ስም አትጥሪ፡፡ ያስፈራኛል!*" ጮክ ባለ ደምጽ፥ "***አምላኬ ሥላሴ**፥ እርዳኝ!*" ብዬ ጮህኩ፡፡ መንፈሱም መልሶ ጮኸ፥ "*ያ ያስፈራኛል ብያለሁ፡፡ ያን ስም አትጥሪ! ልምንድነው ደጋግመሽ **እግዚአብሔርን** የምትጠሪው?*"



ወዲያው ፊቱ ተጨመዳደደ፡፡ ከየት እንደመጣ ሳይታወቅ የእሳት ኳስ መጣ፥ ጭራውንም መታው፡፡ እየጮኸ ወደ ፊትና ወደ ኋላ ሮጠ እናም በፍጥነት እግሩን ያዝኩት፥ አርቄም ወረወርኩት፡፡

ከአጭር ጊዜ በኋላ፥ የተሰፋ አንድ ዓይን ያለው እርኩስ መንፈስ መጣ። የትል መንጋ በስፌቱ አካባቢ ይርመሰመሳሉ። ወደ እኔ እየቀረበ ሲመጣ፥ በተደጋጋሚ እንዲህ ይል ነበር፥ *"ወደ ሲኦል ልጎትትሽ ያስፈልገኛል!"* ሆኖም ግን ወደዚያ ሊወስደኝ እንደማይችል ሲያውቅ ተከፋ። *"**አምላኬ ሥላሴ**! እርዳኝ!"* ብዬ ጮኽኩ። መጋቢ ወደሚጸልይበት ቦታ ሸሸ።

ወደ መጋቢ ሲቀርብ፥ ጮኾ፥ *"ይሄኛው ሁሌ ይጸልያል። አብዝተህ የምትጸልየው ለምንድ ነው?"* አለ። ወደ መጋቢው ሚስት ሄደና፥ *"ይህቺኛዋም ሁሌ ትጸልያለች። ስሚ፥ መጸለይ አቁሚ! ጥሩ አይደለም። አያስደስትም!"* አለ። ወደ እኔ መጣና አቋረጠኝ፥ *"አንቺ፥ ጸሎት መጥፎ ነገር ነው። አትጸልዪ!"* ተቆጣሁ፥ *"የምጸልየው እኔ ነኝ! እየደጋገምክ የምታቋርጠኝ ለምንድ ነው?"* እርኩሱ መንፈስ አሾፈብኝ፥ *"ምን ዓይነት ጸሎት ነው ይሄ? ይሄን ጸሎት ብለሽ ትጠሪዋለሽ? እንጫወት!"* ወደ እርሱ ሮጥኩ። ፊቱን እየነካሁ፥ *"የ**ኢየሱስ** ደም! የ**ኢየሱስ** ደም!"* ብዬ ጮኽኩ። እርኩሱ መንፈስ መለማመጥና መጉረምረም ጀመረ። *"ያቃጥላል! ልቀቂኝ! ልቀቂኝ! እባክሽ ልቀቂኝ!"* እርኩሱን መንፈስ ከእኔ አርቄ ወረወርሁት።

በራሱ ላይ ግዙፍ ቀንድና ትላልቅ ዓይኖችና ቀንዶች ያሉት እርኩስ መንፈስ መጣ። ጆሮዎቹን ገንጥዬ ጣልኳቸውና ዓይኑን ጠንቁዬ አወጣሁት። ቀንዱን ቆርጬ ጣልሁትና እግሩን ይዤ አሽከርክሬ ወረወርሁት። ሆኖም፥ እየደጋገመ እየመጣ ከእኔ አልለይ አለ። በመመላለሱ ተበሳጭቼ መሳደብ ጀመርሁ። በድንገት፥ የሆነ ሰው ካኔቴራዬን ሲጎትት ተሰማኝ። **ኢየሱስ** ነው ብዬ አሰብሁኝና፥ በደስታ፥ ወደ ኋላ ዞርኩ። ነገር ግን፥ **ኢየሱስ** አልነበረም። በጥቁር ጥላ የተመሰለ እርኩስ መንፈስ ነበር። ጥቁሩ ጥላ ካኔቴራ ይዞ ተጣበቀበት። *"በ**ኢየሱስ** ስም፥ ጥፋ!"* ብዬ ጮኽኩ። እርኩሱ መንፈስ አሾፈብኝ፥ *"አልሄድም! አልሄድም!"* ጮኽኩ፥ *"**አምላኬ ሥላሴ**! ቅዱሱ እሳት!"* የእሳት ኳስ መጣ ሰውነታቸውን በእሳት አጥለቀለቀው። ተበታተኑ።

የጸሎት ጊዜው ሊያልቅ ሲል፥ **ጌታ** መጣ። ወደ መጋቢ ሄደና ጸሎቱን አዳመጠ። **ጌታ**ም ጀርባውንና ሰውነቱን፥ በተለይ ደግሞ ህመም የሚሰማው ቦታ ላይ መታመታ አደረገው። **ጌታ** ከዛ በኋላ ወደ ሁሉም የቤተክርስቲያኑ አባላት እየሄደ እነርሱንም መታመታ አደረጋቸው።

*እህት ቤይክ ቦንግ ንዮ ሰይጣንን፥ የሲዖል ንጉስ፥ በድጋሚ አገኘችው

ስጸልይ ሳለ፥ ከባድ ጨለማ ሲመጣብኝ ተሰማኝ። ሆኖም ግን፥ በልሳን መጸለዬን ቀጠልሁ። ብርሃን እየተጥመዘመዘ ሲመጣ ማየት ጀመርኩ። መላእክት ከውስጡ መውጣት ጀመሩ። መላእክቱ መጥተው፥ **ጌታ** ቅድስት ቤይክ ቦንግ ንዮን ከ'የ**ጌታ** ቤተክርስቲያን' እንድናጅባት አዝዞናል አሉ። በህዋና በከዋክብት ክምችት ውስጥ አለፍን። **ኢየሱስ**ን እዛው እንዳለ አገኘሁት። ሁለታችንም በመተያየታችን እኩል ደስተኞች ነበርን። **ኢየሱስ** እጄን ይዞ፥ *"ቦንግ ንዮ፥ ሲዖልን እንጎብኝ!"* አለኝ። **ጌታ**ም ወደ ሲዖል ይመራ ነበር።

ልክ ሲዖል እንደደረስን፥ እናቴ ወዳለችበት ቦታ ሄድን። እኔ እንደምመጣ ማወቋን አላወቅሁም። እኔ መምጣቴን እንዳወቀች፥ ፊቷ ገረጣ እናም *"አ፥ ቦንግ ንዮ! ለምን እንደገና መጣሽ? በፍጥነት ይህን ስፍራ ለቀሽ ውጪ!"* ብላ ጮኸች። እኔም መልሼ፥ *"እማ፥ ተመልሼ የመጣሁት፥ ያንቺ ነገር ስላሳሰበኝ ነው። ሰይጣን ምን አልባት በቀሉን በአንቺ ላይ እንዳይወጣ ሰጋለሁ፥ ምክንያቱም ዓይኖቹን ያቆሰልኳቸው እኔ ነኝ። እንዲሁም ጀርባውን አቁስዬዋለሁም እንዲሁም ክንፎቹን ገንጥዬበታለሁ። ለዚህ ነው በድጋሚ ከ**ኢየሱስ** ጋር የመጣሁት።"* አልኋት። በእዛ የተገኘሁበትን ምክንያት ለእናቴ ካስረዳኋት በኋላ፥ *"ተማጸነች፥ እባክሽ አሁን ሰይጣንን አታበሳጪው። በቃ አሁን ሂጂ!"* እያወራን ሳለ፥ የሰይጣንን አስፈሪ ድምጽ ከሲዖል ሲያስተጋባ በድንገት ሰማሁት።

ሰይጣንም፥ *"አንቺን ለማየት ይህቺን ጊዜ በጉጉት ስጠባበቃት ነበር። ድጋሚ እንደምትመጪ አውቅ ነበር! ዛሬ፥ በጣም ልዩ የሆነ ነገር እንድትመለከቺ አደርጋለሁ። የቤተሰብሽን አባለት ሲሰቃዩ ታያለሽ።"* ብሎ ጮኸ። እርሱ በግዙፍ ወንበር ላይ ሲቀመጥ **ጌታ**ና እኔ ከሰይጣን ፊት ቆምን። የቤተሰቤ አባላት ቀድሞውኑ በሰልፍ ቆመው እየተጠባበቁ ነበር። ቤተሰቦቼ እዛ ቆመው፥ ልቤ በድንጋጤ ደነዘዘ። ምን እንደሚፈጠር ባለማወቅ፥ በስሜታዊነት ተንቀጠቀጥሁ። አዕምሮዬ መድከም ጀመረ።

ባለመረጋጋትና በፍርሀት መሀል ውስጥ እንኳ ሆና፥ እናቴ የሚያጽናኑ ቃላትን መናገር ትችል ነበር። *"ቦንግ ንዮ፥ እኛ በሲዖል ነን። ከረዥም ጊዜ በፊት ነው ተሰፋ የቆረጥነው። ከዚህ በኋላ ስለኛ አታስቢ። ለሰይጣን የምትይው ካለሽ፥ አሁን በይው፥ ሁሉንም ንገሪው።"* እኔ ያጠቃሁበትን የቆሰለውን ቦታ

በቅርበት ተመለከትሁት። የሰይጣን የተጎዳ ዓይኑ በጥቁር ነገር ተሸፍኖ ነበር። ሌላኛውን ዓይኑን ስመለከት፥ በቁጣ ነድዶ ነበር። ንዴቱ በጣም አስፈሪ ከመሆኑ የተነሳ እሳት ከእርሱ እየተወረወረ በፊቴ ይወድቅ ነበር። በመጨረሻ እኔን በማግኘቱ እርካታ እንደተሰማው አሳየ። በቀሉን ለመፈጸም ቆርጦ ነበር። ስሜቴን ሰብስቤ ራሴን ለውጊያ አዘጋጀሁ።

በድፍረት *"ሰይጣን፥ እኔ **አምላኬ ሥላሴ**ና የሚንበለበለው ቅዱሱ እሳት በውስጤ አሉኝ፡፡ ራስህን ቆርጬ ወደ ሲዖል እሳት ነው የምጥለው፦"* ብዬ አወጅኩ፡፡ ሰይጣን የእኔን ንግግር ከሰማ በኋላ፥ መልሶ *"እሺ፥ ጥሩ! መመለስሽን ጠብቄ ነበር፡፡ ሁሉም ነገር ለእኔ እቅድ እየሠራ ነው!"* አለኝ፡፡

*ሰይጣን እህት ቦንግ ንዮ ድሮ ታመልካቸው እንደነበሩት አስቀያሚ ጣኦታት ተመስሎ

በሰይጣን ፈጽሞ አልፈራሁም ነበር፡፡ እርሱን በመገዳደር በነጎድጓድ ድምጽ ጮኽኩበት፥ *"አንተ እርኩስ አውሬ፥ ማንነትህን ግለጥ! አንተ አስቀያሚ ጋኔል! ለምንድ ነው ብዙ ሰዎችን የምታሰቃየው? ወንድ ነህ ሴት? አንተ ግራ የገባህ ፍጥረት! አንተ አስቀያሚ ፍጥረት! ለምንድ ነው ማንነትህን የማትገልጠው? ከህመሜ እንዳገገምሁ፥ ትምህርት ልሰጥህ ነበር፡፡ ነገር ግን **ጌታ** እንዳላጠቃህ ጠየቀኝ፡፡ አንተን ከመሳደብ በቀር ሌላ አማራጭ የለኝም፡፡ አንድ ነገር ግን ቃል እገባልሀለሁ፤ ሙሉ በሙሉ ስድን፥ አንገትህን ነው የምቆርጠው! መላዋን ሲዖል ነው ማገለባብጣት፡፡ ራስህን ወደ ምን ዓይት አምሳያ ነው ለመለወጥ የምትሞክረው? ማንነትህን ግለጥ!"*

እየጮህኩ ሳለ፥ ፊቱ በድንገት ነጭ ሆነና ምትሀታዊ ወደ ሆነ ፍጥረት ተለወጠ፡፡ ወደ ተራራ ጠንቋይነት ተለወጠ፥ የተራሮች መንፈስ፡፡ ኮሪያውያን ሕዝቦች የተራራ መናፍስትን እንደ አምላክ ያመልካሉ፡፡

የምትሀቱን መልክ አወቅሁት፡፡ በተራራው ምትሀት መልክ፥ ስሜን በእርጋታ ጠራ፡፡ *"ቦንግ ንዮ፥ ላለፉት ጥቂት አመታት፥ በትህትና ስታመልኪኝና ስታገለግይኝ ነበር፡፡ ነገር ግን አሁን፥ እየተገዳደርሺኝና እያጠቃሺኝ ነው፡፡ ጭራሹኑም እየተሳደብሽ ነው፡፡?"* እንደ ተበደለ ሰውም በበትሩ መሬቱን መቆርቆር ጀመረ፡፡ ከብዙ ጊዜ በፊት ወዳገኘሁት የተራራ ምትሀት ራሱን ለወጠ፡፡ ሌሎች አማልክትን በማመልከበት ዘመን፥ ከእነርሱ ኃይልን ለመቀበል እሻ ነበር፡፡ ትልቅ ስልጣን ካለው አምላክ (ጣኦት) ኃይልን ፈለግሁ፡፡ በኮሪያ የሚገኙ ታላላቅ ተራሮችን እወጣ ነበር፡፡ ሰይጣን ከዚህ በፊት አግኝቼው ወደ ነበረ የተራራ ምትሀት ራሱን ለወጠ፡፡

ሰይጣን በሚያታልል ድምጸት ንግግሩን ቀጠለ፡፡ በድምጹ ውስጥ መርበትበትን አስተዋለሁ፥ ነገር ግን ለማታለል እንደሆነ ተረዳሁና በስድብ ቃል እናገረው ጀመር፡፡ *"አንተ አስቀያሚ ጋኔል! እንዳንተ ዓይነት አስቀያሚ አዛውንት መቼ ነው ያመለኩት?"* ሰይጣንም መልሶ ጠየቀ፥ *"ማንነቴን እንዴት አታውቂም? ቁመናዬን ተመለከች፡፡ በክብር ታገለግይኝ ነበር፥ አልነበረም?"* ከእርሱ ጋር ምንም ነገር እንዳልነበረኝ ማጽናቴን ቀጠልኩ፡፡ *"ሽማግሌው፥ አንተን ፈጽሞ አምልኬህም አገልግዬህም አላውቅም፡፡ በዚህ ቅጽበት ከእኔ ተሰወር! ባትሰወር ግን፥ በውስጤ በሚኖረው በ**አምላኬ ሥላሴ**፣ በቅዱሱ እሳት፣ እናም በ**ጌታ** ደም ኃይል ወደ አመድነት ነው የምለውጥህ! ስለዚህ አሁኑኑ ከእኔ ተሰወር!"* እስከመጨረሻው *"ግን እኮ አንቺ የምታገለግዪው ሽማግሌው ሰውዬ ነኝ!"* እያለ ድርቅ አለ፡፡

የባሰ ብስጩ ሆንኩኝ፥ *"አሁን ከመጣሁብህ፥ ሟች ነህ፡፡ አሁን ብትጠፋ ይሻልሀል!"* እል ነበር፡፡ ሽማግሌ መሳዩ የተራራ ምትሀት ወደ ሰይጣንነቱ ተመለሰ፡፡ ማንነቱን እንዲገልጥ ፈለግሁ እናም በኃይል ጮህኩ፥ *"ስለ ግዙፉ ሰውነትህ መፎከር ከንቱ ነው፡፡ ቁመትህ የሲዖል ጫፍ ቢደርስ እንኳ፥ አልፈራህም፡፡ ማንነትህን ግለጥ!"*

*"**አምላኬ ሥላሴ** በውስጤ ስለሚኖር፥ አንተ ምንም ነህ አታስፈራኝም፡፡ ፍጠን! እውነተኛ ማንነትህን ግለጥ!"* ወደ ሌላ ነገር እንደሚለወጥ አልጠበቅሁትም ነበር፥ ነገር ግን አደረገው፡፡ ረዥም ጸጉር ወዳላት ጥቁር ልብስ የለበሰች ግዙፍ ሴት ተለወጠ፡፡

ይህችም ሴትዮ አመልካት የነበረች ጣኦት ነበረች፡፡ በፊት፥ እያመለክሁ፥ በታዋቂ ተራራዎች ላይ ታላቅን ኃይል እፈልግ ነበር፡፡ ሙሉ በሙሉ ራሴን (ኃይልን ለመፈለግ) ከሰጠሁት በኋላ በመጨረሻ እርሷን አገኘሁ፡፡ በኃይል ጮህኩ፥ *"በመጨረሻ ራስሽን ገለጥሽ! ለምን አርፍደሽ ተገለጥሽ፥ አንቺ አስቀያሚ ፊት? አንቺ መሆንሽን አረጋግጫለሁ፡፡ ዓይንሽን ጠንቁዬ ሳላወጣው አሁን መሄድ ትችያለሽ!"* ሴትየዋ ተሰወረችና ሰይጣን መጣ፡፡

**ኢየሱስ** እጄን ያዘኝና ዞር አደረገኝ፡፡ *"ቦንግ ንዮ፥ ለዛሬ ይህ በቂ ነው፡፡ እንሂድ፡፡"* እየወጣሁ ሳለ፥ ሰይጣንን ተመለከትኩትና በኃይል ጮህኩበት፥ *"አንተ ጋኔል! **ጌታ** መልሶ እየወሰደኝ ስለሆነ አንተ ላይ ስቃይ ማሳደር አልቻልሁም፡፡ ነገር ግን ለሚቀጥለው ጊዜ ተዘጋጅተህ ብትጠብቀኝ ይሻልሀል፡፡ ራስህን ቆርጬ የሲዖል እሳት ውስጥ ነው የምጥለው! አጠፋሀለው! ብቻ ጠብቅ!"*

**ኢየሱስ** ሊያጽናናኝና ሊያበረታታኝ ወደ ገነት ወሰደኝ፡፡ ታላላቅ ብርሃን ወደሚታዩበት ተራራ ደረስን፡፡ በግራና በቀኝ ያሉት ተራሮች በወርቃማ ቀለም ያንጸባርቁ ነበር፡፡ ብርሃኑ ያሳውራል፡፡

በሁለቱ ተራሮች መሀል ክብ ቅርጽ ያለው ቀዳዳዎች ነበሩ፡፡ ቀዳዳዎቹ ነጫጭ ደመናና ጉም ያወጣሉ እናም ወደ ላይ ይወጣል፡፡ ውኃ የሚፈስበት ኩልል ያለ ኩሬም አየሁ፡፡ ከሚፈስሰው ኩሬ፥ **ኢየሱስ** ሦስት ሰዎችን ጠርቶ አዘዛቸው፥ ***"ቅድስት ቤይክ ቦንግ ሰውነቷ ደከም ስላለ፥ እዚህ ገላዋን እጠቧትና በደህና ወደ የጌታ ቤተክርስቲያን ውሰዷት፡፡"***

ወደ ቤተክርስቲያን እንደተመለስሁ፥ መጸለይ ጀመርሁ፡፡ ቤተሰቦቼ በምን ሁኔታ ውስጥ እንደሚያልፉ ሳስብ፥ በሰይጣን የሚደርስባቸው ህማምና ስቃይ ሀሳብ ከባድ ነበር፡፡ እኔ ራሴ ደግሞ በህመም እየተሰቃየሁ ነበር እናም ሰውነቴ ደካማና ታማሚ ነበር፡፡ በቤተክርስቲየኑ ወንበር ላይ ተቀመጥሁና ጸሎቴን ጨረስኩ፡፡

## ==== ቀን 27 ==== (ማርቆስ 11፡22-25) *እርኩሳን መናፍስቱ በዲያቆን ሺን ሱንግ ኪዩን ጆሮ ሲገቡ

ለሰዓታት በልሳን ስጸልይ፥ በጆሮዬ ውስጥ የማያቋርጥ ህመም ተሰማኝ፡፡ የሆነ ሰው እንደ እሾኽ ዓይነት ሹል ነገር ተጠቅሞ በተደጋጋሚ ጆሮዬን የሚወጋኝ ነው የሚመስለው፡፡ ህመሙን ችላ ብዬ ጸሎቴን ብቀጥልም፥ ህመሙ ግን የማይቋቋሙት ሆነብኝ፡፡ ከኋላዬ ይጸልይ የነበረውን ወንድም ሀክ ሱንግን ጠየቅሁት፥ *"ሀክ ሱንግ፥ በጆሮዎቼ ውስጥ ብዙ ህመም ይሰማኛል፡፡ እባክህ ልትመለከትልኝ ትችላለህ? ህመሙን የሚፈጥረው ምን እንደሆነ ለማየት አልቻልሁም፡፡"* ሀክ ሱንግ ጮኸ፥ *"ዲያቆን ሺን፥ አሁ፥ በሰማይ ያለህ **አምላኬ**! ትንሽዬ እርኩስ መንፈስ በጆሮሽ ውስጥ አለ እናም በሹል ነገር ጆሮሽን እየወጋሽ ነው! ምን ብናደርግ ይሻላል?"*

እርኩሱ መንፈስ እንዲወገድ ጸለይሁ ግን አልሄደም፡፡ ሀክ ሱንግም ጸለየልኝ፥ የሚወጋኝ ህመም ግን ቀጠለ፡፡ እኛ ልናወጣው ያደረግነው ሙከራ ስላልተሳካ፥ በኋላ ላይ በመሠዊያው (መድረኩ) ላይ ወዳለው ወደ መጋቢ ሄድን፡፡ መጋቢው በጸሎት ውስጥ ነበር፥ ነገር ግን አቋረጥሁትና በችኮላ፥ "መጋቢ፥ ብዙ ህመም እየተሰማኝ ነው፡፡ ጆሮዎቼ እየወጉኝ ነው፡፡ እባክህ እርኩሱን መንፈስ አስወጣው!" አልኩት፡፡ መጋቢውም ጮኸ፥ *"ሰይጣን፥ በ**ኢየሱስ ክርስቶስ** ስም አዝዝሀለው! ጥፋ!"* እርኩሱ መንፈስ ወዲያው ታዘዘና ተሰወረ፡፡ ከዚያች ቅጽበት በኋላ፥ በቀላሉ ጸሎቴን መቀጠል ቻልሁ፡፡ እንዲያውም፥ ሰውነቴ በ**መንፈስ ቅዱስ** እሳት ጋለ፡፡

**ኪም ጁ ኢዩን፡** *ሎተሪ ለማሸነፍ ልመና

ሁሉም እርኩሳን መናፍስት ከሄዱ በኋላ፥ **ኢየሱስ** ከመላእክቱ ጋር መጣ፡፡ መላእክቱ እጀታ ያላቸውን የወርቁን ጽዋዎች ይዘው መጥተው ነበር፡፡ መላእክቱ በትሕትና በጸሎት ላይ ከነበሩት የቤተክርስቲያኑ አባላት አጠገብ ተቀመጡ፡፡ መላእክቱ ሁሉንም የጸሎት ይዘቶች በወርቅ ጽዋዎቹ ውስጥ አደረጉ፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ፥ **ኢየሱስ** ወደ እኔ ቀረበና አናገረኝ፡፡ ***"ጠቃጠቆ፥ ተመልከችኝ፡፡"*** **ጌታ** የእሾኽ አክሊል አድርጓል፡፡



**ኢየሱስ** የሆነ ነገር በአፌ ውስጥ አስቀመጠ፡፡ ***"ጠቃጠቆ፥ ቅመሺው፡፡"*** ልክ እንደ እንጆሪ ጣዕም አለው፡፡ ፍሬው ጣፋጭና የሚቆመጥጥ ጣዕም አለው፡፡ በጣም ጣፋጭ ነበር፡፡ ሁሉንም ጨረስኩት፡፡

*"**ኢየሱስ** ሆይ፥ በጣም አመሰግናለሁ፡፡"* **ጌታ**ን ሳመሰግነው፥ ደስ ተሰኘ፡፡ **ጌታ** በጥሩ ስሜት ውስጥ ስለነበረ፥ ይህንን አጋጣሚ ተጠቅሜ ውለታ ልጠይቀው ወሰንሁ፡፡ *"**ኢየሱስ** ሆይ፥ ሁል ጊዜ በገንዘብ እየተቸገርን ነው፡፡ ሁላችንም ደሃ ነን፡፡ እባክህን ሎተሪ እንድናሸንፍ እርዳን!"* **ጌታ** ለጥቂት አፍታ ዝም አለና በሳቅ ፈነዳ፡፡ ተመለከተኝና ሳቀ፡፡ ተጨማሪም ውለታ ለመጠየቅ ወሰንሁ፡፡ *"**ኢየሱስ** ሆይ፥ በክፍሌ ውስጥ ትንሿ ልጅ እኔ ነኝ፡፡ እባክህ ረዥም ልታደርገኝ ትችላለህ?"* ስለሎተሪው የጠየኩትን አልመለሰልኝም፥ ነገር ግን ስለ ቁመት ለጠየቁት ጥያቄ ፈቃዱን ሰጠኝ፡፡

*ጁ ኢዩን የሲዖልን ንጉስ ስታጠቃ

**ኢየሱስ**፥ ***"ጠቃጠቆ፥ ሲዖልን እንጎብኝ፡፡"*** ብሎ ጠየቀኝ፡፡ የእኔን ምላሽ ሳይጠብቅ፥ ወደ ሲዖል ወሰደኝ፡፡ ወዲያው እንደ ደረስን፥ የእርኩሳን መናፍስት ሁሉ ንጉሥ በሆነው፥ በሰይጣን ፊት መቆማችንን አስተዋልሁ፡፡ እውነትም አስፈሪ ነበር፡፡ የሰይጣን ቁመናው በጣም ግዙፍ ነበር፡፡ አስቀያሚና ዘግናኝ ገጽታውን ሳይ የሰውነቴ ጸጉሮች ሁሉ ቆሙ፡፡ ለጥቂት አምልጦኝ የውስጥ ሱሪዬን አበስብሼው ነበር፡፡ ከፍርሀቴ ነቃሁና **ኢየሱስ** አጠገቤ እንዳለ አስታወስሁ፡፡ **ኢየሱስ** ይጠብቀኛል እናም ምቾትና መረጋጋት ተሰማኝ፡፡ የፍርኃትና የድንጋጤ ስሜት ጠፋ፡፡

እህት ቤይክ ቦንግ ንዮ ሰይጣንን እንዴት እንዳጠቃችውና ደካማ ጎኖቹ የት እንደሚገኙ ምስክርነትዋን አስታወስሁ፡፡ የቱ ጋር ላጠቃው እንደምችል ሙሉ መተማመን ነበረኝ፡፡ ወደ ሰይጣን ዓይኖች ስመለከት፥ አንዱ ዓይን ከዚህ በፊት እንደተወጋና ወደ ውስጥ እንደ ገባ ማየት እችል ነበር፡፡ የዓይኑን ኳስ ማየት አልቻልሁም፡፡ የተጎዳው ዓይኑ እህት ቤይክ ቦንግ ንዮ ካደረሰችበት ጥቃት የመጣ ነው፡፡ ሰይጣንን እየቃኘሁት፥ አንገቴን ህመም ተሰማኝ፡፡ ወደ ላይ ማየቴን ስቀጥል አንገቴ እየደረቀ መጣ፡፡ ሰይጣንም አንዴ ይቀመጣል አንዴ ከመቀመጫው ይነሳል፡፡ ለሆነ ምክንያት ይህን ደጋግሞ ያደርጋል፡፡ ጥርሱን በተደጋጋሚ እንደሚያፋጭና ክንፎቹም እንደተገነጣጠሉና እንደተጎዱ አስተዋልሁ፡፡

"*ኦ፥ እንዴት ያለ ውርደት! በጣም ተማርሬአለሁ፡፡ እያላችሁኝ ያላችሁት ምንም እንኳ ሠራዊቴን ወደ የ'**ጌታ** ቤተክርስቲያን' ብልካቸው፥ አባላቱ ሁሉንም አሸንፈዋቸዋል ነው? ይህ ለእናንተ ምንድ ነው? እናንተ ጅሎች፥ ለምንድ ነው በየቀኑ የምትሸነፉት? አሁን እናንተ የአውነት አገልጋዮቼ ናችሁ? አሁን ደግሞ ማንን ልላክ?*" ሰይጣን በንዴት ሲጮህ፥ ድንገት በጣም ተበሳጨሁና አጠቃው ጀመር፡፡

"*ዝም በል፥ ጋኔል! ስለ የ'**ጌታ** ቤተክርስቲያን' ምንድ ነው እያቀደህ ያለኸው?*" ጮኽኩኝ፡፡ በመጨረሻ ወደ እኔ ገላመጠና ጮክ ባለ ሰቅጣጭ ድምጽ፥ "*ራስሽን ማን እንደሆንሽ ታስቢያለሽ? እንዴት ነው የተደፋፈርሽኝ?*" **ኢየሱስ** አጠገቤ ስለነበር፥ ሰይጣንን በድፍረት ገሰጽሁት፡፡ "*ዝጋ፥ ጋኔል! ምንም እኮ ነህ! አንተ አመጸኛ እብድ!*" በእርሱ ላይ በስድብ መጮሄን ስቀጥል፥ ሰይጣን ተናደደና ተንቀጠቀጠ፡፡ ሆኖም ግን፥ ፈገግ አለና እኔ ምንም እንዳልሆንኩ አድርጎ ተመለከተኝ፡፡ "*አንቺ፥ ማነሽ አንቺ? አመጸኛ ጫጩት? ከየት ነው የመጣሽው?*"

ለማጥቃት ድፍረቱን ከየት እንዳገኘሁት አላውቅም፥ ወደ ሰይጣን ቀረብሁና በጀርባው በኩል ዞርኩ፡፡ እግሩን በእርግጫና በቦክስ መታሁት ግን ምንም አልመሰለውም፡፡ ይልቁንም፥ በእኔ ላይ በማሾፍና በመቀለድ ሊያበሳጨኝ ሞከረ፥ "*አህ፥ ያስቃል፡፡*" ይል ነበር፡፡ ጮኽኩኝ፥ "***ጌታ** ሆይ፥ ብርታትን ስጠኝ!*" በእግሩ ላይ ወደ ላይ ወጣሁና በመጨረሻ ትከሻው ላይ ደረስሁ፡፡ የሰይጣን ቆዳ ልክ እንደ ጦር ልብስ ጠንካራ ነው፡፡

ወደ ሰይጣን ትከሻ እየወጣሁ፥ እየተማጸንሁ ጮኽኩ፥ "***እግዚአብሔር** ሆይ፥ ብርታትን ስጠኝ! እባክህን የ**መንፈስ ቅዱስ**ን ሠይፍ ስጠኝ!*" **ጌታ** የ**መንፈስ ቅዱስ**ን ሠይፍ ሰጠኝ፡፡ ሠይፉ በእጄ እንደገባ፥ ክንዶቼና እጆቼ ደግሞ እንደጠነከሩ አስተዋልሁ፡፡ ጅማቶቼና



መገጣጠሚያዎቼ ጠንካራና ጽኑ ሆኑ፡፡ በተደጋጋሚ ያለ ርኅራኄ የሰይጣንን ጀርባ በሳሳሁት፡፡ ሰይጣን ተበሳጨና በንዴት በገነ፡፡ "*እየበሳሳሽኝ ነው! አውች! ያማል! አቁሚ!*"

ሰይጣን በወፍራም ደምጽ ጮኸ፥ "*እገድልሻለሁ! የ'**ጌታ** ቤተክርስቲያን' ምንም ሰላም አይኖራትም!*" **ኢየሱስ** አጨበጨበና አበረታታኝ፥ "***ጠቃጠቆ፥ ጥሩ እየሠራሽ ነው፡፡ ቀጥይበት!***" ሰይጣን እህት ቤይክ ቦንግ ንዮ ባደረሰችበት ጥቃት ምክንያት በተፈጠረበት ጉዳትና ቁስል በፊቱኑም ተማርሮ ነበር፡፡ የሰይጣን መዘናጋት በበፊት ቁስሉ ላይ እንዳጠቃው እድል ከፈተልኝ፡፡ ሰይጣን በስቃይ ጮኸ፡፡

ወደ ታች ወረድሁና በአጋንንት ንጉስ ፊት ወለሉ ላይ በጀርባዬ ተጋደምኩ፡፡ እህት ቤይክ ቦንግ ንዮ እንዳደረገችው አማርረው ጀመር፡፡ "*ዋው! በተሻለ ማየት እችላለሁ፡፡ አንተን በዚህ መልኩ መመልከት ለእኔ የበለጠ ምቾትን ይሰጠኛል፡፡*" ሰይጣን የባሰ እየተማረረና እየተበሳጨ ሲሄድ፥ ንዴቱን በታዛዦቹ ላይ መወጣት ጀመረ፡፡ "*እናንተ አመጸኞች! ምንድ ነው የምታዩት? እዛ አትገተሩ፤ በፍጥነት አጥቁ፡፡ አሁኑኑ!*" ብሎ ጮኸ፡፡ **ጌታ** ከፍ ባለ ድምጽ ተናገረ፥ "***ማንን ነው ለማጥቃት የምታስቡት? ያለ እኔ ፈቃድ እንዴት ደፍራችሁ ታጠቃላችሁ?***" **ኢየሱስ** ሲገስጻቸው፥ ሁሉም እርኩሳን መናፍስት አንገታቸውን አቀርቅረው በዝምታ ቆሙ፡፡ አንዲት ሊንቀሳቀሱ አልደፈሩም፡፡ ታግደው ነበር፡፡

በደስታ ሰይጣንን የበለጠ ማማረር ጀመርሁ፡፡ **ኢየሱስ** ከአጠገቤ ቆሞ ስለነበር፥ ሰይጣን ምንም ማድረግ በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ነበር፡፡ ወደ ሰይጣን ጀርባ እንደገና ተመልሼ ወደ አናቱ ወጣሁ፡፡ ጸጉሩን ሁሉ ነቀልሁና መላጣ አደረግሁት፡፡ በ**መንፈስ ቅዱስ** ሠይፍ፥ የተጎዳውን ክንፉን መቀዳደድ ጀመርሁ፡፡ በ**ኢየሱስ** ፊት፥ የአጋንንት ንጉስ ምንም አይደለም፡፡ ተደንቄ ሳለ፥ ሰይጣንን በድጋሚ ለማበሳጨት አሰብሁና በፊቱ ሄጄ እንደ ገና በጀርባዬ ተኛሁ፡፡ **ኢየሱስ** ያለማቋረጥ ሳቀ፡፡ **ጌታ** ቆሞ እንዲህ አለ፥ "***ጠቃጠቆ፥ የሚያዝናና ይመስላል፡፡ እኔም እንዳንቺ አጠገብሽ ልጋደም?***" ተነሣሁና እንዳያደርገው ወደ **ጌታ** አውለበለብሁ፡፡ "*በጭራሽ፥ **ጌታ** ሆይ፡፡ **አንተ ፍጹም ቅዱስ ነህ**፡፡ እንዴት ሆኖ እጅግ አስቀያሚ ፍጥረት ከሆነው ከሰይጣን ፊት ትተኛለህ! አይሆንም! ትርጉም አይሰጥም፡፡*" ሰይጣን በቁስሎቹ ምክንያት አብዝቶ እየደማ ነበር፡፡ የሰይጣን ደም ግራ የገባው ቀለም ነበረው፤ ላብራራው አልችለም፡፡ ሰይጣን በምቾት ማጣት እየተወራጨ በንዴት አስሬ ከወንበሩ

ላይ ቁጭ ብድግ ይላል፥ እናም እንደተለመደው በንዴት ጥርሱን ያፋጫል። ሰይጣንን ማበሳጨቴን እንደቀጠልሁ፥ **ኢየሱስ**፥ "*ጠቃጠቆ! ይበቃል። አሁን እንሂድ። ሰይጣን የበቃው ይመስለኛል። ሳይማር አልቀረም። ረፍዷል። መሄድ አለብን።*" አለኝ። **ጌታ** እጄን ይዞ ወደ ቤተክርስቲያን አደረሰኝ። ከዛም **ኢየሱስ** ወደ ቤት፥ ወደ ገነት ተመለሰ።

**ሊ ዩ ክዩንግ:** *በቅዱሱ ሠይፍ የእርኩሳን መናፍስትን አንገት መቆራረጥ

ስጸልይ ሳለ፥ **ኢየሱስ** መጣ። ከትላንት ወዲያ፥ ወንድም ሀክ ሱንግ በገነት የገነትን ፍሬ የመብላት እድሉን እንዳገኘ ነግሮኝ ነበር። **ጌታ**ም እነዚያኑ ዓይነት ፈሬዎችን አመጣልኝ፥ ወይንን ይመስሉ ነበር። "*ጠቃጠቆ፥ ይህን ፍሬ ቅመሺውና ስትዘምሪ መስማት እፈልጋለሁ።*" የገነት ፍሬዎቹ በጣም ጣፋጭ ከመሆናቸው የተነሣ መብላቴን ላቋርጥ አልቻልሁም። በተለምዶ መብላትን እወዳለሁ እናም በምግብ ሰዓት ብዙ ምግብ ነው የምበላው። ሆኖም ግን፥ **ኢየሱስ** ትንሽ ፍራፍሬዎችን ነበር ያመጣው።

ፍራፍሬዎቹን በልቼ እንደጨርስሁ፥ መዘመር ጀመርሁ፥ 'ነፍሴ ሆይ አወድሺ፣ በ**መንፈስ ቅዱስ** አጥምቅ' እና 'ተነሱና ዲያቢሎስን ተዋጉ።' እኔ እየዘመርሁ፥ **ኢየሱስ** ወደ ዲያቆን ሺን እና ዮሴፍ ሄደ። **ኢየሱስ** ከእኔ ጋር በሄደበት ቅጽበት፥ እርኩሳን መናፍስት በዝግታ ከክፍሉ ማዕዘን ወደ እኔ መቅረብ ጀመሩ። "***ኢየሱስ**! አባ! አባ!*" ወደ **ጌታ** ጮኽኩ እናም በፍጥነት መጣ።

"*ለምንድ ነው የጠራሺኝ?*" ብሎ ጠየቀኝ። ስመልስም፥ "***ጌታ** ሆይ፥ እርኩሳን መናፍስት ከዛ ጠርዝ መጡ።*" አልሁት። ልክ እጄን ወደ እርኩሳን መናፍስቱ አቅጣጫ ስጠቁም፥ ተሰወሩ። **ጌታ**ን ጠየቅሁት፥ "***ኢየሱስ** ሆይ፥ እባክህን ጁ ኢዩንን ይዤ ገነትን ለመጎብኘት መሄደ እችላለሁ?*" **ጌታ**ም መለሰ፥ "*አይሆንም፥ በአንድ ጊዜ ለአንድ ሰው ብቻ ነው የምፈቅደው።*" **ጌታ** ንግግሩን ቀጠለ። "*ዩ ክዩንግ፥ እርኩሱ መንፈስ ተመልሶ*

*ሲመጣ፥ አትፍሪ ምክንያቱም በእኔ ስም ልታባሪያቸው ስልጣን አለሽ። ከመሸሽ በስተቀር ምንም እድል የላቸውም። በእምነትሽ አድርጊው!*" እኔም "*አሜን!*" አልኩኝ።

ልክ **ኢየሱስ** እንደሄደ፥ ሌላ እርኩስ መንፈስ መጣ። "*የ**ኢየሱስ** ደም!*" ብዬ ጮኽኩ። እርኩሱ መንፈስ ተሰወረ። እየሸሸ ዛተብኝ፥ "*ይህች ዲቃላ የ**ኢየሱስ**ን ደም እየጠራች ታስፈራራኛለች። ወይኔ!*" ከዛ፥ ሌላ እርኩስ መንፈስ መጣ። ይሄኛው ትከሻዬ ላይ ወጥቶ ጭንቅላቴንና ትከሻዬን ይጫነኝ ጀመረ። መጸለይ ከበደኝ። "***አምላኬ ሥላሴ**፥ እርዳኝ!*" ብዬ ድምጼን ከፍ አድርጌ ጮኽኩ። እርኩሱም መንፈስ ጮኸ፥ "*አሳምሜ ወደ ሲኦል ነው የምወስድሽ!*" በዚያ ቅጽበት፥ **ኢየሱስ** ተገለጠና እርኩሱን መንፈስ አሳደደው።

መላእክቱም ደግሞ መጡና ደኅንነቴን ጠየቁኝ። **ኢየሱስ** አበረታታኝ፥ "*ቆንጆ፥ የእኔ ውድ ዩ ክዩንግ። እርኩሳን መናፍስትን እንዴት ማስወጣት እንዳለብሽ አውቀሻል። ቆንጆ ነው!*" **ጌታ** አሁንም ሄደ እና የተለያዩ እርኩሳን መናፍስት መጡ። በዚህ ጊዜ መጀመሪያ መጋቢውን ለማወክ ሞከሩ። "*አንተ ሁል ጊዜ በጸሎት ውስጥ ነህ፥ በየቀኑ! ስትጸልይ ምንድ ነው የምታገኘው? ማዕዶች? ምግብ? መጸለይህን አቁም! እስቲ እንጫወት!*" መጋቢው በሹፈታቸው አልተናወጠም። እርኩሳን መናፍስቱን ችላ ብሎ ጸሎቱን ቀጠለ። እርኩሳን መናፍስቱ ወደ እኔ ቀረቡና ጸሎቴን ለማወክ ሞከሩ። "***ጌታ** ሆይ፥ እባክህ የ**መንፈስ ቅዱስ**ን ሠይፍ ስጠኝ!*" ብዬ ጮኽኩ። ሠይፉ በእጄ እንዳለ አስተዋልሁ። ሰንዝሬ እርኩሱን መንፈስ ቀላሁት። በስቃይ ጮኸ፥ "*አህ! ጭንቅላቴ! አህ!*" ማወናጨፌን ቀጥዬ፥ እጁንና ሌሎች የሰውነቱን ክፍሎች ቆራረጥኩት። "*ሰውነቴ! እጆቼ! እግሮቼ!*" እየጮኸ ተሰወረ።

**እህት ቤይክ ቦንግ ንዮ:** *እርኩሳን መናፍስት በሙሉ ኃይላቸው የመልሶ ማጥቃት

በአገልግሎት መሐል፥ ሰውነቴን ማመም ጀመረኝ እናም በመላው ሰውነቴ የሚወጋ ህመም ሲንቀሳቀስ ተሰማኝ። ህመሙ የራሱ ህይወት ያለው ነው የሚመስለው። መጋቢው ስብከቱን አቁሞ ከመሰዊያው በችኮላ ወደ እኔ ሮጦ መጣና በእኔ ምን እየሆነ እንዳለ እንዲያዩ ወደ ጁ ኢዩንና ሌሎች በመንፈስ ወደ ነቁ የቤተክርስቲያኑ አባላት ጮኸ። ጁ ኢዩን ለተወሰነ ጊዜ ባለመጠንቀቁ እርኩሳን መናፍስቱ ወደ እኔ እንዲገቡ በር እንደ ከፈትሁላቸውና እድል እንደሰጠኋቸው ተናገረች። አንዴ አንዱ እርኩስ መንፈስ ከገባ በኋላ፥ ሌሎቹ እንዲገቡ በር ከፈተላቸው። ትላንት፥ ሲኦልን ስጎበኝ፥ የሰይጣንን ዓይን ወግቼው ነበርና ጀርባውንና ክንፉን ጎድቼው ነበር። ጁ ኢዩን ሰይጣን በጣም እንደተናደደና እርኩሳን መናፍስቱን በሙሉ ኃይል እንዲያጠቁ አዝዟቸው እንደነበር አስረዳች።

*"ኢጋንንት! እርኩሳን መናፍስት! በሙሉ ኃይል አጥቁ! ሁላችንም ወደ የጌታ ቤተክርስቲያን እንዝመትና ቤይክ ቦንግ ንዮን እናጥቃ!"* ብዙ እርኩሳን መናፍስት ሰውነቴ ውስጥ ገብተው በአንድ ላይ ክምር ፈጠሩ:: ከዚያ ተነስተው፥ ወደ መላ ሰውነቴ ተሰራጩ:: አንዳንዶቹ ቀንዳም ጭራቆችን ሲመስሉ፣ የተለያየ ቀለም አላቸው፥ አንዳንዶቹ የሚያብረቀርቅ ዓይንና ስለታም ጥርሶችና ጥፍሮች፥ ነጫጭ የለበሱ እባቦችን ይመስላሉ:: መላ ሰውነቴ በከባድ ህመም ውስጥ ነበር እናም መላ መገጣጠሚያዬን ሁሉ ጠምዝዘውት ነበር:: መጋቢው በፈተናው ወቅት በምን ውስጥ እንዳለፈ አሁን ተረዳሁ:: ለመጸለይና እስከመጨረሻው ጥቃታቸውን ለመቋቋም ሞከርሁ፥ ሆኖም ብዙ ሳይቆይ በፊቴ ወደ መሬት ወደቅሁ:: የጸሎት ቡድኑ ከአመሻሹ ጀምሮ እስከ ሊነጋጋ ፲፩ ሰዓት እስከሚሆን ድረስ በትጋት ጸለዩልኝ:: ቀጣይነት የነበረው ጸሎታቸው ሁሉንም እርኩሳን መናፍስት ከውስጤ አወጣቸው:: ከፈተናው በኋላ፥ ሁሉም ተዳክመው ነበር::

፲፩ ሰዓት ላይ፥ ሁላችንም መጸለይ እንችል ነበር:: የተወሰኑ የጸሎት ሰዓታት ስላሉኝ እድለኛነት ተሰማኝ:: እርኩሳን መናፍስቱ ያለ ርኅራኄ ሰውነቴን ሲያሰቃዩ ስለነበር በጠና ታመምሁ:: **ጌታን** በጠና ስለታመመው ሰውነቴ ጠየቅሁት:: እርኩሳን መናፍስት ከሰዎች ውስጥ ሲወጡ፥ ተጠቂዎቹ ላይ አካላዊ ጉዳት ይተዋሉ:: መጋቢው አሁንም ድረስ በትከሻውና በጀርባው ላይ ስላለ ህመም ለምን እንደሚያጉረመርም ገባኝ:: ይመስለኛል ወደ ሠላሳ እርኩሳን መናፍስት በሰውነቴ ውስጥ ነበሩ::

**ሊ፥ ሀክ ሱንግ:** *ሊ፥ ሀክ ሱንግ ሰይጣንን አጠቃ

በልሳን ስጸልይ ሳለ፥ **ኢየሱስ** መጣና በቅጽል ስሜ ጠራኝ፥ ***"ሳም፥ ሲዖልን እንጎብኝ::"*** የ**ጌታ**ን እጅ እንደያዝሁ፥ ወደ ሲዖል መብረር ጀመርን:: ወደ ሰይጣን ዙፋን ስንደርስ፥ የእርኩሳን መናፍስት ንጉስ ተረጋግቶ ቁጭ አለ:: ረዥምና ግዙፍ ነበር፤ ቁመቱ የሲዖል የላይኛው ጥግ ድረስ ደርሷል:: በቁጥጥሩ ሥር ያሉ የማይቆጠሩ ታዛዦች አሉት:: የማሰቃያ መሣሪያዎች እንደ ተራራ ተከምረው አየሁ:: የማሰቃያ መሣሪያዎቹ የሰይጣንን ዙፋን ከበውታል::

ከማሰቃያ መሣሪያዎቹ መካከል፥ የእርሻ መሣሪያዎችንም አይቻለሁ፥ ማረሻ፣ የብረት መንጠቆና፣ ማጭድ:: ከብረት ከተሠሩት ከሌሎች የማሰቃያ መሣሪያዎች ጋር ሸጉጦችና ቢላዎችም ነበሩ:: አያቴን፣ አጎቴን፣ የአክስቴን ልጆች፣ እናም አክስቴን በሰይጣን ዙፋን ፊት በማየት ተደምሜ ነበር::

ከዘመዶቼ ቀጥሎ መስቀልያ ቅርጽ ያላቸው ዛፎች ነበሩ:: ተላላኪዎቹ እርኩሳን መናፍስት ዘመዶቼን በመስቀልያ ዛፎቹ ላይ ለመስቀል በዝግጅት ተወጥረዋል:: ዘመዶቼ በፍርኃት ተመትተው ፊታቸው ገርጥቶ በስሜት ይንቀጠቀጣሉ:: እኔ በዚያ መሆኔን እንዳወቁ፥ ወደ እኔ መጮህ ጀመሩ:: *"ሀክ ሱንግ፥ ለምን ወደዚህ ተመልሰህ መጣህ? በቃ ሂድ! ፍጠን! ሂድ! ይህ ቦታ የሚጎበኝ ቦታ አይደለም:: ሂድ! ፍጠን፥ ጥፋ!"* ሰይጣን የሆነ ነገር የሚያደርግ እንደሆነ ለማየት ፊቱን በጨርፍታ አዩት:: ኢጋንንቶቹ በዘመዶቼ ላይ ጮኹባቸው:: *"ሁላችሁም፥ ስለምንድ ነው የምትነጋገሩት? ሁላችሁም ዝም በሉ!"* በፍርሀት፥ ዘመዶቼ ጸጥ ብለው ቆሙና በመሸበር ተንቀጠቀጡ::

በድንገት፥ ሰይጣን የአክስቴን ልጅ ማሰቃየት ጀመረ:: ይመስለኛል ሆን ብሎ እኔን ለማበሳጨትና የሆነ ነገር እንዳደረግ ለማድረግ ነበር:: ሰይጣን ረዥም ጥፍሮቹን ተጠቅሞ የአክስቴን ልጅ ጀርባ ሥጋ ቦጫጨቀው:: የአክስቴ ልጅ በህመም ጮኸና ወድቆ ተንፈራፈረ:: ቢሆንም፥ ያ የሰይጣንን ንዴት አላረካውም:: የጭንቅላቱን ሥጋ ቦጫጨቀና የራስ ቅሉን አደቀቀው:: የአክስቴ ልጅ በስቃይ እየጮኸ የራስ ቅሉ ትቢያ ሆነ፥ *"ኢድኑኝ! እባካችሁ! አህ!"* ትግስቴ አለቀብኝና ወደ ሰይጣን ሮጥኩ፥ እግሩን መታሁት፥ እርሱ ግን ውልፊት አላለም:: ሰይጣን ጠንካራና ግዙፍ ነበር፤ ውጤታማ አልነበርሁም::

**ኢየሱስ** ሁኔታውን እንዴት እንደወሰድሁት ተመለከተ:: የጁ ኢዩንን ሰይጣጣንን ማጥቃት ታሪክ አስታወስኩ:: በሰውነቱ ላይ ወጥታ ጎድታዋለች:: የሆነ ነገር ማድረግ እንዳለብኝ ተሰማኝ፥ እርዳታ ቢስ ሆኜ መመልከት አልቻልሁም:: በሰውነቱ ላይ ያሉትን ጸጉሮቹን እየያዝሁ የሰይጣን ሰውነት ላይ ወጣሁ:: እንዲሁም ሰውነቱን እየበሳው ወደ ላይ ለመውጣት ጥፍሬን ተጠቀምሁ:: ከመጠኑ የተነሣ፥ ወደ ታች ስመለከት፥ ከዳገት ላይ እየተመለከትሁ ነው የመሰለኝ:: መንቀጥቀጥ ጀመርሁ:: ከረዥሙ ከፍታ የተነሣ ፍርሀት አሸመደመደኝ::

ምንም እንኳ በሰይጣን ላይ ጉዳት ማድረስ ብፈልግም፥ መሣሪያው ስላልነበረኝ አልቻለሁም:: በግልጽ ጸለይሁ፥ *"**እግዚአብሔር** ሆይ፥ እባክህ የ**መንፈስ ቅዱስ**ን ሠይፍ ስጠኝ!"* ልክ እንደጸለይሁ፥ በወርቅ የተሠራ ሠይፍ ቀስ እያለ ከሰማይ ወረደ:: ወዲያውኑ ያዝሁትና በሌሎቹ የቤተክርስቲያኑ አባላት የተጎዳውን ቦታ ማጥቃት ጀመርሁ::

አስቀድሞ፥ ሰይጣንን ማሳመም አልቻልሁም ነበር። አሁን፥ ጉዳት ማድረስ ቻልሁ፥ እንዲጮህ አደረግሁት፥ “*አሀሀ! ያማል! ማነው የሚያስቸግረኝ? ለምንድ ነው በተደጋጋሚ ወደዚህ ቦታ የምትመጡት? እናንተ ትናንሽ ሰዎች እንዴት ነው የምትደፋፈሩኝ! ቆይ ጠብቁ በቀሌን እወስዳለሁ!*”

በፊት የተጎዱትን አካባቢዎች በመላ ኃይሌ ማጥቃት ቀጠልሁ። ዓይኑን ወጋሁትና በክንፎቹ ላይ መንዥዋዠው ጀመርሁ። ሙሉ በሙሉ ልገነጥላቸው ቻልሁ። አሁን፥ መቼም ቢሆን እነዚህን ክንፎቹን በድጋሚ ሊጠቀምባቸው አይችልም።

ሰይጣን ከመቀመጫው ዘለለና መረበሽ ጀመረ። “*አሀሀ! ምን እያደረጋችሁብኝ ነው? አንተ ባልሆንክ ጊዜ ሌላው ይሆናል! አሀሀ! በህመም ነኝ! እናንተን እበቀላችኋለሁ! በቀሌን እስካገኝ ደረስ አላርፍም! እንዲህ ሲያደርጋችሁ እንድታመልጡ አልተዋችሁም!*” ሰይጣን ጥርሱን እያፋጨ በንዴት ቦግ አለ፥ በስቃ በኃይል ጮኸና ተንጠላጥሎ ወጣ።

እርኩሶቹ አገልጋዮቹ በጣም ተናደዱና ወደ የአክስቴ ልጅ ሄዱ። እርኩሱ ፍጥረት ሥጋውን ሁሉ በቢላ ከታተፈና በድስት ውስጥ ጨመረው። የአክስቴ ልጅ በአጥንቶቹ ብቻ ቀረ። የአክስቴ ልጅ ሲጮህና ሲያለቅስ እያየሁ፥ “*የአክስቴ ልጅ እየተሰቃየ ያለው ሰይጣንን ስላጠቃሁትና ስላሰቃየሁት ይሆን?*” ብዬ አሰብሁ። **ኢየሱስ**ም፥ “***ሳም፥ ይበቃል። እንሂድ።***” አለኝና ሲያልን ትተን ወጣን።

**መጋቢ ኪም ዮንግ ዱ፡** *የጌታን ቀን ጠብቅ*

እጆቼ በተለያዩ ዓይነት እንቅስቃሴዎች መንቀሳቀስ ቀጠሉ። የተለያየ ዓይነት የሆኑት እንቅስቃሴዎች እንዴት ተፈጥሯዊ ለመሆን እንደቻሉ ተገርሜና ለማወቅ ጓጉቼ ነበር። እንደማንኛውም ነገር፥ **መንፈስ ቅዱስ** ይመራል ወይም ይመክራል፥ እኔ በዚህ ውስን በሆነች አዕምሮዬ ላስበው አልችልም። ሁልጊዜም ደስ የሚል እንግዳ ነገር ነበር እናም አንዳንዴ በጣም ነው የምደነቀው።

ሁልጊዜም ጸሎት ስጀምር፥ ራሴን እጠይቃለሁ፥ “*ዛሬ ደግሞ እጆቼ ምን ዓይነት እንቅስቃሴዎችን ይፈጥሩ ይሆን?*” በምፈልገው መንገድ፥ እጆቼንና ክንዶቼን በአንድ ላይ አድርጌ እንዳይንቀሳቀሱ ላደርጋቸው እፈልጋለሁ። በጸሎቴ ላይ ማተኮር እፈልጋለሁ። በ**መንፈስ ቅዱስ** ቁጥጥር ውስጥ ስሆን፥ ድምጼ፣ ክንዶቼ፣ እጆቼ በ**እርሱ** ኃይል ነው የሚመሩት ስለዚህም መቃወም አልችልም።

ድንገት ከተቃወምኩት፥ የገፋሁትና የካድሁት ያህል ይሰማኛል። ልታዘዘው ይገባኛል። ሁሉንም ነገር ለመጠቅለልና በተቻለ መጠን በቶሎ ለመጨረስ እፈልጋለሁ፥ ግን **እግዚአብሔር** በጣም በቀስታ የሚሠራ ነው የሚመስለው፥ እንደ ማይቸኩል ዓይነት። ቢሆንም የ**ያህዌ መንፈስ** (የ**እግዚአብሔር መንፈስ**) በውኃ ላይ በእርጋታ እንደሚሄድ ነው።

**ጌታ** ስለማይቸኩል፥ በሂደቱ ፍጥነት ላይ የምሰላቸው እኔ ነኝ። ትዕግስት ስለሌለኝና ፈጣንና ኃይለኛ ውጤትን ስለምፈልግ፥ የ**እግዚአብሔር**ን ሕግ በአግባቡ አልፈጸምሁም ወይ ብዬ አስባለሁ። ፈጣን ለውጥን በሚፈጥር ዓለም ውስጥ ነው የምኖረው። ማንኛውም ዓይነት መዘግየት ኋላ እንደ ቀረው እንዳስብ ያደርገኛል። ዘመናዊውን የህይወት ዘይቤ እንደተላመድሁ አድርጌ ነው የማስበው። በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚፈጠሩት ነገሮች፥ በተለይ እኔ በግሌ ከ**መንፈስ ቅዱስ** ምሪት ሥር ሆኜ ያሉኝ ገጠመኞች በጣም በዝግታ እየተለወጥሁ ሆኖ እንዲሰማኝ ያደርጉኛል። በ**እግዚአብሔር** ፈቃድ ውስጥ ለመቆየት ከፈለግሁ፥ እንደ መጋቢ የበፊት ልማዶቼንና የግል ገጠመኞቼን እርግፍ አድርጌ መተው ይኖርብኛል።

**ጌታ** በተደጋጋሚ ተልዕኮውን እንደ **እርሱ** ፈቃድ ወይም ምሪት አልያም እንደ ራሴ አረዳድ እንደምመራ ይጠይቀኛል። የእኔ አረዳድ መሠረት የሚሆነው ለዓመታት የተማርኳቸው ትምህርቶች፥ ሥርዓቶች፥ እናም ፍልስፍናዎች ይሆናሉ። እንደ **እርሱ** ፈቃድ የሆነ አገልግሎትስ ምንድ ነው? እነዚህ ሁሉ የአገልግሎት ዘመናት በከንቱ ነበሩ? በስሜት በማገለግልበት ጊዜ ምን እያደረግሁ ነበር? አንድ ነገር ግልጽ ነው። **ጌታ** በብዙ ድፍረትና እንደ **እርሱ** ፈቃድ ነበር ሳደርግ የነበረው በሚል ግምት ሳደርግ የነበረውን የቀድሞውን አገልግሎት አያውቀውም። ተገዝቼለት የነበረው አገልግሎት በ**ጌታ** ተቀባይነት እንደሌለው ተረዳሁ፥ መላ ሰውነቴ በፍርሀት ተንቀጠቀጠ። **ጌታ** ሁኔታዬን ነጥሎና መርምሮ አወጣው። የመጀመሪያውን መጽሐፍ እንኳ በመጻፍ ሂደት ውስጥ ሳለሁ፥ **ጌታ** በአብዛኛው የአባላቱን ገጠመኞች ብቻ በመጻፍ እንዳተኩር አዝዞኛል። በተለይ ደግሞ፥ **ጌታ** መጽሐፉን ስጽፍ ሙሉ በሙሉ ታዛዥ እንድሆን ጠይቆኛል። የእኔ ትጋትና ታዛዥነት የበለጠ ተአማኒነት ያለውን መጽሐፍ ለማዘጋጀት ያስችላል።

በመንፈሳዊ መነቃቃት ጉዳይ ላይ ጸለይሁ፥ ከገነት አጠገብ እንደሆንሁ ተሰማኝ። ሆኖም ግን፥ ርኩሳን መናፍስቱ በታላቅ ኃይል አጠቁኝ። ጸሎቶቼ ጥልቅ እየሆኑ ሲመጡና ወደ ገነት የበለጠ ስቀርብ፥ በፊት እኔ ያሸነፍኳቸው እርኩሳን መናፍስት

ሌሎች የቤተክርስቲያኑ አባላትን ማጥቃት ጀመሩ:: አላማቸው እኔን ከጸሎቴ ለማደናቀፍ የቤተክርስቲያኑ አባላትን ማጥቃትና ሰውነታቸውን ማዳከም ነበር:: ማሰናከያው እኔ መንፈሳዊ መነቃቃትን እንዳላገኝ ያግደኛል::

በመንፈስ ንቁ የነበሩት፣ *“የመጋቢ ኪም መንፈሳዊ ዓይኖች እንደተከፈቱ፥ ያልቅልናል:: በሙሉ ኃይል አጥቁ!”* እያለ ሰይጣን ሲያዝ ዓዩት:: በ**ጌታ** እርዳታ፥ የሰይጣን ጥቃት ከንቱ ነበር:: መልሰው ተቀናጁና

እንደጋና ማጥቃት ጀመሩ:: በዚህ ጊዜ፥ ዓላማቸው አባላቱን አንድ በአንድ ወደ መሬት እንዲወድቁ ማድረግና መጋቢው እነርሱን ሲያስወጣ ጊዜውን እንዲያባክን ማድረግ ነው::

በድጋሚ፥ እህት ቤይክ ቦንግ ንዮ በእርኩሳን መናፍስቱ ተሸነፈችና ብዙዎቹ የእርኩሳን መናፍስቱ ቡድን ወደ ሰውነቷ ገቡባት:: በዚያን ምሽት ከረፈደ ስለነበረ የተጠቃችው እስከ ጠዋቱ ll ሰዓት ድረስ ስንዋጋ ቆየን:: ከበፊቱ ጥቃት የተነሣ፥ ሰውነቴ ቀድሞውኑ በቀጣይና በሚጨምር ህመም ውስጥ ነበር:: አብዛኞቹ ህመሞችና ስሜቶች ቀኑን አብዛኛውን ተኝቼ እንዳሳልፍ ሆነ::

*ውጊያ በጠባቂ መላእክትና በእርኩሳን መናፍስት መሐከል

አብዛኛውን ሌሊት ሙሉ ስንዋጋና እርኩሳን መናፍስቱን ስናስወጣ አሳለፍን:: ሌሊት ll ሠዓት ላይ እንደ ምንም ጸሎታችንን የምንጀመርበት ጊዜ ነበረን፥ ጠዋት 2:30 ላይ ጨረስን:: ከጠላቶቻችን ጋር የነበረው ውጊያ አብዛኛውን የጸሎት ጊዜ ወሰደብን:: ከጸሎት በኋላ አባላቱን በመኪና አደርስኳቸው:: ወደ ቤቴ ስደርስ፥ ከጠዋቱ 3 ሰዓት ሆኖ ነበር:: ወደ ቤት ስገባ፥ ሴት ልጄ፥ በመደነቅ ሁኔታ ጮኸች፥ *“አባዬ፥ በዋናው መኝታ ክፍል ውስጥ መላእክትና እርኩሳን መናፍስት እየተዋጉ ነው!”* በመነቃቃት፥ መልሼ፥ *“ምን? በይ እንሂድና በጸሎት መላእክቱን እናግዛቸው!”* አልኳት:: ባለቤቴና ዮሴፍ በቤት ውስጥ ሁለተኛውን ጸሎት ስንጀምር ከእኛ ጋር ተቀላቀሉ::

ዮሴፍና ጁ ኢዩን እየጸለዩ፥ ሁኔታውን በመንፈሳዊ ዓይናቸው ተከታተሉ:: እርኩሳን መናፍስቱ በቡድን ሆነው እንደ መጡ ገለጹ:: ምንም እንኳ የዮሴፍ መንፈሳዊ ዓይኖች ሙሉ በሙሉ ባይከፈቱም፥ በእርሷ እርዳታ እርኩሳን መናፍስቶቹን ማደንና ማጥቃት ችሎ ነበር:: *“እርኩሳን መናፍስት መቼም አያቆሙም፤ መቼም እረፍት አይሰጡንም::”* በልሳን መጸዬን ቀጠልሁ፥ ነገር ግን ሁሉንም አድኖ ለመያዝ ብቃቴ የተወሰነ እንደነበረ ተረዳሁ::

በተደጋጋሚ ጥቃታቸው ተዳክመንና ተሰላችተን ነበር:: ቅዱሱን እሳት ተጠቀምንና እርኩሳን መናፍስቱን አሸነፍናቸው:: ሁሉም ተበታትነው ነደዱ:: ውጊያው ሲያልቅ፥ በመጨረሻ ቁርሳችንን የምንበላበት እድል አገኘን:: ሆኖም ግን፥ የምሳ ሰዓት ሆኖ ነበር:: ጁ ኢዩን ስትገልጽ፥ *“አባ፥ አራቱ መላእክት እየጠበቁን ነበር::”* አለች:: *“ጁ ኢዩን፥ ከመላእክቱ ጋር መነጋገር የምትችዪ ይመስልሻል?”* ብዬ ጠየቅኋት:: *“አዎን፥ ለሆነ ያህል ጊዜ ከእነርሱ ጋር ስነጋገር ቆይቻለሁ::”* ብላ መለሰች:: ለጁ ኢዩን ለመላእክቱ ዛሬ ጥሩ ሥራ ሠርታችኋል ብለሽ ንገሪያቸው አልኳት:: ጁ ኢዩን መላእክቱን ስለራሳቸው አንዳንድ ጥያቄዎችን ትጠይቃቸው ጀመር:: ከዛም፥ **ጌታ** ተገለጠና ንግግራችንን ቀጠልን::

**ኪም ጁ ኢዩን:** *የመላእክት ክንፎችና ትርጉማቸው

“**ኢየሱስ** ሆይ፥ በቤቴ ውስጥ አራት መላእክት አሉ:: እነማን ናቸው? ለምንድ ነው በቤቴ ያሉት?”

**ኢየሱስ:** ***“እነዚህ ቤተሰብሽን ለመጠበቅ የተመደቡ አራት ጠባቂ መላእክት ናቸው:: በእግዚአብሔር አብ ነው የተላኩት እናም እያንዳንዳችሁን እየጠበቁ ነው::”***

**ኪም ጁ ኢዩን:** *“ነገር ግን **ኢየሱስ**፥ እናቴን፣ ወንድሜንና እኔን የሚጠብቁት መላእክት ክንፎቻቸው አንድ ጥንድ ብቻ ለምን ሆነ ለምን ሁለት ጥንድ አልሆነም? የመጋቢ ጠባቂ መላእክት ለምን ሁለት ጥንድ ክንፍ ኖራቸው?”* (አንድ ጥንድ: በግራና በቀኝ አንድ አንድ ባጠቃላይ ሁለት ክንፎች ማለት ነው::)

**ኢየሱስ:** ***“መጋቢ ብዙ ሰዓት ለቤተክርስቲያኑ አባላት በመጸለይ ያሳልፋል:: በተጨማሪም፥ መጋቢዎች በእግዚአብሔር አገልግሎት ትልቁ ደረጃ ላይ ናቸው:: መጋቢዎች ለጌታ አብዝተው በትጋት ይሠራሉ:: በዚህም ምክንያት፥ ላቅ ያለ ማእረግ ባለው መላእክት ይጠበቃሉ:: ሁለት ጥንድ ክንፍ ያላቸው መላእክት ከፍ ያለ ማእረግና አንድ ጥንድ ክንፍ ካላቸው መላእክት የበለጠ ኃይል አላቸው:: ተልዕኮአቸውን በታላቅ ብቃት የሚመሩ መጋቢዎች ሦስት ጥንድ ክንፎች ባሏቸው መላእክት ይጠበቃሉ:: ባለ ሦስት ጥንድ ክንፍ መላእክት የበለጠ ደረጃና ኃይል አላቸው::”***

**ኪም ጁ ኢዩን፡** “***ኢየሱስ*** *ሆይ፥ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ወደ እቤቴ ስገባ፥ በእርኩሳን መናፍስትና በመላእክት መካከል ውጊያን አየሁ፡፡ አባቴና እናቴ ሲጨቃጨቁ መላእክት እንዴት ነው ምላሽ የሚሰጡት?*”

**መላእክቱ፡** (ንግግራችንን ሲያዳምጡ ቆይተው፥ ጣልቃ ገቡ፡፡) “*ቅድስት ጁ ኢዩን፥ መጨቃጨቅም ሆነ መጣላት የለባችሁም፡፡ በማንኛውም ጊዜ ቅዱሳን እርስ በእርሳቸው ሲጨቃጨቁ ወይም ሲጣሉ፥ ሽልማታቸው በሚገርም ሁኔታ ይቀንሳል፡፡ እባካችሁ ከዚህ በኋላ አትጨቃጨቁ፡፡*”

**ኪም ጁ ኢዩን፡** “***ጌታ*** *ሆይ፥ አንዳንዴ ስንተኛ ሰውነታችንን ከባድ ሸክም ይሰማናል፡፡ እንደዚህ ዓይነት የሰውነት ሁኔታ የሚፈጠረው ለምንድ ነው?*”

*የመኝታ ሽባነት

**ኢየሱስ፡** “***ያ ብዙ ጊዜ የሚከሰተው እርኩሳን መናፍስት በሰዎች ሰውነት ላይ ሲጫኑ ነው፡፡ ይህ የሚሆነው የሰውዬው ጠባቂ መልአክ ሲሸነፍ ነው፡፡ ሆኖም ግን፥ መላእክቱ እርኩሳን መናፍስቱን ካሸነፏቸው ይህ አይከሰትም፡፡ አንዳንዴ፥ ከፍ ያለ ስልጣን ያላቸው እርኩሳን መናፍስት ወደ ሰው ሰውነት ውስጥ ለመግባት ሲሞክሩ ጠባቂ መልአኩን ሊያሸንፉት ይችላሉ፡፡ ሰዎች እኔን እንደ ጌታቸውና አዳኛቸው አድርገው ሲቀበሉኝና በሙሉ ልባቸው ሲያምኑ፥ በዛ ቅጽበት ጠባቂ መልአክ ይመደብላቸዋል፡፡ ጠባቂ መልአኩ ያን ሰው በእድሜ ዘመኑ ሙሉ ይጠብቀዋል፡፡ አማኞች የሚጠብቋቸው ጠባቂ መላእክት አሏቸው፡፡ የማያምኑት የሚያስቸግሯቸው እርኩሳን መናፍስት አሏቸው፡፡ የማያምኑትን በመኝታ ጊዜ ወደ ታች ይጫኗቸዋል አልያም ይለቋቸዋል፡፡ በእርኩሱ መንፈስ ሁኔታ ይወሰናል፡፡ ልጆቼ በተደጋጋሚ ኃጢአትን ሲሠሩ ወይም እምነታቸው ሲዳከም በቀላሉ ይጋለጣሉ፡፡ በእንቅልፍ ጊዜ ለጥቃት ምቹ ይሆናሉ፡፡ ከፍ ያለ ደረጃ ያለው እርኩስ መንፈስ ከጠባቂ መልአኩ ያየለ ሲሆን፥ ለጥቃት የታቀደው ሰው በሰውነቱ ላይ ወደ ታች የሚጫነው ግፊት ይሰማዋል፡፡ በአጠቃላይ፥ አንድ ሰው በመልአኩና በእርኩሱ መንፈስ መካከል ያለውን ውጊያ ሊያይ አይችልም፡፡ ሆኖም ግን፥ በአጠቃላይ ህይወታችሁ የተጠበቀ ነው ምክንያቱም ጠባቂ መልአኩ እርኩሳን መናፍስትን ማሸነፍ ስለሚችል፡፡ ይህን ሁል ጊዜ አስታውሱ፡፡***”

**ኪም ጁ ኢዩን፡** “***ኢየሱስ*** *ሆይ፥ ሰውዬው ከእምነት ሲያፈገፍግና ወደ ዓለም ሲመለስ ጠባቂ መልአኩ ምን ይሆናል? እንደዚህ ዓይነት ብዙ ሰዎች አሉ፡፡*”

**ኢየሱስ፡** “***አንድ ታማኝ የነበረ ሰው ቢያፈገፍግ፥ ጠባቂ መልአኩ ወደ ገነት ሊመለስና በእግዚአብሔር ፊት ሊቆም ይገባዋል፡፡ በእግዚአብሔር ፊት ቆመው ሊገሰጹ ይገባቸዋል፡፡ ጠባቂ መላእክቱ ወደ መጀመሪያ ሥራቸው ይመለሳሉ፡፡ ያፈገፈገው ሰው ቢመለስ፥ መልአኩ ተመልሶ ይመደብና እንደ መጀመሪያው ሰውየውን ይጠብቃል፡፡ ጠባቂ መልአኩ ለመጠበቅና በአስፈላጊ ሁኔታ ውስጥ ለማገዝ በዚያ ይኖራሉ ነገር ግን ብዙውን ጊዜ እንደ ሰውየው ምርጫ ነው፡፡ እንደ ሰውየው ሥራ የመልአኩ ስልጣንና ደረጃ ከፍ ይላል፡፡***”

**ኪም ጁ ኢዩን፡** “*አንድ መልአክ ምን ያህል ጥንድ ክንፎች ሊኖሩት ይችላል?*”

**ኢየሱስ፡** “***አንድ መልአክ ሊኖረው የሚችለው ጥንድ ክንፎች ቁጥር ሦስት ነው፡፡ ምንም ክንፍ የሌላቸው አንዳንድ መላእክትም አሉ፡፡ የክንፋቸው ብዛትና ቁመናቸው ቦታቸውንና ደረጃቸውን ያንጸባርቃል፡፡ ክንፎቻቸው ከሰውነታቸው ሊያድጉ ይችላሉ፡፡ በአንዳንድ ልዩ ሁኔታዎች፥ እኔ ራሴ ክንፎችን እገጥምላቸዋለሁ፡፡***”

**ኪም ጁ ኢዩን፡** “***ኢየሱስ*** *ሆይ፥ ስለእነርሱ ስናወራ፥ የተደሰቱ ይመስላሉ!*”

**ኢየሱስ፡** “***ትክክል ነው፡፡ መንፈሳዊ ንግግሮችን መስማት ያስደስታቸዋል፡፡ እናም ዓለማዊ ወሬዎችን ሲሰሙ በቅጽበት ይከፋሉ፡፡***”

**ኪም ጁ ኢዩን፡** “***ኢየሱስ*** *ሆይ፥ መላእክቱ ስለእነርሱ ማውራታችውን ስንቀጥል ሲደንሱ አስተዋልሁ፡፡ ዋው! እናቴ በ**መንፈስ ቅዱስ** የምትደንሰውን ዓይነት ዳንስ ነው የሚመስለው፡፡ መልአክ፥ መጋቢው የእናንተን አቋምና ንግግር በማስታወሻ እየያዘ ነው፡፡ መጋቢ ስለእኛ ግንኙነት መጽሐፍ ይጽፋል፡፡*”

**መላእክት፡** “*ዋው! እውነት ነው? ታሪካችን በመጽሐፍ ሊጻፍ ነው?*”

**ኪም ጁ ኢዩን፡** “*አዎ፥ በእርግጠኝነት!*”

መላእክቱ ደስተኞች ነበሩ እናም በበለጠ በሚስብ ሁኔታ መደነስ ቀጠሉ፡፡ ንግግራችን እንዲቀጥል ፈልገው ነበር፥ ነገር ግን **ጌታ** አቋረጠን፡፡

**ኢየሱስ**: *"ጠቃጠቆ፥ ከእኔ ጋር ነበር ልታወሪ የሚገባሽ፡፡ ከመላእክቱ ጋር ለማውራት የምትሞክሪው ለምንድ ነው?"*

**መላእክት፡** (**ጌታ** ሲናገር፥ በትሕትና አንገታቸውን ዝቅ አድርገው ወደ ኋላ ቆሙ፡፡)

**ኪም ጁ ኢዩን**: *"**ኢየሱስ** ሆይ፥ አንድ ሰው ሲሞት ምን ይሆናል? ምን ያህል መላእክት ናቸው የሚያጅቡት?"*

**ኢየሱስ**: *"ለአማኞች፥ ጠባቂ መላእክቶቻቸውና አንድ ሌላ መላእክት ወደ ገነት ይዘዋቸው ይመጣሉ፡፡ የማያምን ሲሞት ደግሞ፥ ከሲዖል የሆነ ፍጥረት ይመጣና ወደ ሲዖል ይወስደዋል፡፡"*

**ኪም ጁ ኢዩን**: *"**ኢየሱስ** ሆይ፥ በገነት ያለውን ቤቴን ለመጎብኘት እመኛለሁ፡፡"*

**ኢየሱስ**: *"መጥተሽ በገነት ያለውን ቤትሽን ልትጎበኚ ያስፈልግሻል፡፡ ሆኖም ግን፥ ልታዪው ከፈለግሽ፥ በጽናት መጸለይ ይኖርብሻል፡፡ በጸሎትሽ የበለጠ ለመትጋት የማትሞክሪ አትሁኚ፡፡ ለዚህ ነው በቀላሉ ገነትን እንድትጎበኚ የማልፈቅድልሽ፡፡ ምኞትሽን ካሳካሁልሽ በጸሎትሽ ሰነፍና የማትጣጣሪ ልትሆኚ ትችያለሽ፡፡"*

**ኪም ጁ ኢዩን**: *"**ኢየሱስ** ሆይ፥ ብዙ ጥያቄዎች ስለጠየቅሁህ ይቅርታ፡፡ መላእክት ያለቅሱ እንደሆነ ለማወቅ በጣም ጓጉቻለሁ፡፡ ወደ ገነት ስንሄድ፥ የቤተሰብ አባላት እርስ በእርሳቸው ሊተያዩ ይችላሉ? ቅዱሳን በገነት ይጣሉና ይጨቃጨቃሉ?"*

**ኢየሱስ**: *"ጠቃጠቆ፥ ስለብዙ ነገሮች ለምን ትጓጊያለሽ? የትንቢትን ጸጋ ከሰጠሁሽ በኋላ ዝም ብለሽ ትጨቀጭቂኛለሽ፡፡ ሀሀሀ፡፡ ደህና፥ ቀጥይ ተጨማሪ ጥያቄዎችን ጠይቂኝ፥ አንድ በአንድ፡፡ መላእክት ሐዘንን በፊታቸው ገጽታ መግለጽ ይችላሉ፡፡ ማልቀስ ወይም ከዓይናቸው እንባን ማፍሰስ አይችሉም፡፡ ሊቀ መላእክት ሚካኤል፣ ሊቀ መላእክት ገብርኤልና እኔ ብቻ ነን በእንባ ማልቀስ የምንችለው፡፡ የቤተሰብ አባላት አዎን በገነት በደስታ ይገናኛሉ ይተያያሉ፡፡ ቢሆንም፥ ሁል ጊዜ መገናኘት አይችሉም፥ በልዩ ሁኔታዎች ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን፥ በገነት የቤተክርስቲያን አገልግሎቶች ላይ መገናኘት ይችላሉ፡፡ ገነት ያለነውርና ያለነቀፋ የሆነ ቦታ ነው፡፡ ፍጹም ቦታ ነው፡፡ እግዚአብሔር አብ ሁሉን ነገር በራሱ ያስተባብራል ያቀናጃል፡፡ ለዚህ ነው ገነት ፍጹም ቦታ የሆነው፡፡ ለመጣላትም ሆነ ለመከራከር ምንም ምክንያት የለም፡፡ እነዚህ ነገሮች የሚከሰቱት ሰዎች ኃጢአተኛ ባህሪ ስላላቸው ነው፡፡ ኃጢአታዊ ባህሪ ጭንቀትና ስጋትም ሊሆን ይችላል፡፡ ሰዎች የሚጣሉባቸው ወይም የሚከራከሩባቸው ሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች አሉ፡፡ መላእክት ፈጽመው አይጣሉም፡፡ መቼም ሊሆን አይችልም፡፡ ያ የሚሆን ቢሆን ኖሮ፥ ለንስሐ የሚሆን ምንም እድል ሳይሰጣቸው ከገነት ይባረሩ ነበር፡፡ ያለ ርኅራኄ ወደ ሲዖል ይጣላሉ፡፡ የዳኑ ነፍሳት አይጣሉም ወይም አይጨቃጨቁም፡፡ በገነት የማይቻል ነው፡፡ ያ ድንገት ቢሆን፥ ወደ ሲዖል አይጣሉም፥ ምክንያቱም ከእግዚአብሔር ጸጋ በታች ናቸው፡፡ የተመቻና ደስተኛ ህይወት ይኖራሉ፡፡"*

# ==== ቀን 28 ====

(ዕብራውያን 4፡12-16)

**መጋቢ ኪም ዮንግ ዱ፡** **የእርኩሳን መናፍስቱ በሙሉ ኃይል ማጥቃት*

የ30 ቀን የጸሎት ዘመቻው ቀናት እየተቆጠሩ በሄዱ ቁጥር፥ ከእርኩሳን መናፍስት ጋር ያለው ውጊያ በረታ፡፡ በማንኛውም ጊዜ "ግልገሎቹ" በአስቸጋሪ የአየር ሁኔታ ውስጥ ሲጸልዩ፥ ልቤ ይራራላቸዋል ነገር ግን ከማልቀስ ውጪ ምንም ልረዳቸው አልችልም፡፡ ከእርኩሳን መናፍስቱ ተደጋጋሚ ድንገተኛ ጥቃቶች የተነሳ በአካልም በመንፈስም ተዳክመናል፡፡

ውጊያው ወደ ኋላ ወደ ፊት ይላል፡፡ አንዳንዴ እኛ ይቀናናል አንዳንዴ ደግሞ እርኩሳን መናፍስቱ ይቀናቸዋል፡፡ ይህ ሁኔታ አሁንም አሁንም ይደጋገማል፡፡

ምንም ውጊያዎቹ ጽኑ ቢሆኑ፥ በውጊያ ወቅት ወደ **ጌታ** መጮህችንን አናቋርጥም፡፡ እውነታው፥ በተደጋጋሚ ወደ **እርሱ** እንጮህለን፡፡ ከምሽቱ 3 ሰዓት አካባቢ ተሰበሰብን፡፡ ከአገልግሎት በፊት፥ ዘመርንና **ጌታ**ን አመሰገንን፡፡ እያመለክን ሳለ፥ እህት ቤይክ ቦንግ ንዮ ተጠቃች፡፡ በእርኩሳን መናፍስት የተገኘችው የመጀመሪያዋ እርሷ ነበረች፡፡ በጥቃቱ ጊዜ፥ ወደ ፊት ወደቀች፡፡ እርኩሳን መናፍስቱ እህት ቤይክ ቦንግ ንዮ ሰውነት ውስጥ መግባት ጀመሩ፡፡ የማይታዩ ነበሩ፤ ቅርጻቸውን ሆነ

መልካቸውን በዓይኔ ማየት አልቻልሁም ነበር፡፡ ጥቃቱ ድንገተኛ ነበርና እርኩሳን መናፍስቱን ለመጋፈጥ ዝግጁ አልነበርንም፡፡

እንደ ሰው፥ በመጋቢነት ጥሪ ላይ ጥርጣሬ ተሰማኝ፡፡ *"በመንፈሳዊ ጭለማ ውስጥ እየኖርሁ መሆን አለበት፡፡ መንፈሳዊ ጥቃቶቹን መከላከል ለምን አልቻልሁም? ከሆነ በኋላ ውጊያ ውስጥ የምገባው ለምንድ ነው?"* ብዬ አሰብሁ፡፡ የቤተክርስቲያኒቱ አባላት ወደቁ፥ መሬት ላይ እየተንከባለሉ በህመም ይጮህሉ፡፡ እርዳታ ቢሰና ልራዳቸው እንደማልችል ተሰማኝ፡፡ ከዚያም በድንገት፥ ባለቤቴ መንቀሳቀስ አቃታት፤ እግሮቿ ሽባ ሆኑ፡፡ ወንዱ ልጄ፥ ዮሴፍ፥ ተጠቃና እራስ ምታት ያዘው፡፡ ሴቷ ልጄ፥ ጁ ኢዩን፥ እጇ እንደተሰበረ ተጎድታ ወደቀች፡፡ ዩ ክዩንግና ሀክ ሱንግ እንደ ሌሎቹ በእርኩሳን መናፍስቱ ተጠቅተው መሬት ላይ ወደቁ፡፡

እርኩሳን መናፍስቱን ከአንዱ አባል ሳስወጣ፥ ወደ ሌላ አባል ይሄዱና ቀጣይ ኢላማቸውን ያጠቃሉ፡፡ የቤተክስቲያናቻን አባላት በሥቃይ ውስጥ ይሆናሉ፡፡ እንደ መጋቢ፥ ብቁ እንዳልሆንሁ አሰባለሁ፡፡ በጣም መንፈሳዊ እንዳልሆንሁ ይሰማኛል፡፡ የቤተክርስቲያን አባላቱን መንፈሳዊ ጥማት ለማርካት አልችልም፡፡ የዛሬው ውጊያ መንፈሳዊ ደካማነቴን በግልጽ ነው ያሳየው፡፡ በአሁኑ ሰዓት ግራመጋባትና የመጨናነቅ ስሜት ተሰማኝ፡፡

ለሦስት ቀናት፥ ከእርኩሳን መናፍስት ጋር ስንዋጋ ነበር፡፡ በመሆኑም፥ ጥሩ እንቅልፍ ማግኘት አልቻልሁም፡፡ ያለሁበት ቦታ አይወስነውም፥ ቤተክርስቲያንም ሆነ እቤት ውስጥ፡፡ እርኩሳን መናፍስቱ ምንም እረፍት አልሰጡኝም፡፡ በተለይ የትላንትና ማታው ውጊያ አደካክሞናል፡፡ ውጊያው እስከ ጠዋቱ 2 ሰዓት ድረስ ቀጠለ እናም እሁድ ነበር፡፡ እምነቴንና መንፈሳዊ ብቃቶቼን ሁሉ ብጠቀምም እንኳ፥ ውጤታማ አልነበርሁም፡፡

ስለዚህ፥ ከ**ጌታ** ዘንድ እርዳታ ከመጠየቅ በቀር ምንም ምርጫ አልነበረኝም፡፡ ወደ **ጌታ** ተማጸንሁ፥ ነገር ግን ጌታ ሁሉንም እርኩሳን መናፍስት በእምነቴ እንዳሸንፋቸው ፈለገ፡፡ የእሁድ አገልግሎት እየቀረበ ስለነበረ፥ ትዕግስት አጣሁና **ጌታ**ን አስጨነቅሁት፡፡ *"**ኢየሱስ** ሆይ፥ እርዳኝ! እለምንሀለሁ! ወይ ጣልቃ ግባ አልያም ሊቀመላእክት ሚካኤልን እንዲያግዘኝ ላከው፡፡ እባክህ ፍጠን! ማንም ቢረዳን ችግር የለውም፡፡"* እኔ በአስቸኳይ ስማጸን፥ ዮሴፍ፣ ጁ ኢዩንና ሀክ ሱንግ የእርዳታ ጥሪውን ተቀላቀሉ፡፡ ሁላችንም በእንባ ተሸፍነን ነበር፡፡ ሰውነታችን በላብ ተዘፍቋል፡፡ ትንሽ ቆይቶ ብዙ መላእክት ከገነት መጥተው ከፊታችን ቆሙ፡፡

*እርዳታ ከሊቀ መላእክት ሚካኤል


ከብዙ መቶዎች እስከ ብዙ ሺህዎች የሚገመቱ መላእክት መጡ፡፡ መምጣታቸውን ቀጥለው በዙሪያችን ተሰበሰቡ፡፡ በእነርሱ ተከብበን ነበር፡፡ መላእክቱ ይጋርዱንና በሚያንጸባርቅ የብርሃን ደርብ ይሸፍኑን ጀመር፡፡ እርኩሳን መናፍስቱ ለማጥቃት ሞከሩ፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ፥ አስደናቂ ደማቅ ብርሃን ከሰማይ ሲመጣ አየሁ፡፡ ሊቀመላእክት ሚካኤል ወደ እኛ እየቀረበ ነበር፡፡ ነጭ ፈረስ ይጋልብ ነበር፥ ክንፍ ያለው ፈረስ፡፡ ሲጋልብ፥ ታላቅ የሆነ አንጸባራቂ ሠይፍ ያወናጭፍ ነበር፡፡ በአንድ ጊዜ ስንዘራ፥ የተወሰኑትን እርኩሳን መናፍስት ቀላቸው፡፡



የተቀሩት እርኩሳን መናፍስት ግራ በመጋባት ከሊቀመላእክት ሚካኤል ፊት መበታተን ጀመሩ፡፡ ሚካኤል በቤተክርስቲያን አባላቱ አጠገብና ዙሪያ ተመላለሰ፡፡ በቤተክርስቲያኑ አባላት አጠገብ ሲመላለስ፥ እርኩሳን መናፍስቱን አጥቅቶ ቀላቸው፡፡ እርኩሳን መናፍስቱ ሲቀሉ፥ ጥቁር ጭስ ከውስጣቸው ይወጣና ይጠፋሉ፡፡

መላእክቱ የቤተክርስቲያኑን አባላት ለመከላከል ክንፋቸውን ዘረጉ፡፡ ሚካኤል መጋለቡንና እርኩሳን መናፍስቱን በሠይፍ ማጥቃት ቀጠለ፡፡ እርኩሳን መናፍስቱ እየጮሁ ግራ በመጋባት ሸሹ፡፡ ፈጽሞ ተደበላልቀባቸው ነበር፡፡ **ኢየሱስ** ተገለጠና ሁኔታውን ተከታተለ፡፡

**ሊ ሀክ ሱንግ፡** *እርኩሳን መናፍስቱን በቅዱሱ እሳት ማቃጠል



ብዙ እርኩሳን መናፍስት ወደ እናቴ ሰውነት ገቡ፡፡ እርኩሳን መናፍስቱን ከእርሷ በማስወጣት ስናግዝና ስናስወጣ የጸሎት ሰዓታችን አጠረብን፡፡ ምንም እንኳ ሁኔታው የተደበላለቀ ቢሆንና እናቴም በሥቃይ ውስጥ ብትሆንም፥ መጋቢው ራሱን አረጋግቶ ጠንካራና ውጤታማ አገልግሎትን መምራት ችሎ ነበር፡፡ የመጋቢው ቃላት የተዋቀሩና በ**እግዚአብሔር** ኃይል

የተሞሉ ነበሩ፡፡ በመሆኑም፥ የጸሎት ጉባኤያችን ሲጀመር፥ የ**መንፈስ ቅዱስ** እሳት መገኘት ኃያል ነበር፡፡

ዛሬ ከሌላው ቀን በባሰ በጣም ቀዝቃዛ ነበር፡፡ በመሆኑም፥ በጥሩ ስሜት ውስጥ አልነበርሁም እናም አዕምሮዬ በፍርኃት ሀሳቦች ተሞልቶ ነበር፡፡ ቢሆንም፥ ልክ ጸሎቴን እንደጀመርሁ፥ የ**መንፈስ ቅዱስ** ኃያል እሳት ወደ ልቤ ውስጥ ገባ፡፡ እሳቱ በክብ ቅርጽ ነበር የሚንቀሳቀሰው፡፡ እሳቱ አንዴ ልቤ ከገባ በኋላ፥ ከሙቀቱና ከብርታቱ የተነሳ ማላብ ጀመርሁ፡፡ ብዙ መላእክት ከሰማይ ሲመጡ ተመለከትሁ፡፡ ከመሠዊያው በላይ ባለው መስቀል በር ውስጥ ነበር የሚመጡት፡፡ እርኩሳን መናፍስቱ እስካሁን በእናቴ ሰውነት ውስጥ ሆነው እያሠቃዩአት ነው፡፡ ህመሙ እናቴን መሬት ላይ ያንከባልላታል፡፡ እናቴ እርዳታ አልባ ነበረች፡፡ ሥቃይዋን ለማቆም ምን ማድረግ እንዳለባት አታውቅም ነበር፡፡ ያለማቋረጥ ትጮህለች ታቃስታለች፡፡ ሁሉም የቤተክርስቲያኑ አባላት እርኩሳን መናፍስቱን ለማስወጣት እየተሳተፉ ነው፡፡ ውጊያው እስከ ንጋት ቀጠለ፡፡ ደስ የሚለው፥ በሊቀመላእክት ሚካኤል እርዳታ፥ እርኩሳን መናፍስቱን ማሸነፍና የቀኑን አገልግሎት መጨረስ ቻልን፡፡

ሊቀመላእክት ሚካኤልና **ኢየሱስ** ወደ ገነት ሲመለሱ፥ በየግላችን ለመጸለይ ጊዜ አገኘን፡፡ በልሳን ስጸልይ ሳለሁ፥ ከጥግ ላይ ጥቁር ጥላ ሲሳብ አየሁ፡፡ በሰከንዶች ውስጥ፥ ትልቅ ዳይኖሰርን የመሰለ እርኩስ መንፈስ ተገለጠና ወደ እኔ መሮጥ ጀመረ፡፡ ወደ እኔ እየመጣ፥ አናቱ ተከፍሎ ተከፈተና ከውስጡ ቀጫጭን ቀያይ ነገሮች በጭንቅላቱ ውስጥ ሲርመሰመሱ ማየት ቻልሁ፡፡ ሁኔታውን እየቃኘሁ ሳለ፥ ነፍሴ ሰውነቴን ጥላ እየወጣች እንዳለ ተሰማኝ፡፡ በዚያች ሰከንድ፥ በአፍታ መዘናጋት፥ በእርኩስ መንፈስ ተጠቃሁ፡፡ በድንገት ነቅቼ ወደ **ጌታ** ተጣራሁ፡፡ *"**ኢየሱስ** ሆይ፥ እርዳኝ! ፈጥነህ ናና አድነኝ!"* **ጌታ** በቅጽበት መጣና የዳይኖሰሩን ጭራ ይዞ ወረወረው፡፡ እርኩሱ መንፈስ እየጮኸ ሸሸ፡፡

ቀጥሎ፥ የጨለማው ጥላ እርኩሳን መናፍስት በቡድን ሆነው ሰደርያዬን ጎተቱት፡፡ መንጭቄ ለማስለቀቅ ሞከርሁ፥ ነገር ግን አልቻለሁም እናም ጸሎቴ ተስተጓጎለ፡፡ በራሴ ብርታት እንደማላሸንፋቸው እንደተረዳሁ፥ የቅዱሱን እሳት ኃይል መጥራት ጀመርሁ፡፡ *"ቅዱሱ እሳት! ቅዱሱ እሳት!"* እያልሁ መጮህ ጀመርሁ፡፡ በድንገት፥ የሚንበለበል እሳት ከሰውነቴ ወጣና የጨለማውን ጥላ መናፍስት በታተናቸው፡፡

በልሳን መጸለይ ስጀምር፥ ዝማሬ መስማት ጀመርሁ፡፡ በመዝሙሩ ምት መጸለይና መደነስ ጀመርሁ፡፡ የብረት ጭንብል ያጠለቀ እርኩስ መንፈስ ወደ እኔ ሲቀርብ አየሁ፡፡ መጸለዬን ቀጠልሁ እናም እጆቼ በመዝሙሩ ምት እየተንቀሳቀሱ ነበር፡፡ ባለ ብረት ጭምብሉ እርኩስ መንፈስ ቀረበ እናም ጭምብሉን አወለቅሁበት፡፡ ጭምብሉን ሳወልቀው፥ የትል መዓት ከውስጡ ወጡ፡፡ ሁሉንም በቅዱሱ እሳት

አጠፋኋቸው፡፡ እርኩሳን መናፍስቱን እንዳሸነፍሁ፥ **ጌታ** መጣና ከገነት ከረሜላ ሰጠኝ፡፡ በጣም ጣፋጭና የሚጥም ነበር፡፡ ሆኖም፥ በችኮላ በልቼው ማሳል ጀመርሁ፡፡

**ሊ ዩ ክዩንግ፡** *ዩ ክዩንግ ዘመዶቿ በሲዖል እሳት ሲሰቃዩ በድጋሚ አየች

**ኢየሱስ** እጄን ይዞ፥ *"**ዩ ክዩንግ፥ ገነትን መጎብኘት ትፈልጊያለሽ?**"* ብሎ ጠየቀኝ፡፡ ጥያቄውን እንደ ሰማሁ፥ ልቤ በደስታ ተሞላ፡፡ በአየር ውስጥ በረርን፡፡ በህዋውና በከዋክብት ክምችት ውስጥ እያለፍን ወደ ፊት መብረራችንን ቀጠልን፡፡ ሆኖም ግን፥ በጨለማ ሸለቆ ውስጥ በረርንና ወደ ግራ በሚወስደው በኩል ታጠፍን፡፡ የግራው መንገድ ወደ ሲዖል ነው የሚወስደው፡፡ ገነት በቀኝ በኩል በሚወስደው መንገድ ነው፡፡

**ኢየሱስ** ሲዖልን እንጎብኝ ብሎ ቢጠይቀኝ እሺ እንደማልለው አውቋል፡፡

ገነትን መጎብኘት እወዳለሁ፡፡ በማንኛውም ጊዜ ገነትን የመጎብኘት እድል ሲያጋጥመኝ፥ በጣም ነው የምደሰትበት፡፡ አሁን ለዘላለም እዛ ብኖር እመኛለሁ፡፡ ነገር ግን ሲዖል አስቀያሚና አስፈሪ ቦታ ነው፡፡ ልጎበኘውም ሆነ ላስበው የማልፈልገው ቦታ ነው፡፡ **ጌታ** ገነትን መጎብኘት እንደምፈልግ ሲጠይቀኝ፥ የተጠመድሁ መሰለኝ፡፡ ሲዖልን የመጎብኘት አጋጣሚ ውስጥ ባለፍሁ ጊዜ ሁሉ፥ በእንቅልፍ አልባ ሌሊቶች ውስጥ አልፋለሁ፡፡ ሰውነቴ ከሲዖል በተራረፉ ህመሞች ውስጥ ያልፋል፡፡

እያሰብሁ ሳለሁ፥ ዘመዶቼ ሲጎተቱ አየሁ፡፡ የሆነ ረዥም ፍጥረት ወደሚጠብቃቸው ቦታ እንዲሰለፉ ተገደዋል፡፡ እርኩሱ ፍጥረት በጣም ረዥም ከመሆኑ የተነሳ የሲዖል ጫፍ የደረሰ ነው የሚመስለው፡፡ ከግዙፉ ፍጥረት ፊት ለፊት ረዣዥም መስቀልያ ቅርጽ ያላቸው ዛሮች ቆመዋል፡፡

ሌሎቹ እርኩሳን መናፍስት ዘመዶቼን መስቀሎቹ ላይ ለመስቀል እየተዘጋጁ ነው፡፡ ረዥሙ ፍጥረት ንጉሱን ይመስላል፡፡ ባዘዘ ቁጥር፥ ታዛዦቹና ዘመዶቼ በፍርሀት ይንቀጠቀጣሉ፡፡ የእርኩሱ ፍጥረት ግዙፍ መጠን፥ ነጎድጓዳማ ድምጽ፥ እናም አቋሙ አስፈራኝ፡፡ አለቀስኩ፡፡

በመጨነቅ ስሜት፥ አያቴ እንባዬን አበሰችልኝ፡፡ በሲዖል ከማንም ሰው ጋር ለመያያዝ ተፈቅዶልኝ አያውቅም ነበር ነገር ግን፥ በዚህ ሰዓት፥ አያቴ ወደ እኔ ቀርባ እንባዬን እንድታብስ ተፈቀደላት፡፡ እንባዬን ስትጠርግልኝ፥ የእጇ ቅዝቃዜ ተሰማኝ፡፡ እንደ በረዶ ቀዝቃዛ ነበር፡፡ *"ዩ ክዩንግ፥ ለምንድ ነው ተመልሰሽ ወደዚህ ስፍራ የመጣሽው? ይህ የሚኀበኝ ዓይነት ስፍራ አይደለም፡፡ አሁኑኑ ሂጂ፡፡"* እየተናገረች፥ አብራኝ አነባች፡፡

**ኢየሱስ** ወደ **ራሱ** ስቦ አቀረበኝና ቀይ ፍሬ በእጄ ሰጠኝ፡፡ እንድበላውና ከጨረስሁ በኋላ ማልቀሴን እንዳቆም ነገረኝ፡፡ **ጌታ** ከገነት ነበር ያመጣው፡፡ የገነትን ፍሬ እየበላሁ ሳለ፥ አያቴ አፈጠጠችብኝ፡፡ **ጌታ**ም፥ "***ዩ ክዩንግ፥ በአያትሽ ከተነካሽ በኋላ እንዴት ተሰማሽ?***" አለኝ፡፡ እኔም፥ "***ጌታ** ሆይ፥ የአያቴ እጅ በጣም ቀዝቃዛ ነው፡፡ የበረዳትና የምትንቀጠቀጥ ነው የሚመስለው፡፡"*

አያቴ እያለቀሰች በ**ጌታ** ፊት አንገቷን ደፋችና እንዲህ አለችው፥ *"ውዴ **ኢየሱስ** ሆይ፥ የልጅ ልጄን፥ ዩ ክዩንግን ስላመጣሀት አመሰግንሀለሁ፡፡"* ከአያቴ አጠገብ ቆሞ የነበረው አጎቴም፥ *"ዩ ክዩንግ፥ እናትሽ የት ናት?"* ብሎ ጠየቀኝ፡፡ እኔም፥ *"እናቴ በከባድ ህመም ውስጥ ናት፡፡ መጸለይ እንኳን አትችልም፡፡ ቤተክርስቲያን ውስጥ መተኛት ግድ ሆኖባታል፡፡"* አልሁት፡፡ አጎቴም፥ *"የእውነት? ጤናና ደኀና እንድትሆን እመኝላታለሁ፡፡"* አለኝ፡፡ ስለ እናቴ ተጨንቆ ነበር፡፡ አያቴንና የአክስቴን ልጆች ከአጠገባቸው ቆመው ይታዩኛል፡፡ አያቴ ወደዚህ ስፍራ ከመምጣቱ በፊት ምን ዓይነት ስቃይ ውስጥ እንደነበረ አላውቅም ግን ቆዳው ከሰውነቱና ከፊቱ ላይ ተጋግጧል፡፡

*ፊታቸው እንደተጨማደደ፥ አጎቴና የአክስቴ ልጅ ስጋታቸውን ገለጹ፡፡ "ዩ ክዩንግ፥ ለምን ጉዳይ ነው እዚህ የመጣሽው? አሁኑኑ ከዚህ ስፍራ ሂጂ!"* አያቴ እያለቀሰች፥ በድጋሚ ተናገረች፡፡ *"ዩ ክዩንግ፥ እኔም ይህን ቦታ ትቼ መሄድ እፈልጋለሁ፡፡ ከ**ኢየሱስ** ጋር ስለሆንሽ፥ እባክሽን **ጌታ** እኔንም ከአንቺ ጋር እንዲያወጣኝ ጠይቂው፡፡ ሲዖል የማይቋቋሙት ስቃይና ህመም ቦታ ነው፡፡ አጅግ አስፈሪ ስፍራ ነው፡፡ እባክሽ ከዚህ ቦታ እንድወጣ እርጂኝ፡፡"*

*አያቴ ስታለቅስና ስትማጸን አየኋት፥ **ጌታ**ንም ጠየቅሁት፥ "**ኢየሱስ** ሆይ፥ እባክህን ከዚህ ቦታ አውጣት፡፡ ስለአያቴ በጣም ሀዘን ተሰምቶኛል፡፡"* ወደ **አብ**ም ጮኽኩ፥ *"አንድም ሦስትም የሆንክ **አምላኬ** ሆይ፥ እርዳኝ!"* **ኢየሱስ**ም መለሰ፥ "***ዩ ክዩንግ፥ እየረፈደ ነው፡፡ እንሂድ፡፡ ለዛሬ ይበቃል፡፡***" እጄን ያዘኝ እናም በዚያ ቅጽበት አጎቴ ሲጮህ ሰማሁት፥ የአክስቴም ልጅ ሲጮህ ሰማሁ፥ *"ዩ ክዩንግ፥ እባክሽ እርጂኝ! እባክሽ! አድኚኝ!"* ሲጮህ ሳለ፥ ቀይ፣ ሰማያዊና ቢጫ እባብ በእግሩ ላይ ተጠመጠመ፡፡ እባቡ ቀስ እያለ ወደ ጭንቅላቱ ተሳበ፡፡

የአክስቴ ልጅ ጩኸቱን ቀጠለ፡፡ *"ዩ ክዩንግ፥ ወደ ምድር ስትመለሽ፥ ዘመዶቻችንን ሁሉ ሰብከሽ በ**ኢየሱስ** እንዲያምኑ ንገሪያቸው፡፡ ቤተክርስቲያን በታማኝነት እንዲከታተሉ ንገሪያቸው! የፈለገ ቢሆን ወደዚህ ስፍራ እንዳይመጡ ንገሪያቸው! ገባሽ?"* እየጮኸ እያለ፥ ስለታም ቀንድ ያለው እርኩስ መንፈስ ወደ እርሱ ሮጠና በብስጭት፥ *"ምን እያልክ ነው?"* አለው፡፡ በጣም የተናደደ ይመስላል፡፡ እርኩሱ መንፈስ የአያቴን ደረት በቀንዱ ወጋት፡፡ አያቴ እየጮኸች ወደ መሬት ወደቀች፡፡

እኔም በብስጭት፥ *"አያቴ፥ አያቴ! ጋኔል፥ እንዲህ አድርገህ የምተውህ እንዳይመስልህ! አያቴን አትንካ!"* ብዬ ጮኽኩኝ፡፡ እየጮህኩኝ፥ በቤተክርስቲያን እንደሆንሁና እየጸለይሁ እንዳለሁ አወቅሁ፡፡ **ኢየሱስ** ራሴን መታመታ አደረገኝና እያለቀስሁ ስጸልይ አጽናናኝ፡፡

**እህት ቤይክ ቦንግ ንዮ፡** *ሊቀመላእክት ሚካኤል ነጭ ፈረስ እየጋለበ

በአገልግሎት ሰዓት፥ ብዙ እርኩሳን መናፍስት ተሰልፈው ወደ ሰውነቴ ገቡ፡፡ ግራ እጄን አደነዘዙት፡፡ ምን እንደሚመስሉ ላያቸውም ሆነ ልለያቸው አልቻልሁም፡፡ በሰውነቴ ውስጥ መደላደላቸውን ቀጠሉ፡፡ በከባድ ህመም ውስጥ ሆኜ መሬት ላይ እየተንከባለልሁ ነበር፡፡ መጋቢውና ወይዘሮ ካንግ ህዩን ጃ ብጥብጡን አይተው ጸሎታቸውን አቁመው እኔን ለመርዳት መጡ፡፡ ሁሉንም እርኩሳን መናፍስት ከሰውነቴ ውስጥ ማስወጣት ከባድ ነበር፡፡ ቡድኑ በውጊያ ብዙ ጊዜ አሳለፈ፡፡

ከእርኩሳን መናፍስቱ ጋር የነበረው ውጊያ ሌሊቱን ሙሉ ቀጠለ፡፡ በሰውነቴ ውስጥ ያሉት እርኩሳን መናፍስት በኃይል ተቃወሙ፡፡ መጋቢውና ባለቤቱ እርኩሳን መናፍስቱን አንድ በአንድ ያስወጣሉ፡፡ ሌሊቱን ሙሉ ጸለዩ፡፡ በውስጤ ብዙ እርኩሳን መናፍስት ነበሩ፡፡ እርኩሳን መናፍስቱ ሌሊቱን ሙሉ አሰቃዩኝ፡፡ ሰውነቴ በሁሉም አቅጣጫ ተጥመለመለ፡፡

በመጨረሻም ቡድኑ እርኩሳን መናፍስቱን ሁሉ ወደ ንጋት ላይ አስወጧቸው፡፡ በመጀመሪያ ወደ ሰውነቴ ውስጥ ሲገቡ መልካቸውንም ሆነ ቅርጻቸውን ለማየት አልቻልሁም ነበር፡፡ ሆኖም ግን፥ አንድ በአንድ ሲወጡ፥ መልካቸውን በግልጽ ለማየት ቻልሁ፡፡

ብዙ ዓይነት እባቦችን ተመለከትሁ፥ አንዳንዱ ረዣዥም አንዳንዱ ደግሞ አጫጭር ነበሩ፡፡ እንዲሁም የሚቀፉና አስቀያሚ ነፍሳትንም አየሁ፡፡ በተጨማሪም፥ ወጣት ልጅ የምትመስል ቀንድ ካላቸው ሌሎች እርኩሳን መናፍስት ጋር አየሁ፡፡ ሁሉም አንድ በአንድ ወጡ፡፡ ተኝቼ መጸለይ ነበረብኝ፡፡ **ጌታ** ከብዙ መላእክት ጋር ሊጎበኘን መጣ፡፡ **መንፈስ ቅዱስ**ም እንዲሁም መጥቶ ቅዱሱን እሳት ሰጠኝ፡፡ የእሳት ኳስ ወደ ልቤ ገባ፡፡

የእሳቱ ኳስ ወደ ልቤ እንደገባ፥ ሰውነቴ ከምቋቋመው በላይ ጋለ፡፡ ከብርድ የተነሣ እየተንቀጠቀጥሁ ነበር ነገር ግን ቅዱሱን እሳት ስቀበል ሞቃት ሆንሁኝ፡፡ በድንገት፥ የእሳቱ ሙቀት እየጋለ እኔ በኃይል በልሳን እጸልይ ነበር፡፡ ***"ቦንግ ንዮ፥ ከባድ ቀን እንዳሳለፍሽ አውቃለሁ፡፡ ስለዚህ፥ ዛሬ ወደ ሲዖል ልወስድሽ አልፈልግም፡፡ ሰውነትሽ እየታመመ እንቺ ግን እየጸለይሽ ነው፡፡ ነይ እንሂድ፡፡ ህመምሽን ላሳርፍልሽ እፈልጋለሁ፡፡"*** **ጌታ**ም ከዚያ ወደ ገነት ስንበር እጄን ያዘው፡፡

ውቂያኖሱንና እንደ በረዶ ነጭ የነበረውንም ተራራ ጎበኘን፡፡ ዙሪያውን ያሳየኝ ቀጠለ፡፡ ***"እጅሽ እንደ በረዶ ቀዝቅዟል፡፡ በህመም ውስጥ ሳትሆኚ አልቀረሽም፡፡ ይሄ የሰይጣን ሥራ ነው፡፡"*** **ጌታ** እጄን ያዘኝና በዚያ ቅጽበት ጥቁር ጭስ በእባብ ቅርጽ ከእጄ ሲተን አየሁ፡፡ ጭሱ ከዛ ጠፋ፡፡ ከ**ጌታ** የሞቀ ንክኪ በኋላ፥ እጄ ሞቃት ሆነ፡፡ ጌታም በእርጋታ ተናገረ፥ ***"ቦንግ ንዮ፥ አካላዊ ሰውነትሽ በጣም ተዳክሞ ዝሏል፡፡ ጋደም በይና እዚህ እረፊ፡፡ ዛሬ ጥሩ ሥራ ነው የሠራሽው፡፡"***



በገነት ብዙ እረፍት ካገኘሁ በኋላ፥ እንደበረታሁ ተሰማኝ፡፡ ከመላእክቱም ጋር ቆይታ አደረግሁ እናም ጥሩ ጊዜ አሳለፍሁ፡፡ ወደ ቤተክርስቲያን ተመለስሁና ሊቀመላእክት ሚካኤል እርኩሳን መናፍስቱን ሲያድን አየሁ፡፡ ነጭ ፈረስ እየጋለበ ነበር እናም በቤተክርስቲያኑ አባላት መሀከል ይመላለስ ነበር፡፡ መጋቢው እርኩሳን መናፍስቱን ከእኔ ውስጥ ስላስወጣ ሌሉትን የሚጸልይበት አጋጣሚ አልነበረውም፡፡ ስለዚህ፥ ማለዳ ላይ ለመጸለይ ተዘጋጀ፡፡ ወደ ህምሳ የሚሆኑ እርኩሳን መናፍስት መጋቢውን ከበውት አየሁ፡፡ መጋቢውን የሚያጠቁበትን አጋጣሚ እየጠበቁ ነበር፡፡ ሊቀመላእክት ሚካኤል ወደ መጋቢው ቀርቦ፥ *"እናንተ አስቀያሚ እርኩሳን መናፍስት፥ እንዴት ብትደፍሩ እዚህ መጥታችሁ ትሰበሰባላችሁ!"* ብሎ ጮኸ፡፡ የወርቅ ብርሃን የመሰለውን ሠይፉን አስወነጨፈ፡፡ ሊቀመላእክት ሚካኤል አንጸባራቂ ወርቃማ ሠይፉን አስወነጨፈ እናም በመጋቢው አጠገብ የነበሩ እርኩሳን መናፍስት ሁሉ አንገታቸው ተቆረጠ፡፡ ሁሉም አመድ ሆኑ፡፡ እርኩሳን መናፍስቱ ወደ ሲዖል ሲሸሹ ከአመዳቸው ጭስ ሲወጣ አየሁ፡፡ እይታው ደማቅ ነበር፡፡ ጁ ኢዩንን ከሌሎቹ ወጣቶች ጋር ሳነጻጽራት፥ እርሷ በተለየ ደማቅ፥ ማራኪ እናም ሁልጊዜም ደስተኛ ነበረች፡፡

የመጋቢው ቤተሰብ የገንዘብ ችግር እያጋጠመው ነው፡፡ ምንም እንኳ ሁል ጊዜ በድህነት ውስጥ ቢኖሩም፥ ልጆቻቸው በስርዓትና በአግባብ ነው ያደጉት፡፡ ስለሁኔታቸው ፈጽሞ አያጉረመርሙም፡፡ አብዛኞቹ የቤተክርስቲያናችን አባላት ከሌሎች ቤተክርስቲያኖች የተባረሩ ናቸው፡፡ ሁሉም በዚህ ተረጋግተው በእምነት የጸኑ ሆነዋል፡፡

**ኢየሱስ** ወደ ቤተክርስቲያን ተመለሰና ከረዥሙ የጸሎት ጊዜ የተነሣ ተዳክማ ተኝታ የነበረችውን ጁ ኢዩን ለማንቃት እየሞከረ ነበር፡፡ **ጌታ**ን ስመለከተው፥ ጁ ኢዩን ልትነቃ ስላልቻለች በእንባ ተሞላሁ፡፡ ለጁ ኢዩን አዘንሁላት፡፡ **ጌታ**ም፥ ***"ጁ ኢዩን፥ ጠቃጠቆ፥ እኔ ነኝ፥ ጌታ፡፡ ወደ ገነት ልወስድሽ ነው የመጣሁት፡፡ ተነሽ ጁ ኢዩን፡፡ የእኔ ውድ ጁ ኢዩን፥ በገነት ብዙ ቦታዎችን ላሳይሽ መጥቻለሁ፡፡ ጁ ኢዩን፥ አንገትሽን ቀና አድርጊ፡፡"*** **ጌታ** በእርጋታ ሊያሳምናት ሞከረ፡፡

ጁ ኢዩን ለ**ጌታ** ምላሽ አለመስጠቷ በጣም ተዳክማ መሆን አለበት፡፡ **ጌታ** በረዥሙ ተነፈሰ፡፡ ***"አዝናለሁ፡፡ ስለጽኑ ጸሎትሽ ዛሬ ገነትን ላሳይሽ ነበር፡፡ የእውነት አዝኛለሁ፡፡"*** በእርጋታ ጀርባዋን አሻሸቷት ሄደ፡፡

በሊቀመላእክት ሚካኤል የተባረሩት እርኩሳን መናፍስት ወይዘሮ ካንግ ህዩን ጃ ውስጥ ለመግባት ተመለሱ፡፡ ሁሉም ህምሳዎቹም ተቀናጅተው ከበቧት፡፡ ወደ ሰውነቷ የሚገቡበትን አጋጣሚ ጠበቁ፡፡ እንደ መታደል ሆኖ፥ ሊቀመላእክት ሚካኤል ወደ አጠገቧ መጣና፥ *"አልተማራችሁም?"* ብሎ ጮኸ፡፡ ሚካኤል አንድ ጊዜ ሠይፉን አወናጨፈ እናም የእርኩሳን መናፍስቱ ጭንቅላት ተቆረጠ፡፡ ተበታተኑና አመድ ሆኑ፡፡

መጋቢው፣ ባለቤቱና ዲያቆን ሺን በትጋት ሲጸልዩ፥ መላእክት በቡድን መጥተው በክንፎቻቸው ጋረዷቸው፡፡ ሊቀመላእክት ሚካኤል እርኩሳን መናፍስቱን መዋጋቱን ቀጥሎ ሁሉንም እርኩሳን መናፍስት በወርቃማ ሠይፉ ቀላቸው፡፡

## ==== ቀን 29 ====       (2ˢ ቆሮንጦስ 6:1-2)   *የዮሴፍ ምኞት

የጸሎት ዘመቻው ለማብቃት አንድ ቀን ብቻ ነው የቀረው እናም እኔ ገና በመንፈስ አልነቃሁም። ተጨነቅሁ እናም ደግሞ ተረበሽሁ። እንባ በፊቴ ይጎርፍ ጀመር። በፊት፥ ቡድናችን ጸሎቱን ሲጨርስ፥ ስለመንፈሳዊ መነቃቃታቸው የሌሎችን ምስክርነት እሰማ ነበር። በእነርሱ ከመቅናት ውጭ ምንም ማድረግ አልቻልሁም። **ጌታ** አሁንም ዝም ብሏል እናም ከ**ጌታ** ምንም ነገር አልሰማሁም። ጁ ኢዩንና ሌሎች የምእመናን አባላት ለምን በመንፈስ እንዳልነቃሁ አስረዱኝ። ለመጋቢነት አገልግሎት እንደተጠራሁ ነገሩኝ። ስለዚህም፥ **እግዚአብሔር** እስኪረካ ድረስ መጸለይ አለብኝ። መጋቢዎች ለምን ለረዥም ጊዜና በኃይል መጸለይ እንዳለባቸው አልገባኝም። አባቴ፥ መጋቢ ኪም እርሱም በመንፈስ አልነቃም ነበር። ምንአልባት ልቡ በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ይሆናል ብዬ አሰብሁ። ሆኖም ግን፥ መጋቢው

ምንም ዓይነት የተስፋ መቁረጥ ስሜት አይታይበትም፥ ይልቁንም እኔን በሚያጽናኑ ቃላት ያበረታታኛል፥ “*እንጸልይ እናም ትዕግስተኛ እንሁን።*”

በጸሎት ጊዜዬ፥ በንስሐ እንባ ታጠብሁ። ረዘም ላለ ጊዜ አለቀስሁ። “***ጌታ** ሆይ፥ እባክህ መንፈሳዊ ዓይኖቼን ክፈት! የሆነ ነገር አሳየኝ፥ እባክህ?*” በልሳን ስጸልይ፥ በጨለማ መሀል ሰማያዊ ብርሃን ብልጭ ሲል አየሁ። ከዛ ተሰወረ። ጸለይሁ እናም ሰማያዊውን ብርሃን በድጋሚ ላየው ጠበቅሁ። ልቤ ጓጉቶለት ነበር። ሆኖም ግን፥ ሰማያዊውን ብርሃን አላየሁም። ቅር ተሰኝቼ ነበር ግን አልተናደድሁም።

**ዲያቆን ሺን ሱንግ ኪዩንግ፡**    *የዲያቆን ሺን፥ ሱንግ ኪዩንግ እና ጁንግ ሚን መለወጥ

ምንም እንኳ ረዘም ላለ ጊዜ በእንባ ብጸልይም፥ ምንም ራእይ አላየሁም። የጸሎት ምሽቶቹን ሳስታውስ፥ ያ በራሱ ተአምር ነበር። ያለ **ጌታ** እርዳታ፥ የማይቻል በሆነ ነበር። ለጸሎት የነበረኝ ትጋት የ**እግዚአብሔር** ጸጋና ርኅራኄ ውጤት ነው። የአባላቱን የመንፈሳዊ መነቃቃትና በገነትና በሲኦል ያደረጉትን ጉብኝት ስሰማ፥ ሀፍረት ተሰማኝ እናም እምነቴን ተጠራጠርሁ። እምነቴ በአብዛኛው ለታይታ ነበር ከሌሎቹ ጋር ለመስተካከል። በቅርቡ፥ አጽንቼ ኃጢአቴን በንስሐ እንባ እየተናዘዝሁ ነው።

ባለቤቴ፣ ልጄ ጁንግ ሚንን በቅርበት እየተከታተለው ነው። ባህሪው ሙሉ በሙሉ ተቀይሯል። ጁንግ ሚን ከእኔ በፊት ሲኦልን የመጎብኘት አጋጣሚውን አግኝቷል። ልጄ አተኩሮ እያየኝ እንዲህ አለኝ፥ “*እማማ፥ ሲኦልን ልትጎበኚና ምን እንደሚመስል ማወቅ ይኖርብሻል።*” በአጽንኦቱ ስለተነካሁ ራሴን ማረጋጋት ነበረብኝ።

ልጄ፥ ጁንግ ሚን፥ ገና ጀማሪ ትምህርት ቤት ለመግባት እየተዘጋጀ ያለ ነው። በኢንተርኔት ጨዋታዎች እና ካርቱን ፊልም ሱስ የተጠመደ ነበር። ሆኖም ግን፥ ከሚንበለበለው ቅዱስ እሳት ጋር በ**መንፈስ ቅዱስ** ከተገናኘ በኋላ፥ ዳግም ተወለደና መንፈሳዊ ስጦታዎችን አገኘ። ለአንድ ወር ያህል ቴሌቪዥን አይቶም ሆነ ጨዋታዎችን በኢንተርኔት ተጫውቶ አያውቅም። አሁን ራሱን ለጸሎት አትግቷል፥ እጁን ወደ ላይ አድርጎ ለሦስት ሰዓታት ያህል በቀላሉ መጸለይ ይችላል። አሁን ፍላጎቱ መጋቢ መሆን ነው። መጽሐፍ ቅዱስን በየቀኑ እያነበበና እያጠና ነው። እቅዱ ተሳክቶ ለማየት እመኛለሁ።

**ሊ ሀከ ሱንግ፡**    ***ጌታ** በመስቀል ሲሠቃይ

በጸሎት ውስጥ ሳለሁ፥ ሦስት እርኩሳን መናፍስት እኩል ተገለጡ። ከሦስቱ ውስጥ፥ አንዱ በጣም ጠንካራ ይመስላል። ጠንካራ የሚመስለው መንፈስ ባለ ፈርጣማ ጡንቻ ሰውነት አለው። ሦስት ራሶች ያሉት ረዥም መንፈስ ነበር። መንፈሱ እኔን ለማዘናጋትና ግራ ለማጋባት በዙሪያዬ ሮጠ። ተከትዬው ሮጥሁና እግሩን ያዝሁት። መንፈሱን እንደያዝሁት፥ አሽከረከርሁት። የ**መንፈስ ቅዱስ** እሳት ከእጄ ወጥቶ እርኩሱ መንፈስ ውስጥ ገባ። እርኩሱ መንፈስ ወዲያው ወደ ትቢያነት ተለወጠ። ከዲያቆን ሺን ጀርባ ጥቁር ነገር እንደ ተደበቀ አስተዋለሁ። ይህንንም ጥቁር ነገር በጡንቻማው መንፈስ እንዳደረግሁበት አደረግሁት። ብዙም ሳይቆይ፥ ዳይኖሰር የመሰለ ሌላ እርኩስ መንፈስ መጣ። የራስ ቅሉ ብርግድ ብሎ ተከፈተ። ያለ ርኅራኄ፥ ለብዙ ጊዜ አሽከረከርሁት። ተጋጨና ተሰባበረ። ከተበታተነው ሰውነቱ፥ ብዙ የተለያዩ አስቀያሚ፥ ዘግናኝ ትሎች በፍጥነት እየተሳቡ ወጡ። እንደ መንጋ ሆኑ። ድምጼን ከፍ አድርጌ፥ “*የ**መንፈስ ቅዱስ** እሳት!*” ብዬ ጮኽኩ። እሳት ከሰውነቴ ተተኩሶ ወጣ፥ ሁሉንም እርኩሳን መናፍስትና ትሎቹን አቃጥሎ አጠፋቸው።

እርኩስ መንፈሶቹን ካሸነፍኋቸው በኋላ፥ **ጌታ** ተገለጠ። ወዲያው እንዳየሁት፥ እንባ መጣብኝ። **ኢየሱስ**ን ተማጸንኩት፥ “*እባክህ የሴፍና ጁ ኢዩንን ወደ ገነት ውሰዳቸው።*” **ጌታ**ም መለሰ፥ “***እሺ፥ እወስዳቸዋለሁ።***” በቅጽል ስሜ ጠራኝና፥

*"ሳም፥ ና አብረን ወደ ገነት እንሂድ፡፡"* አለኝ፡፡ የ**ጌታ**ን እጅ ያዝሁና በአበባው ግቢ ደረስን፡፡ ጥሩ ደስ የሚል ጊዜ አሳለፍሁ፡፡

በአበባው መናፈሻ ሳለሁ፥ **ጌታ**፥ *"ሀከ ሱንግ፥ ሌላ ቦታ ልንጎበኝ ያስፈልገናል፡፡ በል አሁን እንሂድ፡፡"* አለኝ፡፡ ወዴት እየሄድን ሊሆን እንደሚችል አሰብሁ፡፡ ወደ 'የ**ጌታ** ቤተክርስቲያን' እንደነበር አስተዋለሁ፡፡ በራእይ፥

**ጌታ**ን ወደ ዝቅተኛ ዳገት ሲሂድ አየሁት እናም ተሰወረ፡፡ በድንገት፥ **ጌታ** በዓይኔ ፊት ተገለጠ፡፡ መስቀል ተሸክሞ ነበር የሚሄደው፡፡ ሰዎች ይመቱት ነበር፡፡ በሰውነቱ ላይ ካሉት ቁስሎችና ስንጥቆች ይደማ ነበር፡፡ በ**ጌታ** አሾፉበት፡፡

የእሾህ አክሊል ደፍቶ ነበር፡፡ ራሱን ከበሱት እሾኾች ደም እንደ ጅረት ይወርድ ነበር፡፡ **ኢየሱስ** እጆቹና እግሮቹን ረዣዥም ሚስማሮች ሲቸነክሩት ሥቃዩን አየሁ፡፡ ከዚያም ሞተ፡፡ የ**ኢየሱስ**ን ስቃይ እያየሁ ድምጼን አሰምቼ አለቀስሁ፡፡ የእሾኽ አክሊሉን፥ በሚስማር መወጋቱን፥ እናም ደምና ውኃ ሲፈስው አየሁ፡፡ **ጌታ** ተገለጠና እንባዬን ከዓይኔ አብሶ በእርጋታ እንዲህ አለኝ፥ *"ሀከ ሱንግ፥ አታልቅስ፡፡"* በራእዩ ያየሁትን መቼም አልረሳውም፡፡

**ሊ ዩ ክዩንግ፡** *የገነትን ፍራፍሬዎች ሁሉ በአንዴ መብላት

ዛሬ እንደሌሎቹ ቀናቶች አይደለም፡፡ **ኢየሱስ** ከጸሎታችን አስቀድሞ በቤተክርስቲያን እየጠበቀን ነበር፡፡ በቤተክርስቲያኑ ከተሰቀለው መስቀል ስር ቆሞ ነበር፡፡ መጸለይ ጀመርሁ፡፡ **ጌታ** ወደ እኔ መጥቶ እጄን ያዘኝ፡፡ ወደ ገነት በረርን፡፡ በገነት እንደደረስን፥ መዘመር ስጀመር **ኢየሱስ** ያየኝ ነበር፡፡ ሦስት መዝሙሮችን ዘመርሁ፡፡ 'አወድሺ፥ አ ነፍሴ ሆይ፣ ተነሱ ከዲያብሎስ ጋር ተዋጉ፣ እናም በ**መንፈስ ቅዱስ** አጥምቅ፡፡' መዝሙሮቹን ደጋግሜ ደጋግሜ ዘመርኳቸው፡፡ **ጌታ** በእርጋታ አጨበጨበና፥ *"የእኔ ውድ ወይዘሪት ሞል ደኅና አድርጋ ትዘምራለች፡፡ አስደሳች ነው፥"* አለ፡፡ አበረታታኝም፡፡

እኔም፥ *"**ጌታ** ሆይ፥ ጉሮሮዬን እያመመኝ ነው እናም ሰምኑን እያሳለኝ ነው፥"* አልሁት፡፡ **ጌታ**ም መልሰ፥ *"የእውነት? አንቺ እንድትታመሚ አልተፈቀደም፡፡ ብርድ አለብሽ? እፈውስሻለሁ፤ አትጨነቂ፡፡"* ሰውነቴን በእጆቹ አሻሸኝና በእቅፉ ውስጥ ያዘኝ፡፡ **ኢየሱስ** ሲያሻሽኝ፥ ሙቀት፥ ርኅራኄ፥ ልስላሴ ተሰማኝ፡፡



*"**ኢየሱስ** ሆይ፥ አፍንጫዬም ተደፍኗል፥"* አልሁት፡፡ **እር**ሱም መልሶ፥ *"ያንንም እፈውሰዋለሁ፡፡"* አለኝ፡፡ **ጌታ** የገነትን ፍራፍሬዎች አመጣልኝ፡፡ በገነት ያሉት ፍራፍሬዎች በምድር ካሉት ጋር ይመሳሰላሉ፡፡ **ጌታ** ያመጣልኝ ፍራፍሬዎች ፐለም(ፕሪም)፣ ፒር(ሸክኒት)፣ አፐል፣ እና ወይን፡፡



(ፐለም፣ ፒር - ኤዢያና አውሮፓ አካባቢ የሚገኙ ፍራፈሬዎች ናቸው፡፡ ፎቶዎቹን ይመስላሉ፡፡) ምንም ቢሆን ግን፥ አንዱም ጣዕሙን ሊወዳደር አይችልም፤ የገነት ፍራፍሬዎች ከመጠን በላይ ጣፋጮች ናቸው፡፡



ልክ ሲገመጥ፥ አፍ ውስጥ ይቀልጣል፡፡ የሚገርም ስሜት ነበር፡፡ **ኢየሱስ**፥ *"ዩ ክዩንግ! የምትፈልጊውን ያህል ፍሬ ብዩና ተፈወሺ፡፡"* አለኝ፡፡ ዬ-ጂ ቀረበችኝና፥ *"እህት፥ ብርድ እንዳለብሽ ሰምቻለሁ፡፡ አትታመሚ፤ ሁል ጊዜም ጤነኛ መሆን አለብሽ፡፡"* አለችኝ፡፡

እኔና **ኢየሱስ** ወደ የ**ጌታ** ቤተክርስቲያን ስንመለስ፥ በከዋክብት ከምችቶች መሀል አለፍን፡፡ ከርቀት፥ ጥቁር ደመና ሲንቀሳቀስ ተመለከትን፡፡ *"**ኢየሱስ** ሆይ፥ እነዚያን ጥቁር ደመናዎች ማየቴን አላስታውስም፡፡ ድንገት እንዴት እዚያ ሊሆኑ ቻሉ? በጣም ጨለማ ናቸው፥ ፈርቻለሁ፥"* አልሁት፡፡ **ጌታ**ም አጽናናኝ፡፡ *"እነዚያ ደመናዎች አይደሉም፡፡ አስቀያሚ እርኩሳን መናፍስት ናቸው፥ እንደ ደመና ተመስለው፡፡ እርኩሳን አሳቾች ናቸው፡፡ አትፍሪ፡፡ እኔ እጠብቅሻለሁ፡፡"* ቤተክርስቲያን ደረስን፡፡

**ጌታ**ም፥ *"ዩ ክዩንግ፥ በርዶሻል?"* ብሎ ጠየቀኝ፡፡ እኔም፥ *"አዎን **ጌታ** ሆይ፥ በርዶኛል፥"* አልሁት፡፡ **ጌታ** ሰውነቴን አሻሸኝ፡፡ ሰውነቴ ሞቃት ሆነ፤ እንደሚነድ እሳት ተሰማኝ፡፡ ተሰነባበትንና በእጃችንም ተሸኛኘን፡፡ እርኩሳን መናፍስቱ ራሴን እየጠበቅሁ አለመሆኔን ሲረዱ አጋጣሚውን ተጠቀሙበት፡፡ ሰውነቴ ውስጥ ገቡ፡፡ ሌሊቱን ሙሉ ስሠቃይ ነበር፡፡ ነገር ግን፥ መጋቢው ከጸለየ በኋላ፥ ዳንሁኝ፡፡

*እህት ቤይክ፥ ቦንግ ንዮ ከሰይጣን ጋር ለሦስተኛ ጊዜ ተገናኘች

የንስሐን እንባ እንዲሰጠኝ ወደ **ጌታ** ስጮህ፥ ከአጠገቤ ተቀምጣ ስተጸልይ የነበረችው፥ እህት ጁ ኢዩን፥ በእንባ ጎርፍ ታጠበችና ንስሐ መግባት ጀመረች:: በዚያ ቅጽበት፥ በአግባቡ ተከተልሁ:: ስጸልይ ሳለ መላእክት ከሰማይ ሲመጡ አየሁ እናም የቤተክርስቲያኑን አባላት በዙሪያችን ሁሉ በጠንካራ የብርሃን መከላከያ ሸፈኑን:: መከላከያው ብርሃን ደማቅ ከመሆኑ የተነሣ ትኩር ብዬ ልመለከተው እንኳ አልቻልሁም:: እርኩሳን መናፍስት በሕብረት መጥተው አጠቁን:: በመከላከያው ብርሃን ሊገቡ አጋጣሚ ይጠብቁ ነበር::

መላእክቱ **ጌታ** እንዳዘዛቸው ሊወስዱኝ መጡ:: “*ጌታ እየጠበቀ ነው፥ ፍጠኝ፥ እየጠበቀን ስለሆነ አሁኑኑ መሄድ አለበን::*” ከመከላከያው ብርሃን እንደወጣሁ፥ እኔና መላእክቱ በአየር ላይ እየበረርን ነበር:: በድንገት፥ ከየት መጣ ሳይባል **ጌታ** ተገለጠና እጄን ያዘኝ:: ከዚያም ያልተረጋጋውን ልቤን አጽናናኝ:: ***“ቦንግ ንዮ፥ ብዙ ጠበቅሽ? እስቲ ሲዖልን እንጎብኝ:: አትፍሪ፤ እጠብቅሻለሁ::”***

**ጌታ** ወደ ሲዖል አብሮኝ ወረደ:: ሳይጠበቅ፥ የእርኩሳን መናፍስት ንጉስ ከፊቴ ቆመ:: በመጀመሪያ፥ ምን ዓይነት እርኩስ መንፈስ እንደ ነበረ አላወቅሁም ነበር:: የምለይበትን አጋጣሚ አላገኘሁም ነበር:: ሆኖም ግን፥ ከእኔ ጋር መነጋገር ሲጀምር አወቅሁት::

“*አንቺ፥ ተመልሰሽ መጣሽ! ዓይኔን ጎድተሽ ጀርባዬን አቁስለሽ:: ክንፎቼን አበላሽሽ:: ምንም ሳይሰማሽ ህይወትሽን ዝም ብለሽ የምትኖሪ ይመስልሻል? ጀርባዬን በማቁሰልሽ ምክንያት ሰውነቴን እያመመኝ ነው:: በድጋሚ እዚህ መጥተሽ ሲዖልን እስክትጎበኚ ድረስ ብዙ ጠበቅሁ:: በመጨረሻም፥ መጥተሻል!*” ጮኸ:: ታዛዦቹን አዘዛቸው፥ “*የቤተሰብ አባሎቿን ወደዚህ አምጧቸው::*” በእርሱ ትእዛዝ፥ ወደ እኛ ፊት እየተጎተቱ ሲመጡ አየሁ:: የቤተሰብ አባላቶቼ የዲያቢሎስ ታዛዦች ለማስፈራራት እያፈጠጡባቸው በፊቱ መጥተው እንዲቆሙ ተደረጉ:: የቤተሰብ አባላቶቼ በፍርሀት እየተንቀጠቀጡ ፊታቸው ገርጥቷል:: ተስፋ በመቁረጥ አየት አደረጉኝ:: **ጌታ** እያየ በዝምታ ቆሟል::

ወንድሜ በሲቃ ጮኸ፥ “*እህት ቦንግ ንዮ፥ እኔ ከምትሁ በኋላ የተወለደችውን ልጄን ለማየት እመኛለሁ!*” እናቴ ወዲያው ቀጥላ፥ “*ልጄ ቦንግ ንዮ፥ ህፃን ልጁ በጣም ነው የናፈቀችኝ:: ልጁ እንደተወለደች እኔ ብዙም ሳልቆይ ሞትሁ::*” አለች:: በስቃይ ውስጥ ስለነበሩ ንግግራቸው ሊቋቋሙት ይከብዳል:: በዚህ ቦታ ሆነው እንዴት ልጆቻቸውን ይናፍቃሉ፥ ህመማቸው እጅግ ዘግናኝ ነበር፥ ሌላ ስሜት እንዴት ሊኖራቸው ይችላል?

ለቤተሰባቸው የነበራቸው መጓጓት ትልቅ ስለነበር፥ ያለውን ሁኔታ መናገር ነበረብኝ:: የእናቴ ልጅ፥ የወንድሜ ሴት ልጅ፥ ከ20 ዓመት በላይ ሆኗቸው ነበር:: ለወንድሜ ክርስቲያን እንዳልሆነች ነገርሁት:: ሆኖም ግን፥ እንደምሰብካትና ወደ ‘የ**ጌታ** ቤተክስቲያን’ እንደማመጣት ቃል ገባሁለት::

*ሰይጣን በቤተሰቤ ላይ በቀሉን ወሰደ

የእርኩሳን መናፍስት ንጉስ ንግግራችንን ሲሰማ፥ በጣም ተቆጣ:: በተለይ ደግሞ ስብከት የሚለውን ደምጽ ሲሰማ በጣም ተናደደ:: “*ምን! ማንን ነው የምተሰብኪው? ስለምንድ ነው የምታወሩት? በአንቺ ምክንያት ምን ያህል እንደታመመሁ ኢታውቂም:: ይህችን ጊዜ ስጠባበቃት ነበር:: ቤተሰቦችሽን የበለጠ ለማሰቃየት ምክንያት ይሆነኛል:: ማሰቃየቱን ጀምሩ!*” አዘዘ:: አገልጋዩ ፍጥረት ለትእዛዙ ምላሽ ሰጠ፥ “*እሺ ጌታዬ፥ ንጉስ ሰይጣን!*” እርኩሱ ፍጥረት ወደ እናቴ፣ የወንድሜ ወንድ ልጅና ወንድሜ ሄደ::

እናቴ ነጭ ለብሳ ነበር፥ ወንድሜና የወንድሜ ልጅ ደግሞ ጥቁር ነበር የለበሱት:: እርኩሱ ፍጥረት ቤተሰቦቼን በተርታ መሬት ላይ አጋደማቸው:: ፍጥረቱ የእናቴን ሰውነት ከእግሯ ጀምሮ ይበሳት ጀመር:: ሚስማሩ በጣም ሹል፣ ረዥምና ጠንካራ ነበር:: “*አህህ! ቦንግ ንዮ፥ አድኚኝ! እባክሽ እርጂኝ!*” ቆዳዋ እተቦጫጨቀ ደም ከመላ ሰውነቷ ይፈስ ነበር:: ጩኸትና ሲቃው በሁሉ ቦታ ይሰማ ነበር:: የጆሮዬ ታምቡር ከከባዱ የሰቆቃ ጩኸት የተነሳ የሚፈነዱ መሰለኝ::

የሲዖል ክንውኖች በህሊናዬ ውስጥ አልተፈጠሩም፤ ልቦለዶችም አይደሉም:: ሲዖል የእውነት ነው:: ያየኋቸው ነገሮች ሁሉ፥ ፊት ለፊቴ የተደረጉ ናቸው:: የሥቃይ እይታዎቹና ድምጾች የእውነት ናቸው:: እንደዚህ ዓይነቱን የተቃወሰ ነገር እንዴት ላስበው እችላለሁ! ውስኗ ትዕግስቴ ፈነዳችና እንደ እብድ ሰው ጮኽኩ:: “***ጌታ** ሆይ፥ እባክህ የሆነ ነገር አድርግ! እባክህ! ፍጠን! ከዚህ በላይ ኢያየሁ ልቋቋመው አልችልም! እባክህ! እናቴን ኢያሰቃያት ያለውን እርኩስ ዲቃላ ለምንድ ነው የማትቀጣው?*” በስሜት ጮኽኩ::

እያነባሁ፥ ጮኽኩ፥ *“እናቴ፥ ምስኪኗ እናቴ! እኔ ሰይጣንን በማበሳጨቴ ምክንያት እርሷ በእንደዚህ ያለ ሁኔታ ትሰቃያለች፡፡ ምን ባደርግ ይሻላል? እናቴ፥ እባክሽ ይቅር በይኝ! የእኔ ጥፋት ነው!”* ሰይጣን አገልጋዮቹን እናቴን መብላት እንዲቀጥሉ አዘዛቸው፡፡ ፍጥረቶቹ የእናቴን ሆዷን፣ ደረቷን፣ አንገቷንና ጭንቅላቷን በሳሏት፡፡ ምንም ርኅራኄ አላሳዩም፡፡ እናቴ አልፎ አልፎ ራሷን እየሳተች በየመሀሉ ደግሞ ትጮህለች፡፡ ደምና የቆዳ ቁርጥራጮች በየቦታው ነበሩ፡፡ ከዚህ በኋላ ሰው አትመስልም፡፡

ወንድሜና የወንድሜ ልጅ እናቴ ስትሰቃይ እያዩ ብዙ ተሰቃዩ፡፡ ከቁጥጥር ውጭ በሆነ ሁኔታ ይንቀጠቀጣሉ፡፡ ከእናቴ ጋር ከጨረሱ በኋላ ወደ ወንድሜና ወደ የወንድሜ ልጅ ሮጡ፡፡ ልክ በእናቴ እንዳደረጉት ሰውነታቸውን በሚስማር ይበሳሏቸው ጀመር፡፡ *“አሀሀ! እህት ቦንግ ንዮ፥ እርጂኝ! አክስቴ፥ እባክሽ **ጌታ**ን ጠይቂው፥ ፍቺኝ!”* እርኩሳኑ ፍጥረታት ያለርኅራኄ መውጋታቸውን ቀጠሉ፡፡ የወንድሜና የወንድሜ ልጅ ጩኸት እስከ ሲኦል ጣሪያ ድረስ አስተጋባ፡፡

ሰይጣን በኃይል ጮኸ፥ *“አየሽ፥ ምን ተሰማሽ? ቆንጆ አይደል? ለእኔ ህመም አስተዋጽኦ ስላደረግሽ፥ በቤተሰቦችሽ ስቃይ ህመሙን አስቀምስሻለሁ፡፡ ፊት ለፊት እንድትመለከችው ነው የማደርገው!”* ሰይጣንን ችላ ለማለት ሞከርሁ፡፡ ወደ እናቴ ዞር አልሁና ጮኽኩ፥ *“እናቴ፥ ምስኪኗ እናቴ! ባለፈው ጊዜ ሲኦልን ስጎበኝ፥ አንቺ በሲኦል እሳት ውስጥ ነበርሽ፡፡ በእሳት ውስጥ ባየሁሽ ጊዜ፥ ልቤ በብዙ ታመመ፡፡ የእርኩሳን መናፍስትን ንጉስ በማጥቃት ልበቀልልሽ ሞከርሁ፡፡ ሆኖም ግን፥ የበቀሌ ድርጊት በአንቺ ላይ ከባድ ስቃይን አስከተለ፡፡ ይቅርታ፡፡ እናቴ፥ ይቅር በይኝ! ምን ማድረግ ይሻለኛል?”* ስቅስቅ ብዬ አለቀስሁ፡፡ ተናደድሁና የእርኩሳን መናፍስትን ንጉስ መራገም ጀመርሁ፡፡

*“ሰይጣን፥ አንተ ዲያቢሎስ! አንድም ሦስትም የሆነው **አምላክ** በውስጤ ይኖራል! እኔ የ**እግዚአብሔር** ልጅ ነኝ፡፡ ይህን ስፍራ አወድመዋለሁ፥ ቃል እገባልሀለሁ! እኔ ካልቻልሁ፥ አምላኬ ስለእኔ ይበቀልልኛል፡፡ ትጠፋለህ፡፡ ወደ እሳት ባሕር ትጣላለህ፡፡ እስከዚያች ቀን ድረስ በትእግስት እጠባበቃለሁ፡፡ አንተ አስቀያሚ እርኩስ መንፈስ! አስቀያሚ ሰይጣን! ራስህን ማን እንደሆንህ ታስባለህ? እንዴት ብትገዳደር ነው በምድር ሰዎችን የምታስተው፥ ኃጢአት የምታሠራቸው፥ እናም ወደ ሲኦል የምትመራቸው፡፡ አንተ የተረገምህ ነህ፥ ሰይጣን! ከስርህ የሚሠሩ ታዛዦችህ ሁሉ በ**እግዚአብሔር አብ** የተረገሙ ይሆናሉ!”*

**ጌታ** ከቁጥጥር ውጪ እየተበሳጨሁ መምጣቴን ተመልክቶ፥ ቶሎ ብሎ እጄን ያዘኝ፡፡ በቅጽበት በዓይኔ ፊት ደማቅ ብርሃን ታየ፡፡ በገነት ነበርሁ፡፡ በሲኦል ጨለማ ከነበርሁ በኋላ፥ በገነት ደማቅ ብርሃን ዓይኔ ባዶ የሆነ ዓይነት ተሰማኝ፡፡ ድንገተኛው የአካባቢ ለውጥ ግራ አጋባኝ፡፡

**ጌታ** በእርጋታ አስረዳኝ፥ ***“ቦንግ ንዮ፥ ምንም እንኳ ልረዳሽ ብፈልግም፥ የማይቻል ነበር፡፡ አንድ ሰው አንዴ ሲኦል ከገባ፥ ለእርሱ/እርሷ መቼም መውጣት አይቻልም፡፡ ይህን ለመቀየር ለእኔ አይቻለኝም፡፡ በምድር ላይ በህይወት ሳለሽ ብቻ ነው ልትድኚ የምትችዪው፡፡ አንዴ ሰው ከሞተ፥ ንስሐ የመግባት እድል የለውም፡፡ አልቆለታል፡፡ ለአንቺ ማድረግ የምችለው አብሬሽ ማልቀስ አልያም ወደ ገነት መውሰድ ብቻ ነው፡፡ የቤተሰብ አባላቶችሽ በሲኦል ናቸው፡፡ እኔ ምንም ላደርግ አይቻለኝም፡፡ ከቁጥጥሬ ውጪ ነው፡፡ ማንም ሰው መቼም ሊረዳቸው አይችልም፡፡”*** **ጌታ** በሁኔታው በጣም አዝኖ ነበር፡፡

ምንም እንኳ በገነት ብሆን፥ በሲኦል ያሉት ቤተሰቦቼ ሀሳብ እንባን በዓይኔ ሞላ፡፡ በሲኦል ያሉትን ቤተሰቦቼን ማሰቤን ልተው አልቻልሁም፡፡ ከባድ ህመም ውስጥ ነበርሁ፡፡ ለተሰበረው ልቤ ምንም መጽናኛ የለውም፡፡ **ጌታ** በገነት ሰማይ ላይ ወደ ከፍተኛው ስፍራ ወሰደኝ፡፡ ልዩ ደመናን አየሁ፥ ልክ እንደ ድልድይ

ቅርጽ ነበር፡፡ እኔና **ጌታ** በደመናው ትይዩ እየሄድን፥ እጄን ያዘኝ፡፡ ሆኖም ግን፥ ሀሳቤ አሁንም በስቃይ ያሉት ቤተሰቦቼ ጋር ነበር፡፡

እንደ ሕፃን ማልቀሴን ቀጠልሁ፡፡ ከ**ጌታ** ፊት በማልቀሴ ሀፍረት ተሰማኝ፡፡ *“**ጌታ** ሆይ፥ ይቅርታ፡፡ በገነት እንደማናለቅስ ተምሬአለሁ፡፡ ምን ባደርግ ይሻላል? ልቆጣጠረው አልቻልም፡፡”* **ጌታ** ሦስት መላእክትን ጠራ፡፡ ***“ቅድስት ቤይክ ቦንግ ንዮ አሁን ወደ ‘የጌታ ቤተክርስቲያን’ ትመለሳለች፡፡ በቅርበት ትጠብቋትና ትንከባከቧታላችሁ፡፡”*** መላእክቱና እኔ ወደ ምድር ተመለስን፡፡ ከሲኦል ጉብኝት በተመለስሁ ቁጥር፥ መላ ሰውነቴ በህመም ወስጥ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ጀርባዬን በጣም ያመኛል፡፡ ጸልዬ **ጌታ**ን ጠየቅሁት፡፡ *“**ጌታ** ሆይ፥ ጀርባዬን በጣም እያመመኝ ነው፡፡ በጉልበቴ ተንበርክኬ ለመጸለይ ይከብደኛል፡፡”*

*“የቤተክርስቲያኑ አግዳሚ ላይ ጋደም ብዬ መጸለይ እችላለሁ?”* **ጌታ** በመልካም መለሰልኝ፥ ***“ጥሩ ነው፡፡”*** **እግዚአብሔር አብ**ም እንዲሁ መለሰ፥ ***“ተኝቶ መጸለይ ምንም ችግር የለውም፡፡”***

በአግዳሚው ላይ ጋደም እንዳልሁ፥ ጸለይሁ፡፡ **ኢየሱስ** ተመለሰና ወደ ገነት ተራሮች ወሰደኝ፡፡ በገነት ተራሮች፥ በአስደናቂ ሁኔታ የሚያንጸባርቁ ደማቅ የድንጋይ ምሰሶዎችን አየሁ፡፡ ወደ ምሰሶዎቹ ቀረብሁ፡፡ ምሰሶዎቹ እንደ ብርጭቆ ነበሩ፤ በውስጣቸውም ያሳያሉ፤፡ ብርሃንን በሁሉም አቅጣጫ ያንጸባርቃሉ እናም በጣም ስለሚያማምሩ ክብራቸውን ለመግለጽ ምንም ዓይነት ቃላት የለም፡፡ በጣም የሚያስገርምና የሚደንቅ እይታ ነው፡፡ **ጌታ** እንደተከፋሁ ስላወቀ ወደሚያማምሩት ቦታዎች ሁሉ ወሰደኝ፡፡ አጽናናኝና አነቃቃኝ፡፡ እኔን ለማስደሰት ሁሉንም ጥረት አደረገ፡፡ "***ቦንግ ንዮ፥ ማልቀስሽን አቁሚ!***" ልረዳው አልቻልሁም እና ማልቀሴን ማቆም አልተቻለኝም፡፡

*ወደ ሲኦል ለመሄድ ፈቃደኝነት

ወደ ቤተክርስቲያን እንደተመለስሁ፥ መጸለይ ጀመርሁ ወዲያው ግን እንቅልፍ ወሰደኝ፡፡ ተኝቼ ሳለ፥ ጠባቂ መልአኬ ከሌሎች ሦስት መላእክት ጋር ይጠብቁኝና ይንከባከቡኝ ነበር፡፡ ከነቃሁ በኋላ መላእክቱን **ጌታ** ወዴት እንደሄደ ጠየቅኋቸው፡፡ መላእክቱም መለሱ፥ "*አታስቢ፡፡ **ጌታ** በቅርቡ ይመለሳል፡፡*" እነርሱ እንደመለሱ፥ **ጌታ** መጣ፡፡ "***ጌታ** ሆይ፥ የ30 ቀን የጸሎት ዘመቻችን ነገ ያልቃል፡፡ ሲኦልን በድጋሚ የምጎበኝበት አጋጣሚ አላገኘም፡፡ አንድ ጊዜ የመጨረሻ ሲኦልን ልጎበኝ እፈልጋለሁ፡፡*" ብዬ ጠየቅሁት፡፡

**ጌታ**ም፥ "***የምርሽን ነው ያልሽው? ካለፈው ጉብኝትሽ ሰውነትሽ አላገገመም፡፡ እስካሁን ተረብሸሻል፡፡ ቦንግ ንዮ፥ ለምን ለመመለስ ወሰንሽ? ሲኦልን እንደገና ለመጎብኘት ለምን ወሰንሽ?***" **ጌታ** ተደንቆ ነበር፡፡ እኔም መልሼ፥ "*ከዚህ የጸሎት ዘመቻ፥ ብዙ ነገሮችን ተምሬአለሁ፡፡ በጉባኤው መሀል፥ መጋቢው ብዙ ገራሚ ነገሮችን ተናገረ፡፡ ይመስለኛል አላማው እኛን ለማበረታታትና እምነታችንን ለማጠንከር ይመስለኛል፡፡*" አልሁት፡፡ መጋቢው የሰበከውን ቃላት ደገምኋቸው፡፡ **ጌታ** ድምጹን ከፍ አድርጎ ሳቀና እንዲህ አለኝ፥ "***አሀ፥ እነዚያን ቃላት ሰምቻቸዋለሁ፡፡***" እኔም፥ "*አንድ ጠቃሚ ነገር ተምሬአለሁ፤ በእምነት ብቻ ነው! በተጨማሪም፥ ስለማንኛውም ጥያቄ ያለማቋረጥ መጸለይ እንዳለብኝ ተምሬአለሁ፥ በተለይ፥ መንፈሳዊ ንቃት፡፡ ይመስለኛል ሌሎቹም የጸሎት ቡድኑ አባላት እንደእኔ የምያስቡ ይመስለኛል፡፡*" ብዬ መለስሁለት፡፡

**ጌታ**ም አለ፥ "***ቦንግ ንዮ፥ ሀሳብሽ ይገባኛል፥ ነገር ግን ሲኦልን አንድ ተጨማሪ ጊዜ ከጎበኘሽ፥ ምን አልባት ቤተሰቦችሽን በድጋሚ ልታያቸው ትችያለሽ፡፡ ድጋሚ ስሜትሽ ይጎዳል፡፡ ልረዳሽ እንደማልችል ሳስበው ልቤን ያመኛል፡፡ ለምንድን ነው ደጋግመሽ ሲኦልን ለአንድ ተጨማሪ ጊዜ ለመጎብኘት የምትጠይቂው?***" በችኮላ መለስሁለት፥ "***ጌታ** ሆይ፥ መጋቢያችን የዲያቢሎስንና የሲኦልን ማንነት የሚያጋልጥ መጽሐፍ እየጻፈ ነው፡፡ ሲኦልን አንድ ተጨማሪ ጊዜ ብጎበኝ፥ በተጨማሪ ጠለቅ አርጌ ላየውና ልረዳው እችላለሁ፡፡ የበለጠ ትክክለኛ መረጃ ለመጻፍ እንችላለን፡፡ በዝርዝርና በግልጽ ሲኦልንና እርኩሳን መናፍስቱን ልንገልጻቸው ይገባል፡፡*" ፍቃደኛነቴን ስነግረው፥ **ኢየሱስ** በእኔ የተገረመ ይመስላል፡፡ ስጸልይ ቀና ብዬ በጉልበቴ ተንበረከክሁ፡፡ **ጌታ**ም አለ፥ "***በጀርባሽ ጋደም ብለሽ መጸለይ ምንም ችግር የለውም፡፡***" ሀክ ሱንግን ትራስ እንዲያመጣልኝ ጠየቅሁት፡፡ ጋደም እንዳልሁ፥ መጸለይ ጀመርሁ፡፡

**ጌታ** ወደ ሲኦል መልሶ ወሰደኝና ብቻዬን ተወኝ፡፡ በጨለማው ውስጥ መሄድ ጀመርሁ፡፡ መንገዱ ጠባብ ስለሆነ በጥንቃቄ መጓዝ ነበረብኝ፡፡ መንገዱን አስታወስሁትና በዙሪያዬ ያለውን መንገዴን አገኘሁትና ወደ ፊት መሄድ ቻልሁ፡፡ ወደ ፊት መሄዴን ቀጠልሁ ሆኖም ግን ምንም ነገር ማየትም ሆነ መረዳት አልቻልሁም፡፡ በድንገት እስር ክፍል ውስጥ ተጠመድሁ፡፡ የት እንደተጠመድሁ ለማወቅ ሞከርሁ፥ ነገር ግን ምንም ነገር ላይ አልቻልሁም፡፡ ይባስ ብሎ፥ መንቀሳቀስ እንኳን አልቻልሁም፡፡

*ስቃዩን እንደገና መቅመስ ነገር ግን ያለ ህመም

ጥቂት ቆይቶ፥ የተወሰኑ እርኩሳን መናፍስት መጡና ልብሴን ማውለቅ ጀመሩ፡፡ ጠባብ የእስር ክፍል አነስተኛ መጋዘን ነገር ውስጥ ነበርሁ፡፡ በመሬት ላይ እንግዳ የሆነ የሚያጣብቅ ነገር ተሰማኝ፡፡ በእግሬ ላይና በሰውነቴ ላይ መንጠላጠል ጀመሩ፡፡ ሰውነቴ ላይ ሲጣበቁ፥ የሆነ ሰው በጣም የሚያጣብቅ ማስቲሽ ሰውነቴ ላይ የጨመቀብኝ ነው የመሰለኝ፡፡ ወዲያው ምላሽ ሰጠሁና እርኩሳን መናፍስቱ ላይ ጮኽኩባቸው፡፡ "*እናንተ እርኩሳን ፍጥረታት፥ **ሥላሴ አምላክ** እየጠበቀኝ ነው፡፡ አልፈራችሁም፡፡ **ጌታ**ዬ ይጠብቀኛል! በሲኦል ያላችሁ እርኩሳን መናፍስት ሁላ አዳምጡኝ፡፡ **እግዚአብሔር** ሲኦልን እስኪያጠፋ ድረስ ብዙ ጊዜ አይደለም የቀረው! ያን አስጨናቂ ቀን ጠብቁ ብቻ!*" ሳላስበው አንዳንድ አስጸያፊ ቃላትንም ተናገርሁ፡፡

እኔ እየጮህኩ፥ የሚያጣብቁት ነገሮች ወደ ደረቴ መንጠላጠላቸውን ቀጠሉ፥ አንገቴ ከዛም ወደ አፌ:: ሀሳባቸው አፌ ላይ ተጣብቀው ሊዘጉት ነው የሚመስለው:: ድምጼን የበለጠ ከፍ አድርጌ ጮኽኩ፥ *“እርኩሳን ፍጥረታት፥ እረግማችኋለሁ! በቅርቡ ትጠፋላችሁ!”* ስጮህ፥ መላ ሰውነቴ ተንቀጠቀጠ::

ብዙም ሳይቆይ፥ ከሚያጣብቀው ነገር ውስጥ የመቶ እግር ትሎች መውጣት ጀመሩ:: በመላ ሰውነቴ ላይ ይመላለሱ ነበር:: ሰውነቴን በስተው መግባት ጀመሩ:: መታደል ሆኖ፥ በ**እግዚአብሔር** ስለምጠበቅ፥ ምንም ህመም አልተሰማኝም:: ሳቅሁባቸውና በግዴለሽነት ስሜት ቀለድሁባቸው::

በቸልተኝነቴ የእርኩሳን ፍጥረቶቹ ንጉስ ተበሳጨ:: ምልክትን ሰጠና ወዲያው የማይቆጠሩ እባቦች መጥተው በሰውነቴ ላይ ተጠመጠሙ፥ ያለማቋረጥ ይነክሱኝ ነበር::

በድፍረት፥ *“አዎ፥ ደስ የሚል ስሜት አለው:: እባካችሁ ጨመር አድርጋችሁ ንክሱኝ! የሚያሳክኩኝን ቦታዎች እያረካችሁልኝ ነው፥”* ብዬ ጮኽኩኝ:: ፍጥረታቱንና ትሎቹን እየሳቅሁና እየቀለድሁባቸው፥ መርዛማ እባቦች በቡድን ቀጥ ብለው ቆመው ይነክሱኝ ቀጠሉ::

ምንም ያህል ጊዜ ቢነክሱኝ ወይም ንክሻቸውን ቢያጠብቁ ምንም ለውጥ አልነበረውም፥ እኔ ምንም ህመም ሊሰማኝ አልቻለም:: ድንገት በአንድ ጊዜ፥ የነበርሁበት መጋዘን በእባቦች ተሞላ:: ወደ **ጌታ** ጸለይሁ፥ *“**ጌታ** ሆይ፥ እባክህ እርዳኝ! የት ነህ? እባክህ ፈጥነህ ና!”* ስሙን ደጋግሜ መጥራቴን ቀጠልሁ፥ ነገር ግን ምንም አልጠቀመም:: አልመጣም::

በልሳን ስጸልይ ምን ያህል ሰዓት እንዳለፈ አላውቅም፥ ነገር ግን ረዘም ላለ ጊዜ ነው:: **ጌታ** በደማቅ ብርሃን መሀከል ተገለጠ:: ፈጥኜ ጠራሁት፥ *“**ጌታ** ሆይ፥ **ጌታ** ሆይ!”* **እርሱ**ን በማየቴ በጣም ተደስቼ ነበር:: **ኢየሱስ** እጁን ሲያወዛውዝ፥ መጋዘኑና ሲዖል ተሰወሩ:: ክንፎች ያሉት ደማቅ ነጭ ልብስ ለብሼ ነበር:: የትም ቦታ ብሆን፥ **ኢየሱስ** ከእኔ ጋር ከሌለ፥ እንደ ሲዖል ነው የሚሆንብኝ::

ለግማሽ ዓመት ያህል በሲዖል እንደነበርሁ ዓይነት ተሰማኝ:: ሲዖል የማይታሰብ ነው:: የህመምና የሥቃይ ቦታ ነው:: አንድ ቀን በሲዖል የአንድ ሺህ ዓመት ዓይነት ስሜት ነው ያለው፥ ምናልባትም አስር ሺህ አመታት:: ስለሲዖል ማሰብ አልፈልግም፥ ለአፍታ እንኳ ቢሆን:: የዘላለማዊ ተስፋ መቁረጥ፥ ዘላለማዊ ጩኸት እና ዘላለማዊ ሰቆቃ ቦታ ነው:: **ኢየሱስ** መልሶ ወደ ቤተክርስቲያን ሲወስደኝ፥ ከዚህ በፊት አሞኝ የነበረኝ ቦታ ላይ ነካኝ:: መልካም በሆኑ ቃላት አጽናናኝ:: *“ቦንግ ንዮ፥ ቅድስት ቦንግ ንዮ:: እናንተ ሁላችሁም የእኔ ግልገሎች ናችሁ:: ሁላችሁም ለ30 ቀናት ለመጸለይ ተግታችኋል:: ቃሉን ማጥናትና ቤተክርስቲያን በጋለ ስሜት መምጣታችሁን ቀጥሉ:: ለማጋቢያችሁ ሁሉንም ገጠመኞች በትጋት እንዲጽፍና እንዲያሰፍር ንገሪው::”*

***መጋቢ ኪም ዮንግ ዱ:*** **መጋቢው አጋንንትን አስወጣ*

ትላንትና፥ እርኩሳን መናፍስት በቡድን ሆነው እህት ቤይክ ቦንግ ንዮ ውስጥ ገቡ:: እርኩሳን መናፍስቱን የማስወጣቱ ውጊያ ሌሊቱን ሙሉ ወሰደ:: እሁድ ነበር እናም እኔ ራሱ በእርኩሳን መናፍስቱ ተጠቅቼ ነበር:: ደካማ በነበርሁበት አፍታ፥ አዕምሮዬ እያመነታ ሳለ፥ ሰውነቴ ደግሞ ተመታ::

በሌላ የምሽት አገልግሎት፥ እህት ቤይክ ቦንግ ንዮ ተጠቃችና እርኩሳን መናፍስት ወደ እርሷ ገቡ:: ብዙ ዓይነት የመናፍስት ሠራዊት በእህት ቤይክ ቦንግ ንዮ ላይ ከባድ ህመም አስከተሉባት:: እንደአጋጣሚ፥ እርኩሳን መናፍስቱ ወደ ጭንቅላቷ አልገቡም:: ሆኖም ግን፥ መላ ሰውነቷ ውስጥ በነበረው በየደቂቃው በሚጨመር ከባድ ህመም ምክንያት በስቃይ መሬት ላይ ወድቃ ተንከባለለች:: ባለፈው ምሽት ይህ ሲሆን፥ ከቤተክርስቲያን ባልተረጋጋ መንፈስ ወጣን:: እቤት ስንደርስ፥ ሁላችንም እረፍት አልባ ምሽት አሳልፈን ነበር:: ነገ፥ በድጋሚ ብንጠቃም እንኳ የ30 ቀን የጸሎት ዘመቻውን እንጨርሳለን:: እርኩሳን መናፍስቱ በጥቃታቸው ደጋግመውን ነበር:: ግልጹን ለመናገር ጥቃታቸው ሰልችቶኛል::

እርኩሳን መናፍስቱን መዋጋትና ማስወጣ በመንፈስ ብዙ ይጠበቅብናል እናም ደግሞ ሰውነታችንን ያዳክመዋል:: ሙሉው የጸሎት ቡድን አቅሙ ተዳክሟል:: ቢሆንም፥ **ጌታ** በሂደት ያበረታናል:: *“እስከ ሞት ድረስ እዋጋለሁ!”* ብዬ አሰብሁ:: አንድ በአንድ፥ እርኩሳን መናፍስቱ በጽኑ ትኩረት አስወጣኋቸው:: በድንገት፥ የመጋቢው ሚስት መሬት ላይ ወደቀች:: ከመጋቢው ጋር እርኩሳን መናፍስቱን እያወጣች ሳለ፥ እርኩሳን መናፍስቱ አጥቅተዋት ሰውነቷ ውስጥ ገቡ:: በመንፈስም በአካሏ በተዳከመው አቋሟ ምክንያት ተጋልጣ ነበር::

እርኩሳን መናፍስቱ ጥቃታቸውን በመጋቢው ሚስትና በእህት ቤይክ ቦንግ ንዮ ላይ ያፈራርቁ ነበር፡፡ ኢላማቸው የቱ እንደሆነ እኛን ለማታለል ነው የሚመስለው፡፡ እያሾፉብን ነበር፡ ውጊያው እስከ ማለዳ ድረስ ቀጥሎ ነበር እናም እርኩሳን መናፍስቱ ትእዛዛቶቻችንን አሻፈረን ማለታቸውን ቀጠሉ፡፡ ከዚያም፥ **ጌታ** ጣልቃ ገባ፡፡ በመጀመሪያ፥ ምንም እንኳ ወደ **እርሱ** ብንማጸንም **እርሱ** ግን ቆሞ ድርጊታችንን ይከታተል ነበር፡፡ **ጌታ** እርኩሳን መናፍስቱ እንዲወጡ አላዘዛቸውም፡፡ **ጌታ** ውጊያችንን እየተከታተለ፥ እኛ እርኩሳን መናፍስቱን ለማስወጣት የነበረንን ትጋትና እምነት በጥያቄ ውስጥ ከቶት ነበር፡፡ ሁላችንም በአንድ ድምጽ እርኩሳን መናፍሱትን እናዝ ነበር፡፡ **እርሱ**ም መቃኘቱንና መከታተሉን ቀጠለ፡፡

አዕምሯቸውን የሳቱ እብዶች የሆንን ሁሉ መስሎኝ ነበር፡፡ እንግዳ ሰው አዕምሯችን እንደተቃወሰ ሊል ሁሉ ይችላል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ምስቅልቅል ውስጥ እንዴት አንደገባን ላስበው ራሱ አልችልም፡፡ ህሊናዬ ደካማና በጥርጣሬ ተሞልቶ ነበር፡፡ ነገር ግን፥ መንፈሳዊ ሁኔታዎችን በዓለማዊ አስተሳሰብ ካየኋቸው፥ በ**ጌታ** ፊት በከፋ ሁኔታ እንደምበድል አውቃለሁ፡፡ ራሴን ሰብስቤ አዕምሮዬን አተኮርኩ፡፡ እርኩሳን መናፍስቱን በ**ጌታ** ስም ማስወጣቴን ቀጠልሁ፡፡ እርኩሳን መናፍስትን ማስወጣት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተመስርቶ ጥቂት ቃላትን ብቻ መናገር ብቻ እንደሆነ አምን ነበር፡፡ ሆኖም ግን፥ በጸሎት ዘመቻው ውስጥና ውጊያዎቹን በራሴ በማየቴ፥ መንፈሳዊ ውጊያዎችን አስመልክቶ በ**እግዚአብሔር** ፊት ንስሐ መግባት ነበረብኝ፡፡ እንደተለመደው፥ እርኩሳን መናፍስቱን እስከ ማለዳ ድረስ ሌሊቱን ሙሉ ተዋጋን፡፡ አንዴ ውጊያው ካለቀ በኋላ፥ በየግላችን ለመጸለይ ችለን ነበር፡፡ **እግዚአብሔር** እጆቼን በሚፈውስ መንገድ አንቀሳቀሳቸው፡፡

ከአስራ አምስት ቀናት በፊት፥ በአመጸኛ እርኩሳን መናፍስት በክፉ ተጠቅቼ ነበር፡፡ ተነክሼ ነበር እናም በቆዳዬ ላይ ምልክት ነበር፡፡ በአስከፊ ህመም ውስጥ ነበርሁ፡፡ የንክሻው ቅርጽ ሊጠፋ አልቻለም እናም ህመሙ ቀጠለ፡፡ አሁን በጥቃቱ ጀርባ ያለውን ዓላማ ተዳሁ፡፡ እርኩሳን መናፍስቱ እኔ እየጻፍሁት ስላለው መጽሐፍ አወቁ፡፡ የምጽፈው በቀኝ እጄ ነው፡፡ ጥቃቱ በዋነኛነት በቀኝ ጎኔ በኩል ነበር፡፡ ቀኝ መዳፌ፥ ቀኝ

እጄ፥ ቀኝ ትከሻዬ፥ ጀርባዬ በቀኝ በኩል፥ እናም ነርቮቼ ሁሉ ታምመው ነበር፡፡ እርኩሳን መናፍስቱ መጽሐፉን እንዳልጨርስ ሊያሰናክሉኝ ሞከሩ፡፡

ከጥቃቱ በፊት፥ በነጻነት መስበክ፥ ማምለክ፥ እናም የፈለግሁትን ያህል ብዙ መጸለይ እችል ነበር፡፡ አሁን ግን፥ ባወራሁና በተንቀሳቀስሁ ቁጥር፥ በከባድ ህመም ውስጥ ነኝ፡፡ በአግባቡ መንቀሳቀስም ሆነ መሥራት አልችልም፡፡ ይሄ የቸልተኛነቴ ውጤት ነው፡፡ **ጌታ** መጽሐፉ እስኪወጣ ድረስ ያየሁትንም ሆነ ያሳለፍሁትን ነገር በምስጢር እንድይዝ አዝዞኝ ነበር፡፡ ሆኖም ግን፥ ታዛዥ አልነበርሁም፡፡ ቸልተኝነቴ አስከፊ ወጤትን በእኔ ላይ አስከተለ፡፡ አሁን፥ በሁሉም ጉዳዮች ላይ በደንብ ጠንቃቃ ነኝ፡፡ መጽሐፎቼ እስኪጠናቀቁና እስኪለቀቁ ድረስ፥ ማንኛቸውንም ገጠመኞች ለማንም ላለመግለጥ እጠነቀቃለሁ፡፡ ስለእውነቱ፥ ከቤተሰቦቼ ጋር አጭርም ሆነ ረዥም ንግግሮችን ሁሉ አርቃለሁ፡፡ ትእዛዛቶቹን አለመፈጸም ምን ያህል አስፈሪ እንደሆነ ተረድቻለሁ፡፡ ሁል ጊዜም ንስሐ እየገባሁ፥ በተቻለ መጠን በቅርቡ እንደምፈወስ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

## ==== ቀን 30 ====

([1ኛ ተሰሎንቄ 5፡14-23](1ኛ ተሰሎንቄ 5፡14-23))

**ዲያቆን ሺን ሱንግ ኪዩንግ፡** *መንፈሳዊ ልምምዶችን መጀመር

"*ኢየሱስ ሆይ፥ እባክህን እንደ ወይዘሮ ካንግ ሆዩን ጃ እና እህት ቤይክ ቦንግ ንዮ መደነስ እንድችል እኔንም በ**መንፈስህ** አስታጥቀኝ! እለምንሀለሁ! በጣም ነው የምፈልገው!*" አጽንቼ ስጸልይ፥ ሁለቱም እጆቼ ሲሞቁ ተሰማኝ፡፡ ሙቀቱ በጣም ጽኑ ነበር፥ ልክ የእሳት ኳስ እንደመንካት፡፡ ይህ ባለፈው ጊዜ አጋጠመኝ፥ ነገር ግን ቆይታው አጭር ነበር፡፡ ሆኖም ግን፥ ዛሬ፥ መላ ሰውነቴ ጋለና እጆቼ በራሳቸው ከፍ ብለው ወደ ላይ ተነሱ፡፡ የሆነ የማይታይ ሰው እጆቼን ከፍ አድርጎ የያዛቸውና የእጆቼን ከፍ ማለት ወይም ዝቅ ማለት የሚቆጣጠር ነው የሚመስለው፡፡ እጆቼ በተለያዩ ዓይነት እንቅስቃሴዎች ወደ ተለያዩ አቅጣጫዎች ይንቀሳቀሱ ነበር፡፡ ልቤ በተትረፈረፈ ደስታ ተሞልቶ ነበር፡፡ የንስሐ እንባዎች በፊቴ ላይ ጎረፉ፡፡ ጸሎቴ በመንፈስ ጥልቅ እየሆነ ተሰማኝ፡፡ በምሽቱ ሰማይ ላይ እየበረርሁ ነበር፡፡ በአስደናቂው ምሽት ተደምሜ ነበር፡፡



**ኪም፥ ጁ ኢዩን፡** *አራት ጠባቂ መላእክት

በጸሎት ዘመቻው ወቅት፥ **ኢየሱስ** ቅዱስ ጸጋና የትንቢትን ጸጋ ሰጠኝ፡፡ **ኢየሱስ**ን በጣም ነው የምወደው፡፡ በማንኛውም ጊዜ ዓይኔን ጨፍኜ **ስሙን** ስጠራ፥ ወዲያው **ራሱን** ይገልጥልኛል፡፡ በቅጽል ስሜ ይጠራኛል፥ "ጠቃጠቆ"፡፡ እንዲህም ይለኛል፥ *"ጠቃጠቆ፥ ምን ትፈልጊያለሽ? ጥያቄ አለሽ?"* ከዛም በእርጋታና በቅንነት ጥያቄዎቼን ይመልስልኛል፡፡

ሆኖም ግን፥ ብዙ ጊዜ፥ እርኩሳን መናፍስት እንደ **ጌታ** ተመስለው ይመጣሉ፡፡ እንዲሁም **ጌታ**ን ሁል ጊዜ እንደምጠራውና ጥያቄ እንደምጠይቅ ያውቃሉ፡፡ በመጀመሪያ፥ በ**ጌታ**ና በእርኩሳን መናፍስቱ መሀከል መለየት አልቻልም ነበር፡፡ ብዙ ጊዜ ተታልያለሁ፡፡ አሁን ግን፥ የሚመጣውን መንፈስ እፈትናለሁ፡፡ መንፈሱን በመፈተን፥ **ጌታ**ና እርኩሳን መናፍስቱን መለየት እችላለሁ፡፡ እርኩሳን መናፍስት ደማቸውን ማፍሰስ አይችሉም፡፡ እርኩሳን መናፍስት መስቀሉን መሸከም አይችሉም፡፡ ሁሉም ውሸታሞች ናቸው፡፡ በተገለጡ ጊዜ ሁሉ ይዋሻሉ፡፡ **ጌታ** እርኩሳን መናፍስትን የምለይበት ጥበብ ሰጥቶኛል፡፡ አሁን በቅጽበት እለያቸዋለሁ፡፡

ለሥጋዊ ፍላጎቴ፥ ስስት፥ አልያም ሌሎች ተራ ጥያቄዎችን ስጠይቅ፥ **ጌታ** ጀርባውን ይሰጠኝና ዝም ይላል፡፡ ገና ያልበሰልሁ ሕፃን ልጅ ስለሆንሁ፥ **ጌታ** ጥያቄዎቼን እኔ በምረዳበት መልኩ ማስረዳት ይኖርበታል፡፡ ስለቸርነቱ **ጌታ**ን በጣም አመሰግነዋለሁ፡፡ **ጌታ** ላማረ ልብ በጣም ጉጉ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ፥ **ጌታ** አባቴና እናቴን አስመልክቶ አንዳንድ ነገሮችን በእኔ በኩል ይገልጻል፡፡ ከውጫዊ አቋማቸው ወላጆቼ ምን እንደሚሰማቸው ወይም እንደሚያስቡ ማወቅ አልቻልም፡፡ ሆኖም ግን፥ **ኢየሱስ** በልባቸው ጥልቀት

ስላለ እነርሱ ብቻ ሊረዱት የሚችሉትን መልእክት ነው የሚነግረኝ፡፡ መልእክቱን ለወላጆቼ ስነግራቸው፥ ተደነቁ፡፡ ከ**ጌታ** የሆነው መልዕክት ራሳቸውን ወደ መስጠትና ወደ ንስሐ ይመራቸዋል፡፡

ከቤተሰባችን ጠባቂ መላእክት ጋር መነጋገርም እችላለሁ፡፡ በቤተሰባችን ውስጥ አራት አባላት ስላሉ አራት መላእክት አሉ፡፡ ከመላክቱ ጋር ለመነጋገር ስሞክር፥ **ጌታ** ጣልቃ ይገባል፡፡ እንዲህም ይላል፥ *"ጠቃጠቆ፥ እኔ ጌታሽ ነኝ፡፡ መነጋገር ከፈለግሽም ሆነ ምንም ዓይነት ጥያቄ ካለሽ፥ የእኔን ስም መጥራት ይኖርብሻል እናም ማንኛውንም ነገር ከእኔ ጋር ተወያዪ፡፡ ለምንድ ነው በተደጋጋሚ ከመላእክቱ ጋር ማውራት የምትፈልጊው?"* **ጌታ** ሲቀና፥ በጣም ደስ ይለኛል ምክንያቱም ይፈልገኛል፡፡

የክረምት እረፍት ላይ ስለነበርሁ በዚህ ጊዜ ሁሉንም የጸሎት ዘመቻ ለመሳተፍ ችዬ ነበር፡፡ ስገኝ፥ በትጋት እጸልያለሁ፡፡ መጸለይ እንድችል የፒያኖ ትምህርቴንና ሌሎች ተግባራቶችን እንኳ አቆማለሁ፡፡ በውጤቱም፥ **ጌታ** በጣም ባርኮኛል፡፡ በሌላ መልኩ፥ ትምህርቴንም አጥብቄ ይዣለሁ፡፡ ትምህርት ሲከፈት፥ የመጸለይ እድሌ ውስን እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ ማንኛውም ዓይነት ቴሌቪዢን ካየሁና ኮምፒውተር ከተጠቀምሁ ዘጠኝ ወራት ሆኖኛል፡፡ በመጀመሪያ፥ እነዚህን ድርጊቶች መተው ከባድ ነበር፡፡ ሆኖም ግን፥ አሁን፥ ከ**ጌታ** ጋር ህብረት ማድረግ ያስደስተኛል፡፡ አሁን፥ ቴሌቪዥንና ኮምፒውተር ላይ የማሳልፈው ጊዜ ለጸሎትና **ቃሉ**ን ለማጥናት እጠቀምበታለሁ፡፡

*ስለመላእክት ክንፎች

ከጸሎት በኋላ፥ ወደ ቤት ሄድሁኝ እናም የቤተሰባችን ጠባቂ መላእክት እየተጠባበቁ ነበር፡፡ የመጋቢው ጠባቂ መልአክ 2 ጥንድ ክንፎች ነበር የነበሩት፥ ነገር ግን አሁን 3 ጥንዶች ናቸው፡፡ **ጌታ**ን ጠየቅሁት፥ "*ኢየሱስ! አንድ ጊዜ ታላላቅ ቤተክርስቲያናት ያሉ መጋቢዎች ጠባቂ መላእክቶቻቸው ሦስት ጥንድ ክንፍ እንዳላቸው ነግረኸኝ ነበር፡፡ ቤተክርስቲያናችን በጣም ትንሽ ሆና ሳለ የእኛ መጋቢ ጠባቂ መልአክ ሦስት ጥንድ ክንፍ እንዴት ኖረው? ትላንትና፥ ይህ ጠባቂ መልአክ ሁለት ጥንድ ክንፎች ነበሩት፤ አሁን ሦስት ነው ያለው፡፡*" **ጌታ**ም መለሰ፥ *"ብዙ መጋቢዎች ተልዕኳቸውን ሲጀምሩ በሙሉ ኃይላቸው በትጋት ይጸልያሉ፡፡ ሆኖም ግን፥ ቤተክርስቲያናቸው ማደግ ሲጀምር፥ እንደበፊታቸው አይጸልዩም፡፡ ቅር ብሎኛል እናም ከፍቶኛል፡፡ ነገር ግን መጋቢ ኪም ለብዙ ጊዜ በትጋት ይጸልያል፡፡ እንዲሁም ተልዕኮውን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እየመራ ነው፡፡ ስለዚህ፥ ለዚህ ጠባቂ መልአክ አንድ ተጨማሪ ጥንድ ክንፍ ሰጠሁት፡፡"* የእናቴ ጠባቂ መልአክ አንድ ጥንድ ክንፍ ብቻ ነው ያለው፡፡

**ኪም፥ ዮሴፍ፡** *መንፈሳዊ ዓይኖች በግማሽ ተከፈቱ

ዛሬ የ30 ቀን ጸሎት ዘመቻችን የመጨረሻ ቀን ስለሆነ፥ በትጋት ለመጸለይ ራሴን አዘጋጀሁ፡፡ በትጋትና በሙሉ ልቤ እጸልያለሁ፡፡ ቀኝ እጄን ከወንድም ሀክ ሱንግ ጋር አያያዝሁ፥ ጣቶቻችን ተቆላልፈው ነበር፡፡ ግራ እጄ ወደ ላይ ወደ አየሩ

ተዘርግቶ ነበር እናም በልሳን እጸልይ ነበረ፡፡ ዓይኖቼ እንደተከደኑ ስጸልይ፥ የሆነ ሰው ጣቶቻችን ተቆላልፎ ግራ እጄን እንደያዘኝ ተሰማኝ፡፡ ድንገተኛ ኤልክትሪክ በግራ እጄ በኩል ወደ ሰውነቴ ፈሰሰ፡፡ ተነቃቅቼ፥ ምን እንደሆነ ለማወቅ ፈለግሁ፡፡ የሆነ ሰው ሲነካኝ ተሰማኝ፤ በጣም ጠንካራ ነበር፥ የሆነ ሰው እጄን እንደያዘኝ ዓይነት፡፡ በጸሎት ውስጥ ስለነበርሁ፥ ዓይኔን በጭራሽ አልከፈትሁም፡፡ ሆኖም ግን፥ ወንድም ሀክ ሱንግን ለመጠየቅ ወሰንሁ፡፡ *"ወንድም ሀክ ሱንግ፥ የሆነ ሰው እጄን እንደያዘኝ ይሰማኛል፡፡ ማን እንደሆነ ታውቃለህ? ልታይልኝ ትችላለህ? እባክህ አሳውቀኝ፡፡"* እርሱም፥ *"ወንድም ዮሴፍ፥* ***ኢየሱስ*** *እጅህን ይዞሀል እናም በዚህ ቅጽበት ወደ ገነት እየበረረ ነው፡፡ ዓይንህን እንዳትገልጥ እናም መጸለይህን ቀጥል!"* ብሎ መለሰ፡፡

ጸሎቴን ስቀጥል፥ በሆነ ጨለማ ቦታ ውስጥ እንደምበር ተሰማኝ፡፡ በድንገት፥ ሰማያዊ ብርሃን ታየ፡፡ ወደ እኔ ቀረበና አለፈኝ፥ በብርሃን ፍጥነት፡፡ ከዚያም፥ ሌላ ሰማያዊ ብርሃን አለፈኝ፥ ትልቅ ሰማያዊ ብርሃን፡፡ የበለጠ እየበረርሁ ስሄድ፥ የማይቆጠሩ ከዋክብት እያለፉኝ ሄዱ፡፡ *"ዋው! እንዴት ያለ የሚገርም እይታ ነው! በጣም ነው የሚያምረው፦"* ብዬ ጮኽኩኝ፡፡ ጸሎቴ እየጠለቀ ሲሄድ፥ ብዙ ከዋክብት በብርሃን ፍጥነት በአጠገቤ ሲያልፉ አየሁ፡፡ የከዋክብት ክምችቱ ከዋክብቶች በጣም የተዋቡ ናቸው፡፡ ወደ ህዋ የመጠቀ ከዋክብት ተመራማሪ የሆንኩ ነው የመሰለኝ፡፡ *"ምን አልባት እያለምሁ ነው፦"* ብዬ አሰብሁ፡፡ ራሴን ለመቆንጠጥ ወሰንሁ፡፡ እርግጥ ነው፥ አካላዊ ሰውነቴ በቤተክርስቲያን እየጸለየ ነው፡፡ ሆኖም ግን፥ አካላዊ ሰውነቴን ስነካው፥ በተመሳሳይ ሰዓት በመንፈሳዊ ዓለምም ውስጥ ነበርሁ፡፡



አካላዊ ሰውነቴ በልሳን እየጸለየ፥ በመንፈስ በፍጥነት እየበረርሁ ነበር፡፡ ድንገት፥ ሳንቲም የሚመስል ነገር ወደ እይታዬ መጣ፡፡ ክቡ ነገር በሆነ ጥቁር ነገር ተሸፍኗል፡፡ ሙሉ ጨረቃ ሆኖ ተገኘ፥ እየተመለከትሁት የነበረው ግርዶሽ ሆኖ ተገኘ፡፡ ግርዶሹ ግማሽ ጨረቃን ፈጠረ፡፡ ጨረቃዋ በወርቃማ ጨረሮች ታብራለች፡፡ ወርቃማው ብርሃን በጣም ደማቅ ስለነበር በቀጥታ ላየው አልቻልሁም፡፡ እንዲዚህ ዓይነት ድምቀት ፈጽሞ አጋጥሞኝ አያውቅም፡፡ ብርሃኑ እንደ ፔንዱለም ይወዛወዝ ነበር፡፡ እስከ 120 ዲግሪ ድረስ ወደፊት ወደኋላ ይላል፡፡ ብርሃኑ ወደፊትና ወደኋላ እየተወዛወዘ፥ የቀስተደመና ቀለሞች ፈክተው ወጡ፡፡



ወዲያው እንዲህ አሰብሁ፥ *"ዋው! ምንአልባት ያ ቦታ የገነት አስራሁለት የእንቁ በሮች ይሆናል!"* ዛሬ ገነትን የምጎበኝበት ቀን ሊሆን እንደሚችል ገመትሁ፡፡ በይበልጥ አጽንቼ መጸለዬን ቀጠልሁ፥ ነገር ግን በሆነ ምክንያት ጸሎቶቼ ወደ ፊት ሊወስዱኝ አልቻሉም፡፡ ምንም ያህል ብጮህ አልጠቀመም፥ ወደ ፊት አልሄድሁም፡፡ እንደበፊቱ በታላቅ ፍጥነት እየበረርሁ አልነበረም፡፡ ቀስተደመናውንና የብርሃን ቀለማቱን ካየሁ በኋላ ተገድቤ ነበር፡፡ ሰዓት ቀጥ ብሎ የቆመ ነው የሚመስለው፡፡

በጣም ቀርቤ ነበር፡፡ በጣም ተረብሼ ነበር! የበለጠ ወደፊት መሄድ አልቻልሁም ስለዚህ ወደኋላ ተመለስሁ፡፡ ልቤ ወደቀብኝ እናም ባዶነት ተሰማኝ፡፡ ፔንዱለሙን አልፌ ለመሄድ ሌላ አጋጣሚ ተመኘሁ፡፡ የጸሎት ዘመቻው ሲያልቅ፥ ከጠዋቱ 1 ሰዓት ነበር፡፡

*ዮሴፍ የእርኩሳን መናፍስት ኢላማ ሆነ

የጸሎት ዘመቻችንን ከጨረስን በኋላ፥ እኔና ወንድም ሀክ ሱንግ አወራን፡፡ እየተነጋገርን ሳለ፥ መጋቢውና ዲያቆን ሺን ጁንግ ሚንን በመኪና እቤት አደረሱ፡፡ ወንድም ሀክ ሱንግ እና እኔ በጸሎት ጊዜ ያጋጠመንን ተወያየን፡፡ በድንገት፥ ጥቁር ነገር መጣና በታላቅ ፍጥነት በዙሪያዬ ተሽከረከረ፡፡ ጥቁሩ ነገር እየበረረ ይዞረኛል እናም ፍጥነቱ እየጨመረ እንደ አውሎንፋስ (ቶርኔዶ) እስኪሆን ድረስ ተሽከረከረ፡፡ በዚያ ጊዜ፥ ዙሪያዬ ጨለመብኝና ፈዘዝሁ፡፡ ንቁ ሆኜ ለመቆየት ሞከርሁና የሆነ ነገር ያዝሁኝ፡፡ ነገር ግን ሚዛኔን ስቼ የሲሚንቶው መሬት ላይ ወደቅሁ፥ መሬቱ ጭንቅላቴን መታኝ፡፡ ራሴን ሳትሁኝ፡፡ እህት ቤይክ ቦንግ ንዮና እናቴ ወደ እኔ ሮጡ፡፡ በሁኔታዬ ተደናግጠውና ሰግተው ነበር፡፡ ምን እንደተከሰተ በኋላ ላይ በመንፈስ ንቁ ከሆኑት የቤተክርስቲያኑ አባላት ተረዳሁ፡፡ የሁሉም ማብራሪያ ተመሳሳይ ነበር፡፡



ምንም እንኳ በመንፈስ ብነቃም፥ መንፈሳዊነቴ አልበሰለም፡፡ ትንሽ ረዘም አድርጌ ብጸልይ፥ ገነትንና ሲኦልን እጎበኝና የትንቢትን ጸጋ እቀበል ነበር፡፡ እርኩሳን መናፍስቱ

ይህን እውነታ ተረድተው ነበር:: የጥቃታቸው ማዕከል ነበርሁ:: አላማቸው ሙሉ በሙሉ በመንፈስ እንዳልነቃ ለማገድ ነበር:: ተፈጥፍጬ ስወድቅ ያዩኝ የቤተክርስቲያን አባላት በመልአክ የተመሰለ እርኩስ መንፈስ አይተዋል:: መንፈሱ በዝምታ በላዬ አንጃበበ:: እኔ ወደ መሬት ለመጣል በታላቅ ፍጥነት በዙሪያዬ ተሽከረከረ:: ከወደቅሁ በኋላ እርኩሱ መንፈስ ከሌሎች እርኩሳን መናፍስት ጋር ጭንቅላቴ ውስጥ ሲገባ አዩት:: የራስ ምታቴ መነሻ እነርሱ (እርኩሳን መናፍስቱ) ናቸው::

የቤተክርስቲያኑ አባላት ረድተውኝ ተመልሼ በእግሬ ቆምሁ:: ከባድ የራስ ህመም እየተሰማኝ ነው:: የማስታውሰው ነገር ሁሉ የሰጡኝን ማብራሪያ ነበር:: በመንፈስ የነቁት አባላት በዙሪያዬ ተሰብስበው እርኩሳን መናፍስቱን ማስወጣት ጀመሩ:: ነገር ግን ምንም ቢጥሩ፥ ራስምታቴ ባሰበት::

ሁሉም መጋቢውን በጉጉት ተጠባበቀ:: ከዚህ በፊት ሌሎች እራስ ምታቶች አጋጥመውኛል እናም ግን ቀለል ያሉ ነበሩ፥ ነገር ግን አሁን ከራስምታቴ ጀርባ እርኩሳን መናፍስቱ ኖረውበት፥ ሊቋቋሙት የማይችሉት ህመም ነበር:: የማብድ ነው የመሰለኝ:: ህመሙ እየከፋ መጣ በጣም ጮህኩ:: በህመም ስጮህ ሳለ፥ መጋቢው ደረሰ:: መጋቢው መሬት ላይ ወድቄ እርዳታ ስለምን አየኝ:: ምን እንደተፈጠረ ጠየቀኝ:: የቤተክርስቲያን አባላቱ በአንድ ድምጽ ምን እንደተከሰተ አስረዱ:: መጋቢው እንደተነገረው፥ ተጠንቅቆ፥ *"እርጉማን እርኩሳን መናፍስት፥ በሁሉን ቻዩ በ**ኢየሱስ** ስም፥ ታስራችሁ ውጡ!"* ብሎ ጮኸ:: መጋቢው እንደጮኸ ወዲያውኑ፥ እርኩሳን መናፍስቱ እየጮኹ ጠፉ:: ከዚያ በኋላ መተንፈስና መረጋጋት ቻልሁ:: ራስምታቱ መሄድ ጀመረ::

**እህት ቤይክ ቦንግ ንዮ:** **መጋቢው በገነት ታዋቂ ነው*

የሙሉ ሌሊት ጸሎታችንን ከጨረስን በኋላ፥ መጋቢው በጠዋቱ ማለዳ ላይ ሰበከ:: ሲሰብክ ሳለ፥ **ጌታ** ከመጋቢው ጀርባ ሆኖ ተናገረ:: በጉባኤው መሐል ላይ፥ **ጌታ** እንዲህ አለ፥ ***"ቦንግ ንዮ፥ የ30 ቀኑ ዘመቻ በጣም ነው ያስደሰተኝ! አስደሳች ነበር!"*** **ጌታ** በገነት ስለእኛ ባሰበ ቁጥር ራሱን ከመሳቅና ፈገግ ከማለት ሊከለክል እንደሚሳነው እየደጋገመ ነገረን::

**ጌታ** እንደነገረን በገነት **እርሱ** ሲስቅና ፈገግ ሲል፥ መላእክቱና ቅዱሳኑ ደስተኛ የሆነበትን ምክንያት ያውቃሉ:: መላእክቱና ቅዱሳኑ የቅርብ ጊዜ ዜና ለመስማት ጉጉ ናቸው:: ቅዱሳኑ **ጌታ** እንዲዚህ በጥሩ ስሜት ውስጥ እንዲሆን ያደረገውን ነገር እንዲነግራቸው ይገፋፉታል::

**ጌታ** በ'የ**ጌታ** ቤተክርስቲያን' የሚገኘው መጋቢ ኪም ዮንግ ዱ በገነት ታዋቂ እንደሆነ ነገረን:: መጋቢው በመንፈስ እንደነቃ፥ ከ**ጌታ** ጋር ገነትን ይጎበኛል:: እስከዛ ቀን ቸኩያለሁ:: መጋቢው በምድር ትንሽ ደሀ ቤተክርስቲያንን ነው የሚያስተዳድረው፥ ነገር ግን **ጌታ** በእርሱ ውስጥ ያለውን ዋጋ አውቆታል:: ስለዚህም በጣም በምስጋና እሞላለሁ::

መጋቢው መላ ቤተሰቤን እንደራሱ ነው የሚቆጥራቸው:: በአክብሮትና በሞገስ ነው የሚንከባከበን:: መጋቢው በምላሹ ምንም ሳይጠብቅ ራሱን ይሰጠናል:: ሲያልን ስጎበኝና ከሰይጣን ጋር ስዋጋ፥ **ጌታ** ሽልማቴን ጨምሮታል:: የመጋቢው ሽልማትና የወደፊት ቤት ጨምሯል:: ይልቁንም፥ የመጋቢው ቤት ከእኔ ቤት ይበልጣል:: ገነትን ስጎበኝና የወደፊት ቤቴን የመጎብኘት እድል ሳገኝ፥ 514 ፎቅ ከፍታ ያለውን የመጋቢውን ቤትም አይቻለሁ::

የወይዘሮ ካንግ፥ ህዩን ጃ እና ጁ ኢዩን ጭቅጭቅ የወደፊት ቤታቸው በመጠኑ እንዲቀንስ አድርጎታል:: የወይዘሮ ካንግ ህዩን ጃ ቤት 318 ፎቅ ከፍታ አለው፤ ከጭቅጭቃቸው በፊት 319 ፎቅ ከፍታ ነበረው:: የጁ ኢዩን ቤት 31 ፎቅ ነበር፥ ነገር ግን ከወይዘሮ ካንግ ህዩን ጃ ጋር በተፈጠረው አለመስማማት፥ ቤቷ ወደ 28 ፎቅ ቀንሷል:: የዮሴፍ ቤት 22 ፎቅ ከፍታ አለው እንዲሁም የሀክ ሱንግ ቤት 28 ፎቅ ከፍታ አለው:: ዩ ከዩንግ በተደጋጋሚ ከሀክ ሱንግ ጋር ስለምትጨቃጨቅ፥ ቤቷ ከ20 ፎቅ ወደ 17 ፎቅ ተቀንሷል:: የዲያቆን ሺን ሱንግ ኪዩንግ ቤት 6 ፎቅ ከፍታ አለው እናም መልካም *ሥራዎችን* መሥራት ስለሚኀላት በግንባታ አቅርቦት ላይ እጥረት አለባት:: እያንዳንዱ ሰው ቀጣይነት ላለው የቤት ግንባታ የማእድናት መጋዘን አለው፥ ነገር ግን የእቃዎቹ መጠን የሚወሰነው በእያንዳንዱ ሰው መልካም *ሥራ* ነው:: የዲያቆን ሺን ሱንግ ኪዩንግ ቤት ግንባታ ቆሟል:: የእኔ ቤት 70 ፎቅ ከፍታ አለው:: የወንድማችን ሊ ሀክ ሂ ቤት ከ300 ፎቅ በላይ ከፍታ አለው:: ሆኖም ግን፥ ልረዳው ያልቻልሁት አንድ ነገር አለ:: **ጌታ**ን ጠየቅሁት፥ *"**ኢየሱስ** ሆይ፥ ወንድም ሊ ሀክ ሂ የእሁድ የቀን አገልግሎት ብቻ ነው የሚካፈለው:: እንዴት ነው ታዲያ የእርሱ ቤት እንደዚህ ረዥም የሆነው?"* **ጌታ**ም መለሰ፥ ***"ወንድም ሊ ሀክ ሂ ከ70 ዓመት እድሜ በላይ እንደሆነውና ከእድሜው በተጻራሪ ፈጽሞ የእሁድ ጉባኤ ቀርቶ እንደማያውቅ ታውቂያለሽ:: በረዶ ቢሆን፥ ዝናብ ቢሆን፥ መብረቅ ቢሆን፥ መቼም የእሁድ አገልግሎት ቀርቶ አያውቅም:: ረዥም ርቀት***

*ምተርሳይክሉን እየጋለበ፣ ከሀክ ዶንግ ከተማ እስከ ሱክ ናም ዶንግ ከተማ ድረስ ይጋልባል፡፡ በተጨማሪም፥ ተጨማሪ ገንዘብ ባገኘ ቁጥር፥ ለቤተክርስቲያን ይሰጠዋል፡፡ እነዚህ ናቸው ብዙ ፍቅ እዲኖረው ያደረጉት ምክንያቶች፡፡"*

ለዚህ ቤተክርስቲያን አዲስ አባል ነኝ እናም ስለወንድም ሊ ሀክ ሂ ብዙ አላውቅም፡፡ ለቤተክርስቲያን ምን ያህል አስራት እንዳወጣ አላውቅም፡፡ መጋቢው ስለ ወንድም ሊ ሀክ ሊ ባህሪ ካስረዳን በኋላ፥ ስለእርሱ ብዙ አወቅሁ፡፡ መጋቢው እንደገለጸው፥ ወንድም ሊ ሀክ ሂ ከ70 ዓመት በላይ ነው እናም የሰውነት አቅሙ የተገደበ ነው፡፡ በዚህ እድሜ፥ የጤና ችግር አለበት፡፡ እግሩ ላይ ችግር አለበት እናም ለመራመድ አይመቸውም፡፡ ቢሆንም ግን፥ ከገደቡ በተጻራሪ፥ በታማኝነት ቤተክርስቲያን ይከታተላል እንዲሁም በቤተክርስቲያን የአስተናጋጅነት ስፍራውን ጠብቋል፡፡

ሌላ ወጣት አዋቂዎች ወደ ቤተክርስቲያናችን መጥተዋል ሄደዋል፡፡ የመልቀቃቸው ምክንያት የሁሉም ይለያያል፡፡ አንዳንዶቹ መነቃቃት የለም ብለው ነው፥ አንዳንዶቹ በፈተና ምክንያት ነው የለቀቁት፥ አንዳንዶቹ ደግሞ በራሳቸው ምክንያት ነው የለቀቁት፡፡ ሆኖም፥ ወንድም ሊ ሀክ ሊ ሁኔታዎቹም ሆነ ፈተናዎች ሳይበግሩት የቆየና የጸና እርሱ ብቻ ነው፡፡ እስከዚህ ቀን ድረስ፥ ውጪ ያለው የአየር ጸባይ ምንም የከፋ ቢሆን ቤተክርስቲያን ሲካፈል አየዋለሁ፡፡ መቼም አርፍዶ መጥቶ አያውቅም፡፡

**ጌታ** የቤተክርስቲያናችን አምልኮና አገልግሎት አስደሳችና አርኪ እንደሆነ እውቅና ሰጥቶታል፡፡ ማንኛውም በምድር ላይ ከሚገኝ ቤተክርስቲያን ለ**ጌታ** በጣም አስደሳች የሆኑ በጣም አልፎ አልፎ ነው ያሉት፡፡ **ጌታ** እንደገለጸው በራሳቸው ስሜትና ራዕይ ተልዕኮአቸውን ይመሩ የነበሩ ብዙ መጋቢዎች ነበር፡፡ እናም እንደመጽሐፍ ቅዱስ ሕግ ተልዕኮአቸውን ይመሩ የነበሩ መጋቢዎች ጥቂቶች ነበሩ፡፡ ስለዚህም ስለእኛ መጋቢ **ጌታ**ን መጠየቅ ነበረብኝ፡፡ **ጌታ** እንዳለው መጋቢያችን **ጌታ** እንዳዘዘውና እንደ **ጌታ** ፈቃድ ለማድረግ እየሞከረ ነው፡፡ ለመጋቢያችን **ጌታ** እንዴት እውቅና እንደሰጠው ስነግረው፥ መጋቢው በጣም ተደስቶ ነበር፡፡

**ጌታ** መንፈሳዊ ዓይኖቻችንን ለመክፈት አስቦ እንዳልነበረ ነገረን፡፡ ነገር ግን በየቀኑ በታማኝነት መጸለያችንና እንደጸሎት አርበኞች ከአጋንንት ጋር በነበሩን መንፈሳዊ ውጊያዎች፥ ትኩረቱን ሳብነው፡፡ **ጌታ** በመጀመሪያ ያሰበው ጥቂት ከሞከርን በኋላ እንደምናቋርጥ ነበር፡፡ ሆኖም ግን፥ ያለማቋረጥ በታማኝነት ስንጸልይ ካየን በኋላ፥ በጣም ተሳበ፡፡ በጣም ተሳበና መንፈሳዊ ዓይኖቻችንን ሊከፍትልን ወሰነ፡፡ መንፈሳዊ ዓይኖቻችንን አንድ በአንድ መክፈት ጀመረ፡፡

**ጌታ** ያለማቋረጥ በመጸለያችን ምክንያት የተጎዳውን ሰውነታችንን እንድንንከባከብ ጠየቀን፡፡ የጸሎት ዘመቻውን ስንጨርስ፥ መጋቢው፥ *"ከአሁን ጀምሮ፥ የሙሉ ሌሊት ጸሎት የሚኖረን እሮብ፣ አርብና እሁድ ብቻ ነው፡፡ በሌሎቹ ቀናት፥ የማለዳ አገልግሎት ብቻ ይኖረናል፡፡"* አለ፡፡ መጋቢው ይህን እቅዱን እንደገለጠ፥ **ጌታ** አጨበጨበና እንዲህ አለ፥ ***"ይህ ጥሩ እቅድ ነው፡፡ በእቅዱ እስማማለሁ፡፡ ልክ አንተ እንዳቀድኸው እያሰብሁ እንደነበር እንዴት አወቅህ?"*** **ጌታ** በጣም ተደስቶ ነበር፡፡ ዘመርን አመለከን፥ 'ነፍሴ ሆይ አመስግኚ' **ጌታ**ን አመስግነንና ጸልየን ወደ ቤት ሄድን፡፡

**ወይዘሮ ካንግ ህዩን ጃ፡** *የእሳቱ ጥምቀት ጊዜ አስገራሚ ጊዜያቶች

የ30 ቀን የጸሎት ዘመቻችን ፍጻሜ በጣም አለመርካት እንዲሰማኝ አድርጎኛል፡፡ በመንፈስ ስላልነቃሁ እንዲያልቅ ፍላጎት አልነበረኝም፡፡ ለመጋቢው ለተጨማሪ ጥቂት ቀናት እንዲያራዝመው ጥያቄ አቅርቤ ነበር፡፡ ሆኖም ግን፥ **ጌታ** ለመጋቢው ውሳኔ እንድገዛ አዘዘኝ፡፡ በሳምንት ቢያንስ ሦስት የጸሎት ጉባኤዎች እንደሚኖሩን ሳውቅ ተረጋጋሁ፡፡ በቀጣይ የጸሎት ጉባኤዎቻችን ውስጥ መንፈሳዊ ንቃትን ለመቀበል እየተጠባበቅሁ ነው፡፡

የመጋቢ ሚስት ሆኜ ስኖር ከአስር ዓመት ባላይ ሆኖኛል፡፡ በአገልግሎታችን ጊዜያት፥ መጋቢውን በብዙ ከባድ ፈተናዎች ውስጥ እንዲያልፍ የሚያደርጉት ብዙ ችግሮችን ፈጥሬአለሁ፡፡ ሙሉ በሙሉ ንስሐ መግባት ይገባኝ ነበር፡፡

ከግንኙነታችን መጀመሪያ ጀምሮ፥ መጋቢውና እኔ በእምነታችን ልዩነት ነበረ፡፡ እንደ ወጣት እንኳን፥ መጋቢው ጠንካራ፥ የማይናወጽ እምነት ነበረው፡፡ ችግር ባጋጠመው ጊዜ ሁሉ፥ ይጸልይና በ**ጌታ** ይታመን ነበር፡፡ ሙሉ በሙሉ በ**ጌታ** ላይ ጥገኛ ነበር፡፡ እምነታችን ቢነጻጸር፥ የእኔ እምነት በጥርጥር የተሞላ ነበር እናም በጸሎታችን ውስጥ እንኳ የሚታይ ነበር፡፡

ምንም እንኳን መጋቢው በ**ጌታ** ቢተማመንም፥ ለእኔ ግን የሚታየኝ ቤተሰቡን እንኳን በገንዘብ መደገፍ እንደማይችል ነው፡፡ ሆኖም፥ ዓመታት ሲያልፉና ጸሎቴ ሲጠነክር፥ ከ**ጌታ** ጋር በመገናኘት **እግዚአብሔር** ባለቤቴን እንደሚወደውና እንደ ታማኝ አገልጋይ እንደሚቆጥረው ተረዳሁ፡፡ **እግዚአብሔር** ለባለቤቴ ያለው ፍቅር ጥልቅ ነበር፡፡ **ጌታ**ን ሊያስደስተው በሚችል

መልኩ ለረዥም ሰዓት ጸልዬ አላውቅም፡፡ ባለፈው ዓመት ጁላይ ወር ላይ፥ በበለጠ ትጋት መጸለይ ጀመርሁ፡፡ ከ**ጌታ** ጋር ብዙ ሰዓት በጸሎት ሳሳልፍ፥ 2005 ዓመት ብሩኅ ይሆን ጀመር፡፡

ተልዕኮው ወይም አገልግሎቱ ምንድ ነው? የመጋቢ ሚስት ድርሻዋ ምንድ ነው? የእኔ ተግባር ምንድ ነው? ለጥያቄዎቼ መልስ ለማግኘት በኮሪያ ውስጥ ወደሚገኙ የጸሎት ቤቶች መሄድ አዘወትር ነበር፡፡ ነገር ግን ፍሲጋዬ በከንቱ ነበር፡፡ ቀን ቀን፥ እኔና መጋቢው ከቦታ ቦታ እየተዘዋወርን እንሰብክ ነበር፡፡ ያለማቋረጥ ሌሊቱን እንጸልያለን፥ በእያንዳንዷ ምሽት፡፡ እየደከምሁ መጣሁና በሽታዬ እየከፋ ሄደ፡፡ የሳንባ ነቀርሳ በሽታ ነበረብኝና በበሽታው ለረዥም ጊዜ ተሠቃየሁ፡፡ በተከታታይ መድኀኒት እወስድ ነበር፡፡ ሆኖም ግን፥ **ኢየሱስ**ን ሳገኘው፥ በሚገርም ሁኔታ ከህመሜ ተፈወስሁ፡፡ አሁን፥ በፍጹም ጤንነት እገኛለሁ፡፡

ደካማና ውጤታማ ባልነበረው አገልግሎታችን ምክንያት፥ ቤተክርስቲያናችንን ለማሳደግ ምንም ዓይነት መንገድ አልነበረንም፡፡ የቤተክርስቲያናችን ስርዓትና አገልግሎት የተገደበ ነበር፡፡ አንድ ቀን፥ **ጌታ** ልዩ እድልን ሰጠን፡፡ ለረዥም ሰዓት ጸለይሁ፥ ነገር ግን ፍሬ አልባ መሰለ፡፡ ጸሎቶቼ ውጤታማ አልነበሩም ወይም አልተመለሱም፡፡ አገልግሎታችን ውጤታማ ያልነበረና ሥራችን በከንቱ የሆነ ይመስል ነበር፡፡ በ2005 ዓ.ም፥ መጋቢው ከተገደበው ሁኔታችን ለመውጣት ወሰነ፡፡ አገልግሎታችን በአምልኮና በንስሐ ጸሎት ጀመረ፡፡ ከዚያም መጋቢው በኃይል በተሞላ ስብከት ቀጠለ፡፡ ለአንድ ሰዓት ብቻ ነበር የሚሰብከው፥ ነገር ግን አሁን ስብከቶቹ ከሁለት እስከ ሦስት ሰዓት ይወስዳሉ፡፡ ምንም እንኳን አገልግሎቱ ከሁለት እስከ ሦስት ሰዓት ቢወስድም፥ ምእመናኑ ብዙ ይፈልጉ ነበር፡፡ በ30 ቀኑ የጸሎት ዘመቻ ላይ የተሳተፉት የምእመናኑ አባላት አሁንም አለመርካት ይሰማቸዋል እናም ተጨማሪ ይፈልጋሉ፡፡ ሁሉም ዓይነት አገልግሎቶቻችን ሲረዝሙ፥ ረሀባቸው የባሰ እየጨመረ ይሄዳል፡፡ የጸሎት ዘመቻውን ሲካፈሉ፥ ሰዓት ቦታ አልነበረውም፡፡ አምልኮ ከሦስት እስከ አራት ሰዓት ይቆያል፡፡ ስብከቱ ቢያንስ ለሦስት ሰዓት ረዝሟል፡፡ የእለት ተእለት ጸሎት አምስት ሰዓት ያህል ይቆያል፡፡ የመጋቢው ስብከት በ**መንፈስ ቅዱስ** የታገዘ እና ምእመናኑ ልብና መንፈስ ውስጥ ጠልቆ የሚገባ ነበር፡፡ **ጌታ ኢየሱስ** በቅዱስ ዳንሴ የፈውስ አገልግሎት እንደሚኖረኝ ነግሮኛል፡፡

ይሄ ሲነገረኝ፥ ለማወቅ ጓጓሁና **ጌታ**ን ስለ ፈወስ አገልግሎት ጠየቅሁት፡፡ **ጌታ** በቅንነት በምሳሌ አስረዳኝ፡፡ የፈወስ ቅዱስ ዳንስ አገልግሎትን ለመቀበል የተወሰኑ የመንፈሳዊነት ደረጃዎች አሉ፡፡

ለምሳሌ፥ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሁለተኛ ዓመት ብሆን፥ ብቁ አልሆንም አልያም ልወጣው አልችልም፡፡ ሆኖም፥ በኮሌጅ ሁለተኛ ዓመት ብሆን፥ የቅዱስ ዳንስን ፈውስ አገልግሎት ለመፈጸም ብቁ ልሆን እችላለሁ፡፡ እህት ቤይክ ቦንግ ንዮ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጀማሪ ደረጃ ላይ ናት፡፡ የኮሌጅ ጀማሪዎች ስንሆን፥ ከፍ ወዳለ ደረጃ እንሸጋገራለን እናም ቀስ እያልን ማከናወን እንችላለን፡፡ በ**መንፈስ ቅዱስ** መደነስ አንድ ሰው የሚለማመደው ወይም የሚሰለጥነው አይደለም፡፡ ማንም በራሱ ሊፈጥረው አይችልም፡፡ ይሄ በ**ጌታ** ጸጋ ብቻ የሚያሳኩት ነው፡፡

**መጋቢ ኪም ዮንግ ዱ፤** *መመለሻ የሌለውን ድልድይ መሻገር

**ጌታ** ብዙ ጊዜ አስጠንቅቆናል፥ ***"በ'የጌታ ቤተክርስቲያን' ያሉ የጸሎት አርበኞች ጥልቅ መንፈሳዊ እውቀት አላቸው፡፡ መቼም ቢሆን መደበኛ የክርስቲያን ህይወት አትኖሩም፡፡ ድልድዩን ተሻግራችኋልና ፈጽሞ መመለስ አትችሉም!"***

ልዩ ስለሆነው ስለ**ጌታ** ጣልቃ ገብነት አክብሮት አለኝ፡፡ በአደጋ ላይ የነበረችውን ቤተክርስቲያኔን እንደ **ጌታ** ፈቃድ እንዴት እንደምመራ ተጨንቄ ነበር፡፡ ድፍረቴ ዝቅተኛ ፍርሀቴም ከፍተኛ ነበር፡፡ የቤተክርስቲያን አባላት በእርኩሳን መናፍስት ሲሸነፉ አይቻለሁ፡፡ ያስተሳሰብ መሠረቴ እውቀት የጎደለውና የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀቴም በጣም የተወሰነ እንደነበር ተረድቻለሁ፡፡ ባልዳበረ አዕምሮና በውስን እውቀት፥ በመንፈሳዊ ዓለም ለመዋጋት ዝግጁ አልነበርሁም፡፡ ይህንን ስረዳ፥ በጣም ነበር ያፈርሁት፡፡

ብዙ ኮሪያውያን መጋቢዎች የየራሳቸውን አስተምህሮና አገልግሎት መንገድ ይጠቀማሉ፥ በራሳቸው ፍልስፍና ላይ በመመስረት፡፡ ውጪያዊ ቅድስናን ማንጸባረቅ በተደራጁ ሀይማኖቶች የተለመደ ነው፥ በአገልግሎታቸው የ**ጌታ** ህልውና የለበትም፡፡ በድርጅት ሀይማኖቶች በመካፈሌ ተጠያቂ ነኝ፡፡ *"የ**ጌታ** ፍቃድ ይሁን"* የሚለውን በሰማሁ ጊዜ ሁሉ ልቤ በፍጹም አድናቆትና ክብር ይሞላል፥ ምክንያቱም **ጌታ** ብዙ የኮሪያ መጋቢዎችንና ምእመናኖቻቸውን ሁኔታ አሳይቶኛል፡፡ እኔ ልፈርድባቸው አይደለም፥ ነገር ግን **ጌታ** እነዚህን ጉዳዮች እንዲፈታቸው እየጠበቅሁ ነው፡፡

**ጌታ** በራሴ ልፈታቸው የማልችላቸውን የግል ችግሮቼን ፈቷቸዋል፥ አሁን ሌሎች መጋቢዎች እንደሚያጋጥሟቸው ችግሮች ዓይነት፡፡ **ጌታ** በእነዚህ ጉዳዮች ረድቶናል እናም ለእነርሱ(ለችግሮቹ) የሚሆን ትክክለኛውን መፍትሄ ሰጥቶኛል፡፡ መላ ህይወታችንን ለ**ጌታ** እንድንኖር ተመርጠናል፡፡

መጋቢዎችና ምእመናኖቻቸው እንደየ ሥራቸው ይፈረድባቸዋል፡፡ ህይወታቸው፥ ጥረትና ሀሳቦቻቸው ሁሉ ይመዘናሉ፡፡ ከግዙፍ ቤተክርስቲያን እስከ ትናንሾቹ፥ ሁሉም ከ**ጌታ** ፊት ይቆማሉ፡፡ በዚያች ቀን ሁሉም ሥራዎች ፍርድ ያገኛሉ፡፡

በፊት፥ አዲስ ስለተሠራ ሕንጻቸው የሚመኩትን ጉባኤያቸውን እካፈልና ማስታወቂያቸውን አነብ ነበር፡፡ እቀና ነበር፥ ምክንያቱም ቤተክርስቲያኖቻቸው በፍጥነት ነበር የሚገነቡት እናም ብዙ ምእመናንን ይይዛሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ በመነቃቃት (ሪቫይቫል) ምክንያት እንደሆነ ይላሉ፡፡ በእነርሱ ስኬት የዝቅተኛነት ስሜት ይሰማኝና እጨናነቅ ነበር፥ ምክንያቱም ውድቀት እንደሆንሁ ነበር የሚሰማኝ፡፡ ሆኖም፥ ይህ ከዚህ በኋላ አያሳስበኝም፡፡

ይህ ማለት አገልግሎቴ በአዝጋሚ ሁኔታ አልያም ያለ ጽኑ ልብ ይደረጋል ማለት አይደለም፡፡ ብዙውን ጊዜ፥ መጋቢዎችና ቅዱሳን የእምነት እርምጃቸውን በንጹህ መነሳሳት ይጀምራሉ፡፡ ሆኖም ግን፥ ጊዜው እየገፋ ሲሄድ ሳያስቡት የዓለም ወዳጅ ይሆናሉ፡፡ ይህ **ጌታ**ን ያስቆጣዋል፥ እናም በኋላ ላይ ይፈርድባቸዋል፡፡ (ያዕቆብ 4፡4)

እያንዳንዱ ሰው ህይወቱን በራሱ ደረጃ ነው የሚኖረው፡፡ አብዛኞቹ የቤተክርስቲያናችን አባላት በዙሪያቸው ያሉ ሰዎች የእኛ ቤተክርስቲያን መተተኛ እንደሆነች እንደሚሏቸው ነግረውኛል፡፡

አንድ ግልጽ የሆነ ነገር ልጥቀስላችሁ፥ *“ምን ዓይነት ቤተክርስቲያን ናት አዲስ አማኞች በአንድ ጊዜ በልሳን የሚናገሩባት? ምን ዓይነት ቤተክርስቲያን ትንቢት ትናገራለች፥ እርኩሳን መናፍስትን ትዋጋለች፥ እናም የገነትና የሲኦል ራእዮች ያሏት? ሰው ወደ ገነት ወይም ሲኦል ሊሄድ የሚችለው ከሞተ በኋላ ነው፡፡ ምን አልባት በህልም ገነትንና ሲኦልን ሊጎበኝ የሚችልበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ ነገር ግን አንዴ ወይም ሁለት ጊዜ ብቻ ነው ሊጎበኙ የሚችሉት፡፡ ሆኖም ግን፥ እለት እለት ወደ ገነትና ሲኦል መሄድ የማይቻል ነው፡፡ ትርጉም አይሰጥም!”* የእኔን ምእመናን ወደ ራሳቸው ቤተክርስቲያን ለመሳብ ይሞክራሉ፡፡

በድፍረት አውጃለሁ፥ *“ትክክል ናቸው፡፡ ከሞትን በኋላ ገነት ወይም ሲኦል እንሄዳለን፡፡ ነገር ግን፥ በህይወት ሳለን ገነትንና ሲኦልን ጎብኘት ግን በ**እግዚአብሔር** ሁሉንቻይ ኃይል ብቻ ነው፡፡”* እኔ ራሴ፥ የገዛ የቅርብ ቤተሰቦቼ ካሾፉብኝና ከተዘባበቱብኝ እንዲሁም ስለመተት ከወነጀሉኝ በኋላ፥ ስለሚናገሩት ነገር ግድ የለኝም፡፡ ገነትና የእኛ **ጌታ** ታላቅ ምስጢራት ናቸው፡፡ ምንም እንኳ የተቀጠረው የጸሎት ዘመቻችን ቢያልቅም፥ ያለማቋረጥ መጸለያችንን እንቀጥላለን፡፡ ያሳለፍኳቸውና የመዘገብኳቸው መለኮታዊ ክስተቶች ለዚህ መጽሐፍ ዓላማ ሲባል አጥረዋል፡፡ እያንዳንዷን ገጠመኝ ብመዘግባት፥ የመረጃው ብዛት ለአንድ መጽሐፍ ሊበዛ ይችላል፡፡ ስለዚህ፥ ሌሎቹን ገጠመኞች በቀጣይ መጽሐፍቶች እጽፋቸዋለሁ፡፡ ከተቀጠረው የጸሎት ዘመቻ በኋላ እንኳን **ጌታ** ጉብኝቱንና ሥራውን አላቆመም፡፡ **ጌታ** በሁሉም የእለት ተእለት ተግባራችን ጣልቃ ይገባል፡፡ ሀክ ሱንግና ዪ ክዩንግ በገጠመኞቻቸው ብልሆች ሆነዋል፡፡

**ጌታ** ስለ ገነትና ሲኦል ብዙ መጻሕፍትን የመጻፍ እድልን እንደሚሰጠኝ ነግሮኛል፡፡ በመጀመሪያው መጽሐፋችን፥ ቦታ አንሶን ስለነበር አንዳንድ አስደናቂ ክስተቶችን አልመዘገብናቸውም፥ ነገር ግን **ጌታ** እነዚያን ክስተቶች ወደሚቀጥለው መጽሐፍ አሸጋግሯቸዋል፡፡ የሚቀጥለው መጽሐፍ አስደናቂና አስደንጋጭ ይዘቶች ይኖሩታል፡፡ ስለዚህ፥ በጣም እጠነቀቃለሁ፡፡

ሁለተኛው መጽሐፍ ተፈጸመ

[**ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣** ኃጢአት የሌለበት ንፁህ **የእግዚአብሔር በግ፣** ንፁህ **የእግዚአብሔር ልጅ፣** ንፁህ **የእግዚአብሔር ቃል እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ** የሰው ልጆችን ሁሉ ከኃጢአት ሊያድን ስለ እኛ ኃጢአትና እርግማን ሆኖ በመስቀል ላይ ተሰቀለ። ያመነ የተጠመቀ ይድናል ያላመነ ግን ይፈረድበታል አለ ጌታ በከበረ ቃሉ።

ኃጢአታችንን በሥጋው ተሸክሞ በቀራንዮ በመስቀል ላይ ተሰቀለ፣ ሞተ፣ ተቀበረ፣ በሦስተኛውም ቀን በአባቱ ኃይል፣ በራሱም ሥልጣን በመንፈስ ቅዱስም ከሙታን ተለይቶ ተነሣ። ሃሌ ሉያ፣ የጌታችን የአምላካችን የመድኃኒታችን የንጉሣችን የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ፍፁም ፍቅር እጅግ እጅግ እጅግ ማረከኝ።
ከአባቱ ቅዱስ ፈጣሪ ከ**አብ** ወጥቶ እንደመጣ ላመኑት አማኝ ቅዱሳን ታያቸው፣ ወደ አባቱም አረገ፣ ዳግመኛም በእርሱ ያመኑትን ቅዱሳንና ለእርሱ በንስሐ ንጽህናና ቅድስና የተዘጋጁትን ቅዱስ የሆኑ ክርስቲያኖችን ወደ ቅዱስ አባቱና ወደ ቅዱስ መንግሥቱ ሊወስድ እጅግ በቅርቡ ይመጣል፤

የሚመጣበትን ሰዓቱንና ቀኑን ግን ከአባቱ ከ**እግዚአብሔር አብ** በቀር የሚያውቅ እንደሌለ **ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ** በቅዱስ ወንጌል ላይ ነግሮናል፤ እኛ ግን ሁል ጊዜ በጸሎት ተግተን በንስሐና በቅድስና በእምነትም በጽድቅም ሥራ በእርሱ ሆነን እየጠበቅነው እንድንዘጋጅ አዞናል። **እኛ አንድ አምላክ እግዚአብሔር አለን ቅዱስ ቃሉም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ቅዱስ መንፈስም አለው።**

**ጌታ ኢየሱስ** በመስቀል ላይ የፈሰሰው ቅዱስ ደሙ ከኃጢአት ሁሉ ያነፃናልና፣ ንስሐ እንግባ፣ ለእርሱ ራሳችንን ሙሉ በሙሉ እናስገዛ፣ እኛ ለስጋ ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር **ክርስቶስ ኢየሱስ** ስለ እኛ አንዴ በመስቀል ላይ ሞቷልና ከሞትም ተነስቶልናልና በንፅህና ጌታን በፍጹም ልባችን፣ በፍጹም ነፍሳችን፣ በፍጹም ኃይላችን እንውደደው ተግተን እንፈልገው ወደ እርሱም እንቅረብ እርሱም ወደ እኛ ይቀርባል፣ የፊቱንም ብርሃን ያበራልናል፤ ወንድሞችንም እንደራሳችን እንውደድ፣ ቅዱስ ቃሉን ከመጽሐፍ ቅዱስ ዘወትር እንመገብ፤ የከበረውን የዘላለም ሕይወት የሚሆነንን ቅዱስ ሥጋውን እንብላ ክቡር ደሙንም እንጠጣ፣ አምላካችን መድኃኒታችን **ጌታችን ኢየሱስ** እንዲህ በፍቅር አዞናልና። **መጋቢያችን መመኪያችን ሕይወታችን አለኝታችን መደገፊያችን አለታችን አቅራቢያችን ቤዛችን እግዚአብሔር መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ተመስገን።**

ዳግም ከውሃና ከ**መንፈስ ቅዱስ** የተወለዳችሁ ሁሉ የጨለማውን ሥራ አውልቃችሁ **ቅዱስና መልካም ጌታ ብርሃን ኢየሱስ ክርስቶስ**ን ለብሳችሁታልና ደስ ይበላችሁ፣ እጅግ ደስ ይበላችሁ፣ ንስሐ ግቡ፣ ከኃጢአት ሁሉ ራቁ፣ ራሳችሁን ክዳችሁ እለት እለት መስቀሉን ተሸክማችሁ የሰላሙን **ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ**ን በቅድስና በንጽህና በትእግስት እንደቃሉ ተከተሉት፣ **የሰላም አምላክ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ** ሰላም፣ ደስታ፣ ታላቅ ፍቅርና ዘላለማዊ እረፍት ሊሰጣችሁ እጅግ በቅርቡ ይመጣል። **በጌታችን በክርስቶስ** ሆናችሁ በጸሎት ትጉ፣ **ስለ ኢየሩሳሌም ሰላም ጸልዩ**፣ ሰዎች ሁሉ **የሕይወትን ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ**ን አውቀው ንስሐ ገብተው ከውሀና ከመንፈስ ቅዱስ ዳግም ተወልደው የ**እግዚአብሔር** ልጆች ሆነው በመንግሥተ ሰማይ የበጉ ክርስቶስ ኢየሱስ የሕይወት መጽሐፍ ላይ ስማቸው ይጻፍ ዘንድ ጸልዩ፣ ለዚህም የክብር ጌታ ራሱ **ጌታችን መድኃኒታችን አምላካችን የናዝሬቱ ኢየሱስ** ይረዳችኋል።

በ**ጌታ** ሁኑ፣ የሕይወትን ወንጌል የእግዚአብሔርን ቃል፣ ከብጽዕት ቅድስት ድንግል ማርያም በቤተልሔም የተወለደውን፣ በናዝሬት ገሊላ ያደገውን፣ ስለ ኃጢአታችን በቀራንዮ ለዓለም ሁሉ የተሰቀለውን፣ የሞተውና የተነሣውን፣ አልፋና ኦሜጋ መጀመሪያውና መጨረሻው፣ ያለና የነበረው የሚመጣውም፣ **ቅዱሱን እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን** በሕይወታችሁ ሁሉ ምሰሉት ተከተሉት አክብሩት ውደዱት እመኑት፣ ትእዛዛቱንም በመፈጸም ደስ አሰኙት ውደዱት የሚላችሁን ሁሉ በማድረግ ታዘዙት እንታዘዘው፣ እርሱ እጅግ እጅግ እጅግ በታላቁ ያፈቅራችኋልና ለእርሱ የተለያችሁ ቅዱስና ጻድቅ ህዝቦች ሁኑ። ከኃጢአት ራቁ፣ ከኃጢአት ራቁ፣ ከኃጢአት ራቁ! የእግዚአብሔር ልጆች በህይወታቸው ሁሉ ጌታ ክርስቶስ ኢየሱስን ይመስላሉ። እነርሱ እንደ ጌታ ኢየሱስ ንፁሐን፣ እውነት አድራጊ፣ ቅዱሳን፣ ጌታ እግዚአብሔር ኢየሱስን የሚፈሩና የሚወዱ በጽድቅ የሚመላለሱ ታዛዦች ጌታ መድኃኒታቸውን ኢየሱስ ክርስቶስን መስለው የዓለም ብርሃን የሆኑ ናቸው። የንስሐና የትሕትሕና የጥበብም መንፈስ አድሮባቸዋል ከኢየሱስ ክርስቶስ ባገኙት ጸጋ አማካኝነት። ጌታ ሆይ ተባረክ ከፍ ከፍ በል!!!

**በእግዚአብሔር አብ ልጅ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያመነ የተጠመቀ እንደቃሉም በቅድስና በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የኖረ** የዘላለም ሕይወት አለው፣ **በጌታ እግዚአብሔርም** መንግሥት **በጌታ ኢየሱስ** ፊት ለዘላለም በፍቅር በክብር ደስታ ይኖራል። **እግዚአብሔርንም** ያመልካል ያወድሳል ያስደስታል።

እናንተ የሕያው አምላክ የ**እግዚአብሔር** ማደሪያዎች ቅዱሳን የ**ኢየሱስ ክርስቶስ** ቅዱሳን ልጆችና ተከታዮች ሆይ እስከ ሞት ድረስ ለወደዳችሁና ላፈቀራችሁ ለ**እግዚአብሔር** በታላቅ ምስጋና እልል በሉ አመስግኑ፣ **እግዚአብሔር ታላቅ ነው የታረደው በጉም ኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒትና ንጉሥ ጌታም ኃያል አዳኝም ጥበብም ነው** በሉ። በመንፈስና በእውነት አምልኩት ስሙንም ቀድሱ፣ ሃሌ ሉያ። የናዝሬቱ **ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ነው፣ ክብር፣ ጥበብ ውዳሴ ሁሉ ለኤልሻዳይ ያህዌ እግዚአብሔር ይሁን።**

**የጌታዎች ጌታ የነገሥታት ንጉሥ የእግዚአብሔር አብ ቀኝ ክንድ፣ የእግዚአብሔር አብ ፍቅርና ስጦታ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ይባረክ። ጌታ ሆይ** ካንተ ጋር በአንተ ላንተ መኖር እጅግ ደስ ያሰኛል **ብርሃን ኢየሱስ የክብር ድህነት ተስፋ።**

**በኃያሉ ቅዱስ ንጉሥ በክርስቶስ ኢየሱስ** ያላችሁ ወንድሞቼ ሆይ፣ ከቅዱስ አባቱ **ከእግዚአብሔር አብ** ወጥቶ በሥጋ የመጣው ቃል፣ ስለ እኛ ብሎ በቀራንዮ የተሰቀለው፣ ደሙን ያፈሰሰው፣ የሞተው የተቀበረው በሦስተኛውም ቀን **ከሙታን ተለይቶ የተነሣውን አምላኬን፣ የእግዚአብሔርን ቃል ጌታችንና መድኃኒታችን ክርስቶስ ኢየሱስ**ን መግለጥ እንዳለብኝ ያህል እገልጠው ዘንድ ስለእኔም ጸልዩ፣ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እና ንጹህ ፍጹም ፃድቅ በሆነ በአምላኬ **እግዚአብሔር አብ** ፊት ዘወትር **በክርስቶስ ኢየሱስ** በጸሎቴ አስባችኋለሁ እወዳችኋለሁ። አጽናኛችን ረዳታችን የሆነ፣ ወደ እውነት ሁሉ የሚመራን **የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ** ይርዳችሁ ያበርታችሁ፣ **በክርስቶስ ኢየሱስ** ባለን አንድ እምነት ያጽናችሁ። በ**እግዚአብሔር** ቅዱስ የወይን እርሻ

የምታገለግሉ **በክርስቶስ ኢየሱስ** ያላችሁ ቅዱሳን ሁሉ በርቱ ጽኑ፣ የሥራችንን ዋጋ ጌታችን **ኢየሱስ ክርስቶስ** ሊከፍለን ተዘጋጅቷል፤ **የቅዱስ አባታችን የእግዚአብሔር አብ ፍቅር የቅዱስ ጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ እና የመንፈስ ቅዱስ ሕብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን። ክብር ሁሉ ለአዶናይ እግዚአብሔር ይሁን በሰማያት እንዲሁም ሰላም ለሰው ልጆች፤ ሃሌ ሉያ፤ አሜን ሃሌ ሉያ። ሰላም ለእስራኤል ይሁን፣ ድንቅ መካር ኃያል አምላክ የዘላለም አባት የሰላም አለቃ ኢየሱስ ክርስቶስ ይባረክ።**

**ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ** ወዳጄ፣ ወንድሜ፣ ጌታዬ፣ አዳኜ፣ መልካም እረኛዬ፣ መምህሬ፣ ሙሽራዬ፣ ፈላጊዬ **አምላኬ ኢየሱስ ክርስቶስ** ሆይ አምንሃለሁ አመሰግንሃለሁ አወድስሃለሁ አመልክሃለሁ። **መንፈስ ቅዱስ** እወድሃለሁ፣ ቅዱስ ስምህ ይባረክ፣ ወደ እውነቱ ስለመራኸኝ፣ **ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ** የነገረኝን ሁሉ ስላሳሰብኸኝና በእርሱ እንድኖር ስለመራኸኝ አመሰግንሃለሁ፣ እወድሃለሁ።

ቅዱስ ቸር የዋህ ፍቅር ሊቀ ካህኔ ኢየሱስ ሆይ በዘላለም **የቅዱስ እግዚአብሔር አብ** ቅዱስ በረከት ተባረክልኝ፤ በኃጢአት ጨለማ ተቅበዝብዤ ሳለሁ ልታድነኝ የመጣህልኝ፣ ተጨንቄ ሳለ ትንፋሽ አጥሮኝ በሞት አፋፍ ሳለሁ ሕይወት ልትሆነኝ የደረስክልኝ ወዳጄ **ክርስቶስ ኢየሱስዬ**፣ በኃጢአት ባርነት ተይዤ መውጫው ጠፍቶኝ ሳለ **መንገድ እውነትና ሕይወት የሆንክ ኢየሱስ መጣህልኝ**፤ እድንም ዘንድ ወደ ንስሐና ወደራስህ መራኸኝ፣ ከቅዱሱ አባትህ ከፈጣሪዬ **ከእግዚአብሔር አብ ጋር አስታረቅኸኝ**፣ በመስቀል ላይ በፈሰሰውም ክቡር ቅዱስ ደምህ ስለኔ ማለድህ፣ በደምህም አጥበህ ንጹህ አደረግኸኝ የኔ ጌታ፣ ልብሶቼንም ሁሉ በከበረው ቅዱስ ደምህ ከበረዶ ይልቅ ከኃጢአት አነፃሃቸው። አንተ እኮ ለኔ ብርሃኔ ነህ የኔ ፍቅር፣ ፈጥኖ ደራሼ፣ መልካም እረኛዬ። ጠፍቼ የነበርኹ ልጅህ ነበርሁ፣ ጌታዬ ሆይ ንስሃ የማያስፈልጋቸውን ዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ቅዱሳን በጎችህን በቅዱሱ ተራራህ በጽዮን ላይ ትተህ ስለጠፋሁት ስለ ኃጢአተኛው ስለኔና ስለዓለሙ ሁሉ ድህነት ብለህ ወደዚህ ምድር በሥጋ መጣህ፣ በእኔ ፈንታ ኃጢአቴን ተሸክመህ ተሰቀልክልኝ፣ ሞትክልኝ፣ ተቀበርክልኝ፣ ሃሌ ሉያ ክብር ሁሉ ላንተ ይሁን የእኔ የልብ ትርታና የነፍሴ ደስታ **አምላኬ ኢየሱስ** ሆይ፣ በሦስተኛውም ቀን ሞትን ድል አድርገህ በቅዱስ አባትህ ቅዱስ በሆንክ በአንተና በቅዱስ መንፈስህ ሥልጣን ተነሳህ ሁሌም ለዓለም ሁሉ **መድኃኒት ኢየሱስ**። ዓይኖቼን በቅዱስ ቃልህ ከፈትክልኝ፣ በቅዱስ መንፈስህ ጥበብህን ገለጥክልኝ፣ ካንተ ከቅዱሱ አባቴና ፍቅረኛዬ ጋር ሕብረት ይኖረኝ ዘንድ **በመንፈስ ቅዱስህ** አጠመቅኸኝ የኔ ጌታ ኢየሱስ፣ በሕይወቴ ሁሉ እባርክሃለሁ አባብዬ፤ **ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ ነህ፣ ለጠፉት ሁሉ ቤዛ የዓለም ቤዛ ኢየሱስ አንተ ብቻ ነህ አንተ ብቻ መጠጊያና ለሁሉም መልስ ነህ። ኢየሱስ ክርስቶስ የጌታዎች ጌታ የነገሥታት ንጉሥ፣ የእግዚአብሔር አብ ልጅ፣ ልዑል ወቅዱስ ቤዛ ለዓለም**፤ ቅዱሱ ስምህ ይባረክ ጌታ ሆይ አምላክ ሆይ አስታራቂ ሆይ። የልቤ ደስታ፣ መካሪዬ፣ መምህሬ፣ **ፈጣሪዬ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ** ቅዱሱ ስምህ ይባረክልኝ፤ ኃይል፣ ጥበብ፣ ውዳሴ፣ ፍቅር፣ አምልኮ፣ ገዢነት፣ ክብር፣ በረከት ቅድስና ለአንተ ይገባል **ፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ**፣ ሃሌ ሉያ አሜን። በቃልህ በከበረው በገናናው በቅዱስ የወይን እርሻህ ላይ ያሰማራኸንን ባሪያዎችህንና ልጆችህን እጅግ ብዙ ፍሬ እናፈራ ዘንድ በአንተ እንድንጣበቅ ሁል ጊዜም **ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ በአንተ እየኖርን ብዙ ፍሬ አፍርተን ቅዱስ አባ አብ ይከብር ዘንድ** በቅዱስ ቃልህ በቅዱስ አባትህ ፈቃድ በቅዱስ መንፈስህ ጠብቀን አጽናን አበርታን ጌታዬ ሆይ። **አምላኬ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ አላማዬና ትኩረቴ ደስታዬና ሕይወቴ አለቴና ጋሻዬ ጽድቄና መንገዴ እውነቴም ነው ዛሬም ለዘላለም። በእግዚአብሔር አብ ልጅ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን ሃሌ ሉያ።**

እውነትና ጽድቅ መሠረቱ የሆነ እግጅ እጅግ እጅግ በጣም በከበረው ቅዱስ ዙፋንህ ላይ ያለኸው፣ **ምህረትን የምትወድ፣ በዘላለም ፍቅር** ያፈቀርኸኝ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አምላኬ ወዳጄ **እግዚአብሔር አብ** ሆይ አከብርሃለሁ፣ እፈራሃለሁ፣ አፈቅርሃለሁ፣ እወድሃለሁ፤ ትሁት ልጅህን **ኢየሱስን** መንገድና እውነት ሕይወትም አድርገህ ስለላክህልኝ አመሰግንሃለሁ አገንሃለው አመልክሃለሁ ለዘላለም። ዓለማት ከመፈጠራቸው በፊት በአንተ ዘንድ የነበረውን **ቅዱሱን ቃልህን ኢየሱስ ክርስቶስን** ለድህነቴ ስለሰጠኸኝ አመሰግንሃለሁ፣ በሰማይም በምድርም በሁሉም ቦታ የተከበርከው የተፈራኸው በሰማይ የምትኖረው **ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ጻድቅና ፈራጅ አባቴ እግዚአብሔር አብ** ሆይ አፈቅርሃለሁ፣ **ልጅህንም እወደዋለሁ እከተለውማለሁ** የነገረኝን ቃል ሁሉ በደስታና በፍጹም ፍቅር ሰምቼ አደርገዋለሁ። እጅግ እጅግ እጅግ ቸር ደግ ቡሩክ የዋህ አባብዬ **እግዚአብሔር አብ** ሆይ ምስጋና፣ ኃይል ውዳሴ ጥበብ ክብር ሁሉ ላንተ ይሁን። **በልጅህ በናዝሬቱ ኢየሱስ** ፈልገህ ስላዳንከኝ ወደ ንስሐ ስለመራኸኝ አመሰግንሃሁ፣ **ቅዱስ መንፈስህንም** እታዘዘዋለሁ እወደዋለሁም። አባባዬ፣ **በልጅህ በጌታዬና በመድኃኒቴ** በ**ክርስቶስ ኢየሱስ** እስከመጨረሻው እንጸና ዘንድ በ**ክርስቶስ** ያሉ ቅዱሳንህን ሁሉ በቃልህ በቅድስና፣ በትህትና፣ በእምነት፣ በየዋህነት፣ በፍቅር፣ በተስፋ፣ በርህራሄ በጽድቅ በ**ክርስቶስ** በጸጋህ ሁሉ እባክህ ሙላ፣ **እጅግ በከበረው በጌታዬ በኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ስም አሜን። የናዝሬቱ ጌታ ኢየሱስ ፍፁም ውበትና ሕያው ፍቅር ነው። ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር በጽድቅና በእውነት ፈራጅ ነው።**

የእስራኤል አምላክ የሠራዊት ጌታ፣ የአብርሃም የይስሃቅ የያዕቆብ አምላክ፣ **አንድ እግዚአብሔር ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር አብ ቃሉና ልጁም ጌታ መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ መንፈሱም ከዘላለም እስከ ዘላለም ይባረክ።**

ሕይወቴ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ እጅግ አፈቅርሃለሁ እወድሃለሁ፣ እባርክሃለሁ፣ ውበቴ ሰላሜ ጌታዬ ክርስቶስ ሆይ ነፍሴንም በፊትህ አፈስሳለሁ፣ የኔ ጌታ የኔ ፍቅር መድኃኒቴ፣ አባቴ መምህሬ ወዳጄ መንገዴ ብርሃኔ አለቴ ታዳጊዬ መሸሸጊያዬ መመኪያዬ ማደሪያዬ መጠጊያዬ ጠባቂዬ ጋሻዬ ደስታዬ መኖሪያዬ እጅግ የከበርኸው የምታበራው የንጋት ኮከቤ፣ የአብርሃም የዳዊት አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ተባረክልኝ፣ ቅዱሱ ሊቀ ካህናት ጌታዬ መድኃኒቴ አምላኬ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ፍቅረኛዬ አምላኬ መልካም አባቴ እረኛዬ የናዝሬቱ ጌታ ኢየሱስዬ የእግዚአብሔር አብ ውድ ቅዱስ ንጹህ ልዩ ፍቅር ልጅና ቅዱስ ቃል፣ አልፋና ኦሜጋ መጀመሪያውና መጨረሻው የሁሉም ፈጣሪ፣ ጌታዬ መድኃኒቴ ንጉሤ አምላኬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ሕዝብህን አድን ርስትህንም ባርክ፣ ቀድሳቸው በምህረትህ ይቅር በላቸው ባርካቸውም፣ የቅዱስ አብ ቃል የናዝሬቱ ኢየሱስ ክበር ንገሥ ለዘላለም። መንፈስ ቅዱስ አከብርሃለሁ አገንሃለሁ እወድሃለሁ እታዘዝሃለሁ። እጅግ በከበረው ደምህ ከዋጀኸው ከልጅህ ቶማስ ቶሙክዳህታ]

የአብርሃም፣ የይስሃቅ፣ የያዕቆብ፣ የሙሴ፣ የኤልያስ፣ የዳንኤል፣ የጴጥሮስ፣ የጳውሎስ፣ የእስራኤል፣ የመጋቢ ዮንግ ዱ ኪም አምላክ የሠራዊት ጌታ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ሥላሴ እግዚአብሔር ይባረክ፤ ሃሌ ሉያ።

በእስራኤል አምላክ በሠራዊት ጌታ፣ በነገሥታት ንጉሥና በጌቶች ጌታ በናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ሙሉ ፈቃድና እርዳታ፣ በእግዚአብሔር ፈቃድ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የእግዚአብሔር አብ ባሪያ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም ደቀ መዝሙር የሆኑ ሙሉነህ አዲሱ እና ቶማስ ጌታቸው ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ተረጎሙት። Translated to Amharic by Muluneh Addisu Abdissa and Thomas Getachew TomukDahta, servants of **God the Father** and disciples of the **LORD of Lords and KING of Kings – Our Holy Holy Holy Lord and Beloved Savior KING JESUS Christ of Nazareth by the will of YAHWEH ELOHIM**. matoughen@gmail.com, hithomasgetachew@gmail.com. ኃይልና ክብር ሁሉ ለአንድ እግዚአብሔር (ለአባታችንና አምላካችን እግዚአብሔር አብ ለቅዱስ ቃሉና ልጁም ለጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለቅዱስ መንፈሱም) ይሁን፣ ሃሌ ሉያ። ንጹህና ቅዱስ መዓዛዬ ኢየሱስ ጌታዬ ደስታህን እሻለሁ፣ ጌታዬ ሆይ እጅግ አፈቅርሃለሁ አሜን። ሃሌ ሉያ]